# የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ወደ ዕብራውያን

# ትርጓሜ

ዳ. እ.

ጎንደር

# መቅድም

የሐዋርያው የጳውሎስ ______________________

______________________ መልእክት ______________________

______________________ ወደ ዕብራውያን።

## 1፤ ስለ ደራሲው።

በእውኑ የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ነውን? አርእስቱ እንደዚህ ይላል፥ አርእስቱን ግን ጳውሎስ አልጻፈውም፥ በመጀመሪያ ግልባጮችም ላይ ስሙ አልተጠራም። ስሙ በአርእስት ላይ የተጻፈው ቆይተው በወጡት በግሪክ ግልባጮች ላይ ነው፥ ከእነርሱም ቫልጌት ወደ ተባለ ወደ ላቲን ትርጉም ገባ፥ ከእርሱም ደግሞ ወደ ሌሎች ብዙዎች ግልባጮች ገባ። ይሁን እንጂ ብዙዎች ሰዎች መልእክቱ የጳውሎስ አይደለም ይላሉ። ምክንያቱም፥ 1ኛ በመልእክቱ ላይ ስሙ በፍጹም አልተጻፈም። የሐዋርያው የጳውሎስ ቢሆን ኖሮ ስሙ በመጀመሪያ ላይ በተጻፈ (ሮሜ 1፡1፤ 1ቆሮ. 1፡1፤ 2ቆሮ. 1፡1፤ ገላ. 1፡1፤ በቀሩትም በጳውሎስ መልእክቶች ሁሉ)፥ ፊርማውም በመጨረሻ ላይ በተገኘ ነበር። (2ተሰ. 3፡17፤ 1ቆሮ. 16፡21፤ ቆላ. 4፡18።) 2ኛ በብዙ ቦታዎች ላይ ቃሉና አነጋገሩ የጳውሎስን አይመስልም። 3ኛ ጳውሎስ የአሕዛብ ሐዋርያ ነበረ እንጂ የዕብራውያን አልነበረምና ወደ ዕብራውያን ባልጻፈም ነበር። 4ኛ በም. 2፡3 ላይ ደራሲው «የሰሙትም ለእኛ አጸኑት» ብሎአል፤ ጳውሎስ ግን እርሱ ራሱ ወንጌልን ከሰው ዘንድ አለመቀበሉን አረጋግጦአል። (ገላ. 1፡11፥12)

ከመጀመሪያ ጀምሮ በደራሲው ስም ላይ ጥርጥር ወድቆአል፥ በዚህም ምክንያት መጽሐፉ ወደ ካኖኑ ከመግባት በአንዳንድ አገሮች ቆይቶአል። በአበው ዘንድ ስለ ደራሲው ስም ስምምነት አልተገኘም፥ የዛሬውም መምህራን አልተስማሙበትም። ብቻ፥ ጳውሎስን ያወቀና ንግግሩንና አሳቡን የለመደ ሰው እንደ ሆነ ሁሉም ያምናሉ። ከአበው አንዱ «በርናባስ ጽፎታል» ይላል። አንዱም ደግሞ «ሉቃስ» ይላል፥ አንዱም «አጵሎስ» ይላል፥ አንዱም ደግሞ «ቀሌምንጦስ» ይላል። እጅግ ስሙ ጥር የሆነ አንዱም «የጻፈው ማን እንደሆነ በእውነት የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ነው» ይላል። አንዳንዶችም መምህራን «ጳውሎስ ራሱ ባይጽፈው እንኳ ጳውሎስ አስቀድሞ የተናገረውን የጳውሎስ ጓደኛ የሆነ አንድ ሰው በኋላ ጽፎት ይሆናልና መልእክቱ ምንም ቢሆን የጳውሎስ ነው» ይላሉ።

ጳውሎስም ጽፎት ይሆናል። ምነው? ቢሉ፥ ዕብራውያን እንደ ጠሉት ተረድቶ (ሐዋ. 21፡20-22፤ 22፡22) ስሙን ከመልክቱ አውቆ አስቀርቶት ይሆናል። ሁለተኛ ደግሞ፥ «ጳውሎስ የአሕዛብ ሐዋርያ ነበረ እንጂ የዕብራውያን አልነበረምና ወደ ዕብራውያን ባልጻፈም ነበር» ቢባል፥ የአሕዛብ ሐዋርያ ይሁን እንጂ በአይሁድ ሥርዓት ልዩ ማስተዋል እንደ ነበረውና ለዕብራውያን ዘመዶቹም ታላቅ ናፍቆት እንዳደረበት ታውቆአል። (ገላ. 1፡14፤ ሮሜ 9፡1-3፤ 10፡1፤ 11፡13-14።) ሦስተኛም፥ በመጀመሪያ መልእክቱ ወደ ተበተኑት ወደ ዕብራውያን መጻተኞች የጻፈው ቅዱስ ጴጥሮስ በሁለተኛ መልእክቱ ላይ ጳውሎስ ጽፎላቸው እንደ ነበር ያረጋግጣል። (2ጴጥ. 3፡15-16) ብዙም መምህራን ጴጥሮስ እንዲህ ብሎ

ይጽፋል። (ም. 12፡25-29)። መዕራፍ 13 መጨረሻው ነው። በእርሱም ላይ ደራሲው ለአማኞች አመላለስ የሚሆነውን ልዩ ልዩ ምክር ይሰጣል። ገንዘብን ሳይወዱ ክርስቲያን ወንድሞቻቸውን፥ እንግዶችንም፥ የእግዚአብሔር ቃል የነገሩአቸውንም እንዲወዱ፤ ነቀፈታውን እየተሸከሙ ለክርስቶስ እንዲለዩ፥ መልካም ማድረግንና ለሌሎች ማካፈልን እንዳይረሱ ይመክራቸዋል። በፍጻሜውም ላይ የሰላም አምላክ ፈቃዱን ያደርጉ ዘንድ ፍጹማን እንዲያደርጋቸው ይጸልያል። በሰላምታም መእክቱን ያቆማል።

ለ) አከፋፈሉ፥ መልእክቱ በሦስት ክፍል ይከፈላል፡-

1ኛ ክፍል፡- ም. 1 - ም.4። ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጻሜ የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል ወደ ሰው ያደረሰ የእግዚአብሔር ሐዋርያ ነው።

(እንግዲህ ባለማመን ጠንቅ እንዳንወድቅ እንጠንቀቅ።)

2ኛ ክፍል፡- ም. 5 - ም. 10። ኢየሱስ ክርስቶስ ሰውን ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርብ ሊቀ ካህናት ነው።

(እንግዲህ ወደ ቅድስት እንድንገባ ድፍረት ስላለን እንቅረብ።)

3ኛ ክፍል፡- ም. 11 - ም. 13. የአማኞች አመላለስ

ሐ) መተንተኑ

1ኛ ክፍል፡- ኢየሱስ፥ የሃይማኖታችን ሐዋርያ

መቅድም፤ መሾሙ፡- (ም. 1፡1፥2)

ም. 1፤ የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ መላእክት ይበልጣል።

ም. 2፤ የሰው ልጅ ሆኖ የክብርና የምስጋናን ዘውድ ተጭኖአል።

ም. 3፤ እስራኤላውያን የተነገረውን ቃል አላመኑምና ወደ ተሰጣቸው ዕረፍት አልገቡም።

ም. 4፤ እኛ በተስፋ ወደ ተሰጠን ዕረፍት ለመግባት እንትጋ።

2ኛ ክፍል፡- ኢየሱስ፥ የሃይማኖታችን ሊቀ ካህናት

የኢየሱስ ክህነት የተሻለ ነው።

ም. 5፤ መሾሙ

ም. 6፤ ሳንጠራጠር ወደ ፍጻሜ እንሂድ

ም. 7፤ ክህነቱ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት በመሆኑ

የኢየሱስ አገልግሎት የተሻለ ነው

ም. 8፤ የሚሻል ኪዳን መካከለኛ ስለ ሆነ

ም. 9፤ በሚሻል መቅደስ ውስጥና በሚሻል ደም ስለሚያገለግል

በእነርሱ በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ፥ የጎደለ ነገር ያለ ይመስላል፥ አለም። ይህ ጉድለት ምንድንር ነው? ጸንተው ይቆሙ ዘንድ ጤናና ኃይልን የሚሰጣቸውስ ምንድር ነው? መልሱ እንደሚከተለው ነው፡-

ስለ ጌታችን ስለ ኢየሱስ በመጀመሪያ ላይ ያገኙት እውቀት ዳግመኛ ይወለዱ ዘንድ በቅቶ ይሆናል፤ ነገር ግን ሊያሳድጋቸውና ወደ ፍጻሜ ሊያደርሳቸው አልበቃም። በሃይማኖታቸው ይጸኑ ዘንድ ስለ ኢየሱስ የበለጠ እውቀት ያስፈልጋቸዋል፥ ይህም እውቀት ለዕብራውያን በተጻፈው መልእክት ውስጥ ይገኛል። የክርሲትያኖችን ድካም ወደ ኋላ ማፈግፈጋቸውንም ሁሉ የሚያስወግድ ይኸው እውቀት ነው። ኢእየሱስ ክርስቶስ አሁን ዛሬ የሚሠራልንን ሥራ ማወቅ ያስፈልጋቸዋል። እርሱ ሊቀ ካህናታችን ሆኖ በሰማያዊው መቅደስ የሚሠራልንን ሥራ ሲያውቁ ይበረታሉ፥ ይጎለምሳሉ፥ ጸንተውም እስከ መጨረሻ ድረስ ይሄዳሉ። ኢየሱስ በዚያ ሰማያዊ መቅደስ ሆኖ ያን የሚያስፈልገንን ኃይልና ሕይወት ያድላል። ይህን ስናስተውልና ወደ ቅድስት የሚያደርሰውን መንገድ ስናገኝ በዚህ ዓለም ውስጥ፥ ከነችግሩና ከነፈተናው ሁሉ፥ ወደ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም አሁን እንደ ደረሱት ሰዎች ሆነን ለመኖር እንችላለን። በዚያ መቅደስ ውስጥ ገብተን ሰማያዊውን ሕይወት እንቀበላለን፥ በዚያችም ሕይወት ተመልተን በዓለም ውስጥ በማይቋረጥ ድል እንኖራለን።

ለድካማችንና ለውድቀታችን ሁሉ የሚሆን መድኃኒት ሊቀ ካህናታችን የሆነውን ሕያውን ኢየሱስን ማወቅና እርሱ ወደሚያገለግልበቱ ወደ ሰማያዊው መቅደስ ገብተን ሊሰጠን የሚጠብቀውን ሰማያዊውን ሕይወት ዛሬውኑ ከእጁ መቀበል ነው። ስለዚህም ነገር የሚያስተምረን ይኸው ወደ ዕብራውያን የተጻፈው መልእክት ብቻ ነውና ጥቅሙ ለዛሬ ክርስቲያኖች በእውነት ታላቅ ነው።

## 3፤ ስለ ዕብራውያን

መልእክቱ የተጻፈ ለዕብራውያን ነው። ዕብራውያን የተባሉት እናማን ናቸው? ቢሉ፥ ዕብራውያን የዕብራዊው የአብርሃም ልጆች ናቸው። (ዘፍ. 14፡13) አብርሃም ይስሐቅን ወለደ፤ ይስሐቅም ያዕቆብን ወለደ፤ ያዕቆብም ከእግዚአብሔር ጋር ከተገናኘ በኋላ እስራኤል ተባለ (ዘፍ. 32፡28)፥ ልጆቹም እስከ ዛሬ ድረስ እስራኤላውያን ይባላሉ፥ አንዳንድ ጊዜም አይሁድ እንላቸዋለን። እንግዲያውስ ይህ መልእክት የተጻፈ የአብርሃምና የያዕቆብ ወገኖች ለሆኑት ለዕብራውያን ወይም ለእስራኤላውያን ወይም ለአይሁድ ነው። ሦስቱም ስም አንድ ነው።

ሆኖም መልእክቱ የተጻፈላቸው ሰዎች ክርስቲያኖች ናቸው። (ም. 3፡1፤ 6፡12-14፤ 4፡14፤ 5፡12፤ 6፡9፥10፥ 12፡1፥2)። ቤተ ክርስቲያን የተጀመረው በእስራኤል አገር እንደ ሆነና ብዙዎች ዕብራውያን በክርስቶስ እንዳመኑ እናውቃለን። (ሐዋ. 2፡5፥14፥22፥41፤ 4፡4) ስለዚህ መልእክቱ የተጻፈ ለዕብራውያን ክርስቲያኖች ነው።

ይሁን እንጂ እነኝህ ዕብራውያን የት ነበሩ? መልእክቱ አይነግረንም። የቀሩት መልእክቶች ሁሉ አድራሻ አድራሻ ሲኖራቸው (ሮሜ 1፡7፤ 1ቆሮ. 1፡2፤ 2ቆሮ. 1፡1፤ ኤፌ. 1፡1፥ እንደዚሁም ሌሎቹ)፥ የዕብራውያን መልእክት አድራሻ የለውም፤ ስለዚህ ከተጻፈው ነገር ብቻ እነዚህ ዕብራውያን የት እንደነበሩ መገመት ያስፈልገናል። ስለ እነርሱም አንዳንድ ነገር እናውቃለን፡-

ሀ) ክርስቲያኖች ከሆኑ ብዙ ጊዜአቸው ነው (ም. 5፥12) ከቀደሙት መሪዎቻቸውም አንዳንዶች አሁን ሞተዋል። (ም. 13፥7)

ለ) በመልእክቱ ዘመን የኖሩ ክርስቲያኖች ገና ደምን እስከ ማፍሰስ ድረስ አልተቃወሙም ነበር (ም. 12፡4)፤ ሆኖም የስደትን ነገር አውቀዋል። (ም. 10፡32-34።)

ሐ) ጢሞቴዎስን አውቀዋል። (ም. 13፡23)።

መ) ከኢጣሊያ የሆኑትን አውቀዋል። (ም. 13፡24)

ሠ) ደራሲው ታውቆላቸዋል ቀድሞውንም በመካከላቸው ተቀምጦ ነበር። (ም. 13፡18፥19)

ረ) በእስክንድርያ የወጣውን፥ ሰብዓ ሊቃናት የተረጎሙትን የብሉይ ኪዳንን ትርጉም ደኅና አድርገው አውቀዋል፥ በዕብራይስጥም ከተጻፈው መጽሐፍ ይልቅ በዚህ ትርጉም ይሠሩ ነበር። ይህን የምናውቅበቱ የተጠቀሰው ጥቅስ ሁሉ ከዚያ ትርጉም በመሆኑ ነው።

ሰ) ቅዱሳንን ልታገለግል የቻለች ቤተ ክርስቲያን ነበረች። (ም. 6፡10)

ሸ) የመልእክቱ የትምህርቱ ሥነ ሥርዓት የእስክንድርያ ዓይነት ነውና እነኝህ ዕብራውያን የእስክንድርያን ዓይነት ክርክርና የትምህርት ሥነ ሥርዓት የለመዱ ናቸው።

ብዙዎች መምህራን እነኝህ ዕብራውያን የነበሩት በኢየሩሳሌም ነው ይላሉ፥ ነገር ግን ከዚህ ሐሳብ ጋር የማይስማሙ ብዙ ነገሮች አሉ። ለምሳሌ፥ የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ምጽዋትን ተቀባይ እንጂ ሰጭ እንዳልነበረች ታውቆአል። (ሮሜ 15፥25-27) ሁለተኛም፥ መልእክቱ ወደ ኢየሩሳሌም የሚጻፍ ከሆነ ደራሲው የሰብዓ ሊቃናትን ትርጉም እየጠቀሰ በእስክንድርያ ዓይነት ትምህርት ባልጻፈም ነበር። ሦስተኛ ደግሞ፥ የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ደምን እስከ ማፍሰስ ድረስ ተቃውማ እንደ ነበረች እናውቃለን። (ሐዋ. 7፡59 - ም. 8፡2፤ 12፡2)

ስለዚህ ሌሎች መምህራን «የለም መልእክቱ የተጣፈው ለእስክንድርያ ነው» ይላሉ። ይህም የሚቻል ነገር ነው። ስለምን? ቢሉ፥ በእስክንድርያ ከተማ ውስጥ ታላቅ የዕብራውያን ቀበሌ እንደ ነበረ ታውቆአል እነዚህም ዕብራውያን ከአገራቸው ተለይተው ስለ ኖሩ ዕብራይስጥን እየረሱ በግሪክ ቋንቋ ይናገሩ ነበር፥ ይሠሩበትም የነበረው መጽሐፍ የሰብዓ ሊቃናት ትርጉም ነበረ።

ሌሎች መምህራን ግን በም. 13፡22 ላይ የተጻፈውን ከኢጣሊያ የሆኑትን ሰዎች ሰላምታ አይተው «ከእነዚህ ከኢጣሊያ ከነበሩት ሰዎች ዘንድ ሰላምታን መቀበል የሚወዱት የሮም ሰዎች አይደሉምን?» ብለው መልእክቱ የተጻፈላቸው ዕብራውያን በሮም የተገኙ ናቸው ይላሉ። ይህም ደግሞ ይቻላል። በሮም ከተማ ብዙ አይሁድ ይገኙ እንደ ነበር እናውቃለንና

የሆነ ሆኖ እርግጡን ለማወቅ ሳንችል፥ እነኝህ ዕብራውያን ወይም በኢየሩሳሌም ወይም በእስክንድርያ ወይም ደግሞ በሮም ነበሩ እንላለን።

መልእክቱስ መቼ ተጻፈ? ቢሉ፥ ጢሞቴዎስ በወንጌል ሥራው ምክንያት ከታሰረ በኋላ፥ ነገር ግን ሳይሞት መሆኑን እናውቃለን፤ (ም. 13፡23) ስለመታሠሩ በሐዋርያት ሥራም ላይ ሆነ በጳውሎስ መልእክት ላይ የተጻፈ ነገር የለምና መታሰሩ ቆይቶ ይሆናል። ምናልባት ጳውሎስን ለመጠየቅ ወደ ሮም በመጣ ጊዜ ይሆናል። (2ኛ ጢሞ. 4፡9፥21)። ስለዚህ መልእክቱ ከ66

ዓ.ም በፊት የተጻፈ አይመስልም። እንደዚሁም በ95 ዓ.ም. ሮማዊው ቀሌምንጦስ መልእክቱን ጥቅሶአልና ከዚያ በፊት እንደ ተጻፈ ታውቆአል። ስለዚህ የተጻፈበት ዘመን ከ66 ዓ.ም. እና ከ95 ዓ.ም መካከል ይሆናል። አንዳንዶቹ መምህራን ደራሲው በ70 ዓ.ም. ስለ ሆነው ስለ ኢየሩሳሌም መፍረስ አለመጻፉን ተረድተው «መቅደስና ካህናት መሥዋዕቶችም ለጊዜው ብቻ ነበሩ የሚል ደራሲ እነዚያን ሁሉ ያስቀረውን የኢየሩሳሌም መፍረስ ቢያይ ኖሮ የግድ «ይኸውላችሁ!» ብሎ በጻፈ ነበር፥ አልጻፈምና ያየው አይመስልም» ይላሉ። በተጨማሪ ደግሞ «በም. 7፡8፥23 እና በም. 13፡10፥11 ላይ የዱሮ ሥርዓት ገና ደራሲው በጻፈ ጊዜ የሚፈጸም ይመስላልና መልእክቱ ከ70 ዓ.ም. በፊት ተጽፎአል» ይላሉ። ይህም ከሆነ መልእክቱ በ66 ዓ.ም. እና በ70 ዓ.ም. መካከል ተጽፎ ይሆናል።

# 1ኛ ክፍል፡- ኢየሱስ፥ የሃይማኖታችን ሐዋርያ፤ (ም.1 - ም.4)

## ምዕራፍ አንድ

### ም. 1፡1፥2፤ መሸሙ

ም. 1፡3-14፤ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ከመላእክት ይበልጣል።

የመልእክቱ ዓይነተኛ ሐሳብ «እግዚአብሔር በአዲሱ ኪዳን የተናገረው ቃል በአሮጌው ኪዳን ከተናገረው ስለሚበልጥና ስለሚሻል አሮጌውንም ስለሚተካ ለምን ብላችሁ ወደ አሮጌኤው ትመለሳላችሁ?» የሚል ነውና በዚህ በመጀመሪያ ምዕራፍ ላይ ደራሲው 1ኛ፥ የተነገረውን የቃሉን ታላቅነት (ቁ. 1-4)፤ 2ኛ፥ ቃሉ የመጣበትን የመካከለኛውን ታላቅነት ያስረዳል፤ (ቁ. 5-14)። ይህንም ሲያስረዳ ኢየሱስ ፍጹም አምላክ እንደሆነ ይገልጣል።

ቁ. 1-4

1 ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ 2 ጎዳና ለአባቶቻችን
በነቢያት ተናግሮ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ
በዚህ ዘመን 3 መጨረሻ ለእኛ ተናገረን፤ እርሱም የክብሩ መንጸባረቅና የባሕርዩ
ምሳሌ ሆኖ፥ ሁሉን በሥልጣኑ ቃል እየደገፈ፥ ኃጢአታችንን በራሱ ካነጻ በኋላ
በሰማያት በግርማው ቀኝ 4 ተቀመጠ፤ ከመላእክት ይልቅ እጅግ የሚበልጥ ስምን
በወረሰ መጠን እንዲሁ ከእነርሱ አብዝቶ ይበልጣል።

እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የሚድኑበትን መንገድ ሊገልጥ በወደደ ጊዜ በሁለት ቃል፥ ማለት በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን ተናገራቸው። ፊተኛው ቃል፥ እርሱም ብሉይ ኪዳን፥ ከቶ ሙሉ ሳይሆን በከፊል በከፊል ነበረ፤ በአንድም ጎዳና ብቻ ስያሰጥ በልዩ ልዩ ጎዳና፥ ማለት በሕግ በታሪክ በመዝሙር በምሳሌ በራእይ በትንቢትም ተሰጥቶአል። ሁለተኛው ቃል ግን ወዲያውኑ ፍጹምና ለምን ጊዜም በቂ ነበረ። እግዚአብሔር በብሉይ ዘመን ፊተኛውን ቃል ሲናገር ነቢይን በየጊዜው አስነስቶ በእርሱ ተናገረ፤ በዚያ ዘመን መጨረሻ ግን በነቢይ ሳይሆን ልጅ በሆነ ተናግሮአል። ይህም ልጅ የእግዚአብሔርን ቃል ተናጋሪ ብቻ ሳይሆን ራሱ የእግዚአብሔር ቃል ነበረ፤ (ዮሐ. 1፡1)። የተናገረውም በአንደበቱ ብቻ አልነበረም፤ የነበረውም ሁሉ እግዚአብሔርን ገለጠ፤ (ዮሐ. 14፡9)።

ስለዚሁ ልጅ 7 ነገሮች ተነገሩ፡-

1፥ እግዚአብሔር ሁሉን ወራሽ አድርጎታል። (መዝ. 2፡8፤ ማቴ. 28፡18)። «ወራሽ» ሲል ሰው ከሞተ በኋላ የሚወርሰው ዓይነት ወራሽ ማለቱ ሳይሆን ገዥ ማለቱ ነውና እግዚአብሔር ለእርሱ ሁሉ አስገዝቶአል ማለት ነው፤ (መዝ. 109፡1፤ 1ቆሮ. 15፡25)። ይህ ልጅ የጌታዎች ጌታና የነገሥታት ንጉሥ ነው (ራእ. 17፡14)።

2፥ እግዚአብሔር ዓለማትን በእርሱ ፈጥሮአል። (ቁ. 10፤ ም. 11፡3፤ ዮሐ. 1፡3፥10፤ ቆላ. 1፡16፥17) የተፈጠረው ሁሉ በእርሱ ተፈጥሮአልና ልጁ ከማናቸውም ፍጥረት ሁሉ በላይ ነው።

2፥ እግዚአብሔር ዓለማትን በእርሱ ፈጥሯል። (ቁ. 10፤ ም. 11፡3፤ ዮሐ. 1፡3፥10፤ ቆላ. 1፡16፥17) የተፈጠረው ሁሉ በእርሱ ተፈጥሯልና ልጁ ከማናቸውም ፍጥረት ሁሉ በላይ ነው።

3፤ የእግዚአብሔር የክብሩ መንጸባረቅ ነው። የክብሩ መንጸባረቅ ነውና ራሱ እግዚአብሔር ነው። ስለምን? ቢሉ፥ ጮራ ከጸሐይ ብርሃንም ከመብራት እንደሚሠርፅ እንደዚሁም ልጁ የእግዚአብሔር የክብሩ መንጸባረቅ ነው። ጮራ ከፀሐይ ብርሃንም ከመብራት አይለይም። ፀሐይ ከኖረ ጀምሮ ጮራ አብሮ ኖሯል፤ መብራትም ሲኖር ብርሃን አብሮ አለ። የግዴታ ነገር ነው። እንደዚሁም ልጁ የእግዚአብሔር የክብሩ መንጸባረቅ ሆኖ ከአብ አይለይምና ከዘላለም ነው፤ (ዮሐ. 8፡58)። እንደዚህም የጮራው ባሕርይ የፀሐዩ ባሕርይ ነውና፥ የብርሃኑም ባሕርይ የመብራቱ ነውና፥ የእግዚአብሔር የክብሩ መንጸባረቅ የሆነ ልጅ ባሕርይ የእግዚአብሔር ባሕርይ ነው፥ ልጅም በመለኮቱ ከአብ ጋር አንድ ነው (ዮሐ. 10፡30)።

4፥ የእግዚአብሔር የባሕርዩ ምሳሌ ነው። በሰም ላይ እንደሚታየው የማኅተም ምልክት ማኅተሙን እንደሚመስል እንደዚሁም «እኔን ያየ አብን አይቶአል» እስኪል ድረስ (ዮሐ. 12፡ 45፤ 14፡9፤ 2ቆሮ. 4፡4)። ልጁ በኅላዌ በአርአያም እግዚአብሔርን መስሎአል። የማኅተሙ ምልክት የተመለከተው ሰው ምልክቱን ያደረገው ማኅተም እንዴት እንደሆነ እንደሚያይ እንዲሁም ኢየሱስን የተመለከተው ሰው እግዚአብሔር እንዴት እንደሆነ ያያል።

5፥ ሁሉን በሥልጣኑ ቃል ይደግፋል። ዓለማት በእርሱ ተፈጥረው ነበር አሁንም እርሱ በሥልጣኑ ቃል ሀሉን ይደግፋል ያካሄድማል። ከዋክብትን በአካሄዳቸው፥ ባሕሮችን በስፍራቸው ዘመናትንም በተራቸው የሚጠብቅ፥ ኮከብና ኮከብም እንዳይጋጭ፥ የሚያደርግ እርሱ ነው።

የሰውነቱን ክብር አይተናል፥ አሁንም የሥራውን ክብር እናያለን። ይህም ሥራው በሁለት ክፍል ነው፥ አንዱ በምድር ላይ የሚሠራው አንዱም በሰማያት፤ እኛም ሁለቱንም ክፍሎች ማወቅ ያስፈልገናል።

6፥ ኃጢአታችንን አነጻ። ይህ በምድር ላይ የሠራው ሥራ ነው። በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የነበረው ታላቁ መሰናክል የሰው የኃጢአቱ እድፍ ነበረና (እንባ. 1፡13) እግዚአብሔር ሰውን ከመታረቁ በፊት ሰው ከኃጢአቱ እንዲነጻ አስፈለገ። ሰው ከኃጢአቱ ካልነጻ ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነትን ለማድረግ በፍጹም የማይቻል ነገር ነውና ልጁ መጥቶ ኃጢአታችንን አነጻ። (ራእ. 1፡5) ኃጢአታችንንም በማንጻት ከኩነኔ አዳነን።

7፥ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ። በምድር ላይ ኃጢአታችንን ካነጻ በኋላ ወደ ሰማይ ዐረገ በእግዚአብሔርም ቀኝ ተቀመጠ፤ (ማር. 16፡19)። ይህም በሰማይ የሚሠራውን ሥራ ያመለክታል። ከኩነኔ ሊያድነን የሠራው ሥራ ባያልቅ ኖሮ ገና እየሠራ በቆመ ነበርና መቀመጡ ሥራው መፈጸሙንና ከሥራ ማረፉን ያስረዳናል። (ም. 10፡11-14)። ሆኖም መቀመጡ በሰልፍና በሥነ ሥርዓት ነበረና በሰማያት ደግሞ ሥራ ለመሥራት ሥልጣን እንደ ተሰጠው እንረዳለን። ዛሬ ምን ሥራ አለው? ቢባል፥ ይኸው ይህ መልእክት እንደሚያመለክተን የሊቀ ካህናትን ሥራ እንሥቶአል። ዛሬ ደግሞ ከሚጣበቅብን ኃጢአት ከነእድፉ እያነጻን በፈተናና በዓለም ላይ እሸናፊዎች እንሆን ዘንድ ኃይል እየላከልን ወደ

ብሎአል? ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላልቸው ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉ መናፍስት አይደሉምን?

ደራሲው አሁን አዲሱ ቃል የመጣበትን የመካከለኛውን ታላቅነት ያስረዳል። እግዚአብሔር አዲሱን ቃል የተናገረብት መካከለኛ ማን እንደ ሆነ በቁ. 2ና 3 ላይ አይተናል። መካከለኛው እርሱ ነውና ደራሲው በቁ. 4 ላይ «ከመላእክት ይበልጣል» ይላል። ይህን የሚለው በምን ምክንያት ይሆን? መላእክትን በነገሩ ምን አገባቸው? ቢሉ፤ አዲሱ ቃል ከፊተኛው እንደሚበልጥ ለማስረዳት ዓይነተኛው ሐሳብ በመሆኑ ነው። ብሉይ ኪዳን የተሰጠ በመላእክት በኩል ሲሆን (ሐዋ. 7፡38፡53፤ ገላ. 3፡19፤ ዕብ. 2፡2) አዲሱ ኪዳን የተሰጠ በልጅ መካከለኝነት ነው። ልጁም ከመላእክት ይልቅ እጅግ የሚበልጥ ስለምን እንደ ወረሰ መጠን ከእነርሱ አብዝቶ ይበልጣል። እርሱ ከእነርሱ አብዝቶ የሚበልጥ ከሆነ በእርሱ መካከለኝነት የመጣው ኪዳን በእነርሱ ከመጣው አብዝቶ ይበልጣል። ይህንም ገልጦ ለማስረዳት ደራሲው በቁ. 2ና 3 ላይ በልጁ የተነገረው ቃል በነቢያት ከተነገረው እንደ በለጠ ለማሳየት ስለ ልጁ ታላቅነት 7 ነገሮች አቅርቦ እንደነበር እንዲሁም አሁን ከቁ. 5-14 ድረስ ልጁ ከመላእክት ምን ያህል እንደሚበልጥ ለማሳየት 7 ጥቅሶች በመጥቀስ የልጁን ስሞች በፊታችን ያሰልፋል።

1ኛ 2፥(ቁ. 5)። «ልጄ ነህ» ተባለለት (መዝ. 2፡7)፥ እግዚአብሔርም «አባት እሆነዋለሁ» ብሎአል። (2ሳሙ. 7፡14)። ማለት፥ አንድያ ልጅ ነው፥ በእርሱ ዓይነት ልጅነት የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ ሌላ ከቶ የለም። መላእክት፥ ሊቃነ መልእክትም፥ ወደዚህ አልደረሱም፥ ለእርሱም ታማኞች ሆነው ወደዚህ ለመድረስ አላሰቡም።

3፥ (ቁ. 6) የሚሰገድለት ለጌታ አምላክ ብቻ ነው። (ማቴ. 4፡9፥10)። ይህም ሲሆን መላእክት እንዲሰግዱለት ሲታዘዙ (ዘዳ. 32፡43 በሰብዓ ሊቃናት ትርጉም) እርሱ አምላክ ስለሆነ አይደለምን? የሚሰግዱለትም እርሱ እጅግ በጣም ስለሚበልጣቸው ነው።

4፥ (ቁ. 7) በዚህ ቁጥር ላይ መልእክትና አገልጋዮች ተስተካከለዋል። ልጁ የተወለደ ሲሆን (ቁ. 5) መላእክት «የተደረጉ» ናቸው። እግዚአብሔር እንደ ፈቃዱ ያደርጋቸዋል ማለት ነው (መዝ. 103፡4)። በተወለደና በተደረገ መካከል ምን ያለ ታላቅ ልዩነት አለ! የተወለደ ከተደረገው እጅግ ይበልጣል።

5፥ (ቁ. 8ና 9) ስለ ልጁ የተባለውን ደግሞ እዩ! አምላክ ሆኖ ዙፋኑ እስከ ዘላለም ድረስ ይኖራል፤ እግዚአብሔርም ከጓደኞቹ ይልቅ በደስታ ዘይት፥ ማለት ሰው በደስታ ቀን (በዓመት በዓል) በሚቀባው ዘይት፥ ቀባው። (መዝ. 44፡6፥7)። ጓደኞቹ እነማን ናቸው? ቢሉ፥ በዳዊት ዙፋን ላይ እንዲነግሡ የተቀቡት ሌሎቹ ነገሥታት ይሆናሉ፤ ወይም ምናልባት በሰማያት ጓደኞቹ የሆኑት መላእክት ይሆናሉ፤ ወይም ደግሞ በኋላ ከእርሱ ጋር የሚነግሡ ምእመናን ይሆናሉ። (ም. 3፡14፤ 2ጢሞ. 2፡12፤ ራእ. 20፡4)። እስከ ዘላለም ድረስ እንዲነግሥ የተባለለት መልአክ ከቶ ይኖራለን? ሎረ ከቶ የለም!

6፥ (ቁ. 10-12) «ልጅ»፥ «መላእክት የሚሰግዱለት»፥ «የዘላለም ንጉሥ» ተባለ አሁንም «ከዘላለም እስከ ዘላለም የሚኖር ጌታ» ተባለ። ምድርን የመሠረተ ሰማዮችንም በእጆቹ የፈጠረ እርሱ እንደሆነ ተባለ። (መዝ. 101፡25-27)። የማያረጅና የማይለወጥ ነው። መላእክት የተፈጠሩ ናቸው፥ እርሱ ግን ፈጣሪ ነው። ፈጣሪ ከፍጥረቱ እጅግ አድርጎ ይበልጥ የለምን? ይበልጣል!

7፥ (ቁ. 13) «በቀኜ ተቀምጠህ ከግርግ መንግሥቴ ተካፈል» የተባለለት ንጉሥ ነው። (መዝ. 109፡1)። ይህ ከመላእክት ከቶ ለማን ተባለ? ሎረ ከቶ አልተባለም! ልጁ ከመላእክት ሁሉ ከፍ ከፍ አለ።

ታዲያስ መላእክት እነማን ናቸው? ቢሉ፥ መላእክትማ የእግዚአብሄር መልእክተኞች ናቸው። ልጁ (ኢየሱስ) በእግዚአብሔር ቀኝ የተቀመጠና ለዘላለም የሚነግሥ ሲሆን መላእክት ከዙፋኑ የሚላኩ አገልጋዮች ናቸው። እግዚአብሔርን እያገለገሉ ስለ ምእመናን፥ ምእመናንን ለማገዝ ይላካሉ። የቤት ልጅ በቤቱ ከሚያገለግሉት አገልጋዮች እንደሚበልጥ (ዮሐ. 8፡35) እንደዚሁም በዚያው መጠን፥ ኢየሱስ ከመላእክት ይበልጣል፤ በእርሱ የተነገረውም ቃል በእነርሱ በኩል ከተነገረው ይበልጣል።

ማስገንዘቢያ፡- ስለ መላእክት፤ መጽሐፍ ቅስዱስ ስለ መላእክት ምን ይላል? ቢሉ፥ አስቀድመን ብሉይ ኪዳንን ቀጥሎም አዲስ ኪዳንን እንመርምር።

ብሉይ ኪዳን መልእክት በቁጥራቸው በጣም ብዙ እንደ ሆኑ ይነግረናል፤ (መዝ. 67፡17)። በብሉይ ዘመንም ሥራቸው በ3 በኩል ይከፈል ነበር፡-

1ኛ፥ የእግዚአብሔር መልእክተኞች ነበሩ። ስማቸው እንደሚያመለክተው ሁሉ መልእክቶቹን (ቃሎቹን) ለሰው ያደርሱ ዘንድ እግዚአብሔር ይልካቸው ነበር። (ዘፍ. 16፡7-14፤ 22፡11-18፤ ዘኁ. 22፡22-35፤ መሳ. 2፡1-4፤ 6፡11-24፤ 13፡3-22)። እግዚአብሔርም ሕግን (ኦሪትን) በመላእክት በኩል እንደ ሰጠ ደግሞ ተነግሮአል። (ሐዋ. 7፥38፡53፤ ገላ. 3፡19፤ ዕብ. 2፡2)

2ኛ፥ ለእግዚአብሔር ሕዝብ የሚያገለግሉ ነበሩ። በምድራዊ ጉዞአቸው ላይ ያሉትን ልጆቹን ያግዙ ዘንድ እግዚአብሔር ይልካቸው ነበር። ያገለግሉትም ያግዙትም በልዩ ልዩ በኩል ነበር፡-

ሀ) በመንገድ ላይ በመምራት። (ዘፍ. 24፡7፤ ዘጸ, 14፡19፤ 23፡20-23፤ 32፡24፤ 33፡2፤ ዘኁ. 20፡16፤ ኢያ. 5፡13-15)።

ለ) በሥጋ ድካም ጊዜ በማበርታት። (1ነገ. 19፡5-8፤ መዝ. 90፡11)።

ሐ) በችግር ጊዜ በማዳን። (ዳን. 3፡28፤ 6፡22፤ መዝ. 33፡7፤ 2ነገ. 6፡15-17።)

መ) የእግዚአብሔርን ነገር በማስረዳት። (ዘካ. 1፡9፡19፥21፤ 2፡4፤ 4፡5፥6፤ 6፡4፥5)።

3ኛ፥ የእግዚአብሔርን ፍርድ የሚፈጽሙ ነበሩ። እግዚአብሔር በሰው ወይም በአገር ላይ ፍርዱን ሲናገር ያን ፍርድ የፈጸሙት አንዳንድ ጊዜ መላእክት ነበሩ። (ዘፍ. 19፡1-3፥15-25፤ 2ሳሙ. 24፡16፤ 1ዜና. 21፡15-27)።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ መልአክ እየተባለ ምሥጢራዊ ሆኖ ከእግዚአብሔር ጋር ልዩ አንድነት ያለውን አንዱን እናያለን። (ዘፍጥ. 16፡7-13፤ 18፡10፥13፥14፥17-33፤ ዘጸ. 3፡2-6፤ 33፡12፥14፤ ሐዋ. 7፡30-35፤ ኢያ. 5፡13፥14፤ መሳ. 6፡11-22፤ 13፡3፥15-23)።

ብዙዎችም መምህራን ይኸው «መልአክ» ሥጋ ከመልበሱ በፊት የሆነ ወልደ እግዚአብሔር ነው ይላሉ።

ስለ ሚካኤልም እናነባለን፣ ስለ እርሱም «ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ» እንደ ሆነና የእስራኤል ሕዝብ ጠባቂ እንደሆነ ተገልጦአል። (ዳን. 10፡13፥21፤ 12፡1)። የአገሮችም መላእክት እንዳሉ እናነባለን። (ዳን. 10፡13፤ 12፡1)።

በብሉይ ኪዳን ዘመን ሥራቸው ይህ ነው። «መላእክት በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ይሠሩ የለም ወይ?» ቢሉም እውነት ነው፥ እላይ እንዳየነው ሁሉ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ይሠራሉ፤ ይሁን እንጂ «በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ይሠራሉ» ስንል በማስታረቅ ሥራ በኩል መካከለኞች ናቸው ማለታችን ከቶ አይደለም። በብሉይ ኪዳን ውስጥ በሞላው ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር የሚያስታርቁ ካህናት ከነመሥዋዕቶቻቸው ናቸው እንጂ መልእክት ከቶ አይደሉም። ለመላእክት ደግሞ አምልኮት በብሉይ ኪዳን ተከልክሎአል፤ (መሳ. 13፡16)።

እንግዲያውስ ብሉይ ኪዳን በዕብ. 1፡14 ላይ ከተጻፈው ቃል ጋር ተስማምቶ «መላእክት ስለ እግዚአብሔር ሰዎች ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም መናፍስት ናቸው» ይላል።

በአዲስ ኪዳንም የመላእክት ነገር ፈጽሞ ያው ነው። በአኳኋናቸውና በሥራቸው ልዩነት በፍጹም የለም። ቁጥራቸው «እእላፋት» ተባለ (ዕብ. 12፡22)፥ ኢየሱስም «አባቴን ብለምን ከአሥራሁለት ጭፍሮች የሚበዙ መላእክት በቀላሉ ይሰድልኛል» አለ (ማቴ. 26፡53)። ሥራቸውም፡-

1ኛ፥ የእግዚአብሔር መልእክተኞች ናቸው። (ሉቃስ 1፡8-20፥26-38፤ 2፡8-14፤ ማቴ. 28፡2-7፤ ማር. 16፡5-7፤ ሉቃ. 24፡4-7፤ ዮሐ. 20፡11-13፤ ሐዋ. 10፡1-7፤ 27፡23፥24፤ ራእ. 1፡1፤ 22፡16)።

2ኛ፥ ለእግዚአብሔር ሕዝብ የሚያገለግሉ ናቸው።

ሀ) በመምራት። (ሐዋ. 8፡26)

ለ) በማበርታት። (ማቴ. 4፡11፤ ሉቃ. 22፡43)

ሐ) በማዳን። (ማቴ. 2፡13፥19፤ ሐዋ. 5፡19፤ 12፡6-11)

መ) በዘመኑም መጨረሻ ላይ የእግዚአብሔርን ሰዎች ወደ እርሱ ዘንድ በመሰብሰብ። (ማቴ. 13፡39፤ 41፥49፤ 24፡31።)

3ኛ፥ የእግዚአብሔርን ፍርድ የሚፈጽሙ ናቸው። (ሐዋ. 12፡23)

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ደግሞ ስለ ሚካኤል እናነባለን፥ እዚህም ላይ እንደ መላእክት አለቃና እንደ እግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ሆኖ ተገለጠ። (ይሁዳ 9፤ ራእ. 12፡7)። ገብርኤልም በእግዚአብሔር ፊት የሚቆም መልአክ ነው። (ሉቃ. 1፡19፥26)። የልጆችም መላእክት እንዳሉ እናነባለን (ማቴ. 18፡10) እንደዚሁም ደግሞ የአብያተ ክርስቲያናት መላእክት ያሉ ይመስላል። (ራእ. 1፡20፤ 2፡1፥8፥12፤ በሌሎችም ቁጥሮች ላይ ደግሞ)። በወንጌልም ነገር መላእክት በጣም እንደተገረሙ ተጽፎአል። (1ኛጴጥ. 1፡12)። ደግሞ የሰይጣን መልእክት እንዳሉ እናያለን (ማቴ. 25፡41፤ 2ጴጥ. 2፡4፤ ራእ. 12፡7-9)።

በብሉይ ኪዳን እንደ ሆነ እንዲሁም በአዲስ ኪዳን ነው። መልእክት በማስታረቅ ነገር በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ሲገቡ ከቶ አናገኛቸውም። ማስታረቅ የመላእክት ሥራ ሳይሆን የካህንና የመሥዋዕቱ ሥራ ነው፤ ነገር ግን በአዲስ ኪዳን ዘመን ካህኑ ኢየሱስ ነው መሥዋዕቱም ነፍሱ ነው። (ኢሳ. 53፡10፤ ዕብ. 7፡11-14፤ 10፡8-18) እንደ አስታራቂ ሆኖ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው መካከለኛው አንድ ብቻ አለ፥ እርሱም ክርስቶስ ኢየሱስ ነው። (1ጢሞ. 2፡5) እንደዚሁም ደግሞ በአዲስ ኪዳን ለመላእክት መስገድ ተከልክሎአል። (ራእ. 19፡10)።

እንግዲያውስ አዲስ ኪዳን በራእ. 19፡10 ላይ «ከአንተ ጋር የኢየሱስም ምስክር ካላቸው ወንድሞችህ ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ» ብሎ ስለ ራሱ የተናገረውን የመልአኩን ቃል ተገንዘበ «መላእክት ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም መናፍስት ናቸው» ይላል። (ዕብ. 1፡14)

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የተቃወመውና የተናገረበትም ልዩ የሆነ የመልእክት አክብሮት የተገኘበት በቆላስይስ ነበረ። (ቆላ. 2፡18፥19) እንደዚሁም ዛሬ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ በሆኑትና ቁጥራቸውም በፍትሐ ነገሥት ውስጥ ባልተገኙ መጻሕፍት ላይ ስለ መላእክት ነገር እንግዳ ትምህርት ይገኝ ይሆናል፤ ቢሆንም ይህ ትምህርት ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ጋር የማይስማማ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መላእክት ነገር የሚናገረው ከዚህ በላይ የተዘረዘረውን ነገር ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የሚለው ይህ ነውና በዚህ ላይ መጨመር ስህተት ነው፥ ፍርድንም ያስከትላል (ዘዳግ. 4፡2፤ ምሳ. 30፡5፥6)። መላእክት የእግዚአብሔር መልእክተኞች ናቸውና የተከበሩ ናቸው፤ ይሁን እንጂ አይሰገድላቸውም፤ አገልጋዮችንም በዙፋን ላይ ከተቀመጠው ልጁ (ከኢየሱስ) ጋር ልናስተካክላቸው ከቶ አይገባንም።

ይህ ወደ ዕብራውያን የተጻፈው መልእክት እንደሚያስተምረን ሁሉ እኛ ዛሬ ኢየሱስ በመረቀልን መንገድ ወደ እግዚአብሔር ዙፋን በቀጥታ ልንቀርብ እንችላለንና ዛሬ ከሰውና ከእግዚአብሔር መካከል ከኢየሱስ በቀር ሰውም ሆነ መልአክ የሚያስፈልግ እንደሌለ የምንገነዘበው ነገር ነው (ዕብ. 4፡14-16፤ 10፡19-22)።

# ምዕራፍ ሁለት

## ኢየሱስ የሰው ልጅ ሆኖ የክብርና የምስጋናን ዘውድ ተጭኖአል።

ደራሲው ገና ኢየሱስን ይሥላል። በም. 1 ላይ ፍሡም አምላክ መሆኑን አሳይቶአል፤ አሁንም በም. 2 ላይ ፍጹም ሰው መሆኑን ያሳያል። ኢየሱስ ፍጹም አምላክ ስለ ሆነ በእርሱ የተነገረው የአዲሱ ኪዳን ቃል በመላእክት በኩል ከተነገረው ከፊተኛው ኪዳን ቃል እጅግ ይበልጣልና ይህን አዲሱን ቃል ቸል እንዳንለው ደራሲው አስቀድሞ በብርቱ ያስጠነቅቀናል። (ቁ. 1-4) ቀጥሎም፥ እግዚአብሔር ለሰው የመደበውን ክብርና ሥልጣን ይጠቅስና ያ የእግዚአብሔር ሐሳብ በሰው ሁሉ ውስጥ ተፈጽሞ ገና ባይታይ እንኳ ሰው በሆነ በኢየሱስ ውስጥ እንደ ተፈጸመ ያሳያል። (ቁ. 5-9) በ3ኛ ክፍል ደግሞ ኢየሱስ ሞትን በማሸነፍ ሰውን ወደ ተመደበለት ክብርና ሥልጣን ለመመለስና ሰውም ኃጢአት ሲሠራ ኃጢአቱን ሊያስተሰርይለት በተፈተነም ጊዜ ሊረዳው እንዲችል ሊቀ ካህናት ለመሆን ፍጹም ሰው እንደ ሆነ ያሳያል። (ቁ. 10-18)።

### ቁ. 1-4

1 ስለዚህ ከሰማነው ነገር ምናልባት እንዳንወሰድ ለእርሱ አብልጠን ልንጠነቀቅ
ያስፈልገናል። 2 በመላእክት የተነገረው ቃል ጽኑ ከሆነ፥ መተላለፍና አለመታዘዝም
ሁሉ 3 የጽድቅን ብድራት ከተቀበለ እኛስ እንዲህ ያለውን ታላቅ መዳን ቸል
ብንለው፥ እንዴት እናመልጣለን? ይህ በጌታ በመጀመሪያ የተነገረ ነበርና፥
የሰሙትም ለእኛ አጸኑት፥ 4 እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ እንደ ፈቀደ በምልክትና
በድንቅ ነገር በልዩ ልዩ ተአምራትም፥ መንፈስ ቅዱስንም በማደል አብሮ
መሰከረለት።

ማስጠንቀቂያ ከሆኑቱ ክፍሎች ይህ መከመሪያው ነው። ደራሲው በም. 1 ላይ እግዚአብሔር በልጁ ስለ ተናገረው ቃል ተናግሮአል፥ ልጁም ማን እንደ ሆነ ዘርዝሮ አስታውቆአል። አሁንም በም. 2 መክፈቻ ላይ «ስለዚህ» ይላል። «ስለዚህ» ማለት «ተናጋሪው ማን እንደ ሆነና ምን ያለ ታላቅ ሥራ እንደሠራልን እየተገነዘብን» ማለት ነው። የተነገረው ቃል ወደ እኛ ዘንድ ደርሶአል እኛም ሰምተነዋል፤ ሆኖም በፈሳሽ ውኃ ላይ ሰፍፎ እንደሚሄድ ጭራሮ ሆነን ከሰማነው ነገር እንዳንወሰድ እጅግ በጣም መጠንቀቅ ያስፈልገናል። መጠንቀቅ ያለብን «አብልጠን» ነው፤ ማለት ያ በመላእክት በኩል የተነገረው ቃል ጽኑ ከሆነ ይህ በልጁ የተነገረው በጽናቱ ምንኛ ይበልጥ ይሆን! ስለዚህ «አብልጠን» መጠንቀቅ ያስፈልገናል። ያም በእውነት ጽንቶአል። ቃሉን የተላለፈው ወይም ሳይፈጽመው የቀረ ሰው በቃሉ ተይዞ እውነተኛውን ብድራት ተቀብሎአል። ሰውም በአገልጋዮች (በመላእክት) በተነገረው ቃል ቢያዝ ብድራቱንም ቢቀበል እኛማ በጌታ በተነገረውና ሐዋርያት ባጸኑት እግዚአብሔርም በምልክትና በድንቅ ነገር በመሰከረለቱ ምንኛ እንያዛለን! ቸል እንለውስ እንደሆነ እንዴት እናመልጣለን? ሎረ ከቶ አናመልጥም! ስለዚህ ከሰማነው ነገር ምናልባት እንዳንወሰድ አብልጠን ልንጠነቀቅ ያስፈልገናል።

<u>ማስገንዘቢያ</u>፡-

ሀ) «ከሰማነው ነገር ምናልባት እንዳንወሰድ» (ቁ. 1) ሰው ከዚያ ቃል እንደምን ይወሰዳል? ቢሉ፥ ቸል በማለት ነዋ! የንጉሥን ጥሪ ቸል ያሉትን እድምተኞች በመምሰል ነው (ማቴ. 22፡5)። ቃሉን እንሰማለን፥ ዳሩ ግን አንጠነቀቅለትም። እግዚአብሔር «በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጁ ይህ ነው እርሱን ስሙት» ሲል፥ ጌታም «እኔ መንገድና እውነት

ሕይወትም ነኝ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም» ሲል፥ ሐዋርያትም «መዳን በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለም» ሲሉ (ማቴ. 17፡5፤ ዮሐ. 14፡6፤ ሐዋ. 4፡12) እኛ በሌላ በኩል ምናልባት ተስፋ እያደረግን የሰማነውን ቃል ቸል ብንል እንወሰዳለን፥ እናመልጥም።

አውሎ ነፋስ ሲነሣ በአንድ ወደብ አፍ ላይ እንደ ተገኘ መርከብ ያለ ነገር ነው። የወደቡ ኃላፊ «በነፋስና በማዕበል ተይዛችሁ አደጋ እንዳያገኛችሁ ኑ ወደ ወደቡ ግቡ» ብሎ ቃሉን ያሰማል። የመርከቡ መሪ ግን ወዲያውኑ ከመግባት ፋንታ የሰማውን ቃል ቸል እያለ ይዘገያል። ነፋሱና ማዕበሉ ያን መርከብ ጥቂት በጥቂት ይወስዱታል ከወደቡም ያርቁታል፥ የሚያገኘውም ጥፋት የሚያሰቅቅ ነው። እንደዚሁም የሰማነውን ቃል አንቆ ወደ መዳን እንዳንገባ የሚያስቀረን ብዙ ጊዜ የዚህ ዓለም ሐሳብና የባለጠግነት ማታለል፥ በመካከልም የሚገባው የሌላው ነገር ምኞት ነው (ማር. 4፡19)።

ክርስቲያንን የሚወስድ ሌላ ነገር ደግሞ አለ። እነዚያን ዕብራውያንን ወደ መውሰድ የደረሰው ኀዘንና ስድብ ስደትም ነበረ፤ ይህም እኛን ዛሬ ሊወስድ ይችላል። አብዛኛውን ጊዜ ግን የሚወስደን ስንፍና ነው። መጽሐፍ ቅዱሳችንን ማንበብና ያነበብነውን ነገር ማሰላሰል፥ ወይም የግል ጸሎትን ማድረግ እንተዋለን። ወይም እሁድ ዕለት ከክርስቲያኖችም ጋር መሰበብ ሰልችቶን እንተወዋለን። የምንወሰደውም ጥቂት በጥቂት ነው እንጂ የፍጥነት ነገር አይደለም። በዚያ በፈሳሽ ውኃ ላይ እንዳለው ጭራሮ ነው። ፈሳሹ ቀስ በቀስ ይወስደዋል። ክርስቲያንም እንደዚሁ ቀስ በቀስ እያንሸራተተ ይሄዳል። ወደ ሌላ ሁሉ የሚያደርስ መጀመሪያው እርምጃ ነውና ከሰማነው ነገር ምናልባት እንዳንወሰድ ዕለት ዕለት እንጠንቀቅ።

ለ) «እንዲህ ያለ ታላቅ መዳን» (ቁ. 3) እግዚአብሔር በብሉይ ዘመን መጨረሻ ላይ በልጁ የተናገረው እኛም የሰማነው ነገር ይህ ነው። የታላቅ መዳን ነገር ነው። «ታላቅ መዳን ምን ማለት ነው?» ቢሉ፥ ብዙዎች ሰዎች «በኃጢአታችን ምክንያት ከሚመጣብን ኩነኔ ማምለጥ ወይም መዳን ማለት ነው» ይላሉ። እርግጥ! ሆኖም ይህ ብቻ አይደለም። እውነት ነው፥ ከኩነኔ መዳን ትልቅ ነገር ነው፤ ቢሆንም ቅዱስ ጴጥሮስ «እግዚአብሔር ሰላምን እየሰበከ ላከ» ሲል ፍሬ ነገርን ተናግሮአል። (ሐዋ. 10፡36)። አዳም ኃጢአትን በሠራ ጊዜ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የነበረው ሰላምና ኅብረት መገናኘትም ጠፋ ጠብም ገባ። (ዘፍ. 3፡23፥24)። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመካከል ገብቶ እግዚአብሔርንና ሰውን አስታረቀ። (2 ቆሮ. 5፡18) ስለዚህ አሁን እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን ሰበከ፤ ማለት ጠብ አለቀ ሰውም እንደ ገና ወደ ማይቋረጥ ኅብረት ተጠራ። «እንዲህ ያለ ታላቅ መዳን» የተባለው ይህ ነው። ፍጹም ወይም ሙሉ መዳን የኅብረት መመለስ ነው። ሰው ከኩነኔ እንደ ዳነ ብቻ አይደለም፤ በአዳም ኃጢአት ምክንያት ጠፍቶበት ከነበረው ሁሉ እንደ ዳነ ነው እንጂ። በዚህ ፍጹም መዳን ውስጥ ጽድቅ፥ ቅድስና፥ የሰውነታችን ቤዛ፥ ክብርም ሁሉ ተጠቅልሎአል። (ሮሜ. 8፡23፥30)። ይህ ሁሉ የተገኘው ግን ያ የዱሮ ኅብረት ተመልሶ እንዲገኝ ነው። የመዳን ዋና ዓላማ ይህ ነው፥ የዘላለምም ሕይወት ይህ ነው። (ዮሐ. 17፡3) እንዲህ ያለውን ታላቅ መዳን ቸል ብንለው በእውነቱ እንዴት እናመልጣለን?

ሐ) «እግዚአብሔር፡... መንፈስ ቅዱስንም በማደል አብሮ መሰከረለት።» (ቁ. 4) እነዚህ በ1 ቆሮ. 12፡4-11 የተናገረባቸው ልዩ የሆነ መንፈሳዊ ጸጋዎች ወይም ስጦታዎች ናቸው። እነዚህ ስጦታዎች ለክርስቲያን ሃይማኖት እውነተኝነት የሚመሠክሩ ነበሩ።

[5] ስለ እርሱ የምንናገርበትን የሚመጣውን ዓለም ለመላእክት ያስገዛው አይደለምና።
[6] ነገር ግን አንዱ በአንድ ስፍራ፡- ታስበው ዘንድ ሰው ምንድን ነው? ወይስ
ትጎበኘው [7] ዘንድ የሰው ልጅ ምንድን ነው? ከመላእክት ይልቅ በጥቂት
አሳነስኸው፤ [8]የክብርና የምስጋናን ዘውድ ጫንህለት በእጆችህም ሥራ ላይ
ሾምኸው፤ ሁሉን ከእግሮቹ በታች አስገዛህለት ብሎ መሰከረ። ሁሉን ከእርሱ በታች
ባስገዛ ጊዜ ያልተገዛለት ምንም አልተወምና። አሁን ግን ሁሉ እንደ [9] ተገዛለት ገና
አናይም፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋ ስለ ሰው ሁሉ ሞትን ይቀምስ ዘንድ፥
ከመላእክት ይልቅ በጥቂት አንሶ የነበረውን ኢየሱስን ከሞት መከራ የተነሣ የክብርና
የምስጋናን ዘውድ ተጭኖ እናየዋለን።

ደራሲው ብርቱ ማስጠንቀቂያ በመጻፍ ዕብራውያን ያን ታላቅ መዳን መቀበላቸውን ካረጋገጠ በኋላ አሁን ወደ ምዕ. 1፡14 ሐሳብ ይመልሳቸዋል። መላእክት ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም መናፍስት ናቸው እንጂ እነርሱ የሚመጣውን ዓለም፥ ማለት አዲሲቱ ኢየሩሳሌም የተባለችውንና ንጉሥዋ ኢየሱስ የሚሆነውን አዲሲቱን ምድር አይገዙም። (ምዕ. 11፡16፤ ራእ. 21፡1፥2) ይህ ግዛት በመዝ. 8 ላይ እንደ ተባለው ሁሉ ለመላእክት ሳይሰጥ ለሰው ተሰጥቶአል። እግዚአብሔር ለሰው የማይቋረጥ መግባትና ኅብረት ሊሰጥና ሰውን ወደ ግርማ መንግሥቱ ሊያደርስ አስቦ ሰውን በመጀመሪያ በመልኩ እንደ ምሳሌው ፈጥሮ ንጉሥና ገዥ አደረገው፥ ለእርሱም ሁሉ አስገዛ። (ዘፍ. 1፡26-28፤ ሮሜ 5-2።) ስለዚህ ክብር ዳዊት በዚያ በመዝ.8 ላይ እየመሰከረ «ታስበው ዘንድ ሥጋም ለብሰህ ትጎበኘው ዘንድ ሰው ምንድር ነው?» ብሎ እዚህ ከቁ.6-8 ድረስ የተጠቀሰውን ቃል ጽፎአል። እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር ከመላእክት «በጥቂት»፥ ማለት በጥቂት ያህል ወይም ለጥቂት ጊዜ፥ አሳነሰው፤ ያሰበለት መጨረሻ ሐሳቡ (እቅዱ) ግን የክብርና የምስጋናን ዘውድ እንዲጭን ነበረ፤ ሹመትም ሰጥቶት ከእግሮቹ በታች ሁሉን አስገዛ። ሰው ግን ኃጢአትን በመሥራቱ ወደቀ፥ መልኩ ተበላሸ፥ የምድር አራዊትም ግዛቱን እስኪከላከሉት ድረስ ከሹመቱ ተዋረደ። እግዚአብሔር ሁሉንም አስገዝቶለት ነበረ፥ ነገር ግን ሰውን ዛሬ ብንመለከት «ሁሉ እንደ ተገዛለት ገና አናይም»። «ገና» የተባለበቱ ወደ ቀደመው ክብር ተመልሶ ሁሉን ይገዛ ዘንድ ገና የእግዚአብሔር ሐሳብ ነውና። ቢቆይ እንኳ ሐሳቡ (እቅዱ) ገና ይፈጸማል። ተራ ሰው ሁሉ ዛሬ ሲገዛ አናየውም፥ ነገር ግን ኢየሱስ ሲገዛ እናየዋለን፥ እርሱም ሰው ነው! እግዚአብሔር በምሕረቱና በጸጋው ባለ ጠጋ ነውና (ኤፌ. 2፡4፥7) ኢየሱስ ስለ ሰው ሁሉ ሞትን ይቀምስ ዘንድ ከመላእክት ለጥቂት ጊዜ አንሶ ሞተ፥ የሞትንም መከራ ስለ ታገሠ፥ በዚህ ምክንያት፥ እግዚአብሔር ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው፥ የክብርንና የምስጋናንም ዘውድ ጫነለት። (ፊልጵ. 2፡9-11።)

**ማስገንዘቢያ፡-**

**ሀ) «ታስበው ዘንድ ሰው ምንድር ነው? ወይስ ትጎበኘው ዘንድ የሰው ልጅ ምንድር ነው?» (ቁ.6) እውነት ነው፥ ወልደ እግዚአብሔር ይሞትለት ዘንድ ሰው ምንድር ነው? ከመላእክት ሁሉ በላይ ከፍ ከፍ ያለው ሰውን ከውርደቱ አስነሥቶ እርሱ ባለበት በአባቱ መንግሥት የክብሩ ተካፋይ እንዲያደርገውና ለተቸገሩት ለተፈተኑትም የሚምርና የታመነ**

ሊቀ ካህናት እንዲሆንላቸው ለጥቂት ጊዜ ከመላእክት ሁሉ አነሰ። (ዮሐ. 17፡24) እግዚአብሔር ሰውን ሲያስብ ሊያድነውም ሲጎበኘው በእውነት ምንኛ ያስገርማል!

ለ) «አሁን ግን ሁሉ እንደ ተገዛለት ገና አናይም።» (ቁ.8) እውነት ነው፤ የሁሉ ገዢ እንዲሆን የተፈጠረው ሰው ግዛቱን አጥፍቶ ዛሬ ባሪያ ሆኖ ይገኛል። እንደምን፣ ቢሉ፥ ራሳቸውንም ሆነ መጥፎ ባሕርያቸውን ሊገዙ የማይችሉ፥ የኃጢአትም ባሪያዎች ሆነው የሚኖሩ ብዙዎች አሉ። (ዮሐ. 8፡34) በሁሉም ላይ ሞት ነግሦአል። (ሮሜ 5፡14፥17) ከዚህ ባርነት ሁሉ ነፃነት አውጥቶ ወደ ጥንቱ ክብራችን የሚመልሰን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። (ዮሐ. 8፡36፤ ሮሜ 8፡18-25)።

ሐ) «ስለ ሰው ሁሉ» (ቁ. 9) ኢየሱስ ያደረገውን «ስለ ሰው ሁሉ» (ቁ. 9)፥ የሰውም «ራስ» (ቁ. 10)፥ ስለ እኛም «ቀዳሚ» (ምዕ. 6፡20) ሊሆን አደረገው። ኢየሱስ እኮ ሰው ነው፥ ስለ ሰውም ገብቶአል። እግዚአብሔር ከፍ ከፍ ያደረገው ሰውን ነው፥ ኢየሱስም የክብርና የምስጋናን ዘውድ ተጭኖ ስናየው ሰውን ሲገዛ እናያለን። እርሱ እንዳለ እኛ ደግሞ እንዲሁ በዚህ ዓለም ነን። (1 ዮሐ. 4፡17) እርሱ ገዥ እንደ ሆነ ሁሉ እኛም ገዦች ነን፤ ነገር ግን ዛሬ የምንገዛ «በእርሱ» ስንሆን ብቻ ነው። በሚመጣው ዓለም ግን (ቁ. 5) እንዲያው እንገዛለን። (1ዮሐ. 3፡2) እርሱ የሚገዛ ስለ ሰው ሁሉ እንደ ሆነ፥ ቅርንጫፎችም በግንድ ሕዋሳትም በአካል እንደ ሆኑ እንዲሁም እኛ ከእርሱ ጋር እንደ ተዋሐድን ስንቀጥር (ዮሐ. 15፡5፤ 1ቆሮ. 12፡27፤ ሮሜ 6፡11)፥ በእርሱ መግዛት በኃጢአትና በሞት ፍርሃት ገናም ሲገዛልን በማይታይ ነገር ሁሉ ላይ ድል መንሣትንና መግዛትን እንደ ገና እናገኛለን። እርሱ የሚገዛ ስለ ሰው ሁሉ ስለ እያንዳንዳችን ነው።

## ቁ. 10-18

10 ብዙ ልጆችን ወደ ክብር ሲያመጣ የመዳናቸውን ራስ በመከራ ይፈጽም ዘንድ፥
ከእርሱ የተነሣ ሁሉ በእርሱም 11፥12 ሁሉ ለሆነ፥ ለእርሱ ተገብቶታልና።
የሚቀድሰውና የሚቀደሱት ሁሉ ከአንድ ናቸውና፥ ስለዚህም ምክንያት፡- ስምህን
ለወንድሞቼ እነግራቸዋለሁ በማኅበርም መካከል በዜማ አመሰግንሃለሁ፤
13 ደግሞም፡- እኔ በእርሱ እታመናለሁ፤ ደግሞም እነሆኝ እኔን እግዚአብሔር
የሰጠኝንም ልጆች ሲል ወንድሞች 14፡15 ብሎ ሊጠራቸው አያፍርም። እንግዲህ
ልጆቹ በሥጋና በደም ስለሚካፈሉ፥ እርሱ ደግሞ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን
በሞት እንዲሽር፥ ይኸውም ዲያብሎስ ነው፥ በሕይወታቸውም ሁሉ ስለ ሞት
ፍርሃት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ሁሉ ነፃ እንዲያወጣ፥ በሥጋና በደም እንዲሁ
16 ተካፈለ። የአብርሃምን ዘር ይዞአል እንጂ የያዘው መላእክትን 17 አይደለም።
ስለዚህ የሕዝብን ኃጢአት ለማስተሰረይ፥ ለእግዚአብሔር በሆነው ነገር ሁሉ
የሚምርና የታመነ ሊቀ ካህናት እንዲሆን፥ በነገር ሁሉ ወንድሞቹን ሊመስል
ተገባው። 18 እርሱ ራሱ ተፈትኖ መከራን ስለ ተቀበለ የሚፈተኑትን ሊረዳቸው
ይችላልና።

በቁ. 9 ላይ ኢየሱስ ስለ ሰው ሁሉ ሞትን እንደ ቀመሰና የሞትንም መከራ ስለ ተቀበለ እግዚአብሔር የክብርንና የምስጋናን ዘውድ እንደ ጫነለት አንብበናል። አሁንም ያን መከራና ሞት የተቀበለበት ምክንያት ምን እንደ ሆነ እናነባለን። ያ መከራና ያ ሞት የግዴታ ነገሮች ናቸው። ስለምን? ቢሉ፥ ኢየሱስ ሰውን ከጥፋት የሚያድን ከሆነ፥ ስለ ሰውም የሚምርና የታመነ

ሊቀ ካህናት፥ የሚሆን ከሆነ መከራና ሞት የግድ ይቀበል ነበር። ያለ መከራ ሰውን ለማዳን ሊቀ ካህናትም ለመሆን ባልቻለም ነበር።

በእርሱ አስነሽነት ሁሉም የሆነ የሁሉም መድረሻ የሆነው እግዚአብሔር ጥቂቶችን ሳይሆን ብዙዎችን፥ ዓለማውያንን ሳይሆን ልጆችን፥ ወደ ክብር ሊያመጣ ሲያስብ እነዚያን ልጆች ወደ ደኅንነት የሚመራቸውን አለቃቸውን (ም. 12፡2) በመከራ ይፈጽም ዘንድ፥ ማለት ለሚሠራው ሥራ ፈጽሞ ተገቢና ቻይ ያደርግ ዘንድ ተገባው። (እግዚአብሔር «ፈጸመው» ሲባል ትርጉሙ ይህ ነውና። ም. 5፡8-10ን ተመልከት።) የሚመራቸው፥ ቅዱሳን (ም. 10፡10፥14፤ 13፡12)፥ ከእግዚአብሔር የተወለዱ ልጆች ናቸውና (ዮሐ. 1፡12፥13) ራሱ ልጅ የሆነ ኢየሱስ «ወንድሞች» ሊላቸው አላፈረም፡ (ዮሐ. 20፡17)። ይህን የሚያስረዱ 3 ጥቅሶች አሁን ቀርበዋል፥ በእያንዳንዱም ላይ ኢየሱስ ሲናገር እንሰማዋለን። መጀመሪያው ጥቅስ የመጣው ከመዝ. 21 ነው፤ ይህም መዝሙር ስለ ክርስቶስ እንደሚናገር ሰው ሁሉ ያምናል። በዚያ መዝሙር በቁ. 22 ላይ ክርስቶስ ስለ «ወንድሞቹ» ይናገራል፥ ራሱም በማኅበር መካከል ከሰዎች እንደ አንዱ ሆኖ እግዚአብሔርን በዜማ ሲያመሰግን ይታያል። ሁለተኛውና ሦስተኛው ጥቅሶች ከትንቢተ ኢሳይያስ የተቀዱ ናቸው። በዚያ ትንቢት በም. 8፡17፥18 ላይ በኢሳያስ የተነገረው ቃል በመንፈሳዊ ረገድ ተተርጉሞ የኢየሱስ ቃል ሆኖ ተቆጥሮአል። እዚህ ላይ ኢየሱስ እንደ ሌሎች ሰዎች ሁሉ ሆኖ በእግዚአብሔር ሲታመንና እርሱ ልጅ ሲሆን እግዚአብሔርም ስለ ሰጠው ስለ ሌሎች ልጆች ሲናገር ይገኛል። (ዮሐ. 17፡6-12፥24)። ይህን በማድረግ ኢየሱስ ወንድሞች ያደርጋቸዋል። ስለዚህ እርሱ በፊቱ ወደ ነበረው ክብርና ደስታ ሲጓዝ (ም. 12፡2) የብዙ ወንድሞች በኩርና የብዙ ልጆች መሪ አለቃ ነበረ።

አባቱ እነዚህን ልጆች አድኖ ወደ ክብር ሊያመጣ ነበረና (ቁ. 10) ክርስቶስ እንደ እነርሱ ሆኖ በሥጋና በደም ተካፈለ። ይህን ያደረገው ሊሞት እንዲችል ነው። መሞት ለምን ያስፈልገዋል? ቢባል፥ የሚያድናቸው ከሞት ኃይልና ከሞት ፍርሃት ስለ ሆነ ነው። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና፥ ሰውም ሁሉ ኃጢአትን ሠርቶአልና (ሮሜ 6፡23፤ 3፡23)፥ የሞት ሥልጣን ለዲያብሎስ ተሰጥቶአል፤ እርሱም በሰው ሁሉ ላይ ሠልጥኖአል። ኢየሱስ ግን በመሞቱ የኃጢአትን ደመወዝ በሙሉ ለሰው ሁሉ ስለ ከፈለ (ም. 9፡15፥28) በሞት ላይ ያለው የሰይጣን ሥልጣን ተሽሮአል፥ ሰውም ከሞት ኃይል ድኖአል። (1ቆሮ. 15፡56፥57)። እንደዚሁም ደግሞ ክርስቶስ ከሞት ፍርሃት አድኖናል። እንደምን? ቢሉ፥ ክርስቶስ ስለ ሰው ሁሉ ሞትን ቀመሰ ጣዕሙንም ፈጽሞ አወቀ (ቁ. 9)፤ እንደዚህም ቢሞት እንኳ የሞትን እስራት በጥሶ ከሙታን ተነሣና ለተከታዮቹ ሁሉ የሕይወትን መንገድ አበጀ። ስለዚህ ዛሬ ክርስቲያን እድሜውን ሁሉ ተይዞበት ከነበረው ፍርሃት ድኖአል። ሰው ሞትን በመፍራት ምክንያት በባርነት ተይዞ ነበር፥ አሁን ግን ከዚያ ከሞት ውል ነጻ ወጥቶአል። ክርስቶስ የአብርሃምን ዘር በእጁ ይዞ ለመርዳት ቀርጦአል እንጂ መላእክትን ለመርዳት አላሰበምና የመላእክትን ሁኔታ ትቶ ሰው እስኪሆን ድረስ ራሱን አዋረደ (ፊልጵ. 2፡6-8)። ሰውን ለመርዳት ቆርጦአልና የሰውን ኃጢአት ለማስተሰረይ ድካሙንና ችግሩን መፈተኑንም ተረድቶ የሚምርና ምንጊዜም ሳይተወው እስከ መጨረሻ ድረስ ታማኝ የሆነ ሊቀ ካህናት እንዲሆንለት ፈጽሞ ወንድሞቹን ሊመስል ተገባው። በነገር ሁሉ ወንድሞቹን እየመሰለ ተፈቶ መከራን ስለ ተቀበለ (ም. 4፡11) ኢየሱስ ዛሬ የሚፈተኑትን ሊረዳቸው ይችላል።

ማስገንዘቢያ፡-

ሀ) «ስለ ሰው ሁሉ ሞትን ይቀምስ ዘንድ።» (ቁ. 9) ሰው ሆይ፥ ክርስቶስ ስለ ሰው ሁሉ ሞትን እንደ ቀመሰ፥ ስለዚህ አንተ እንደማትቀምሰው ተረድተሃልን? «ሞትን እቀምሳለሁ ጣዕሙም መራራ ይሆናል» ብለህ በሞት ፍርሃት ተይዘህ እድሜህን ሁሉ ትጨርሳለህን? አይ! አስፈላጊ አይደለም። ክርስቶስ ስለ ሰው ሁሉ ሞትን ቀምሶአል። እርሱ ስለ አንተ ቀምሶታልና አንተ አትቀምሰውም። እነዚህን ከዚህ ቀጥለው የተጻፉትን ጥቅሶች አውጥተህ እውነተኛ ክርስቲያን ከሆንህ ሞትን እንደማትቀምስ የእግዚአብሔርን ቃል አንብበህ እመነው። «ሞትን አያይም» ተባለ። ዮሐ. 8፡51፤ 11፡25፥26፤ 5፡24፤ ማቴ. 16፡28። ታምነዋለህን? የሞት መውጊያ ተወግዶአል፥ ሞትም አሁን የሕይወት መግቢያ ብቻ ነው። (1ቆሮ. 15፡55-57)።

ለ) «የመዳናቸው ራስ» (ቁ. 10)። ኢየሱስ መሪ አለቃችን ነው። ኢያሱ የእስራኤልን ሕዝብ በተስፋ ወደ ተሰጣቸው አገር ወደ ከነዓን እንደ መራቸው እንዲሁም ኢየሱስ ክርስቲያኖችን ወደ መዳናቸው ፍጻሜ ይመራቸዋል። ሆኖም ነገሩ እንደ መርፌና እንደ ክሩ ነው። መሪአችን ወደ ሄደበት ዘንድ እኛ ልንከተል ብንፈልግ በእርሱ ላይ እንድንታሰር ያስፈልጋል። አንባቢ ሆይ፥ በክርስቶስ ላይ ታስረሃልን?

ሐ) «የመዳናቸውን ራስ በመከራ ይፈጽም ዘንድ፡.... ተገብቶታልና።» (ቁ. 10) እግዚአብሔር ይህን ሲያደርግ እንዴት «ተገብቶታል»? ቢሉ፥ እግዚአብሔር ይህን ሲያደርግ ቅድስናውን ስላረጋገጠ፥ ኃጢአትን መጥላቱን ስለ ገለጠ፥ ጽድቁን ስላጸና፥ የመንግሥቱን ሕግ ስላስከበረ፥ ለሰው የሚሆን ፍቅሩን ስላስረዳ (ሮሜ 5፡8)፥ ያደረገው ሥራ ተገብቶታል። ከዚህ ሌላ ደግሞ፥ ብዙ ልጆችን ወደ ክብር የሚያመጣ ከሆነ የመዳናቸውን ራስ በነገር ሁሉ ተገቢና ቻይ ያደርግ ዘንድ «ይፈጽም ዘንድ» ተገቢ ነገር መሆኑን አንዘነጋም።

መ) «የአብርሃምን ዘር ይዞአል።» (ቁ. 16)። ምነው፥ ሰውን ሁሉ፥ ዓለምን ሁሉ ይዞ የለም ወይ? ቢሉ፥ የለም፥ የአብርሃምን ዘር ብቻ ይዞአል። ክርስቶስ ለሁሉ፥ ለዓለም በሞላው፥ እንደ ሞተ እውነት ነው (ዮሐ. 3፡16፤ ሮሜ 10፡13)፤ ሆኖም የሞቱ ፍሬ (ጥቅም) ማዳኑን በእምነት ለሚቀበል ብቻ ነው። (ማር. 16፡16፤ ሐዋ. 16፡31፤ ዕብ. 11፡6)። በዚህ ምዕራፍ ላይ ደጋግመን እንደምናይ ኢየሱስ ወደ ክብር የሚያመጣቸው «ልጆችን» ብቻ ነው። ሰው የሚድን፥ ማለት ወደ ክብር የሚደርስ ከሆነ ዳግመኛ ከእግዚአብሕር ይወለድ ዘንድ ያስፈልገዋል (ዮሐ. 3፡3)፤ የሚወለደውም ኢየሱስን እንደግል መድኃኒቱ በእምነት ሲቀበል ነው። (ዮሐ. 1፡12፥13)። ስለዚህ «የአብርሃምን ዘር ይዞአል» ተባለ እንጂ «ሰውን ይዞአል» አልተባለም፥ የአብርሃም ዘር «ከእምነት የሆኑቱ» ናቸውና፥ (ገላ. 3፡7፥9፥29)።

በዚህ ቁጥር ላይ ደራሲው ስለ መላእክት 3ኛውን ቃል መናገሩን እናስተውል። በም. 1፡4 ላይ ኢየሱስ «ከመላእክት አብዝቶ ይበልጣል» ብሎአል። ቀጥሎም በም. 2፡5 ላይ «የሚመጣውን ዓለም ለመላእክት ያስገዛው አይደለም» ብሎአል። አሁን በዚህ ቁጥር ላይ «የአብርሃምን ዘር ይዞአል እንጂ የያዘው የመላእክትን አይደለም» ይላል። ከዕብራውያን መካከል መላእክትን ከሚገባ በላይ ያከበሩ ሰዎች የተገኙ ይመስላል።

ሠ) «የሚምርና የታመነ ሊቀ ካህናት እንዲሆን በነገር ሁሉ ወንድሞቹን ሊመስል ተገባው።» (ቁ. 17)። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ ካህናታችን እንዲሆን በሥጋና በደም ተካፈለ። ኃጢአት ከእግዚአብሔር ዘንድ ይለያልና ዓይነተኛ የካህን ሥራ ኃጢአትን በማስወገድ ሰውን ወደ እግዚአብሔር ለማቅረብ ነው። እንዲሁም ደግሞ የሚፈተኑትን ሰዎች ጩኸት ሰምቶ ሮጦ የሚረዳቸው ካህኑ ነው። ይህን ሁለቱን ሥራ ለመሥራት ኢየሱስ ተገቢና ቻይ ነው፥ እንደ እርሱም ሊረዳን የሚችል ሊቀ ካህናት የለም። በዓለም ላይ በመሞቱ የኃጢአታችንን ማስተስረያ ሆኖ የነበረብንን ዕዳ በሙሉ በመክፈል ከእግዚአብሔር ጋር አስታረቀን (ሮሜ 3:25፤ 2ቆሮ. 5:18)፥ አሁንም በመንግሥተ ሰማያት ሕያው ሆኖ በመኖሩ ጩኸታችንን ሰምቶ ሊረዳን ይችላል። ይኸውም በተለይ ወንድሞቹን በነገር ሁሉ መስሎ ራሱ ተፈትኖ መከራን ስለ ተቀበለ ነው። የፈተናን መከራ ስለ ተቀበለ የፈተናን ብርታት በሞላ አውቆአል። ይልቁንም የፈተናን ብርታት የሚያውቀው ችሎ እስከ መጨረሻ ድረስ ኃጢአትን የማይሠራ ነውና እንደ ኢየሱስ የፈተናን ብርታት ያወቀ የለም። ያውቀዋልና ይምረናል፥ በማናቸውም ፈተና ሁሉ የሚፈተነውን ክርስቲያን ሊረዳ ዝግጁ ነው።

# ምዕራፍ ሦስት

## እስራኤላውያን የተነገረውን ቃል አላመኑምና ወደ ተስጣቸው ዕረፍት አልገቡም።

ደራሲው፥ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ወይም ሐዋርያ ሆኖ በብሉይ ዘመን መጨረሻ ላይ ፍጻሜ የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል ስለ ተናገረው ስለ ልጁ በም. 1 ላይ ጽፎአል፤ ፈጽሞ አምላክ ነው ብሎም ታላቅነቱን አስረድቶአል። እንደዚሁም፥ ስለ ሰው ሁሉ ሊቀ ካህናት ሆኖ ኃጢአትን ስለሚያስተሰርይና ሰውን ወደ እግዚአብሔር ስለሚያቀርብ ስለ ኢየሱስ በም. 2 ላይ ጽፎአል፤ ፈጽሞ ሰው ነው ብሎም በሁሉም በኩል ተገቢነቱን ገልጦአል። አሁንም ኢየሱስን አትኩረው እንዲመለከቱትና እርሱ ከብሉይ ኪዳን ሐዋርያና ሊቀ ካህናት ከሆነው ከሙሴ እንደሚበልጥ ተረድተው እንደ አባቶቻቸው ሆነው ባለመታዘዝና ባለማመን ጠንቅ ከሃይማኖታቸው ወደ ኋላ በማፈግፈግ ወደ እግዚአብሔር ዕረፍት፥ ወደ ደኅንነት ሙላት፥ ከመግባት እንዳይቀሩ ደራሲው በም. 3 ላይ ክርስቲያን የሆኑትን ዕብራውያን ይመክራቸዋል።

በዚህ ምዕራፍ ላይ ደራሲው የአዲሱን ኪዳን ሐዋርያ ታላቅነትና የሊቀ ክህንነቱንም ፍጹም ተገቢነት ገና እያስታወሰ (ቁ. 1-6) ያመኑትን ዕብራውያን እንዳይመለሱና እንዳይከዱ ያስጠነቅቃቸዋል (ቁ. 7-19)።

### ቁ. 1-6

1 ስለዚህ፥ ከሰማያዊው ጥሪ ተካፋዮች የሆናችሁ ቅዱሳን ወንድሞች ሆይ፥
የሃይማኖታችንን ሐዋርያና ሊቀ ካህናት 2 ኢየሱስ ክርስቶስን ተመልከቱ፤ ሙሴ
ደግሞ በቤቱ ሁሉ የታመነ እንደሆነ፥ እርሱ ለሾመው የታመነ ነበረ። 3 ቤትን
የሚያዘጋጀው ከቤቱ ይልቅ የሚበልጥ ክብር እንዳለው መጠን፥ እንዲሁ እርሱ
ከሙሴ ይልቅ የሚበልጥ 4 ክብር የተገባው ሆኖ ተቆጥሮአልና፥ እያንዳንዱ ቤት
በአንድ ሰው ተዘጋጅቶአልና፥ ሁሉን ያዘጋጀ ግን እግዚአብሔር ነው። 5 ሙሴስ
በኋላ ስለሚነገረው ነገር ምስክር ሊሆን 6 በቤቱ ሁሉ እንደ ሎሌ የታመነ ነበረ፥
ክርስቶስ ግን እንደ ልጅ በቤቱ ላይ የታመነ ነው፤ እኛም የምንደፍርበትን
የምንመካበትንም ተስፋ እስከ መጨረሻው አጽንተን ብንጠብቅ ቤቱ ነን።

የእግዚአብሔር ቅዱስ ሕዝብ የሆኑት እስስራኤል ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥሪ ተቀብለው በፊታቸው ወደ ተሰጣቸው ተስፋ ወደ ከነዓን፥ እንደ ተጓዙ እንዲሁም እነዚህ በክርስቶስ ኢየሱስ የተቀደምሱት ዕብራውያን (1ቆሮ. 1፡2) ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥሪ ተቀብለው ወደ ተሰጣቸው ተስፋ በክርስቶስ ወዳለው ሙሉ ደኅንነት፥ ይጓዛሉ። (ፊል. 3፡14፤ 2ጢሞ. 1፡9) እነዚያ እስራኤላውያን የሃይማኖታቸው ሐዋርያና ሊቀ ካህናት የሆነውን ሙሴን እንደ ተመለከቱት እንዲሁ እነዚህ ዕብራውያን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲመለከቱ ያስፈልጋቸዋል። በተለይም መመልከት የሚያስፈልጋቸው እርሱ ከነቢያትና ከመላእክት እጅግ ስለሚበልጥና ሥራው ከሁሉም ይልቅ ጠቃሚ ስለ ሆነ ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስን ሊመለከቱ ሲጀምሩ ከሁሉ አስቀድመው ሙሴ በእግዚአብሔር ቤት፥ በእስራኤል፥ የታመነ እንደ ነበረ እንዲሁም ኢየሱስ የታመነ እንደነበረ ያያሉ። ነገር ግን ይህ ብቻ አይደለም፤ አትኩረው ቢመለከቱት እርሱ ከሙሴ እንደሚበልጥ ያያሉ! ይህም ለዕብራውያን እጅግ በጣም አስገራሚ ሐሳብ ነበረ። እግዚአብሔር ራሱ «በመካከላችሁ ነቢይ ቢኖር እኔ እግዚአብሔር በራእይ እገለጥለታለሁ፥ ወይም በሕልም እናገረዋለሁ። ባሪያዬ ሙሴ

ግን እንዲህ አይደለም፡ እርሱ በቤቴ ሁሉ የታመነ ነው። እኔ አፍ ለአፍ በግልጥ እናገረዋለሁ» ብሎ መስክሮለት ነበርና (ዘኍ. 12፡6-8) እነርሱ ሙሴ ከነቢያት ሁሉ የተለየ የበለጠም መሆኑን አስበዋል። ታዲያ ኢየሱስ ከእርሱ ይበልጣልን? ይህማ ግሩም የሆነ ሐሳብ ነው! በእውነት መብለጡን ለማስረዳት ደራሲው አሁን ክርስቶስንና ሙሴን ደፍሮ ያነጣጥራቸዋል። በም. 1፥4 ላይ አድርጎ እንደ ነበር አሁንም መጠንን እየጠቀሰ የክርስቶስን ብልጫ ያስረዳል። እስኪ፥ ዕብራውያን ራሳቸው ይፍረዱ። ማናቸው ይከብራል? ሞላ ሕዝብን ያዘጋጀው ነውን፥ ወይስ ከዚያ ሕዝብ አንዱ ነው? ያዘጋጀው አይደለምን? ነው! ሁሉን ያዘጋጀ እግዚአብሔር ነው፥ ያዘጋጀውም በልጁ ነው! (ም. 1፡2)፥ ስለዚህ ልጁ (ክርስቶስ) በቤቱ ውስጥ ከሚገኘው ከማናቸውም ሰው፥ ከሙሴ እንኳ ይበልጣል። ሁለተኛም ማስረጃ አለ። ሙሴ ራሱ ፍጻሜ ነገር ሳይሆን ለሚመጣው ነገር፥ ማለት ለክርስቶስና እርሱ ለሚናገረው ቃል፥ ምስክር ብቻ ነበረ። (ዘዳ. 18፡15፥18)። እርሱ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ እንደ ከበረ ሎሌ ነበረ፥ ክርስቶስ ግን እንደ ልጅ በቤቱ ላይ ጌታ ነው። (ዮሐ. 8፡35)። ከማናቸውም ሎሌ ጌትየው ይበልጥ የለምን? ይበልጣል! እንዲሁም ክርስቶስ ከሙሴ በለጠ። ሙሴ ስለ እግዚአብሔር የሚያውቅ ሲሆን ክርስቶስ ራሱ እግዚአብሔር ነው።

በሙሴ ዘመን የእግዚአብሔር ቤት የተባለው እስራኤል ነው፥ በክርስቶስም ዘመን የእግዚአብሔር ቤት ቤተ ክርስቲያን የምንሆን እኛ ነን (1ቆሮ. 3፡9፥16፥17፤ 1ጴጥ. 2፡5፤ 4፡17)። ሆኖም በክርስቶስ ያለንን አለኝታና ተስፋ እስከ መጨረሻው ድረስ አጽንተን ካልጠበቅን ቤቱ አይደለንም። በዚህ ራሳችንን ሌሎችንም ልንፈትን እንችላለን። የጸናው ሰው ከቤቱ ነው፥ ያልጸናውም ከቤቱ አይደለም። (1ዮሐ. 2፡19)።

<u>ማስገንዘቢያ፡-</u>

ሀ) «ኢየሱስ ክርስቶስን ተመልከቱ።» (ቁ. 1) ክርስቲያን ሁሉ ክርስቶስን አትኩሮ መመልከት ያስፈልገዋል። ቅዱስ ዳዊት «እግዚአብሔር ቸር እንደ ሆነ ቅመሱ እዩም» እንዳለ (መዝ. 33፡8) ክርስቶስ በእውነቱ ማን እንደ ሆነ ከዚህ በፊት ለእኛ ምን እንደ ሠራ፥ ዛሬም ምን ሊሠራልን እንደሚችል መርምረን ካልተገነዘብን ሃይማኖታችንን እስከ መጨረሻው አጽንተን ልንጠብቅ ከቶ አንችልም። ስለ ክርስቶስ ማወቅ ብቻ አይበቃም፤ መርምረን ተመልከተን እርሱን ማወቅ ያስፈልገናል። በማቴ. 16፡13-16 ላይ እንደ ተባለው ነገር ነው። ሌሎች ሰዎች ስለ ሰው ልጅ የሚሉትን መስማት ብቻ አይደለም፤ እኛ እያንዳንዳችን ክርስቶስ ለእኛ ማን እንደ ሆነ ማወቅ ያስፈልገናል። «ወደ ሰማይ ወፎች ተመልከቱ» እንደ ተባለው ደግሞ (ማቴ. 6፡26) ወደ ክርስቶስ ተመልከተን የእርሱን ነገር ስናሰላስል ክብሩን እናያለን። (1ጴጥ. 2፡6፥7) ወደ ኋላ እንዳናፈገፍግ የሚጠብቀን ክርስቶስን ስንመለከት ነው። መምህራን ሆይ፥ ይህን ልብ አድርጉ። ብዙዎች ተማሪዎቻችን ወደ ኋላ የሚያፈገፍጉት ክርስቶስን አትኩረው ባለመመልከት ነው። ኢየሱስ ክርሶትስን አሳዩ ተማሪዎቻችሁም ሃይማኖታቸውን አጽንተው ይጠብቃሉ።

ለ) «ሐዋርያና ሊቀ ካህናት።» (ቁ. 1) ሐዋርያ ከአንድ ባለ ሥልጣን የተላከ መልእክተኛ ነው። ልዩ የሆኑ ምልክቶቹ ምንድን ናቸው? ቢሉ፥

1ኛ፤ ሐዋርያ የላኪው ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ሆኖ የላኪውን ሥልጣን ለብሶ ይወጣል። መልእክተኛው በአንድ መንግሥት ስም የመጣ እንደሆነ የላኪው መንግሥት ኃይል ሁሉ ከኋላው አለ። እንዲሁም ኢየሱስ ሐዋርያ ሆኖ ከእግዚአብሔር ኃይል ጋር ወደ እኛ መጣ።

2ኛ፤ የተላከው መልእክተኛ ቃል የራሱ ሳይሆን የላኪው ቃል ነው። እንዲሁም ኢየሱስ የመጣው የራሱን ቃል ይዞ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ቃል ይዞ ነው። (ም. 1:2፤ ዮሐ. 12:49፥ 50፤ 14:10)። በእርሱ እግዚአብሔር ይናገራል፥ እርሱንም ስናዳምጥ እግዚአብሔርን ማዳመጣችን ነው።

ካህን ደግሞ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ድልድይን የሚያበጅ ነው። ይህን ማድረግ እንዲችል ሰውንም እግዚአብሔርንም ማወቅ ያስፈልገዋል። ለሰው ብሎ እግዚአብሔርን መናገር፥ ለእግዚአብሔርም ብሎ ሰውን መናገር ማወቅ ያስፈልገዋልን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው በመሆኑ የሰውን፥ ፍጹም አምላክም በመሆኑ የእግዚአብሔርን ነገር ያውቃልና እንደ እርሱ ያለ ሌላ ሊቀ ካህናት ከቶ አንድም የለም።

ሐ) «ቤት» (ቁ. 3-6)። በእነዚህ ቁጥሮች ላይ «ቤት» ሲል ሕንፃ ማለቱ ሳይሆን ትውልድ ወይም ቤተ ሰብ ማለቱ ነው። (1ዜና. 17:10፥25)። የእግዚአብሔር ሕዝብ የእግዚአብሔር «ቤት» ናቸው። (1ጢሞ. 3:15፤ 1ጴጥ. 4:17፤ ኤፌ. 2:21፥22፤ ሆሴ. 8:1) ሙሴ ያስተዳደረው የእግዚአብሔርን ቤት ቤተ እስራኤል ነው፤ ኢየሱስም ያስተዳደረው ቤተ ክርስቲያንን ነው።

መ) «የምንደፍርበት የምንመካበትም ተስፋ»። (ቁ. 6) የክርስቲያን ተስፋ ጭጋጋሚና የማይጨበጥ ተስፋ ሳይሆን የምንደፍርበትና የምንመካበት ተስፋ ነው። እንደ አብርሃም ያለ ነገር ነው። «አብርሃም ቀኔን ያይ ዘንድ ሐሴት አደረገ፥ አየም ደስም አለው» ብሎ ጌታ መሰከረለት። (ዮሐ. 8:56)። ወይም ደግሞ በዕብ. 11:13 ላይ እንደ ተጻፈ ነገር ነው:- «እነዚህ ሁሉ እምነው ሞቱ የተሰጣቸውን የተስፋ ቃል አላገኙምና፤ ዳሩ ግን ከሩቅ ሆነው አዩትና ተሳለሙት» ተባለ። የእኛ የክርስቲያን ተስፋ እንደዚሁ ነው። (ሮሜ 8:23-25፤ 1ጴጥ. 1:8፥9)። የእኛ መንፈስ የትምክህት መንፈስ ነው እንጂ የጥርጥር መንፈስ አይደለም። (ሮሜ 5:2)። እኛ «ድነናል!» እናም «መድኃኒታችን ክርስቶስ ነው!» ብለን በድፍረትና በትምክህት ልናስታውቅ እንችላለን። አንባቢ ሆይ፥ ይህ ያንተ ተስፋ ነውን? እንዲህ ያለ ድፍረት እንዲህ ያለም ትምክህት አለህን?

## ቁ. 7-19

[7] ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ እንደሚል:- ዛሬ ድምጹን [8:9] ብትሰሙት፥ አባቶቻችሁ
እኔን የፈተኑበት የመረመሩበትም አርባ ዓመትም ሥራዬን ያዩበት በምድረ በዳ
በፈተና ቀን በማስመረር እንደ ሆነ፥ ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ። [10] ስለዚህ ያን
ትውልድ ተቆጥቼ:- ዘወትር በልባቸው ይስታሉ [11] መንገዴን ግን አላወቁም
አልሁ፤ እንዲሁ:- ወደ [12] ዕረፍቴ አይገቡም ብዬ በቁጣዬ ማልሁ። ወንድሞች
ሆይ ምናልባት ሕያው እግዚአብሔርን የሚያስክዳችሁ ክፉና የማያምን ልብ
ከእናንተ በአንዳችሁ እንዳይኖር ተጠንቀቁ፤ [13] ነገር ግን ከእናንተ ማንም
በኃጢአት መታለል እልከኛ እንዳይሆን፥ ዛሬ ተብሎ ሲጠራ ሳለ፥ በእያንዳንዱ
[14] ቀን እርስ በእርሳችሁ ተመካከሩ፤ የመጀመሪያ እምነታችንን እስከ መጨረሻው
አጽንተን ብንጠብቅ፥ የክርስቶስ ተካፋዮች [15] ሆነናልና፤ እየተባለ:- ዛሬ ድምጹን
ብትሰሙት በማስመረር እንደ ሆነ ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ። [16] ሰምተው
ያስመረሩት እነማን ነበሩ? በሙሴ ተመርተው ከግብጽ የወጡ [17] ሁሉ
አይደሉምን? አርባ ዓመትም የተቆጣባቸው እነማን ነበሩ? ሬሳቸው በምድረ በዳ
የወደቀ፥ ኃጢአትን [18] ያደረጉት እነርሱ አይደሉምን? ካልታዘዙትም በቀር ወደ

[19] ዕረፍቱ እንዳይገቡ የማለባቸው እነማን ነበሩ? ባለማመናቸውም ጠንቅ ሊገቡ እንዳልተቻላቸው እናያለን።

ከም. 3፡7 ጀምሮ እስከ ም. 4፡13 ድረስ ከሚያስጠነቅቁ ክፍሎች ሁለተኛውን እናገኛለን። ደራሲው በቁ. 7 ላይ «ስለዚህ» ብሎ የሐዋርያውንና የሊቀ ካህናቱን ታላቅነት ያሳስብና ከቁ. 8 እስከ ቁ. 11 ድረስ ማስረጃ ካቀረበ በኋላ «ምናልባት ሕያው እግዚአብሔርን የሚያስክዳችሁ ክፉና የማያምን ልብ ከእናንተ ከአንዳችሁ እንዳይኖር ተጠንቀቁ» ብሎ ያስጠነቅቃቸዋል። (ቁ. 12)። ቀጥሎም እስከ ምዕራፉ መጨረሻ ድረስ የእስራኤላውያንን ምሳሌ እየጠቀሰ የመጀመሪያ እምነታችንን እስከ መጨረሻው ድረስ አጽንተን ካልጠበቅን የሚደርስብንን ጉዳት ያመለክታል።

ከቁ. 8 ጀምሮ እስከ ቁ. 11 ድረስ የምናገኘው በመዝ. 94፡7-11 ላይ የተጻፈውን ቃል ነው። በዚያ መዝሙር ላይ መንፈስ ቅዱስ በዳዊት አድሮ የእግዚአብሔርን ቃል ሲጠቅስ በሙሴ ዘመን የሆነውን ነገር ያሳስባል። እስራኤላውያን የተባሉ የዱሮ ዕብራውያን በሙሴ በኩል የመጣውን የእግዚአብሔርን ቃል ቢሰሙ አናምን ብለው ልባቸውን እልከኛ አደረጉና በእግዚአብሔር ላይ ዐመፁ። እግዚአብሔር በፊታቸው ታላቅ ተአምራት ሠርቶ ነበር። ከግብጽ አውጥቶ ባሕርን ከፍሎ አሳልፎአቸው ነበር። «አይዞአችሁ! እኔ አገባችኋለሁ» ብሎ ወደ ከነዓን ሊያገባቸው ቃሉን ሰጥቶ ነበር። (ዘጸ. 6፡2-8)። ነገር ግን አላመኑም፥ በመድኃኒቱም አልተማመኑም። ያደረገላቸውን ሁሉ ቢያዩ እንኳ «እግዚአብሔር በምድረ በዳ ማዕድን ያሰናዳ ዘንድ ይችላልን?» ብለው ተጠራጠሩት። (መዝ. 77፡12-22)። ማሳህና መሪባ በተባለውም ሥፍራ «እግዚአብሔር በመካከላችን ነውን ወይስ አይደለም?» ብለው ተፈታተኑት አስቆጡትም። (ዘጸ. 17፡1-7፤ ዘኁል. 20፡1-13)። ስለዚህ እግዚአብሔር «እረ! ልባቸው ጠማማ ነው መንገዴንም ሊያውቁ አልፈቀዱም» ብሎ ወደ ዕረፍቱ ማለት ወደ ከነዓን (ዘዳ. 12፡9፥10)፥ እንዳይገቡ ማለ።

«እንደሚል» የተባለው ቃል (ቁ. 7) መንፈስ ቅዱስ እንዲህ ብሎ ገና ዛሬ መናገሩን ያመለክታልና ደራሲው አሁን ምሳሌውን ወደሚጽፍላቸው ዕብራውያን ያዞረዋል። አስቸጋሪው የሰው ልብ ነው፥ በሽታውም (አለማመን) የሚመነጭ ከልብ ነው። (ኤር. 17፡9፤ ምሳ. 4፡23)። በዱሮ ዕብራውያን ዘንድ የተገኘው ጠማማ ልብ «ኑ፥ አለቃ ሾመን ወደ ግብጽ እንመለስ» እያሉ እግዚአብሔርን ፈጽሞ ወደ መካድ አድርሶአቸዋልና (ዘኁ. 14፡4፤ መዝ. 77፡36፥37) በአሁኑ ዕብራውያን ዘንድ እንዲህ ያለ ክፉና የሚያስክድ ልብ እንዳይኖር ይጠንቀቁ። ነገር ግን በመካከላቸው አንድ ሰው ምናልባት በኃጢአት መታለል ማለት፥ እውነተኛውን ለመካድ ተባብሎ ወደማይሆን ነገር በመመለስ፥ ልቡን እልከኛ እንዳያደርግ፥ መንፈስ ቅዱስ «ዛሬ» ብሎአልና (ቁ. 8) ዛሬውኑ እርስ በርሳቸው ይመካከሩ። ስለምን? ቢሉ፥ በቁ. 6 ላይ እንደ ተባለው ሁሉ ያን የመጀመሪያ እምነታችንን ወይም አለኝታችንን እስከ መጨረሻው አጽንተን ካልጠበቅን የክርስቶስ ተካፋዮች አይደለንምና። ማለት፥ የዱሮ ዕብራውያን በእነርሱ ሐዋርያ በሙሴ በኩል የመጣላቸውን የእግዚአብሔርን ቃል ቢሰሙ አላመኑም፥ ዳሩ ግን ልባቸውን እልከኛ አደረጉ፤ ስለዚህ ደግሞ ሕያው እግዚአብሔርን ወደ መካድ ደረሱ፥ እርሱም «የዕረፍቴ የከነዓን ተካፋዮች አይሆኑም» ብሎ ማለ። አሁንም እነዚህ የአሁኑ ዕብራውያን በታላቁ ሐዋርያ በክርስቶስ የመጣላቸውን የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተዋል። (ም. 4፥2)። ባያምኑና ልባቸውን እልከኛ ቢያደርጉ እነርሱ ደግሞ ወደ መካድ ይደርሳሉ፥ የክርስቶስም ተካፋዮች አልሆኑም ማለት ነው። ምነው፥ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው ያስመረሩት፥ 40 ዓመት ሙሉ በምድረ በዳ ያስቆጡት፥ እግዚአብሔርም ወደ ዕረፍቱ እንዳይገቡ የማለባቸው ሁሉ ከግብፅ የወጡ ዕብራውያን፥ አባቶቻቸው አልነበሩምን? ቢሆንም

በተስፋ ወደ ተሰጣቸው አገር እንዳይገቡ አለማመናቸው ከለከላቸው። እንግዲያውስ እነዚህ የአሁኑ ዕብራውያን ደግሞ እንዲህ ያለ ክፉ ልብ እንዳይኖርባቸውና በክርስቶስ ውስጥ ወደሚገኘው ሙሉ መዳን ከመግባት እንዳይከለከሉ ይጠንቀቁ።

ማስገንዘቢያ፡-

ሀ) «ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ።» (ቁ. 8) የልብ እልከኝነት ቀስ በቀስ ነው እንጂ በአንድ ጊዜ የሚሆን ነገር አይደለም። ከጊዜ ወደ ጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል ስንሰማ ብንቃወመው፥ «ጸጋውን ተቀበሉ» ሲባል እንቢ ብንል ልባችን እልከኛ ይሆናል። በመጀመሪያ ላይ ይህ አለማመናችን ትንሽ ነገር ሆኖ ይታይ ይሆናል፥ በኋላ ግን እግዚአብሔርን ፈጽሞ ወደ መካድ ያደርሳልና እጅግ የሚያስፈራ ነገር ነው። በየጊዜው መቃወም የመቃወምን ልማድ ይፈጥርብናል፥ በመጨረሻም ብንወድ እንኳ ልናምን አንችልም። ለምሳሌ፥ የእግዚአብሔር ቃል ወደ ፈርዖን ቢመጣ ፈርዖን «ቃሉን እሰማ ዘንድ እስራኤልንስ እለቅቅ ዘንድ እግዚአብሔር ማን ነው? እግዚአብሔርን አላውቅም፥ እስራኤልንም ደግሞ አለቅም» አለ። (ዘጸ. 5፡2)። የእግዚአብሔር ቃል ደጋግሞ ወደ እርሱ ቢመጣ እንቢ በማለት ጸና። ስለዚህ እግዚአብሔር እንቢተኛነቱን አይቶ ፍርዱን አስከተለ፥ ፈርዖንም ማመን እስከማይችል ድረስ ልቡ እልከኛ ሆነ። የእግዚአብሔርን ቃል ማመን አስቀድሞ የማይፈቅድ ሰው በመጨረሻ ላይም ማመን አይችልም ማለት ነው። እስራኤላውያንንም እንመልከት፥ በእነርሱ ዘንድ ነገሩ እንደዚሁ ነውና። አለማመን የራስ (የአእምሮ) ነገር ሳይሆን የልብ ነገር ነው። ከክፉና ከማያምን ልብ የሚመጣ ነገር ነው። እስራኤላውያን ከግብጽ እንደ ወጡ በመጀመሪያ ዓመት ውስጥ አላመኑም (ዘጸ. 17፡1-7)፥ ከ40 ዓመትም በኋላ ገና ሳያምኑ ይገኛሉ። (ዘኁ. 20፡1-13)። ያም 40 ዓመት ሙሉ በልባቸው ውስጥ ያደረው አለማመን ልባቸውን እልከኛ አድርጎአል! በፍጻሜውም ላይ በእግዚአብሔር ላይ ወደ ማመፅና ፈጽሞ እርሱን ወደ መካድ አደረሳቸው። ስለዚህ እግዚአብሔር ወደ ዕረፍቱ፥ ማለት ወደ ከነዓን፥ እንዳይገቡ ማለ፥ ሬሳቸውም በምድረ በዳ ተዘረከርኮ ወደቀ።

ስለዚህ «ዛሬ ድምፁን ብትሰሙት ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ።» የእግዚአብሔርን ቃል ስንሰማና ጥሪው ሲደርሰን፥ አንዳች ነገር አድርጉ ወይም አታድርጉ ሲለን፥ እንቢ በማለት ልባችንን እልከኛ አናድርግ። ተጣልተን መታረቅ የተገባን ሲሆን እንቢ ብንል፥ ቅዱሳን ሁኑ ሲል መጥፎ ልማድን ብንጭበጥ፥ እንዲህ ያለ ነገር ሁሉ ልባችንን እልከኛ ያደርጋልና እንጠንቀቅ። የማንጠነቀቅ ከሆነ እስራኤላውያን ወደ ከነዓን እንዳልገቡ እኛ ምናልባት በክርስቶስ ወዳለልን ሙላት ሳንገባ እንቀር ይሆናል።

ለ) «ዛሬ ተብሎ ሲጠራ» (ቁ. 13) ይህ ማለት፥ «ዛሬ» የሚባል ጊዜ ገና ሲኖር ማለት ነው። «ዛሬ» የተባለው የሕይወታችን አጭር ጊዜ ናት! ለእኛ «ነገ» ማናልባት አይመጣም።

ለእያንዳንዳችን «ዛሬ» የሚባል ጊዜ አለ። በዚህ ጊዜ ውስጥ የእግዚአብሔርን ጸጋ ልንቀበል እንችላለን። ሆኖም ጊዜው ያልፋል! ብንወድም እንኳ ልንቀበል የማንችልበት ጊዜ ይመጣል። (ሉቃ. 16፡34-36፤ ዕብ. 12፡17)። ለምሳሌ፡- ክርስቶስንና ጸጋውን ሁሉ የምንቀበል ዛሬ ነው (2ቆሮ. 6፡1፥2) ዛሬ ልባችንን እልከኛ ብናደርግ ቀኑ ያልፋል በሩም ይዘጋል። (ማቴ. 25፡10-12)። አንባቢ ሆይ፥ ቀንህ መቼ እንደሚያልፍ ታውቃለህን? አታውቅም! ዛሬ አለ! ነገ...? ስለ ነገ ምንም አልታወቀም።

እግዚአብሔር ሕይወትን ሊሰጥ ወድዶአል (1ዮሐ. 5፡11) ነገር ግን ስጦታውን ለሚሰጥበት ጊዜ ወሰን አለ። የሚሰጠው ዛሬ ነው። እንግዲያውስ ዛሬ ተብሎ ገና ሲጠራ ልባችንን እልከኛ ሳናደርግ በኢየሱስ ክርስቶስ የሚመጣልንን ጸጋ ሁሉ እንቀበል።

ሐ) «በእያንዳንዱ ቀን እርስ በርሳችሁ ተመካከሩ።» (ቁ. 13) ሕያው እግዚአብሔርን የሚያስክድ ክፉና የማያምን ልብ ነው፥ እልከኞችም የምንሆነው በኃጢአት መታለል ነው። ከዚህ ጥፋት የምንጠበቅ ቀን በቀን እርስ በርሳችን ስንመካከር ነው። ክርስቲያን በክርስቶስ ያለውን የገዛ ራሱን ሁኔታ ብቻ ቢመለከትና ቢጠብቅ በቂ አይደለም፥ እያንዳንዱ የባልንጀራውን መንፈሳዊ ጤና ደግሞ መመልከትና መጠበቅ ያገባዋል። (ፊልጵ. 2፡4) በግሪክ ቋንቋ «ተመካከሩ» የሚለው ቃል «መጽናናት» እና «አጽናኝ» (ዮሐ.14፡16) ከሚለው ቃል ሥር መጥቶአልና እኛ እርስ በርሳችን ስንመካከር እንዱ ሌላውን ማጽናናትና ማደፋፈር ይገባናል፥ ይህንም የምናደርገው «በእያንዳንዱ ቀን» ነውና እንዳይሰለቸን እንጠንቀቅ። እንዳንዶች የሚወድቁ እኛ ባናጽናናቸውና ባናደፋፍራቸው ይሆናል።

መ) «ባለማመናቸው ጠንቅ ሊገቡ እንዳልተቻላቸው እናያለን።» (ቁ. 19) ይህ ማለት ወደ መንግሥተ ሰማያት ሳይገቡ ቀሩ ማለት ነውን? ኧረ ከቶ አይደለም! ሙሴና አሮን ወደ ከነዓን ሳይገቡ አብረው ቀርተው የለምን? እነርሱም ጻድቃን መሆናቸውን እንተማመናለን። (ማቴ. 17፡3) ይህ ምዕራፍ ወደ ከነዓን ስላለመግባት ይናገራል እንጂ ስለ ደኅንነትና ስለ ዘላለም ሕይወት በፍጹም አይናገርም። መንፈሳዊ ፍጻሜአቸው አልተነገረም፥ የተነገረው በዚህ ዓለም ሳሉ በእግዚአብሔር ተስፋ ወደ ተሰጣቸው አገር ሳይገቡ እንደ ቀሩ ነው። «ዕረፍታቸውን»፥ ወይም ደግሞ በምድረ በዳ መውደቃቸውን፥ ከዘላለም ደኅንነታቸው ጋር በፍጹም አለማስተካከል ነው። እርግጥ ነው፥ አላመኑም አልታዘዙምም፥ «አለቃ ሾመን ወደ ግብጽ እንመለስ» አሉም! ቢሆንም ሙሴ ለሕዝብ ሲጸልይ እግዚአብሔር ሰምቶ «እንደ ቃልህ ይቅር አልሁ» አለ። (ዘኁል. 14፡19፥20)። ይቅር ተባሉና ከመንግሥተ ሰማያት አልተከለከሉም። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ይቅር ቢላቸውም ቀጥሎ «ነገር ግን» አለ። «ነገር ግን ለአባቶቻቸው የማልሁላቸውን ምድር አያዩም» አለ። (ዘኁ. 14፡21-23)። ስለዚህ ከከነዓን ተከለከሉ።

እንግዲያውስ ይህ ምዕራፍ ወተትና ማርም ከምታፈስ፥ እግዚአብሔር ይሰጣቸው ከነበረው ምድር ሊገቡ እንዳልተቻላቸው ይነግረናል እንጂ በመንፈሳቸው ለዘላለም ጠፉ አይልም። እግዚአብሔር «ዕረፍትን»፥ ማለት ከነዓንን፥ በተስፋ ቃል ሰጥቶአቸው ነበር። (ዘጸ. 3፡8)፥ እስራኤላውያን ግን ባለማመናቸው ጠንቅ ሊገቡባት አልተቻላቸውም።

ሐዋርያውም አሁን በእርሱ ዘመን ወደ ተገኙት ክርስቲያን ዕብራውያን ሲጽፍ፡- «እግዚአብሔር ወተትና ማር የምታፈስሰውን ከነዓንን የሚመስለውን ተስፋ ለእናንተ ደግሞ ሰጥቶአልና እነዚያ እስራኤላውያን ባለማመናቸው ጠንቅ በመውደቅ ምክንያት በተስፋ ቃል የተሰጣቸውን ነገር ሳያገኙ እንደ ቀሩ እንዲሁም እናንተ ወደ ኋላ በማፈግፈግ ጠንቅ ከመግባት፥ ማለት ያን ተስፋ ከመውረስ እንዳትቀሩ ተጠንቀቁ» ይላቸዋል።

«ምሳሌው ከነዓን የሆነው ለክርስቲያኖች የተሰጠው ተስፋ ምንድን ነው?» ቢሉ፥ በዚህ ዓለም ላይ አገር ወይም ስፍራ ሳይሆን መንፈሳዊ አቀማመጥ ወይም ኑሮ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረትን በማግኘት የእርሱን ሕይወትና የእርሱን ዕረፍት ተካፍሎ መኖር ነው። ይህም «የዘላለም ሕይወት» ይባላል። (1ኛ ዮሐ. 1፡3)። የእግዚአብሔርን ሕይወትና ዕረፍት መካፈል ምን

ማለት ነው? ቢሉ እግዚአብሔር በሚኖርበት ዓይነት ሕይወትና ዕረፍት መኖር ነው። አዳም ኃጢአትን በሠራ ጊዜ ሕይወቱ ተቋረጠ። (ዘፍ. 2፡17) በዓለም ላይ 930 ዓመት ቢቀመጥ ቅሉ የኖርበቱ ሕይወት ቀድሞ የነበረው የሕይወቱ ጥላ ብቻ ነበረ። (ዘፍ. 5፡5) ከአዳም የተወለደውም ሰው ሁሉ ዛሬ የሚኖርበቱ ሕይወት ይህ ዝቅተኛ ዓይነት ሕይወት ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛውን ሕይወት፥ የዘላለምን ሕይወት እግዚአብሔር የሚኖርበትን ዓይነት ሕይወት ሊመልስልን መጣ፥ በእርሱም የሚታመን ሁሉ በዚያ ሕይወት ሊኖር ይችላል። (ዮሐ. 1፡4፤ 6፥47፤ 1ዮሐ. 1፡1-5) እንደዚሁም ሁሉ እግዚአብሔር በዕረፍት እንደሚኖር እኛም በዕረፍት ልንኖር እንችላለን። ከእርሱ ጋር ያለንን ኅብረት በሥራ ላይ ስናውል ዓለምንና ሥጋን ዲያብሎስንም እያሸነፍን በዕረፍት እንኖራለን። (ሮሜ 7፡25፤ ኤፌ. 2፡4-7)። ለዚህ ኅብረት ሰው በእግዚአብሔር መልክ እንደ ምሳሌው ተፈጠረ (ዘፍ. 1፡26፥27)፤ የተሟነለትም የክብርና የምስጋና ዘውድ ይኸው ኅብረት ነው። (ም. 2፡7፥9) እግዚአብሔር በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ከመውደቃችን አድኖን በልጁ የተናገረው ቃል ይኸው የኅብረት ቃል ነው። (ም. 1፡1፥2፤ ሐዋ. 10፡36)። ወተትና ማር የምታፈስ «ከነዓን» ይኸው በቃኝ ማለትና ደስታ የሞላበት ኅብረት ነው። (መዝ. 15፡11)። የመጀመሪያ እምነታችንን እስከ መጨረሻው አጽንተን ባንጠብቅ «ቤቱ» እና «የክርስቶስ ተካፋዮች» የማንሆንበት ምክንያቱ ማፈግፈጋችን ይህን ኅብረት ስለሚበጥስ ነው። (ም. 3፡6፥14)። ለእግዚአብሔር ሕዝብ የቀረው «የሰንበት ዕረፍት»፥ የምንሄድለት «ፍጻሜ»፥ የሚሞላልን «ተስፋ»፥ የምንቀበለው «ርስት» ይኸው ኅብረት ነው። (ምዕ. 4፡9፤ 6፡2፤ 7፡11፥25፤ 6፡11፤ 9፡15) ሊቀ ካህናቱም እጅግ በጣም አስፈላጊአችን የሆነበት ምክንያቱ ከዛሬ ኃጢአታችን እያነጻን ወደዚህ ኅብረት ስለሚያገባን ነው። (ም.10፡19-23።) ይህ የኅብረት ሕይወት አንዳንድ ጊዜ የተትረፈረፈ ሕይወት ይባላል፤ ምክንያቱም፥ የሕይወትን ሙላት የምናገኘው ከእርሱ ጋር ኅብረት ሲኖረን ነው። (መዝ.15፡11።) የኃጢአት ይቅርታ ብቻ አይደለም፥ ከይቅርታ በላይ የተጨመረ ጸጋ ነው። ለክርስቲያን ሁሉ የተመደበ ነው፥ ቢሆንም የሚያውቁት ጥቂቶች ብቻ ናቸው። ክርስቶስ የመጣው ይህንኑ ሕይወት ሊመልስልን ነው። (ዮሐ. 10፡10)።

ለክርስቲያን ሁሉ የተመደበ ሕይወት ነው፤ ሆኖም እነዚያ እስራኤላውያን ከግብጽ ባርነት የዳኑ ምንም ቢሆኑ በሙሴ በኩል የመጣላቸውን ቃል ሰምተው አናምንም ብለው እልከኞች እንደ ሆኑና ወደ ከነዓን ዕረፍት ሊገቡ እንዳልተቻላቸው፥ እንዲሁም እኛ ክርስቲያኖች እንዲህ ያለ ተስፋ እንደተሰጠን፥ ወይም እግዚአብሔር ወደዚያ «ዕረፍት» እንደሚያገባን ባናምን፥ ወይም ደግሞ ከሰማነው ነገር በመወሰድ ወይም በማፈግፈግ ባንታዘዝለት፥ እኛ ደግሞ ወደዚያ ኅብረት ወደ ተትረፈረፈም ሕይወት ሳንገባ እንቀር ይሆናል። ወንድሞች ሆይ፥ ሳንገባ በምድረ በዳ ብንወድቅ ታላቅ ጉዳት ነውና «በእምነትና በትዕግሥትም የተስፋውን ቃል የሚወርሱትን እንድትመስሉ እንጂ ዳተኞች እንዳትሆኑ፥ ተስፋ እስኪሞላ ድረስ እያንዳንዳችሁ ያን ትጋት እስከ መጨረሻ እንድታሳዩ እንመኛለን።» (ም. 6፡11፥12)።

ሠ) «ኅብረት! ኅብረት ምን ማለት ነው? ትርጉሱ ምንድን ነው? ምንስ አገኝበታለሁ?» ትላለህን? እንግዲያውስ በምሳሌ እንዲህ ብዬ እመልስልሃለሁ። ይሁን እንጂ አማናዊውን ሐሳብ ለማስተዋል ምሳሌዬን እስከ በማይኖረው ስፋት ልታጎላው ይገባል።

አንዲት ውድ ልጅ ከአባትዋ ጋር የሚኖራትን ያላትን ኅብረት አስብ። ከአባትዋ ጋር ስትሆን ብርሃንና ሕይወት አለ፥ ዋስትና፥ ዕረፍት፥ ሰላም፥ ደስታም አለ። የፍቅር ሙላት አለ። ጥብቅ አንድነት አለ። በአስቸጋሪ ስፍራዎች የሚረዳት የእርሱ ኃይል አለ። ድል አድራጊነትን፥ ማለት

ማሸነፍን የምታገኘው በእርሱ ነው። ለባላጋራ ስድብ መልስ የምትሰጥ እርስዋ ናትን? ኧረ አይደለም! ይህስ የአባትዋ ፋንታ ነው። እርስዋ ግን ማረፍና የሕይወቱም ተካፋይ በመሆን አብራው መራመድ ብቻ አለባት። ይኸውም በእርስዋ ውስጥ አዲስ ኃይል ወይም ልዩ ኃይል ያለ አይደለም። አብሮአት፣ በመገኘቱ በተወዳጅነቱና እርሱ ለእርስዋ ምን እንደሆነ በመገንዘብ ግን በማያቋርጥ ደስታ ደስ ይላታል።

እርሱስ በእርስዋ በልጁ በጥቂቱ ደስ አይለውምን? በእርግጥ ደስ ይለዋል! ይህች ልጅ ብታጠፋ ወይም ከእርሱ ኅብረት ፈቀቅ ብትል ምንኛ ያዝን! በችሎታው መጠን ሊመክትላትና ሊመክራትስ ምን ያህል ባለማቋረጥ ይፈልግ!

ኅብረት! በአባትና በልጅ መካከል የሚኖር ጣፋጭ ኅብረት! እስቲ በል! የአባትዋን ኅብረት ትጠራጠር ይመስልሃልን? የጋለ ፍቅሩንስ አታውቅምን? ከአባትዋ ጋር ያላት ኅብረት የሚሰጣትን ትርፍ አትረዳምን? ኧረ በጣሙን ታውቃለች!

እንግዲያውስ እኔም ከሰማያዊ አባቴ ጋር ኅብረት ይኖረኝ ዘንድ ልሻ፤ ትርፉንም ላስተውል።

# ምዕራፍ አራት

## እኛ በተስፋ ወደ ተሰጠን ዕረፍት ለመግባት እንትጋ።

ይህ ገና የማስጠንቀቂያ ክፍል ነው። ደራሲው በም. 3 ላይ የእስራኤላውያንን ምሳሌ ጠቅሶ እነርሱ በተስፋ ወደ ተሰጣቸው አገር፣ ወደ ከነዓን፣ ባለማመናቸው ጠንቅ ከመግባት እንደ ተከለከሉ ዕብራውያንን አሳሰቦአል። አሁንም በም. 4 ላይ እነርሱ ደግሞ እንደ እስራኤላውያን ምሳሌ በፊታቸው ወደ ተሰጣቸው ተስፋ ሳይገቡ እንዳይቀሩ ያስጠነቅቃቸዋል። እኛም ምዕራፉን ስንጀምር ጉዳዩ፣ ማለት ተስፋው፣ ምን እንደ ሆነ እናስታውስ። እውነተኛ ሕይወት ከእግዚአብሔር ጋር በኅብረት መኖር ነው። ከእርሱ ጋር በሕብረት ስንኖር የእርሱን ሕይወት እንካፈላለን፤ ሕይወቱን እየተካፈልን የምኖርበቱም ሕይወት «የዘላለም ሕይወት» ይባላል። እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው ለኅብረት ነው። ሲፈጥረውም በመልኩ እንደ ምሳሌውም የፈጠረው ለዚህ ነው። ይህ ኅብረት በተድላ ገነት ተጀመረ። (ዘፍ. 3:8፣9) ነገር ግን በኃጢአት ተቋረጠ ሰውም ከእግዚአብሔር ዘንድ ተለየ። (ዘፍ. 3:24) ሆኖም ሰው የተፈጠረው ከእግዚአብሔር ጋር እንዲገናኝና እንዲተባበር ነውና የትም ዘንድ ቢገኝ ሰው እግዚአብሔርን ሲፈልግ ይታያል (ሐዋ. 17:26፣27) እርሱንም ካላገኘ በቃኝ ማለትን ማለት ነዋሪ ደስታንና ሰላምን በጠቅላላም ዕረፍትን፣ አያገኝም። አምላኩን እንደ በደለ ተሰምቶት መሥዋዕትን በማቅረብ ሊታረቅ ይመኛል፣ መሥዋዕቱንም የሚያቀርብለትን ካህን ያበጃል። መሥዋዕትን በማቅረብ እንቅፋቱን፣ ማለት ኃጢአቱን፣ የሚያስወግድና እንቅፋቱን በማስወገድ ኅብረትንና ዕረፍትን የሚመልስ ካህኑ ነው። ካህኑ ባቀረበው መሥዋዕት መግባትን አስገኝቶ ሰውን ወደ እግዚአብሔር ያቀርባል ማለት ነው። ካህኑ የኢየሱስ ምሳሌ ነው። ኢየሱስ በጎልጎታ ላይ እውነተኛውን መሥዋዕት አቅርቦ ኃጢአታችንን አስወገደ አሁንም ሊቀ ካህናታችን ሆኖ ወደ እግዚአብሔር አቅርቦ ያን የጠፋውን ኅብረት ይመልስልናል። ወደ ዓለም የመጣው ለዚህ ነው። የተመለሰልንም ኅብረት ዕረፍት ነው፤ የዘላለምም ሕይወት ነው። የተፈጠርንለት ፍጹምነት ይህ ነው፤ በኃጢአት የጠፋብንም ይህ ነው፤ እግዚአብሔርም በክርስቶስ የመለሰን ለዚህ ነው። ሊቀ ካህናታችን ክርስቶስ ከኃጢአታችን በማንጽሉት ወደ እግዚአብሔር ዘንድ ያገባናል (ሮሜ 5:2፤ ኤፌ. 2:18፤ 3:12)፣ እኛም ስንገባ የዘላለም ሕይወት የሚሆንልንን ያን ግሩም የሆነውን ኅብረት እናገኛለን። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የምናገኘው ነገር ይህ ነው። ከኩነኔ መዳን ሳይሆን፣ ለእስራኤላውያን ወደ ከነዓን መግባት፣ ለዕብራውያንና ለእኛም ወደዚያ ወደ ፍጹም መዳን፣ እርሱም ወደማይቋረጥ ኅብረት፣ መግባት ነው።

### ቁ. 1-10

1 እንግዲህ ወደ ዕረፍቱ ለመግባት ተስፋ ገና ቀርቶልን ከሆነ፣ ምናልባት ከእናንተ
ማንም የማይበቃ መስሎ እንዳይታይ እንፍራ። 2 ለእነዚያ ደግሞ እንደ ተነገረ ለእኛ
የምስራች ተሰብኮልናልና፤ ዳሩ ግን የሰሙት ቃል ከሰሚዎቹ 3 ጋር በእምነት
ስላልተዋሐደ አልጠቀማቸውም። ሥራው ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ምንም እንኳ
ቢፈጸም፡- እንዲህ፡- ወደ ዕረፍቴ አይገቡም ብዬ በቁጣዬ ማልሁ 4 እንዳለ፣ እኛስ
ያመንን ወደ ዕረፍቱ እንገባለን። ስለ ሰባተኛው ቀን በአንድ ሥፍራ፡-
እግዚአብሔርም በሰባተኛው ቀን 5 ከሥራው ሁሉ ዐረፈ ብሎአልና፤ በዚህ
ሥፍራም ደግሞ፡- 6 ወደ ዕረፍቴ አይገቡም። እንግዲህ አንዳንዶች በዚያ እንዲገቡ
ስለ ቀሩ፣ ቀድሞም የምሥራች የተሰበከላቸው ባለመታዘዝ 7 ጠንቅ ስላልገቡ፡-
ዛሬ ድምፁን ብትሰሙት ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ በፊት እንደ ተባለ፣ ይህን
ከሚያህል ዘመን በኋላ በዳዊት ሲናገር፡- ዛሬ ብሎ አንድ ቀን 8 እንደገና ይቀጥራል።

ኢያሱ አሳርፍአቸው ኖሮ ቢሆንስ፥ [9] ከዚያ በኋላ ስለ ሌላ ቀን ባልተናገረ ነበር። እንግዲያስ [10] የሰንበት ዕረፍት ለእግዚአብሔር ሕዝብ ቀርቶላቸዋል። ወደ ዕረፍቱ የገባ፥ እግዚአብሔር ከሥራው እንዳረፈ፥ እርሱ ደግሞ ከሥራው አርፎአልና።

ከነዓን የተባለው፥ እስራኤላውያን ይገቡበት የነበረው ስፍራ የእውነተኛ ዕረፍት ምሳሌ ነበረ እንጂ እርሱ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ሊሰጥ የወደደው እውነተኛ ዕረፍት አልነበረም። ያ ምድራዊና ዘመናዊ ሲሆን ይህ መንፈሳዊና ዘላለማዊ ነው። በሁለቱም ግን የሚገባበት በእምነት ነው። እስራኤላውያን ባለማመናቸው ጠንቅ ወደ ከነዓን እንዳልገቡ እንዲሁም ምናልባት ከዕብራውያን አንድ ሰው በተስፋ ወደ ተሰጠው ዕረፍት ሳይገባ እንዳይቀር ደራሲው ይፈራል። ምክንያቱም፥ ሰው ወደ መዳን መንገድ የሚገባው በእምነት ሲሆን ያን የእምነቱን መጀመሪያ አጽንቶ ካልጠበቀ ወደ ፍጻሜው ከመግባት ይቀር ይሆናል። «የማይበቃ መስሎ እንዳይታይ» የተባለበቱ በዚህ ምክንያት ነው። የእምነቱን መጀምሪያ እስከ መጨረሻው አጽንቶ ካልጠበቀ ወደ ፍጻሜው ለመድረስ አይበቃም ማለት ነው። ለእስራኤላውያን «ከነዓን የምትባል፥ ወተትና ማር የምታፈስ ምድር በፊታችሁ አለ» የሚል የምስራች እንደ ተነገረ (ዘኁል. 13፡27፤ 14፡6-9)፥ እንዲሁም ለእኛ «በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን በማግኘታችሁ ከእግዚአብሔር ጋር ፍጹም በቃኝ ማለትና ደስታ የሞላበት ኅብረት አለላችሁ» የሚል የምሥራች ተነግሮናል (ሮሜ 4፡23 ም. - 5፡2)። ስለዚህ በእነርሱ ፊት የዕረፍት ተስፋ እንደ ተቀመጠ እንዲሁም በእኛ ፊት የዕረፍት ተስፋ ተቀምጦአል። ሆኖም እስራኤላውያን በሰሙት ቃል ላይ አስፈላጊውን እምነት ስላልጨመሩ አልተጠቀሙም፥ የተነገረውንም አላገኙም። እግዚአብሔር በስድስት ቀን ሰማይንና ምድርን፥ ባሕርንም፥ ያለባቸውንም ሁሉ ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን ዐርፎአልና ዕረፍቱ ከዚያ ቀን ጀምሮ ተከፈተ። (ዘፍጥ. 2፡1-3፤ ዘጸ. 20፡11)። ሆኖም እስራኤላውያን አላመኑም አልታዘዙምም፥ ስለዚህ እግዚአብሔር እነርሱ አይገቡበትም ብሎ ማለ። እንግዲያውስ የሚገቡበት እነማን ናቸው? የሚያምኑ አይደሉምን? ናቸው! ስለዚህ እኛ ያመንን ክርስቲያኖች እንገባበታለን።

ይህ ልዩ የሆነ የእግዚአብሔር ዕረፍት ገና እንዳለ የምናውቅበቱ፡- ከእነዚያ እስራኤላውያን 500 ዓመት በኋላ እግዚአብሔር በዳዊት አፍ ቀድሞ እንዳለው ሁሉ አሁንም ደግሞ «ዛሬ ድምፁን ብትሰሙት ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ» ብሎ ስለ ዕረፍቱ እንደ ገና ስለ ተናገረ ነው። (መዝ. 94፡7-11)። «ዛሬ» በማለቱም ገና በዚያ ቀን ዕረፍቱ እንዳለ ታውቆአል። ኢያሱ እስራኤላውያንን ወደ እውነተኛ ዕረፍት አግብቶአቸው ቢሆን ኖሮ እግዚአብሔር ገና በዳዊት ዘመን ስለ ዕረፍቱ ባልተናገረም ነበር። ኢያሱ ግን ወደ ዕረፍቱ ምሳሌ እንጂ ወደ እውነተኛ ነገር አላገባቸው። እውነተኛው የእግዚአብሔር ዕረፍት ለእኛ ቀርቶአል ማለት ነው። እግዚአብሔር የፍጥረት ሥራውን ጨርሶ፥ ያደረገውን ሁሉ አይቶ እጅግ መልካም መሆኑን እንደ ተገነዘበና በዚህ ምክንያት ተደስቶ እንዳረፈ (ዘፍ. 1፡31፤ ዘጸ. 31፡17) እንዲሁም ወደ እግዚአብሔር ዕረፍት የገባው ክርስቲያን ገና ሥራን ለመሥራት ሳይጨነቅ እርፎ! ብሎ ተደስቶ ይቀመጣል።

<u>ማስገንዘቢያ</u>፡-

ሀ) «የሰሙት ቃል ከሰሚዎቹ ጋር በእምነት ስላልተዋሐደ አልጠቀማቸውም።» (ቁ. 2) የምስራችን ስንሰማ እንጠቀምበት እንደሆነ እንድናምንበት ያስፈልጋል። ለምሳሌ፡- አንድ ሰው መጥቶ «እገሌ እኮ ይህን ያህል ገንዘብ አውርሶሃል» ብሎ የምስራች ቢያሰማኝ አምኜ ያ ገንዘብ ወደሚገኝበት ካልሄድኩኝ አላገኘውምና አልጠቀምበትም። እንዲሁም «እነሆ፥

ለሕዝብ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምስራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ! ዛሬ መድኃኒት ተወልዶላችኋልና» በተባለው (ሉቃ. 2፥10፡11) በመልአኩ ቃል ላይ እምነትን ካልጨመርን በሕይወታችን ዘመን ሁሉ ያን መድኃኒት ገና ስንፈልግ እንገኛለን። አልተጠቀምንበትም ማለት ነው። እንደዚሁም ደግሞ «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የነበረውን እንቅፋት ሁሉ ስላስወገደ ያ በእግዚአብሔርና በአዳም መካከል የነበረው ኅብረትና መገናኘት ተመልሶአል» የተባለውን ቃል ስንሰማ ካላመንበትና ያን ኅብረት ለማጽናትና ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት ካላሰብን የዳንን ሰዎች ብንሆን እንኳ የመዳንን ፍጻሜ አንቀምስም። እንዲህ ያለ እረፍት እንዳለልን ማመንና እስከናገኘውም ድረስ መከታተል ያስፈልገናል። ያላመንን እንደሆን ሳንገባ እንቀራለን ማለት ነው። ስለዚህ ወደዚያ ዕረፍት ለመግባት እንትጋ።

ለ) «እግዚአብሔርም በሰባተኛው ቀን ከሥራው ሁሉ ዐረፈ።» (ቁ. 4)። የፍጥረትን ታሪክ ስናነብ በስድስቱ ቀኖች ውስጥ የተፈጠረው ነገር ከተዘረዘረ በኋላ «ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ፥ አንድ ቀን» ተብሎ ስለ ተጻፈ (ዘፍ. 1፡5፥8፥13፥19፥23፥31) ለእነዚያ ቀኖች ሁሉ መጀመሪያና መጨረሻ እንዳለ እንረዳለን። ስለ ሰባተኛው ቀን፥ ስለ ሰንበት ግን ስናነብ እነዚህን ቃሎች አናገኝምና ለዚያ ቀን መጨረሻ እንደሌለ እንገነዘባለን። ማለት፥ ለእግዚአብሔር ዕረፍት ቀን መጨረሻ የለም። ስለዚህ እስራኤላውያን ባይገቡበት እንኳ የሰንበት ዕረፍት ለእግዚአብሔር ሕዝብ ቀርቶአል፥ እኛም እንገባበት ዘንድ ተጠራን።

ሐ) «የሰንበት ዕረፍት።» (ቁ. 9፡10)። በእነዚህ ቁጥሮች ላይ የተነገረለት ዕረፍት ተራ ዕረፍት ብቻ አለመሆኑን የምናውቅበቱ በቃሉ ለውጥ ነው። እስከ አሁን ድረስ «ዕረፍት» ብቻ ተባለ፥ አሁን ግን «የሰንበት ዕረፍት» ተባለ። ማረፍ ብቻ ሳይሆን ሰው በሰንበት ዕረፍት የሚደሰትበትን ነገር ሁሉ ማግኘት ነው። ሰንበት እንደ ከነዓን አገር ሆኖ በቃኝ በማለትና በደስታ የምናርፍበት፥ በተለይም ከእግዚአብሔር ጋር የምንገናኝበትና በመካከላችን ያለውን ኅብረት የምናጸናበት ቀን ነው። እንደዚሁም ሁሉ «እግዚአብሔር በሰንበት ቀን ከሠራው ሥራ ሁሉ ዐረፈ» ሲባል ከዚያ ቀን ጀምሮ ሥራ አልሠራም ማለቱ አይደለም። ዓለማትንና ያለባቸውንም ሁሉ ገና ያስተዳድራል ይደግፋልም፥ ሕዝቡንም ገና ይጠብቃል። (ዮሐ. 5፡17፤ መዝ. 120፡4፤ ኢሳ. 40፡28)። ሆኖም የፍጥረት ሥራውን ሲጨርስ በተሠራው ሥራ ሁሉ፥ በተለይም ከሰው ልጆች ጋር ባገኘው ኅብረት ተደስቶ ተቀመጠ። ከተፈጸመ ሥራ የተገኘ የበቃኝ ማለትና የደስታ ዕረፍት ነበረ እንጂ የሥራ ዕረፍት አልነበረም። የሠራውን ሥራ አይቶ «እጅግ መልካም ነው!» ብሎ በደስታ ተቀመጠ። እኛም የተጠራን ለዚህ «ሰንበት ዕረፍት» ነው። እግዚአብሔር ሰንበትን በባረከ ጊዜ ለሰው ልጆች ሁሉ ባርኮታል፤ ማለት የሰው ልጆች ሁሉ እንዲገቡበትና አብረውት እንዲካፈሉት አቅዶአል። (ዘፍ. 2፡3) አንድ ክርስቲያን የሚገባው ወደ እግዚአብሔር ዕረፍት ነው እንጂ ወደ ገዛ ዕረፍቱ አይደለም። እግዚአብሔር በጌታችን በእየሱስ ክርስቶስ የማዳኑን ሥራ ሠርቶአልና ክርስቲያን ተመልሶ ወደ እግዚአብሔር ዕረፍት ሊገባ ይችላል። ከእንግዲህ ወዲህ ሥራ አይሠራም ማለቱ አይደለም፤ ከበፊቱ ይልቅ አሁን ሥራ ይሠራ ይሆናል (1ኛቆር. 15፡58፤ ቆላ. 1፡29)፤ ነገር ግን ይህን ሥራ ሁሉ ሲሠራ ሳለ በቃኝ በማለትና በደስታ በኅብረትም ዕረፍት ያርፋል። ከእግዚአብሔር ጋር የማይቋረጥ ኅብረትን ስናገኝ ከብስጭትና ከጭንቀት ከጥርጥርና ከፍርሃት ድነን በሰንበት ዕረፍት እንቀመጣለን። የለመለመውን መስክና የዕረፍትን ውኃ የምናገኝ በዚያን ጊዜ ነው። (መዝ. 22፡2)። ሊቀ

ካህናትን የምንፈልግ ለዚህ ነው፥ ከኃጢአታችን የሚያነጻንና ወደ እግዚአብሔር አቅርቦ ኅብረትን የሚያስገኝልን እርሱ ነውና። ይህም የክርስቶስን የዛሬ ሥራው ነው። (ማቴ. 11፡28-30)።

ከዚህ በፊት «በመዳናችን ውስጥ ብዙ ነገሮች ተጠቅልለዋል» ብለናል። ከእነዚህም ነገሮች ደራሲው አሁን ሦስቱን አሳይቶናል፡-

1ኛ፥ የዱር ገዥነታችን እንደ ተመለሰልን። (ም. 2፡8፥9)

2ኛ፥ ከሞት ሥልጣንና ከሞት ፍርሃት ነፃ እንደወጣን። (ም. 2፡14፥15)።

3ኛ፥ ወደ ዱሮ ኅብረታችን፥ ማለት ወደ ዕረፍት፥ እንደ ገና ዛሬ እንደ ተጠራን (ም. 4፡1-13)።

## ቁ. 11-13

*11 እንግዲህ እንደዚያ እንደ አለመታዘዝ ምሳሌ ማንም 12 እንዳይወድቅ ወደዚያ*
*ዕረፍት ለመግባት እንትጋ። የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና፥ የሚሠራም፥*
*ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው፥ ነፍስንና መንፈስንም ጅማትንና*
*ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል፥ 13 የልብንም ስሜትና ሐሳብ*
*ይመረምራል፤ እኛን በሚቆጣጠር በእርሱ ዓይኖች ፊት ሁሉ ነገር የተራቆተና*
*የተገለጠ ነው እንጂ፥ በእርሱ ፊት የተሰወረ ፍጥረት የለም።*

በእስራኤላውያን ምሳሌ እንዳየን ሁሉ ወደ ተሰጠው ተስፋ ሳይገቡ መቅረት ለእግዚአብሔር ሕዝብ እንኳ የሚቻል ነገር ነውና በፊታችን ወደ ተቀመጠልን ዕረፍት ለመግባት እንትጋ። መትጋት የሚያስፈልገን እግዚአብሔር ቃልን በልጁ ስለ ተናገረና እኛ የተነገረውን ቃል ስለ ሰማን ነው (ም. 1፡2፤ 2፡1፤ 4፡2)። አሁን ያ ቃል ከእኛ ዘንድ መልስ ይፈልጋል። ወይም ተግተን የመጀመሪያ እምነታችንን እስከ መጨረሻው አጽንተን መግባት፥ ወይም ባለማመንና ባለመታዘዝ ጠንቅ ሳንገባ መቅረት፥ እነኝህ ሁለት ነገሮች በፊታችን አሉ፥ ከሁለቱም አንዱን መያዝ የግድ አለብን። ምክንያቱም፥ የእግዚአብሔር ቃል የሞተ ነገር አይደለም፤ በእስራኤላውያንም ዘመን ሆነ በዕብራውያን በእኛም ሕያው ነው። ለእነዚያ ደግሞ እንደ ተነገረ ለእኛ የምስራች ማለት የዕረፍት ተስፋ፥ ተነግሮአል። (ቁ. 2)። እናምን አንታዘዝለትም እንደሆነ ወደ ዕፍረፍቱ እንዳንገባ አስጠንቅቆናል። ቃሉ ገና እንደ ቆመ ነው። ደግሞ ይሠራል። (ኢሳ. 55፡11)። ሰይፍ ሆኖ (ኤፌ. 6፡17) ውስጥ ውስጣችንን ሁሉ፥ ሥጋዊ ሕይወታችንን መንፈሳዊንም፥ ነገር ከነገር እየለያየ ጥልቅ የሆነውን የልብን ምሥጢራት ሁሉ፥ ምኞቱንና ሐሳቡን፥ ሥራም የምንሠራበትን ምክንያትና ፈቃዱን ሁሉ ይመረምራል ይመዝናልም። የእኛን እውነተኛ ሁኔታ የሚገልጥ የእግዚአብሔር ቃል ነው፥ ያንም ቃል ተቀብለንና አልተቀበልን እንደሆነ ቃሉን ለተናገረው በፍጹም ታውቆአል። ልብሳችንን ለውጠን ሌሎች ሰዎች መስለን ብንሰወር እንኳ በእርሱ ፊት ስንቆም ራሳችን እንደሆንን እንታወቃለን። (1ነገ. 14፡2-6)። በቃሉ ዘንድ ያደረግነው በእርሱ ዓይን የተገለጠ ነው። ሁሉንም ያያል እንጂ ከእርሱ ዘንድ ልንሰውረው የምንችል አንዳች ነገር የለም። ስለዚህ እንትጋ!

ሀ) «የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነው የሚሠራም።» (ቁ. 12) የእግዚአብሔርን ቃል እንደሚገባው ሁሉ በቅንነት ስንናገር ምንኛ ኃይለኛ ነው! (2ጢሞ. 2፡15)። በጸንጠቆስጤ

ቀን ሲሠራበት በአንድ ጊዜ 3 ሺህ ሰዎች ለጌታ ተማረኩ! (ሉቃ. 5፡10)። ጳውሎስም ሲሠራበት አገረ ገዥ ትንቀጠቀጠ! (ሐዋ. 24፡25)። ሰው ይህን ቃል እንደ ሰው ቃል ሳይሆን በእውነት እንዳለ እንደ እግዚአብሔር ቃል ሲቀበለው ቤተ ክርስቲያን ትቋቋማለች! (1ኛተሰ. 2፡13)። መንፈሳውያን ወንድሞቼ ሆይ፥ ልንሠራበት የተሰጠን ሰይፍ፥ ሁለት ልሳን ካለው ሰይፍ ይልቅ እንኳ ኃይል ያለው ነው። ኧረ እንሥራበት! እኛ ግን የእግዚአብሔርን ቃል፥ መጽሐፍ ቅዱስን፥ ለራሳችን ካላወቅን እንዴት አድርገን ልንሠራበት እንችላለን? አንችልም! የአንድ አገር ሕዝብ እጁን ወደ እግዚአብሔር ሲዘረጋ ወዲያውኑ መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን ሊያውቅ ይፈልጋልና እኛ ራስችን ቃሉን ካልተማርን ሌሎችን እንደምን እናስተምራለን? (መዝ. 67፡31)። ኧረ እንዘጋጅ!

ሁለተኛ ደግሞ፥ ኅብረትን የምናገኝ በእግዚአብሔር ቃል በኩል ነው። በሰውና በሰው መካከል ኅብረት የሚፈጠር ተገናኝተው ሲጨዋወቱ ነው። የእግዚአብሔር ድምፅ ዛሬ በዚህ ዘመን በግዳ ሲናገር አንሰማውም፤ ዛሬ የሚመጣልን በተጻፈው ቃል በኩል ነው። እኛ ለእርሱ በጸሎት ስንናገር እርሱ ለእኛ በመጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። እንግዲያውስ ያን መጽሐፍ ቸል እንለው እንደሆነ ኅብረትን እንደምን እናገኛለን?

ለ) «የእግዚአብሔር ቃል ይወጋል፥ የልብንም ስሜትና ሐሳብ ይመረምራል።» (ቁ. 12) የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ እንዲመረምረን እንፈቅዳለንን? «አቤቱ፥ መርምረኝ ልቤንም እወቅ፤ ፈትነኝ መንገዴንም እወቅ፤ በደልንም በእኔ ውስጥ ብታገኝ እይ፤ የዘላለምንም መንገድ ምራኝ» ብለን ከዳዊት ጋር መጸለይ እንደፍራለንን? (መዝ. 138፡23፥24) ዓይኖቹ እንደ አማልክት (ጣኦታት) ዓይኖች አይደሉም። የእነኝህ አያዩም፥ የእርሱ ግን ሁሉንም ያያሉ። (ዘፍ. 16፡13፥14፤ መዝ. 13፡2) ከእርሱም ዓይኖች የሚሰወር ሰውም ሆነ ነገር የለም። የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚያደርገውን ዓለም አያይም፥ የእግዚአህሔር ዓይኖች ግን ያዩታል። ካህኑ ነውር ወይም እድፍ ምናልባት ያለበት እንደሆነ ሊያይ ለመሥዋዕት የሚታረደውን በግ አስቀድሞ እንደ መረመረውና ያ በግ በፊቱ ተጋድሞ በዓይኖቹ ፊት ሁለመናው የተገለጠ እንደሆነ እንዲሁም እኛ በእግዚአብሔር ዓይኖች ፊት የተራቆትንና የተገለጥን ነን። ወንድሞቼ ሆይ፥ የዳንን ሰዎች እንሆን ይሆናል፥ ቢሆንም በድካማችን ሊራራልን የሚችልና ኃጢአታችንን እያነጻ ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርበን ሊቀ ካህናት ያስፈልገን የለምን? እንዲህ ያለ እንዳለልን አሁን በሚመጡት ቁጥሮችና ምዕራፎች ላይ ልናነብ ነው። አስተውለን እናዳምጥ።

ሐ) ማስጠንቀቂያው አስጠንቅቆናል። ከእግዚአብሔር ጋር በቃኝ ማለትና ደስታ የሞላበት የኅብረት ዕረፍት በፊታችን እንዳለልን ሰምተናል። አሁንም እንደዚያ እንደ አለመታዘዝ ምሳሌ እንዳንወድቅ ምንኛ መጠንቀቅ ያስፈልገናል! (ቁ. 11) ከክርስቲያኖች ብዙዎቹ እንዲህ ያለ ታላቅ መዳን እንዲህም ያለ ግሩም የሆነ ሕይፍወት እንዳለ ቢሰሙ እንኳ ይህ ነገር ለእነርሱ እንደ ሆነ አያምኑም። ድካማቸውን ተመልክተው «ሌሎች ምናልባት ሊገቡ ይችላሉ፥ እኛ ግን ከቶ አንችልም» ይላሉ። እንዴ! እስራኤላውያን ያሉት ይኸው አይደለምን? አለማመናቸው እግዚአብሔርን አስመርሮ የለምን? እንዳይገቡ የማለባቸው እንዲህ ስላሉ አይደለምን? እኛም ብዙዎቻችን ምድረ በዳ በሚመስል ሕይወት ገና የምንኖርበት በዚህ ባለማመናችን ጠንቅ ነው። ድነናል በእውነት፥ ነገር ግን አሁን የምንኖርበት ሕይወት የወተትና የማር ሳይሆን የድርቀት፥ የባዶነት፥ የኀዘን ፍሬ የሌለበትም ሕይወት ነው። ተስፋችን ጠፋ፥ የሚከናወንልን ነገር የለም፥ ተሸንፈንም እንኖራለን።

ድካም፥ ፈተናን ለማሸነፍ እንዴት እንደሚቸገር፥ ሥጋው ወደ ኃጢአት እንዴት እንደሚያዘነብል እርሱ ያውቃል። እንግዲህ ላለፈው ኃጢአታችን ምሕረትን፥ ወደ ፊትም ከኃጢአት እንድንጠበቅ ጸጋን እንድናገኝ በዚህ በታላቅ ሊቀ ካህናታችን በኩል ቀርበን ከአምላካችን ጋር እንገናኝና በማይቋረጥ ኅብረት በእርሱ እንረፍ።

ማስገንዘቢያ፡- «ታላቅ ሊቀ ካህናት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ።» (ቁ. 14) ኢየሱስ በአንድ አካሉ አምላክና ሰው ስለሆነ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ገብቶ ሊቀ ካህናት ሊሆን ይችላል። የካህን ሥራ የእግዚአብሔርን ቃል ወደ ሰው ዘንድ ለማድረስ ሰውንም በማይቋረጥ ኅብረት ወደ እግዚአብሔር ዘንድ ለማቅረብ ነውና አምላክና ሰው የሆነው ኢየሱስ ብቻ ሊቀ ካህናት ሊሆን ይችላል።

በብሉያት ዘመን ክርስቶስ እስኪመጣ ድረስ ምሳሌዎቹ የሆኑት ካህናት ነበሩ፤ ነገር ግን ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ሥራቸው ተፈጸመ፥ ዛሬም ካህናት አያስፈልጉም። (ገላ. 3፡24) የክህነት ሥራ አሁን ለክርስቶስ ተሰጥቶአል፥ ለዚህም ሥራ በእግዚአብሔር የተሾመው እርሱ ነው። ሰው ደፍሮ አይግባበት! ለክርስቶስ እንጂ ለእርሱ የማይገባውን ሥራ ለመያዝ ያሰበ ማናቸውም ሰው በድሎአል። (2ኛዜና. 26፡18)። በእውነት አስታርቆ ወደ እግዚአብሔር ሊያቀርብ የሚችል ካህን የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ብቻ ነው። የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች የሆኑ ቀሳውስት ይህን ነገር ልብ ያድርጉ!

# 2ኛ ክፍል። ኢየሱስ፥ የሃይማኖታችን ሊቀ ካህናት።
# (ም. 5-ም. 10)

## ም. 5-ም. 7። የኢየሱስ ክህነት የተሻለ ነው።

## ምዕራፍ አምስት

### መሾሙ

በመልእክቱ መጀመሪያ ክፍል ላይ ዋና ሐሳቡ ኢየሱስ ፍጻሜ የሆነውን የእጊአብሔርን ቃል ወደ ሰው ያደረሰ የእግዚአብሔር ሐዋርያ መሆኑ ቢሆንም ቅሉ፥ ስለ ሊቀ ክህንነቱ ደግሞ አልፎን አልፎን አንብበናል። (ም. 2፡17፤ 3፡1፤ 4፡14፥15) ደራሲው አሁን በሁለተኛው ክፍል ላይ ይህን የመልእክቱ ዓይነተኛ የሆነውን የሊቀ ክህንነቱን ትምህርት ያነሣል።

ም. 5 በሦስት ክፍል ይከፈላል። ከቁ. 1 እስከ ቁ. 4 ድረስ ደራሲው ሊቀ ካህናት የሚሆን ሰው ምን ዓይነት ሰው ሊሆን እንደሚገባ ሲገልጥ፥ ከቁ. 5 እስከ ቁ. 10 ድረስ ኢየሱስ ለዚህ ሥራ ፈጽሞ ተገቢ መሆኑን ያስረዳል። ቀጥሎ ደግሞ ከቁ. 11 እስከ ቁ. 14 ድረስ ሦስተኛውን የማስጠንቀቂያ ክፍል ጀምሮ «የመልከ ጼዴቅን ትምህርት ለማስተዋል ጆሮቻችሁ ፈዝዞዋል» ብሎ ዕብራውያንን ይወቅሳል።

ቁ. 1-4

> 1 ሊቀ ካህናት ሁሉ ስለ ኃጢአት መባንና መሥዋዕትን ሊያቀርብ ከሰው ተመርጦ ለእግዚአብሔር በሆነው ነገር 2 ሁሉ ስለ ሰው ይሾማልና፤ እርሱ ራሱም ደግሞ ድካምን ስለሚለብስ፥ ላልተማሩትና ለሚስቱት ሊራራላቸው ይችላል፤ 3 በዚህም ምክንያት ስለ ሕዝብ እንደሚያቀርብ እንዲሁ ስለ ራሱ ደግሞ መሥዋዕትን ስለ ኃጢአት ሊያቀርብ 4 ይገባዋል። እንደ አሮንም በእግዚአብሔር ከተጠራ በቀር ማንም ክብሩን ለራሱ የሚወስድ የለም።

በቁ. 1 ላይ «ይሾማልና» የተባለው ቃል ይህ ቁጥር የም. 4፡14-16 ተቀጣይ መሆኑን ያመለክታል። በዚያ ክፍል ላይ ደራሲው ስለ «ታላቅ ሊቀ ካህናት ስለ እግዚአብሔር ልጅ ስለ ኢየሱስ» ተናግሮ ነበር። ዕብራውያን መሢሕ ሲመጣ ነቢይ፥ ካህን፥ ንጉሥም እንደሚሆን አውቀው ኢየሱስ ከሌዊ ወገን አልነበረምና እርሱ ሊቀ ካህናት ለመሆን እንዴት እንደ በቃ ለማወቅ ተቸግረው ይሆናሉ። ስለዚህ አሁን ደራሲው መብቃቱንና በእግዚአብሔር መሾሙን ያስረዳል።

የትም ዘንድ ቢገኝ ሊቀ ካህናት የሚሆን ሰው የሚሾምበት ምክንያት የሰው እንደራሴ ሆኖ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን የሰውን ጉዳይ ለመፈጸም ነው። ዓይነተኛ ሥራውም አስፈላጊውን መባና መሥዋዕት በማቅረብ እግዚአብሔርንና ሰውን ማስታረቅ ነው። ይህን ማድረግ እንዲችል፥ መጀመሪያ፥ ሰው እንዲሆን ያስፈልጋል። ሰው ሲሆን እንደሚሠራላቸው ሁሉ ሆኖ እርሱ ራሱ በኃጢአታን በፈተና በድካምም የተከበበ ነው፥ ስለዚህ በትክክለኛ ሚዛን፥ ያለ መጠን ሳያከብድባቸው ስያደልላቸውም ሊመራቸው ይችላል። ፈጽሞ ሰው ነውና ኃጢአትን ይሠራል፤ በዚህም ምክንያት መሥዋዕትን ስለ ሕዝብ ከማቅረቡ በፊት ስለ ራሱ ማቅረብ ይገባዋል። አሮን ያደረገው ይህንኑ ነው (ዘሌዋ. 9፡7፥8፥15፤ 16፡6፥11፥15)። ሁለተኛ ደግሞ የሚሠራው በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ነውና በአንድ በኩል ከሰው መካከል ተመርጦ ስለ ሰው ሲሾም

በሌላ በኩል ደግሞ በእግዚአብሔር የተጠራ እንዲሆን ያስፈልጋል። በእግዚአብሔር ሳይጠራ የክህነትን ክብር ለራሱ መውሰድ የሚገባው ማንም ሰው የለም። በዚህም ነገር ደግሞ አሮን ምሳሌ ነው። (ዘጸ. 28፡1)

<u>ማስገንዘቢያ</u>፡-

ሀ) «ላልተማሩትና ለሚስቱት።» (ኩ. 2) ላልተማሩት ማለት ላላወቁት ማለት ነው። ሰው የሚሠራው ሁለት ዓይነት ኃጢአት አለ፡- 1ኛ፥ ሳያውቅ በስሕተት የሚሠራው፤ 2ኛ አውቆ ወድዶ በትዕቢት የሚሠራው። ለመጀመሪያው መሥዋዕት ይጠቅማል ይሰረይለትማል፤ ለሁለተኛው ግን መሥዋዕት የለም አይሰረይለትምም። (ዘሌ. 4፡2፥13፤ ዘኍ. 15፡22-31፤ ዘዳግም. 17፤12) «ሳያውቅ በስሕተት» ሲባልም ሠሪው ያለ እውቀት እንዳደረገው ብቻ አይደለም። ሊያስብበት ሳይችል በድንገተኛ ፈተና ቢወድቅ ወይም በንዴት ተይዞ ሳለ ኃጢአትን ቢሠራ፥ ወይም ደግሞ ሊያሸንፈው የማይችል ብርቱ ፈተና ቢጥለው በተለይም በሠራው ሥራ በኋላ ቢጸጸት፥ ይህ ሁሉ «ያለ እውቀት የተሠራ ኃጢአት» ይባላል፥ ለእርሱም መሥዋዕት ያገለግላል። አንድ ሰው ግን ያ ሥራ ኃጢአት መሆኑን አውቆ አመዛዝኖ ወድዶ ቢያደርገው፥ አድርጎም ባይጸጸትበት፥ ይህ «በትዕቢት የተሠራ ኃጢአት» ይባላል፥ ለእርሱም መሥዋዕት አያገለግልም፥ (ዕብ. 10፡26)። በኃጢአቱ ተጸጽቶ ወደ እግዚአብሔር ለመምለስ ለሚወደው ሰው ሁሉ ካህኑ ቆሞአል፥ መሥዋዕትን በማቅረብ ወደ ኅብረት ይመልሰዋል፤ ኃጢአትን በትዕቢት ለሚሠራ ሰው ግን ስርየት በፍሡም የለም።

ለ) «በእግዚአብሔር ከተጠራ በቀር ማንም ክብሩን ለራሱ የሚወስድ የለም።» (ቁ. 4)። እውነት ነው፥ ይህ የተጻፈ ለብልዩ ኪዳን ካህናት ነው፤ ሆኖም ለዛሬ ቀሳውስት ደግሞ ያገለግላል። ሰው መንፈሳዊ ሥራን የሚሠራ ከሆነ ከሰው ሹመት በላይ የእግዚአብሔርን ጥሪ እንዲቀበል የተገባ ነገር ነው። የእግዚአብሔርንም ጥሪ ያልተቀበለ ሰው በሰው መሾም አይገባውም።

## ቁ. 5-10

5 እንዲሁ ክርስቶስ ደግሞ ሊቀ ካህናት ሊሆን ራሱን አላከበረም ነገር ግን፡- አንተ ልጄ ነህ እኔ ዛሬ ወልጄሃለሁ ያለው እርሱ ነው፤ 6 እንደዚህም በሌላ ሥፍራ ደግሞ፡- አንተ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘላለም ካህን ነህ 7 ይላል። እርሱም በሥጋው ወራት ከሞት ሊያድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ጸሎትንና ምልጃን 8 አቀረበ፥ እግዚአብሔርንም ስለ መፍራቱ ተሰማለት፤ ምንም 9፡10 ልጅ ቢሆን፥ ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ተማረ፤ ከተፈጸመም በኋላ በእግዚአብሔር እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ሊቀ ካህናት ተብሎ ስለ ተጠራ፥ ለሚታዘዙለት ሁሉ የዘላለም መዳን ምክንያት ሆነላቸው።

አሁንም በእነዚህ ቁጥሮች ላይ ኢየሱስ ለክህነት ተፈላጊ የሆኑትን እነዚህን ሁለት ነገሮች እንደ ፈጸመ፥ ስለዚህም ተገቢ ሊቀ ካህናት እንደ ሆነ እናገኛለን። ደራሲው አስቀድሞ ሁለተኛውን ነገር አንሥቶ ኢየሱስ በእግዚአብሔር እንደተጠራና እንደተሾመ ይነግረናል፥ (ቁ. 5፥6)። ቀጥሎም ኢየሱስ ፈጽሞ ሰው እንደሆነና ሰው በመሆኑ ምክንያት የሰውን ፈተናና ድካም መከራውንም ሁሉ እንዳወቀ፥ ስለዚህም መጀመሪያውን ነገር እንደ ፈጸመ ያስረዳል። (ቁ. 7-10)።

በእግዚአብሔር ሳይጠሩ ሊቀ ካህናት ሊሆኑ ራሳቸውን ያከበሩ ሰዎች ኖረው ይሆናሉ፥ ይሁን እንጂ የክርስቶስ ሊቀ ክህንነት ከዚያ በበለጠ መሠረት ላይ ተመሥርቶአል። እርሱ ራሱን ሳያከብር በእግዚአብሔር የተጠራ ነው። «አንተ ልጄ ነህ፥ እኔ ዛሬ ወልጄሃለሁ» ያለው (መዝ. 2:7) ደግሞ «አንተ እንደ መልከ ጼዴቅ ሥርዓት ለዘላለም ካህን ነህ » ብሎታል። (መዝ. 109:4)። ያ ልጅነቱን ያመለከተ ክህንነቱንም ደግሞ አመለከተ ማለት ነው። እግዚአብሔርም ሲናገር በመጀመሪያው ቃል «ልጄ» በሁለተኛውም «ለዘላለም» በማለቱ በሁለቱ ቃሎች አምላክነቱን አመልክቶአል። ስለዚህ በእግዚአብሔር ወገን (በእግዚአብሔር በኩል) ኢየሱስ ሊቀ ካህን ለመሆን በቃ።

በሰው ወገን (በሰው በኩል) ደግሞ በቂ ሆኖ ተገኘ። በቁ. 1-3 ላይ እንደ ተባለው ሁሉ ስለ ሰው የሚሾም ሊቀ ካህናት ሁሉ ከሰዎች መካከል የተመረጠ እንዲሆንና እርሱ ራሱ ሰው በመሆኑ ምክንያት የሰውን ፈተናና ድካም ሁሉ እንዲያውቅ ተገቢ ነገር ነው። እንግዲያውስ ክርስቶስን እንመልከት። ሥጋ ለብሶ በጌቴሴማኒ አታክልት ገብቶ ከብርቱ ጩኅትና ከእንባ ጋር ጸሎትንና ምልጃን ሲያቀርብ፥ በመፍራት ለእግዚአብሔር ሲገዛ በተቀበለውም መከራ መታዘዝ የሚፈጅበትን ዋጋ (የመታዘዝን ኪሣራ) ሲማር፥ ሰው አይደለምን? ወይስ የሰውን ፈተናና ድካም አላወቀምን? ሊከለከለው ያልቻለው ብርቱ ጩኸቱ የጣዕሩን ብርታት፥ ያፈሰሰው እንባ ታላቅ እጦቱን፥ ምልጃው ለተፐለቀለቀ መዓት ረድኤት መፈለጉን ይገልጥ የለምን? ኧረ ሰው ነው፥ የሰውንም ነገር ሁሉ ፈጽሞ አውቆአል! ስለዚህ በሰው በኩል ደግሞ ሊቀ ካህናት ለመሆን በቃ። መከራን ተቀበለ። መከራንም በመቀበል የሰው ሊቀ ካህናት ለመሆን ፈጽሞ ተገቢ ሆኖ ተገኝቶአልና (ም. 2፥10) «አንተ እንደ መልከ ጼዴቅ ሥርዓት ሊቀ ካህናት ነህ» ብሎ እግዚብሔር ከጥንት የተናገረለት ቃል ሊፈጸመ ቻለ። ስለዚህ ለሚታዘዙለት ሁሉ የዘላለም መዳን ምክንያት ሆነላቸው። (ም. 7:24፥25)

<u>ማስገንዘቢያ:-</u>

ሀ) ሰው ሆይ፥ ሊቀ ካህናት እንዳለህ፥ ያም ሊቀ ካህናት ልዩ በሆነ በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተሾመልህ ታውቃለህን? ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ኃጢአት እግዚአብሔር የጠየቀውን ያን አንዱን ፍጹም የሆነውን መሥዋዕት ስላቀረበ፥ ይህንም ያደርግ ዘንድ እግዚአብሔር ራሱ ስለ ሾመው አንተን ወደ እግዚአብሔር ሊያቀርብ የሚችል የሚያቀርብም እርሱ ነው። «አይ! እርሱ ድካማችንን አያውቅም» ብለህ አትፍራው፥ ነገር ግን ወደ እርሱ ና፥ በስሙም ጥራ፥ በእርሱም በኩል ወደ እግዚአብሔር ያለ ፍርሃት ቅረብ።

ለ) «ከሞት ሊያድነው ወደሚችል» (ቁ. 7)። ብዙዎች ሰዎች፥ ሰማዕታትም ወንበዴዎችም፥ ከእርሱ በባሰ አምዋሚት ፊት ሲቆሙ ሳይፈሩና ሳይጨነቁ ሲሞቱ ክርስቶስ ሞትን ይህን ያህል ለምን ፈራ? ቢሉ፥ እርሱ ሰው ብቻ አለመሆኑን መገንዘብ ያስፈልገናል። ኢየሱስ የሕይወት ራስ ነበረ (ሐዋ. 3:15)፤ የሕይወት ራስ የሆነውም ሲሞት መሰቀቁ ይህን ያህል ነበረ ተብሎ የማይገመት ነው። ቢሆንም ያዘነው፥ የተከዘውም ነፍሱም እስከ ሞት ድረስ እጅግ ያዘነችው በፍርሃትም ሲጣጣር አጽንቶ የጸለየውና ወዙም በምድር ላይ እንደሚወርድ እንደ ደም ነጠብጣብ የሆነው ሞትን ስለ ፈራ ሳይሆን የዓለምን ኃጢአት መሸከሙንና ኃጢአት መደረጉን ከአባቱም ተለይቶ በእርሱ መቀሠፉን ስለ ፈራ ነው። (ማቴ. 26:37፥38፤ ሉቃ. 22:44፤ 2ቆሮ. 5:21፤ ማቴ. 27:46፤ ኢሳ. 53:4፥5)። የፈራው የሥጋን ሥቃይ ሳይሆን ከዚያ እጅግ በጣም የሚበረታውን የልብን ሥቃይ ነው፥ የሞተውም ከዚህ ከልብ ሥቃይ ነው። (ዮሐ. 19:34) ንጹሕና ቅዱስ የሆነው፥ አስጸያፊ

ኃጢአት ሲሆን ምን ያህል ያስቅቀው ይሆን? ኃጢአት መደረጉንም ብቻ ሳይሆን የፈራው ከዘላለም ጀምሮ ከአባቱ ጋር የነበረው ኅብረት መበጠሱን ነው። የፈራው ሞትን ሳይሆን ይህንኑ ነው። «ነፍሴ ታውካለችና ከዚህ ሰዓት አድነኝ» ብሎ የጸለየው ይህንኑ ሲፈራ ነው (ዮሐ. 12፡27)። «ቅዱሱ» ኃጢአት ሲሆን፥ አፍቃሪ አባቱ ተወዳጅ ልጁን ብቻውን ትቶ ሲቀሥፍ፥ ይህ ነው ያስደነገጠው። እኛ በኃጢአት የተወለድን ስንሆን (መዝ. 50፡5፤ ኤፌ. 2፡3) የኃጢአትን አስጸያፊነት ልናውቅ አንችልም፥ የእግዚአብሔር ቅዱሱ ግን በሙሉ አውቆታል። ይፈራት የነበርና «አባት ሆይ፥ ቢቻልስ ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ» ያላት ጽዋ ይህችው ናት። (ማቴ. 26፡49፤ ሉቃ. 22፡42)። በገዛ ብርታቱ ይህን ሞት ሊያልፍ እንደማይቻለው ተሰምቶት ከሞት ሊያድነው ወደሚችል ጸሎትን አቀረበ። እግዚአብሔርም ጸሎትን ሰምቶ የሚያበረታውን መልአክ ላከለት (ሉቃ. 22፡43)፥ በሥቃይ ጊዜውም ሁሉ የጸጥታን መንፈስ ሰጠው።

ሐ) «ምልጃ።» (ቁ. 7)። ምልጃ ማለት አንድ ሰው ታላቅ ጉዳት በፊቱ ሲነሣ እግዚአብሔር ይጠብቀውና ያግዘው ዘንድ የሚለምነው ልመና ነው (መዝ. 56፡1-4)። ቃል መናገሩን ብቻ ሳያመለክት የሰውን ናፍቆትና ጣዕር ያመለክታል። (ፊልጵ. 3፡13)

መ) «ተሰማለት።» (ቁ. 7)። ኢየሱስ ልመናውን ያቀረበው ወደዚያ ሥቃይ እንዳይገባ እንዳይሞትም ነውን? አይደለም! ስለዚያ ሥቃይ ብዙ ጊዜ ተናግሮ ነበር፥ የመጣበቱም ምክንያት ለመሞት ነበረ (ዮሐ. 12፡27)፥ ትንቢትም ሁሉ ይፈጸም ዘንድ እንደሚገባ አረጋግጦ ነበር። የለመነው በዚያ ሥቃይ ውስጥ ሳለ እንዲጠበቅና ከዚያ ሥቃይ እንዲወጣ ነው። ይህስ ባይሆን ኖሮ እንደምን «ተሰማለት» ተባለ? ጸሎቱ እንዳይሞት ከሆነ ኖሮ አልተሰማለትም፥ ሞቶአልና። ነገር ግን በዚያ ሥቃይና በዚያ ችግር ውስጥ ሳለ እንዲጠበቅና አሸናፊ ሆኖ እንዲወጣ ከጸለየ፥ ጸሎቱ ተሰማለት። ተሰማለትና ገና ሲጸልይ ሳለ የሚያበረታው መልአክ መጣለት፥ በገዢው ፊት ሲቆም ጲላጦስ እጅግ እስኪደነቅ ድረስ ዝም አለ፥ የገዢው ጭፍራ ሁሉ ሲከማችበትና ሲዘበትበት ታገሠ፤ ወደ ጎልጎታ ሲያስቸኩሉት ለራሱ ሳይሆን ለሌሎች ማሰብ ቻለ፥ በመስቀልም ላይ ሲሆን ወንበዴው እስኪያምንበት ድረስ በማይናወጥ ሰላም ተጠበቀ፥ በኋላም ከሞት ተነሣ። (ሉቃ. 22፡43፤ ማቴ. 27፡14፤ ማቴ. 27፡27-30፤ ሉቃ. 23፡28፤ ሉቃ. 23፡40-43፤ ዕብ. 13፡20)። ጸሎቱ ተሰማለት።

አንባቢ ሆይ፥ በፊትህ እንደሚያጥለቀልቅህ ጎርፍ የሚመስል በጣም የምትፈራው ነገር አለን? በእውነት እግዚአብሔርን ትፈራ እንደሆነ ጸሎትህና ምልጃህ ይሰማልሃል። ወደዚያ ጉዳት እንዳትገባ እግዘኢብሔር ይጠብቅሃልን? አይ! እንዳትገባ ምናልባት አይጠብቅህም፤ ነገር ግን በውስጡ ሳለህ ይጠብቅሃል፥ አሸናፊም አድርጎ ያወጣሃል። በመከራ እንድትፈጸም ታውቃለህን? ኢየሱስ በመከራ ተፈጸመ። ከዚያ መከራ አይጠብቅህም ይሆናል፥ በዚያ መከራ ግን ታላቅ ነገር ያደርጋል፥ ውጤቱም ግሩም ይሆናል። ጌቴሴማኒ ወደሚመስል ቦታ ብዙዎች ሰዎች ይገባሉ፥ በዚያም ቦታ በሌላ ዘንድ ከቶ ሊማሩ የማይችሉትን ነገሮች ይማራሉ። እዚሁ ትፈጸም ይሆናልና አይዞህ!

ሠ) «መታዘዝን ተማረ።» (ቁ. 8) «ኢየሱስ መታዘዝን ባያውቅ ነውን?» ቢሉ፥ አይደለም! ነገር ግን ሥጋ ከመልበሱ በፊት ለማንም መታዘዝ አላስፈለገውም። አሁን ግን ሥጋ ሲለብስ መታዘዝን ተምሮአል። ከዚህ በፊት በነገር ሁሉ ፍጹም ነበርና መታዘዝን ገዝቶአል!

መታዘዙ ግን አልተፈተነም ነበር፥ የመታዘዝንም ችግርና ኪሣራ አላወቀም። አሁን ግን በተቀበለው መከራ፥ በመፈተኑ፥ በመራቡ፥ በመሰደቡ፥ በጌቴሴማኒ በመጣጣሩ፥ በመገረፉና በመሰቀሉ ተፈትኖአል፥ መታዘዙም ፍጹም ሆኖ ተገኝቶአል። አዳም በወደቀበት በዚያም ነገር ኢየሱስ ፍጹም ሆኖ ተገኝቶአል ማለት ነው። «በመከራ መማር» ወይም «ከመከራ መማር» የተባለው ቃል እንደ «በመመረር መማር» ሆኖ በግሪክ ቋንቋ እንደ ግጥም ነበረና ለግሪኮች ሁሉ የታወቀ ቃል ነበረ። ኢየሱስም መታዘዝን ስለ ተማረ ለሚታዘዙለት ሁሉ መድኃኒት ለመሆን በቃ። (ቁ. 8:10)።

ረ) «ከተፈጸመ በኋላ» (ቁ. 9)። ኢየሱስ ከዚህ በፊት ፍጹም አለመሆኑ ነውን? በራሱ (በሰውነቱ) ፍጹም አለመሆኑ ከቶ አይደለም፤ ነገር ግን በም. 2፥10 ላይ እንዳገኘነው ነገር ነው። ከተቀበለው መከራ መታዘዙ ባይፈተን ኖሮ ኢየሱስ የዓለም መድኃኒት ለመሆን ባልበቃም። ሁለተኛ ደግሞ፥ የመታዘዝን ኪሣራ ባልተማረ ኖሮ የሰውን ፈተናና ድካም ባላወቀም ነበርና የሚምር ሊቀ ካህናት ለመሆን ባልበቃም። አሁን ግን ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ስለ ተማረ ተፈጸመ። ስለዚህ አስቀድሞ የዓለም መድኃኒት፥ ከዚያም በኋላ ሊቀ ካህናታችን ለመሆን ፈጽሞ ቻይና ተገቢ ሆነ። ወደ ታሰበለት ፍጻሜ ደርሶአል ማለት ነው።

እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ «አንተ እንደ መልከ ጼዴቅ ሥርዓት ለዘላለም ካህን ነህ» ብሎ ሾሞት ነበርና ኢየሱስ አሁን ወደ ዓለም ሲመጣ ለዚህ ሹመት የተፈጸመ፥ ማለት እንደ እግዚአብሔር ሐሳብ ሁሉ የተገባ እንዲሆን ያስፈልግ ነበር። መብቃቱ እንዲታወቅ በመከራ ተፈተነ። (ም. 2:10፤ 5:8፥9)። ፍጹም ሆኖ ተገኝቶ ወደ ሹመቱ ገባ ራሱንም ስለ እኛ ብሎ መሥዋዕትን አድርጎ ለእግዚአብሔር አቀረበ (ም. 7:27፤ 9:12፥26፥28፤ 10:10)። ከሙታን ተነሥቶ ያን በኃልጎታ የፈሰሰውን ደም መሠረት አድርጎ ስለ እኛ በማማለድና እኛን ወደ እግዚአብሔር በማቅረብ አገልግሎቱን ይቀጥላል፥ (1ዮሐ. 1:7፤ 2:1፥2፤ ሮሜ 8:34፤ ዕብ. 7:25፤ 9:24)።

ሰ) «የዘላለም መዳን ምክንያት ሆነ።» (ቁ. 10)። በም. 2:10 ላይ «የመዳን ራስ» ሲባል እዚህ ላይ «የመዳን ምክንያት» ተብሎአል። እዚያ ላይ ወደ ዘላለም መዳን የሚያደርስ መሪ አለቃ ሲሆን እዚህ ላይ የዘላለም መዳን ምንጭ ነው። ሁለቱም ሐሳቦች በትክክል ናቸው። ኢየሱስ የዘላለም መዳን ምክንያት የሆነው 1ኛ፥ ሊቀ ካህናታችን ሆኖ በዚህ ዓለም ላይ ሳለ ባቀረበው መሥዋዕት ይህን የዘላለም መዳን በማስገኘቱ ነው፤ 2ኛ፥ ዛሬ ደግሞ ሊቀ ካህናታችን ሆኖ በመንግሥተ ሰማያት ሳለ በማይቋረጥ ኅብረት ወደ እግዚአብሔር ዘንድ በማቅረቡ ነው።

## ቁ. 11-14

11 ስለ እርሱም የምንናገረው ብዙ ነገር አለን፥ ጆሮቻችሁም ስለ ፈዘዙ በቃል
ልንተረጕመው ጭንቅ ነው 12 ከጊዜው የተነሣ አስተማሪዎች ልትሆኑ ሲገባችሁ፥
አንድ ሰው ስለ እግዚአብሔር ቃላት መጀመሪያ ያለውን የሕፃንነትን ትምህርት
እንዲያስተምራችሁ እንደገና ያስፈልጋችኋልና፤ የሚያስፈልጋችሁም ወተት ነው 14
እንጂ ጠንካራ 13 ምግብ አይደለም። ወተት የሚጋት ሁሉ ሕፃን ስለ ሆነ
የጽድቅን ቃል አያውቅምና፤ ጠንካራ ምግብ ግን መልካሙንና ክፉውን ለመለየት
በሥራቸው የለመደ ልቦና ላላቸው ለፍጹማን ሰዎች ነው።

አሁን ደግሞ ከዚህ አንሥቶ እስከ ም. 6 መጨረሻ ድረስ የማስጠንቀቂያን ክፍል እናገኛለን። ታላቅ ጥቅም የሚገኝበት ይህ ግሩም የሆነ የሊቀ ክህንነቱ ትምህርት ተሰጠን፤ አስተውለነዋልን?

አልሠሩም ነበር፤ እንደዚሁም ደግሞ ብዙዎች ክርስቲያኖች አይሠሩም። የእግዚአብሔርን ቃል ተመራምረው ከበለጠ ወደ በለጠ እውቀትና ማስተዋል መድረስ ሳይሰቡ እንዲያው የሚያድጉ ይመስላቸዋል። ስሕተት ነው። በመንፈሳዊ ነገር የምናድገው ሥራ በመሥራት፥ ማለት መጽሐፍ ቅዱስንና ዶክትሪኑን አጥብቆ በማጥናትና በማሰላሰል ነው እንጂ በእግዚአብሔር ቃላት ባለው በህፃንነት ትምህርት ጠግቦ በመቀመጥ አይደለም። ሃይማኖት ማለት እውቀትና ማስተዋል ብቻ አይደለም፥ ሆኖም እውቀትና ማስተዋል ሲያድጉ እምነት እንደሚያድግ የታወቀ ነገር ነው። ጠንካራ ምግብን በማኘክ በመንፈሳዊ ነገር ምሉእንና ፍጹማን ለመሆን እንጣር እንጂ ገና ሕፃናት ሆነን እንዳንቀር እንጠንቀቅ።

# ምዕራፍ ስድስት

## ሳንጠራጠር ወደ ፍጻሜ እንሂድ

ይህን ምዕራፍ ገና ከመጀመራችን በፊት ሐሳቡ የም. 5፥ ሐሳብ መሆኑን እንገነዘብ ዘንድ የሚገባን ነገር ነው። በም. 5፡14ና በም. 6፡1 መካከል ምዕራፍን ከምዕራፍ የሚለያየው አርእስት የገባው በደራሲው ሳይሆን ከእርሱ ዘመን ወዲህ በተነሡ መምህራን ነው። ደራሲው ደብዳቤ (መልእክት) ይጽፍ ነበር፤ ደብዳቤውንም በምዕራፍና በቁጥር አልከፋፈለም። ስለዚህ «ምዕራፍ 6።» የሚለው አርእስት ወደ አዲስ ሐሳብ እንደ ደረስን አስመስሎ አያሳስበን። ደራሲው በቁ. 1 ላይ «ስለዚህ» ብሎአልና ያን የቀደመውን ሐሳብ መቀጠሉን እንረዳለን። ማለት፥ በመንፈሳዊ እውቀትና ማስተዋል ገና «ሕፃናት» ስለ ሆኑ እና በመንፈሳዊ እውቀትና ማስተዋልም «ፍጹማን» ስለ ሆኑ ሰዎች ገና መናገሩ ነው። ምዕራፉም የሦስተኛው ማስጠንቀቂያ ክፍል ሁለተኛ ግማሽ ነው።

### ቁ. 1-3

> 1፥2 ስለዚህ የክርስቶስን ነገር መጀመሪያ የሚናገረውን ቃል ትተን ወደ ፍጻሜ እንሂድ፤ መሠረትን ደግመን እንመሥርት፥ እርሱም ከሞተ ሥራ ንስሐና በእግዚአብሔር እምነት፥ ስለ ጥምቀቶችና እጆችንም ስለ መጫን ስለ ሙታንም 3
> ትንሣኤ ስለ ዘላለም ፍርድም ትምህርት ነው። እግዚአብሔርም ቢፈቅድ ይህን እናደርጋለን።

ደራሲው ስለ «መጀመሪያ ነገር» ሲጽፍ በም. 5፡12 ላይ ስለ «እግዚአብሔር ቃላት»፥ ቀጥሎም በም. 5፡13 ላይ ስለ «ጽድቅ ቃል»፥ ቀጥሎ ደግሞ በም. 6፡1 ላይ ስለ «ክርስቶስ ነገር» ይናገራል። እነዚህም ሦስቱ ነገሮች አንድ ናቸው። እግዚአብሔር ስለ ጽድቅ የተናገረው ቃል ነው ወይም፥ የክርስቶስ ነገር ነው። ሕፃናት የዚያን ነገር መጀመሪያ ብቻ አውቀዋል፥ ለእነርሱም ተስማሚ ነገር ነበረ፤ ነገር ግን እስከ ዘላለም ሕፃን ሆኖ መቅረት መልካም ነገር አይደለምና (1ቆሮ. 14፡20፤ 13፡11) ደራሲው አሁን ሕፃንነትን ትተው ወደ ሽምግልና (ወደ ፍጻሜ) ይሄዱ ዘንድ የሚጽፍላቸውን ዕብራውያንን ይመክራቸዋል። «ፍጻሜ ነገር የተባለውስ ምን ነገር ነው?» ቢሉ፥ ያ በም. 5 ላይ የተጠቀሰው የክርስቶስ ሊቀ ካህንነት ትምህርት ነው። ለክርስቶስ ነገር መሠረት አለው፥ ይኸንኑም መሠረት ዕብራውያን ይዘውታል፤ ነገር ግን መሠረት የአንድ ነገር መጀመሪያ ብቻ ነው፤ ከመሠረቱም በላይ ሌላ ብዙ ነገር እንደሚጨመር ታስቦአል፤ ዕብራውያንም የክርስቶስን ነገር መጀመሪያ ትተው ወደ ፍጻሜ መሄድ ይገባቸዋል።

«የክርስቶስ ነገር መጀመሪያ፥ ወይንም መሠረት የሆነው ትምህርት ምን ትምህርት ነው?» ቢሉ፥ ደራሲው 2፡2 እያደረገ የሚጠቅሳቸው ስለ 6 ነገሮች የሚናገር ትምህርት ነው፡-

1ኛ፤ «ከሞተ ሥራ ንስሐና በእግዚአብሔር እምነት።» ንስሐ መግባት በእውነት የነገሩ ሁሉ መጀመሪያና መሠረት ነው። ሰው ንስሐ ካልገባ ወደ እግዚአብሔር ከቶ አይቀርብም። (ሉቃ. 15፡17-19)። ሆኖም ንስሐ ብቻ አይበቃም። ንስሐ ወደ እምነት እንዲያደርስ ያስፈልጋልና ሁለተኛው ነገር ያው በእግዚአብሔር ማመን ነው፤ ይህም የቀድሞ ሐዋርያት ያስተማሩት መጀመሪያ ትምህርት ነው። (ሐዋ. 2፡38፤ 1፡21)።

2ኛ፤ «ጥምቀቶችና እጆችን ስለ መጫን።» በአንዱ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ እነኝህ ሦስተኛና አራተኛ ነገሮች ናቸው። ንስሐ ገብቶ በእግዚአብሔር ያመነ ሰው ይጠመቃል፤ በሐዋርያትም

ዘመን እንደ ተነገረው ሁሉ ከተጠመቀ በኋላ ደግሞ እጆች ይጫኑበት ነበር። (ሐዋ. 8:14-17፤ 19:5:6)።

3ኛ፤ «የሙታን ትንሣኤና የዘላለም ፍርድ።» እነኝህ በዚህ ዓለም ላይ የአንድ ክርስቲያን የሕይወቱ መጨረሻ ነገሮች ናቸው፥ በመሠረታዊ ትምህርትም ውስጥ መጨረሻዎቹ ናቸው።

እነኝህ ሁሉ የክርስቶስ ነገር መጀመሪያዎች ናቸው። ይሁን እንጂ፥ ጅምር ሲኖር ፍጻሜ የግድ ይኖራልና ደራሲው ዕብራውያን እነዚህን መጀመሪያዎች ትተው ወደ ፍጻሜ እንዲሄዱ ይፈልጋል። ፈቃዱ ይኸው ነውና እነዚህን መሠረታዊ የሆኑትን ነገሮች እንደ ገና ለማስተማር (ለመመሥረት) ሳያስብ እነርሱንም ንቆ ሳይሆን ልጅ ሀ፡ሁን ትቶ ከፍ ወደ አለው እንደሚጓዝ ሁሉ እንደዚሁም እነዚህን ትቶ ወደ ፍጻሜ ትምህርት ለመሄድ ይፈልጋል፤ የእግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ እንደሆን ይኸን ለማድረግ ቆርጦአል፥ ዕብራውያንም አብረውት እንዲሄዱ ይመኛል።

<u>ማስገንዘቢያ</u>:-

ሀ) «ወደ ፍጻሜ እንሂድ።» (ቁ. 1)። እኛ ገና የጀመርን ስንሆን ወዲያውኑ ወደ ፍጻሜ የደረስን አይምሰለን። በክርስቶስ አምነን የኃጢአታችንን ይቅርታ ማግኘት በእውነት እጅግ በጣም ታላቅ ነገር ነው፤ ሆኖም የመዳን መጀመሪያ ነገር ብቻ ነው። ጽኑ መሠረት ነው፤ ይሁን እንጂ በማናቸውም መሠረት ላይ ሌላ ነገር እንደሚጨመር የታሰበ እንደመሆኑ መጠን በዚህም መሠረት ላይ ብዙ ነገር አለ። ስለዚህ በመጀመሪያ ነገሮች ብቻ ሳንጠግብ እነርሱን ትተን ወደ ፍጻሜ ነገር፥ ይኸውም በሊቀ ካህናታችን በኢየሱስ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረትን ወደ ማግኘትና የእግዚአብሔርን ሕይወት ወደ መካፈል እንሂድ።

ለ) «የሞተ ሥራ።» (ቁ. 1)። «ይህስ ምን ኖሮአል?» ቢሉ፥ ከም. 9፥14 ጋር ማነጣጠር ነው። ወይም ወደ ሞት የሚያደርስ፥ ወይም ወደ ሕይወት ለማድረስ የማይችል ሥራ ይሆናል ማለት፥ ኃጢአት ይሆን ይሆናል። (ሮሜ 6:23፤ ኤፌ. 2:1)። እንደዚህም ሲሆን «ከሞተ ሥራ ንስሐ» ማለት የጠፋው ልጅ ኃጢአቱን ትቶ ወደ አባቱ በመምጣት ንስሐ እንደ ገባ ይሆናል። (ሉቃ. 15:20)። ወይም ደግሞ የሞተ ሥራ በማይጠቅሙ የአሪት ሥርዓቶች መታመን ይሆን ይሆናል። (ሮሜ 3:20፤ ገላ. 2:16)።

ሐ) «ጥምቀቶች።» (ቁ. 2)። ይህ ቃል በብዙኑት ስለ ተጻፈ አንዳንዶች መምህራን «ደራሲው የሚናገረው ስለ አይሁድ ጥምቀቶች፥ ስለ እጅ መታጠብና ስለ ዕቃ ማንጻት ነው እንጂ ስለ ክርስቲያን ጥምቀት አይናገርም» ይላሉ። ዳሩ ግን በብዙኑት የተናገረው የዮሐንስንና የአይሁድን ጥምቀቶች የሚመሳስሉ አያሌ ጥምቀቶች ስለ ተገኙ ነው። (ማር. 7:4፤ ሐዋ. 18:25፤ 19:3፤ ዕብ. 9:13)። የሆነ ሆኖ በሐዋርያት ዘመን የተገኙት ምእመናን ሁሉ የክርስቲያን ጥምቀት ምን እንደሆነና ከሌሎቹ ጥምቀቶች በምን እንደ ተለየ ምሥጢሩን ደህና አድርገው እንደ ተማሩ እናውቃለን። ዲድስቅልያ የተባለው መጽሐፍ የሚጠመቁ ሰዎች ሁሉ የክርስቶስን ነገርና የጥምቀትን ምሥጢር አስቀድመው ይማሩ ዘንድ በም. 7 ላይ ያዝዛል። ስለዚህ ደራሲው እዚህ ላይ ስለ ክርስቲያን ጥምቀት ይናገራል እንላለን።

ቁ. 4-8

4 አንድ ጊዜ ብርሃን የበራላቸውን ሰማያዊውንም ስጦታ የቀመሱትን ከመንፈስ
ቅዱስም ተካፋዮች ሆነው የነበሩትን 5 መልካሙንም የእግዚአብሔርን ቃልና
ሊመጣ ያለውን የዓለም ኃይል የቀመሱትን በኋላም የካዱትን 6 እንደ ገና ለንስሐ
እነርሱን ማደስ የማይቻል ነው፤ ለራሳቸው፤ የእግዚአብሔርን ልጅ ይሰቅሉታልና
ያዋርዱትማልና። 7 ብዙ ጊዜ በእርስዋ ላይ የሚወርደውን ዝናብ የምትጠጣ መሬት፥
ለሚያርሱአትም ደግሞ የምትጠቅምን አትክልት የምታበቅል 8 ከእግዚአብሔር
በረከትን ታገኛለችና፤ እሾህንና ኩርንችትን ግን ብታወጣ፥ የተጣለች ናት
ለመረገምም ትቀርባለች፥ መጨረሻዋም መቃጠል ነው።

ሐዋርያው ወደ ፍጻሜ ይሄዱ ዘንድ በመምከር ላይ ነውና ዳተኞች ሳይሆኑ እስከ መጨረሻ እያንዳንዳቸው ትጋትን እንዲያሳዩ ለማደፋፈር ብሎ አሁን በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ወደ ፊት ሳይሆን ወደ ኋላ ስለሚሄዱ ሰዎች ጥቂት ይናገራል። እነኝህ ወደ ኋላ የሄዱ ሰዎች ክርስቲያኖች መስለው በማኅበር ውስጥ ሲቀመጡ ቆዩ። «የክርስቶስን ነገር መጀመሪያ» የሚናገረውን ቃል ተምረው ተረድተውታል፤ ለሰው ልጆች የሚሆነውን በክርስቶስ በኩል የመጣውን የእግዚአብሔርን ስጦታ ቀምሰዋል ጣዕሙንም አውቀዋል ወደውታልም፤ መንፈስ ቅዱስ በምእመናን መካከል በኃይል ሲሠራ አይተዋል፥ እነርሱም ራሳቸው ያንን ኃይል ከማኅበሩ ጋር ተካፍለዋል (ማቴ. 7፡22፥23፤ 1ቆሮ. 13፡1፥2)፥ የእግዚአብሔርም ቃል መልካም እንደ ሆነ ቀምሰዋል ሊመጣ የላውንም የዓለም ኃይል ከሩቅ ሆነው አይተዋል ተሳልመውታልም (ም. 11፡13)፥ ራሳቸውም የመንፈስ ቅዱስን ሥራ በልባቸው ውስጥ አምቀዋል (ዮሐ. 16፡8፥14) እንጂ፥ በእርስዋ ላይ ብዙ ጊዜ የሚወርደውን ዝናብ ጠጥታ እሾህንና ኩርንችትን ብቻ የምታወጣውን መሬት መስለው ይህ ሁሉ በረከት ከተንጠባጠበባቸው በኋላ፥ ከሰሙና ከአወቁ ከተረዱም ወዲያ ቢክዱ፥ እንደ ገና ወደፊት ሊያስኬዳቸው የሚችል የለም። እንግዲያውስ ደራሲው ተመልሶ መሠረትን እንደ ገና ሳይመሠርት ወደ ፍጻሜ ትምህርት ለመሄድ ቆርጦአል። እነዚያ ሰዎች ሁሉን አዩ፥ ሁሉንም ቀመሱ፤ ካዱ! እንግዲያውስ አሁን በምን ይመለሱ? ደራሲው «አይቻልም» ይላል። ክርስቶስን አይተዋል ነገሩንም ሁሉ ቀምሰዋል፤ መልሰውም «እንፈልገውም ይሰቀል!» ብለው አዋርደውታል። (ማቴ. 27፡21-23)። ውጤቱስ? ውጤቱማ መጣል፥ ለመረገም መቅረብ (ማር. 11፡14)፥ በመጨረሻውም መቃጠል ነው።

<u>ማስገንዘቢያ</u>።

ሀ) ልብ እናድርግ፤ እነኝህ ደራሲው እዚህ ላይ የሚናገርላቸው ሰዎች በስም ብቻ ክርስቲያኖች የሆኑት አይደለም፥ በስም ብቻ ክርስቲያን የሆነ ሰው የሚያፈገፍግበት ደረጃ የለውምና። እንደዚሁም ዳግመኛ የተወለዱት ክርስቲያኖች አይደሉም። እነኝህ ግን ክርስቶስን መከተል የጀመሩትም ስንኳንም በክርስቶስ ትምህርት ብዙ እርምጃ ያደረጉት ናቸው፥ ከፍ ወዳለውም ደረጃ ደርሰዋል። ነገር ግን አፈግፍገዋል፥ ማፈግፈግም ብቻ ሳይሆን የተማሩትንና የፈተኑትን የተረዱትንም ጠልተው በፍጹም የካዱና ወደ ሌላ ሃይማኖት የገቡ ናቸው። በቁ. 8 ላይ የተጻፈው ፍርድ የሚደርሰው እንደነዚህ ባሉቱ ላይ ነው።

መቼም ደራሲው በእርሱ ዘመን ወደ ነበሩት ዕብራውያን ይጽፋልና እነርሱ በዚያ ሁሉ ችግር ምክንያት ወደ ኋላ በመመለስ ክርስቶስን ክደው ወደ አይሁድ ሥርዓት ቢመለሱ የሚደርስባቸውን ፍርድ በመግለጽ ሲያስጠነቅቃቸው ነው። ይሁን እንጂ፥ መንፈስ ቅዱስ በእነዚህ ቃላት ውስጥ ለክርስቲያኖች ደግሞ ይናገራል። ብዙዎች ክርስቲያኖች እንደሚያፈገፍጉ

የማይካድ ነገር ነው። ሆኖም፥ ክርስቲያኖች በመሰሉት በሌሎችም ሰዎች ዘንድ ክርስቲያኖች እንደሆኑ በተቆጠሩትና በእውነተኞች ክርስቲያኖች መካከል፥ እንደዚሁም ሁሉ በማፈግፈግና በፍጹም መካድ መካከል ልዩነት መኖሩን ልብ ማድረግ ያስፈልገናል። ክርስቶስን አሳልፎ እንደ ሰጠው እንደ ይሁዳ ሆነው ዳግመኛ ያልተወለዱ በክርስቲያኖች መካከል የሚቀመጡና ከእነርሱም ጋር በክርስቶስ በረከቱን እየተካፈሉ በጎደኞቻቸው ዘንድ ክርስቲያኖች እንደ ሆኑ የሚቆጠሩ አሉ። መቼም ነገሩ በእነዚህ ቁጥሮች ላይ እንደ ተገለጠው ነው። ሰው ክርስቲያን መስሎ በክርስቲያኖች መካከል ሊቀመጥና ሊመላለስ ይችላል። ወንጌል ሲሰበክ ጣዕሙ ደስ ይለዋል፥ በአእምሮም ያምናል። መንፈስ ቅዱስ በልቡ ውስጥ ሊሠራ ይጀምራል ደስታም ይሰማዋል። ይህ ሁሉ ይሁን እንጂ ይህ ሰው ዳግመኛ ሳይወለድ ሊቀር ይችላል፥ በእውነትም ክርስቲያን አይደለም። እንደዚህም ሲሆን አፈግፍጎ በጥራሽ ወደ መካድ ሊደርስ ይችላል፤ ይህም ሲሆን ልቡ ይደነድናል፤ የክርስቶስንም ነገር በሙሉ አውቆአልና ወንጌልን አሁን ሲሰማ ልቡ አይነካም፥ መንፈስ ቅዱስም ምንም ሊሠራ አይችልም። ስለዚህ ያ ሰው ለዘላለም ይጠፋል። እርሱን የመሰሉ ሰዎች እኛንም ራሳቸውንም ሊያታልሉ ይችላሉ። በስንዴ መካከል እንደ ተዘሩት እንድክርዳዶች ናቸው። በፍርድ ቀን ይገለጣሉ እንጂ እኛ ዛሬ ልናውቃቸው አንችልም። (ማቴ. 13:24-30)። ሰው እውነተኛ ክርስቲያን መሆኑ የሚገለጠው የክርስቲያንን ፍሬ ቢያፈራና ይልቁንም እስከ መጨረሻው ቢጸና ብቻ ነው (ማቴ. 7:15-20፤ ዕብ. 3:6፥14)። ሌላ ምልክት የለም። ሰው አፈግፍጎ ወደ መካድ ቢደርስ ያ ሰው ዳግመኛ አለመወለዱን ልናውቅ እንችላለን።

ክርስቶስን በእውነት የተቀበለ ክርስቲያን ለዘላለም ሊጠፋ እንደማይችል መጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ቦታ ያመለክተናል። በክርስቶስ በመታመን ምክንያት የሚያገኘው «የዘላለም» ሕይወት ነውና ከቶውንም አይጠፋም (ዮሐ. 5:24፤ 6:38፤ 7:47፤ 10:27-29፤ ሮሜ 8:1፤ ኤፌ. 4:30፤ 1ጴጥ. 1:3-5)። ዳግመኛ ከእግዚአብሔር የተወለደ ሰው እስከ መቼም ቢሆን የእግዚአብሔር ልጅ ነውና ከቶውንም አይጠፋም። ማፈግፈግ ይቻለዋል፤ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ይጠብቀዋልና ወደ ፍጹም መካድ ከቶ አይደርስም። ያፈገፈገ እንደሆነ ከዕለታት አንድ ቀን ይመለሳል። ማፈግፈግ አፈግፍጎአል፥ ነገር ግን ወደ ፍጹም መካድ አይደርስምና መዳኑ በድንገት እሳት ሌሊት በተነሣ ጊዜ ሰው ሸሽቶ ባዶ እጁን እንደሚድን እንኳ ቢሆን ይድናል። (1ቆሮ. 3:15)

የሆነ ሆኖ፥ ሰው በማፈግፈግ ቢጸና ክርስቶስን ፈጽሞ እንዳይክድ እጅግ በጣም የሚያስፈራ ነገር ነውና መጽሐፍ ቅዱስ በልዩ ልዩ ቦታ እውነተኛ ክርስቲያኖችን እንኳ ከዚህ ነገር የሚያስጠነቅቅ ይመስላል። (ማቴ. 24:13፤ ሉቃ. 9:62፤ ዮሐ. 15:6፤ ሮሜ 11:20-22፤ ይሁዳ ቁ. 5፤ 1ቆሮ. 10:5-12፤ ገላ. 5:4፤ ዕብ. 10:26፤ 2ጴጥ. 2:20-22፤ 1ዮሐ. 5:16፤ ሕዝቅ. 18:24)። ክርስቶስን አንድያውን መካድ መቼም ስርየት ለዘላለም የማይገኝለት ኃጢአት ነው። (ማር. 3:28-30)።

አንባቢ ሆይ፥ አንተስ የት ነህ? የሄድከው ወደ ፊት ነው፥ ወይስ ወደ ኋላ? ዱሮ የክርስቶስን ነገርቀመስህ ጣዕሙንም አጣጣምህ። በዚያን ጊዜ በእርሱ ደስ አለህ። ዛሬሳ? በአንተ ላይ እግዚአብሔር ሰውም ብዙ ሠርተዋል፤ ዝናቡ ከመውረድ መሬቱም ከመታረስ አልቀረም፥ የምትጠቅም አትክልት ሆነህ በቅለሃልን፥ ወይስ እሾህንና ኩርንችትን አውጥተሃል? ያን የቀደመውን ፍቅርህን ትተሃልን? (ራእ. 2:4) ወደ ኋላ ማፈግፈግ እጅግ በጣም የሚያስፈራ ነገር ነውና ገና ጊዜ ሳለ ንቃ ተመለስም። ወደ ፊታችን እንዲህ ያለ ሀብት ሲቆየን፥ ከዚህ በፊትም እንደዚያ ያለ ውለታ ከዋለልን፥ ለምን አሁን እናፈገፍጋለን? (ኤርም.

2፡1-7፥31-37) እጅግ በጣም እንጠንቀቅ! በዚህ ክፍል ውስጥ የተጻፉት ቃሎች ኃይል ያላቸው ናቸው።

ለ) «እንደ ገና ለንስሐ እነርሱን ማደስ የማይቻል ነው።» (ቁ. 6)። «እንደምን አይቻልም?» ቢሉ ደራሲው መችም ስለ ራሱ ይናገራል። ያን መጀመሪያውን ትምህርት እንደ ገና ማስተማር ያላሰበበት ምክንያቱ እነዚያ ሰዎች እንደማይቀበሉት ስለሚያውቅ ነው። ያን ሁሉ ተምረው ከተረዱት በኋላ «በፍጹም አንፈልግም» ብለዋል በመካዳቸውም ጸንተዋል። ለመመለስ ፈቃደኞች አይደሉምና እነርሱን እንደ ገና ማስተማር ዕንቁን በእሪያዎች ፊት የመጣል ያህል ነው። (ማቴ. 7፡6) ስለዚህ እንደ ገና ለንስሐ እነርሱን ማደስ የማይቻል ነው።

## ቁ. 9-12

9 ስለ እናንተ ግን፥ ወዳጆች ሆይ፥ ምንም እንኳ እንዲሁ ብንናገር፥ አብልጦ
የሚሻለውና ለመዳን የሚሆነው እንዲሆንላችሁ ተረድተናል። 10 እግዚአብሔር፥
ቅዱሳንን ስላገለገላችሁ እስከ አሁንም ስለምታገለግሉአቸው፥ ያደረጋችሁትን ሥራ
ለስሙም ያሳያችሁትን ፍቅር ይረሳ ዘንድ ዓመፀኛ አይደለምና። 11፡12 በእምነትና
በትዕግሥትም የተስፋውን ቃል የሚወርሱትን እንድትመስሉ እንጂ ዳተኞች
እንዳትሆኑ፥ ተስፋ እስኪሞላ ድረስ እያንዳንዳችሁ ያን ትጋት እስከ መጨረሻ
እንድታሳዩ እንመኛለን።

ደራሲው ይህን ሁሉ የተናገረው ለማስጠንቀቂያ ያህልና እስከ መጨረሻም እንዲጸኑ ሊያደፋፍራቸው ነው እንጂ ዕብራውያን ክርስቶስን እንደ ካዱ በእውነት አላሰበም። ላለመካዳቸው ሥራቸው ይመሰክራል። መጥምቁ ዮሐንስ ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ወደ ጥምቀቱ ሲመጡ አይቶ፡- ለንስሐ የሚገባ ፍሬ አድርጉ እንዳላቸው (ማቴ. 3፡7፥8) እንዲሁም አሁን ደራሲው፡- እናንተ ወዳጆች ሆይ፥ ለመዳን የሚሆነው ነገር እንደሚሆንላችሁ ተረድተናል ይላል። ስድስቱ ቃላተ ወንጌል የተጻፉበት ምዕራፍ የሚያስተምረው ነገር ነው። ሰው እውነተኛ ክርስቲያን መሆኑ የሚታወቀው በሚያደርገው ፍሬ፥ ወይም በሚሠራው ሥራ ነው። በጎች የተባሉቱ የተጠቀሱትን 6 ነገሮች ያደረጉት፥ ክርስቲያኖች ስለ ነበሩ ነው። እምነታቸው በሥራቸው ተገልጦአል! Cክስቲያኖች መሆናቸውም ታውቆአል። (ማቴ. 25፡34-40)። እንደዚሁም ሁሉ እነኝህ ዕብራውያን ቅዱስሳንን ያገለገሉ የነበረው የክርስቶስን ስም ስለ ወደዱ ነው። እውነተኞች ክርስቲያኖች ነበሩ፥ ስለዚህ ሐዋርያው ደግሞ «ወዳጆች» ይላቸዋል በቁ. 4-8 ላይ ከተጠቀሱትም ሰዎች ሊለያቸው «ግን» በሚባለው አፍራሽ ንግግሩን ይቀጥላል። ይሁን እንጂ፥ ዳተኞች ሳይሆኑ እየበረቱና እየጠከሩ ተስፋ እስኪሞላ፥ ማለት ወደ ፍጽሜ እንዲሄዱ ይፈልጋል። የብሉይ ኪዳን ዘመን አማኞች እነአብርሃም የተስፋውን ቃል አመኑ ሆናም በአንድ ቀን ውስጥ አልተቀበሉም። አመኑ ግን፥ ከአመኑም በኋላ መታገሥ ሆነባቸው። መታገሥም ጠንከር መያዝ መጽናትም ማለት ነው። እንደዚሁም እነዚህ ዕብራውያን (እኛም) ስያሰለቹ ሳይታክቱ ሳይዝሉም (ሳንሰለች፥ ሳንታክት፥ ሳንዝልም) ተስፋ እስኪሞላ ያንን ትጋት እስከ መጨረሻ (ም. 3፡6፥14) እንዲያሳዩ ይለምናሉ። (እንድናሳይ እንለመናለን።)

<u>ማስገንዘቢያ</u>፡-

ሀ) «እግዚአብሔር . . . ያደረጋችሁትን ሥራ ለስሙም ያሳያችሁትን ፍቅር ይረሳ ዘንድ ዓመፀኛ አይደለም።» (ቁ. 10)። እግዚአብሔር የዓመፀኛ ተቃራኒ ነው። ዓመፀኛ ሳይሆን ፈጽሞ

ጻድቅ ነው። ስለዚህ ኃጢአትን እንደማይረሳ ሁሉ እንዲሁም በክርስቶስ ስም የተሰጠውን አንድ ጽዋ ቀዝቃዛ ውኃ ስንኳ አይረሳም (ማር. 9፥41)።

ለ) «ተስፋ እስኪሞላ ድረስ ።» (ቁ. 11፥12)። ይህ ተስፋ ምንድን ነው? ቢሉ፥ ተስፋማ ቀጥሎ ከቁ. 13-20 ላይ የተነገረለት ለአብርሃምና ለዘሩ የተሰጠው የተስፋ ቃል ነው። ስለዚህ ተስፋ በም. 9፡15ና በም. 10፡36 ላይ ደግሞ እናነባለን። በዘፍጥ. 22፡16-18 ላይ እንደምናየው ሁሉ ለአብርሃምና ለዘሩ የተሰጠው የተስፋ ቃል የበረከት ሙላት፥ የመብዛትና የድል መንግሥት ተስፋ ነበረ። እንደ ተስፋውም ቃል ሆነ። የአብርሃም ሕይወት በእውነት የእግዚአብሔር በረከት ያደረበት ሁለተናውም ልዩና ግሩም የሆነ ሕይወት ነበረ። የእግዚአብሔር ወዳጅ እስከ መባል ኅብረትን አግኝቶ ከእግዚአብሔር ጋር ይነጋገር ነበር። እግዚአብሔር ምሥጢሩን እየገለጠለት ልመናውን ይሰማ ነበር። (ያዕ. 2፡23፤ ዘፍ. 18፡17-21፥23-33)። «ዘርህ የጠላቶችን ደጅ ይወርሳል» ሲባል እስራኤላውያን ሰባት አሕዛብ የኖሩበትን ከነዓንን ለማሸነፍ በቁ። (ዘዳ. 7፡1) በአብርሃምና በዘሩ ዘንድ ተስፋው ተፈጸመ። ይህ ተስፋ ለምድራዊ ዘሩ በምድራዊ ረገድ ሲተረጎም ለእኛ ለመንፈሳዊ ዘሩ (ሮሜ 4፡16፤ ገላ. 3፡7፥9፥29) በመንፈሳዊ ረገድ ይተረጎማል። እንግዲያውስ የበረከት ሙላት፥ የመብዛትና የድል መንግሥት ተስፋ ነውና ተስፋው ለእኛ ምሳሌው ከነዓን በሆነ በቃኝ ማለትና ደስታ በሞላበት ሕይወት መኖር ነው። በዚህ መልእክት ውስጥ ሁሉ የተነገረለት የኅብረት ሕይወት ነው። የእግዚአብሔርን ሕይወት መካፈል ነው። ይህም ሲሆን የእግዚአብሔር ኃይል በእኛ ውስጥ ይሠራልና ብዙዎችን መንፈሳዊ ልጆች እንወልዳለን፥ ኃጢአትንም ድል እንነሣለን። ለአብርሃምና ለዘሩ ማለት፥ ለእኛ ለክርስቲያኖች፥ የተሰጠው የተስፋው ቃል ይኸው ነው። ነገር ግን እላይ እንደ ተባለው ሁሉ አብርሃም የተስፋውን ፍጻሜ በአንድ ቀን ውስጥ አላገኘም። ያገኘው ይስሐቅን መሥዋዕት እንዲሆን ካቀረበው ወዲያና ረዥም ዘመንም ከታገሠ በኋላ ብቻ ነው። እንደዚሁም እኛ እያንዳንዳችን ተስፋው እስኪሞላልን ያንን ትጋት እስከ መጨረሻ ማሳየት ያስፈልገናል (ም. 10፡36)።

## ቁ. 13-20

13፥14 እግዚአብሔርም ለአብርሀማ ተስፋ በሰጠው ጊዜ፡- በእውነት እየባረክሁ
እባርክሃለሁ እያበዛሁም አበዛሃለሁ ብሎ፥ ከእርሱ በሚበልጥ በማንም ሊምል
ስላልቻለ፥ በራሱ ማለ፤ 15 ማለት፤ እንዲሁም እርሱ ከታገሠ በኋላ ተስፋውን
አገኘ። 16 ሰዎች ከእነርሱ በሚበልጠው ይምላሉና፥ ለማስረዳትም የሆነው 17፥18
መሐላ የሙግት ሁሉ ፍጻሜ ይሆናል፤ ስለዚህም እግዚአብሔር፥ የተስፋውን ቃል
ለሚወርሱ ፈቃዱ እንደማይለወጥ አብልጦ ሊያሳያቸው ስለ ፈቀደ፥ እግዚአብሔር
ሊዋሽ በማይቻል በሁለት በማይለወጥ ነገር፥ በፊታችን ያለውን ተስፋ ለመያዝ
ለሸሸን ለእኛ ብርቱ መጽናናት 19 ይሆንልን ዘንድ በመሐላ በመካከል ገባ፤ ይህም
ተስፋ እንደ ነፍስ መልሕቅ አለን እርሱም እርግጥና ጽኑ የሆነ 20 ወደ መጋረጃውም
ውስጥ የገባ ነው፤ በዚያም ኢየሱስ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘላለም ሊቀ
ካህናት የሆነው፥ ስለ እኛ ቀዳሚ ሆኖ ገባ።

እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለዘሩ እንዲህ ያለውን ግሩም የሆነውን ተስፋ ሲሰጥ (ዘፍጥ. 22፡16፥17) ቃሉን በመሐላ አጸና። ሰው ግን ሲምል ከእርሱ በሚበልጠው ስለሚምል እግዚአብሔር ተቸገረ፤ ስለምን? ቢሉ፥ ከእርሱ የሚበልጥ ከቶ ስለሌለ ነው። ስለዚህ «በራሴ ማልሁ» ብሎ (ዘፍጥ. 22፡16) በአምላክነቱ፥ በክብሩ፥ በኃይሉም ማለ። ቃሉን የካደ እንደሆነ

እነዚህን ሁሉ ካደ ማለት ነው። አብርሃምም ወዲያውኑ ሳይሆን ብዙ ዓመታት ከታገሠ በኋላ ተስፋውን አገኘ። በሰዎች ዘንድ የነገሩ ማጽኛ በእውነት ይኸው ነው። አንድ ሰው የተሰጠውን ቃል ለማጽናት (ለማስረዳት፥ ቁ. 16) ወድዶ «ማን ይሙት?» ይልና መልስ ሰጪው ከእርሱ የበለጠውን ሰው ስም ጠርቶ ይምላል፤ መሐላም ከገባ በኋላ ጥርጥር የለም፥ ቃሉ ጸና። ስለዚህ እግዚአብሔር ደካማው የሰው ልብ ዘወትር ወደ ጥርጥር ማዘንበሉን አውቆ የአብርሃም ወራሾች የሆንን እኛ «የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ይፈጸም አይፈጸም ይሆን?» በማለት እንዳንጠራጠር ነገር ግን ብርቱ መጽናናት ይሆንልን ዘንድ ሊዋሽ በማይቻል በሁለት ነገር ማለት በተስፋ ቃሉና በመሐላው፥ ወይም ደግሞ በመሐላ በሰጣቸው በሁለት ቃሎቹ (ዘፍጥ. 22፡16-18 እና መዝ. 109፡4)፤ መካከለኛና ዋስ ሊሆን በቃሉና በእኛ መካከል ገባ። መሐላው የተስፋውን ቃል እንድንወርስ መያዣችን ሆነ ማለት ነው። ይህም ተስፋ እንደ ነፍሳችን መልሕቅ ነው። መልሕቅ በጽኑ ቦታ ገብቶ መርከቡን ከመወሰድ እንደሚይዘው (ዕ. 2፡1) እንዲሁም ይህ የያዝነውና በክርስቶስ ላይ የተመሠረተው ተስፋ በጽኑ ቦታ፥ ማለት እግዚአብሔር ወዳለበቱ ዘንድ ከክርስቶስ ጋር ገብቶ ተይዞ ከማፈግፈግ ይጠብቀናል። ይህ ብቻ ሳይሆን ኢየሱስ ራሱ ተስፋውን እንድንቀበል ለማረጋገጥ መካከለኛና ዋስ ሆኖ ወደዚያ ገባ። ተስፋችን ምንኛ ጽኑ ነው! በእግዚአብሔር መሐላ የተሰጠ የተስፋ ቃልና ያን ቃል የሚያስፈጽምልን ታላቅ ሊቀ ካህናት አለን።

ደራሲውም ይህን ተናግሮ በዕ. 5፡10 ላይ ማስጠንቀቂያ ለመጻፍ አሳቡን ወደ አቋረጠበት ወደ ኢየሱስ ሊቀ ካህንነት ሐሳብ ይመለሳል።

<u>ማስገንዘቢያ</u>፡-

ሀ) «አብርሃም ... ከታገሠ በኋላ ተስፋውን አገኘ» (ቁ. 15)። «አገኘ» ሲባል ተስፋው በዚያን ጊዜ እንደ ተሰጠው ማለቱ ይሁን፥ ወይም ፍጻሜውን እንደ ተቀበለ በእውነት አልታወቀም። እርግጥ ነው፥ ይህ ተስፋ የተሰጠው ብዙ ዓመታት ከታገሠ በኋላ ነው። የሆነ ሆኖ «አገኘ» ሲባል «ተቀበለ» ማለቱ ይሆናል። እንግዲያውስ ተቀብሎአልን? በአንዱ አስተያየት ተቀበለ (ዕ. 6፡15)፤ በአንዱ ደግሞ አልተቀበልም። (ዕ. 11፡39)። ማለት የተሰጠው ተስፋ እርሱ ራሱ እንዲባረክ ብቻ አልነበረም፤ ልጆቹም እንደ ሰማይ ከዋክብትና በባሕር ዳር እንዳለው አሸዋ እንዲበዙ ነበረ። (ዘፍጥ. 22፡17)። አብርሃም ይህን ያይ ዘንድ አልቻለም ምክንያቱም ሳይፈጸም ሞቶአልና። ሁለተኛ ደግሞ፥ «የምድር አሕዛብ ሁሉም በዘርህ ይባረካሉ» ተብሎ ነበር (ዘፍጥ. 22፡18)፤ የዚያም ፍጻሜ ክርስቶስ መሆኑን በገላ. 3፡16 እንረዳለን። ይህንም አልተቀበለም ይባላል። ሆኖም በሌላ አስተያየቱ ሁለቱንም ተቀብሎአል። «እንዴት?» ቢሉ፥ በይስሐቅ መወለድ መጀመሪያው ተስፋ የመፈጸሙን መነሻ አገኘ፥ አብርሃምም ይህን አየ። «ክርስቶስን አላየም» ይባል ይሆናል፤ ሆኖም በዮሐ. 8፡56 ላይ ኢየሱስ «አብርሃም ቀኔን ያይ ዘንድ ሐሴት አደረገ አየም ደስም አለው» ብሎአል፥ ስለዚህ አየ ይባላል። አግናቂው ነገር በዕብ. 11፡13 ላይ እንደ ተጻፈው ይሆናል፡- «እነዚህ ሁሉ አምነው ሞቱ፥ የተሰጣቸውን የተስፋ ቃል አላገኙምና፤ ዳሩ ግን ከሩቅ ሆነው አዩትና ተሳለሙት።»

ለ) «ስለዚህም እግዚአብሔር ... በመሐላ በመካከል ገባ።» (ቁ. 17፡18) «ይህስ የትኛው መሐላ ነው?» ቢሉ፥ በመዝ. 109፡4 ላይ «እንደ መልከ ጼዴቅ ሥርዓት አንተ ለዘላለም ካህን ነህ ብሎ እግዚአብሔር ማለ አይጸጸትም» ተብሎ የተጻፈው ነው።

እግዚአብሔር መሐላን እየጨመረ የተናገራቸው ሁለት የተስፋ ቃሎች አሉ። አንደኛውን ለአብርሃም ሲናገር (ዘፍጥ. 22:15-18) ሁለተኛውን ለወራሾቹ ተናግሮአል። (መዝ. 109:4)። ሁለቱም የሚናገሩት ስለ አንድ ነገር ነው፤ እርሱም ስለ ክርስቶስና ስለ ማዳኑ፤ ሁለተኛውም አንደኛውን ያጸድቃል።

እግዚአብሔር የተስፋውን ቃል ለአብርሃም ሲሰጥ «በረከትን እባርክሃለሁ፤ ዘርህም እንደ ሰማይ ከዋክብት አበዛዋለሁ» ብሎ ተናግሮአል አብርሃምም ይህን ለራሱ የተሰጠውን የተስፋ ቃል አምነ ከታገሠም በኋላ አገኘ። በዚያ ቃል ላይ ደግሞ እግዚአብሔር «ዘርህም የጠላቶቹን ደጅ ይወርሳል፤ የምድር አሕዛብ ሁሉም በዘርህ ይባረካል» ብሎ ተናግሮ ነበርና የአብርሃም ዘር የሆኑት እስራኤላውያን «ክርስቶስ መጥቶ [illegible]ናል በእርሱ የሙታን ትንሣኤ የኃጢአት ስርየት ጽድቅም ይገኛል» ብለው ተስፋ አድርገዋል፤ ስለዚህም «የእስራኤል ተስፋ» እየተባለ ቆየ። (የሐዋ. 13:32-39፤ 23:6፤ 24:15፤ 26:6-9፤ 28:20)።

አንደኛው የተስፋ ቃል ለአብርሃም ከተሰጠ 1ሺህ ያህል ዓመት በኋላ እግዚአብሔር ቃሉን ለሚወርሱ ፈቃዱ እንደማይለወጥ አብልጦ ሊያሳያቸው ወድዶ መሐላን እየጨመረ ሁለተኛ ተናገረ። «እንደ መልከ ጼዴቅ ሥርዓት አንተ ካህን ነህ» ሲል የክርስቶስን መምጣትና ሊቀ ካህናት እየሆነ ማዳኑን እንደ ገና አመልክቶአል። እግዚአብሔር ከቶውንም አይዋሽምና ሁለት ጊዜ እንዲናገር አስፈላጊ አልነበረም፤ ይሁን እንጂ፤ ሰው ደካማ መሆኑን አውቆና ተስፋው እስኪሞላ ድረስ እነርሱን ለማጽናናት ብሎ ተናገረ። እንግዲያውስ አብርሃም የተስፋውን ቃል ሰምቶ እንደ አመነና እስኪያገኝ ድረስ እንደ ታገሠ እንዲሁም ወራሾቹ የሆኑት ዕብራውያን ያን ትጋት እስከ መጨረሻ ያሳዩ፤ ምእመናን የሆንን እኛም የአብርሃም ወራሾች መሆናችንን ተገንዝበን (ገላ. 3:7) በፊታችን ያለውን ተስፋ አጥብቀን እንያዝ፤ እግዚአብሔር ሁለት ጊዜ በመሐላ ከተናገረ ተስፋው እንደ መልሕቅ ሆኖ እርግጥና ጽኑ ነውና!

ሐ) «ይህም ተስፋ እንደ ነፍስ መልሕቅ አለን።» (ቁ. 19)። የክርስቲያኑ ተስፋ እንዳችም በማይታመንበት ነገር ላይ ሳይመሠረት በእግዚአብሔር በማይለወጥ ቃሉና በመሐላው ላይ ተመሥርቶአል። ይህ ተስፋ ለነፍሳችን እንደ መልሕቅ ይሆንና ይጠብቀናል። መልሕቅ (መያዣ ብረት) ከመርከብ ተጥሎ ጥልቁን ዘልቆ በጽኑ መሬት ወይም በዓለት ውስጥ ተተክሎ መርከቡን በነፋስና በማዕበል እንዳይወሰድ እንደሚጠብቀው ሁሉ እንዲሁም ይህ ተስፋ ወደ መጋረጃው ውስጥ ገብቶ ከመታከትና ከማፈግፈግ ይጠብቀናል። በሕይወታችን ዘመን ሁሉ በፍርሃትና በፈተና በሥቃይም ጊዜ በፊታችን ያለውን ተስፋ በመመልከት ጸንተን ልንቆም እንችላለን።

መ) «ወደ መጋረጃው ውስጥ የገባ ነው።» (ቁ. 19)። «መጋረጃው ምን ማለት ነው?» ቢሉ፤ በብሉይ ኪዳን ዘመን በእግዚአብሔር ማደሪያ ውስጥ «ቅድስት» እና «ቅድስተ ቅዱሳን» በተባሉት ክፍሎች መካከል የተንጠለጠለው መጋረጃ ነው። (ዘጸ. 25:8፥9፤ 26:31-35)። ቅድስተ ቅዱሳን በተባለው በውስጠኛው (በሁለተኛው) ክፍል ውስጥ እግዚአብሔ ከሙሴ ጋር ይነጋገር ነበር (ዘጸ. 25:22)፤ በዕብ. 9:1-8 ላይም እንደምናየው በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ከገባው ከሊቀ ካህናቱ በስተቀር ወደዚያ የገባ የለም። እግዚአብሔር ያለበት ሥፍራ ነበረና ሰው እንዳይገባ መጋረጃው ይከለክለው ነበር። ስለዚህ «መልሕቁ ወደ መጋረጃው ውስጥ ገባ» ሲል «እግዚአብሔር ወደ አለበት ዘንድ ገባ» ማለት ነው። ይህም ጽኑ ቦታ ነው።

ሠ) «ኢየሱስ ስለ እኛ ቀዳሚ ሆኖ ገባ» (ቁ. 20)። ኢየሱስ እርሱ ራሱ በሚኖርበት ሕይወት ዓይነት እንድንኖር እግዚአብሔር ወዳለበቱ ዘንድ ገባ። አሁንም ሊቀ ካህናታችን ሆኖ እኛን ወደዚያ አግብቶ ኅብረትን አስገኝቶ ገና በዚህ ዓለም ሳለን «ዘላለም» በተባለው ሕይወት እንድንኖር ያደርጋል። የገባውም «ቀዳሚ ሆኑ» እና «ስለ እኛ» ነው። «ቀዳሚ» ማለት፥ ወይም ቀድሞ ሄዶ ለሚከተሉት መንገድን የሚከፍት መሪ፥ ወይም መልሕቅን መጣል ባልተመቸ ጊዜ መልሕቅን ይዞ ማዕበልን ሁሉ ችሎ በወደቡ ውስጥ በደኅና ቦታ የሚያኖረው መርከበኛ ማለት ነው። «ስለ እኛ» ሲል ደግሞ፥ በም. 2፡9 ላይ የተጻፈውን ቃል እናስባለን። በኃልነታም ሆነ አሁንም በሰማያት በግርማው ቀኝ ሲቀመጥ ያደረገውና የሚያደርገው ሁሉ ስለ እኛ ነው። ያን ጊዜ ስለ እኛ ሞተ። ዛሬም ስለ እኛ በሕይወት ይኖራል። ወደ መጋረጃው ውስጥ የገባው ከእግዚአብሔር ጋር ወደ ሙሉ ኅብረት አድርሶን የሰላምን የኃይልንና የደስታን ሕይወት ሊቀበልልንና ሊያስተላልፍልን ነው። (ም. 8ና ም. 9)። እዚያ የሆነው «ስለ እኛ» ነው!

# ምዕራፍ ሰባት

## (የኢየሱስ ክህነት የተሻለ ነው።)

### እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት በመሆኑ።

ከዚህ በፊት አልፎ አልፎ ያገኘነውን የኢየሱስ የሊቀ ካህንነቱን ነገር (ም. 2፡17፥18፤ ም. 3፡1፥2፤ ም. 4፡14-16፤ ም. 5፡5-10፤ ም. 6፡19፥20) አሁን ከም. 7 ጀምሮ እስከ ም. 10፡25 ድረስ በብዙ እናገኘዋለን። በእውነቱ የመልእክቱ ዓይነተኛ ትምህርት ነው። «ኢየሱስ ዛሬ በሰማያት ሆኖ የሚሠራው ሥራ ምንድን ነው?» ቢባል፥ ይኸው በም. 7 ላይ እንደ ተገለጠው ሁሉ የሊቀ ካህንነትን ሥራ ነው። በዚህ ዓለም ላይ በነበረ ጊዜ የሊቀ ክህንነትን ሥራ እየሠራ ስለ ኃጢአት አስፈላጊ የሆነውን መሥዋዕት በማቅረብ ከኃጢአት ፍርድ ካዳነን በኋላ (ኢሳ. 53፡10) ወደ መጣበቱ ወደ ሰማያት ተመልሶ ዐረገ፥ እዚያም የሊቀ ካህንነቱን ሥራ እየቀጠለ ዛሬ ከኃጢአት ኃይል ያድነናል።

ም. 7 የም. 5፡10 ተቀጣይ ነው። ሐዋርያው ዕብራውያንን አስቀድሞ ለመውቀስ ቀጥሎም ለማደፋፈር ከዋና ነገሩ ጥቂት ወጥቶ ነበር፥ አሁን ግን መሥመሩን እንደ ገና ይዞ ወደ ፍጻሜ ይሄዳል (ም. 6፡1)። በመዝ. 109፡4 ላይ የተጻፈውን ቃል እየጠቀሰ ኢየሱስ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ሊቀ ካህናት ተብሎ በእግዚአብሔር እንደ ተጠራ አመልክቶአል። (ም. 5፡10)፥ አሁንም በም. 7 ላይ የመልከ ጼዴቅ ክህነት የክርስቶስን እንደ መሰለና ያ ክህነት ከሌዊ ክህነት እንደሚበልጥ፥ ስለዚህ ደግሞ የክርስቶስ ክህነት ከሌዊ ክህነት እንደሚበልጥ ያስረዳል። ይህም ብቻ ሳይሆን የሌዊ ክህነት ለ1ሺህ ዓመታት ያህል ከረጋ በኋላ እግዚአብሔር ኢየሱስን፥ እንደ ሌዊ ሹመት ሳይሆን እንደ መልከ ጼዴቅሹመት ሊቀ ካህናት አድርጎ ከሾመው የሌዊ ክህነት እንደ ተሻረና የኢየሱስም እንደ ተተካ በማስረዳት «ከሥጋ የተነሣ ስለ ደከመ ለሕግ ያልተቻለውን እግዚአብሔር የገዛ ልጁን ልኮ አድርጎአል» የሚለውን (ሮሜ 8፡3) የቅዱስ ጳውሎስን ቃል ያጸናል። በመጨረሻ ላይ ኢየሱስ በመሐላ ስለ ተሾመ የሚሻል ኪዳን ዋስ እንደ ሆነና ለዘላለም ስለሚኖርም ፈጽሞ ሊያድን እንደሚችል አስረድቶ «እንደዚህ ያለ ሊቀ ካህናት በእውነቱ ይገባናል!» ብሎ ምዕራፉን ይጨርሳል።

### ቁ. 1-3

> [1] የሳሌም ንጉሥና የልዑል እግዚአብሔር ካህን የሆነ ይህ መልከ ጼዴቅ አብርሃም ነገሥታትን ገድሎ ሲመለስ [2] ከእርሱ ጋር ተገናኝቶ ባረከው፤ ለእርሱም ደግሞ አብርሃም ከሁሉ አሥራትን አካፈለው። የስሙም ትርጓሜ በመጀመሪያ የጽድቅ ንጉሥ ነው፥ ኋላም ደግሞ የሳሌም ንጉሥ ማለት [3] የሰላም ንጉሥ ነው። አባትና እናት የትውልድም ቁጥር የሉትም፥ ለዘመኑም ጥንት ለሕይወቱም ፍጻሜ የለውም፥ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ልጅ ተመስሎ ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል።

ሐዋርያው በመዝ. 109፡4 ላይ ተጽፎ በም. 5፡7 ላይ የተጠቀሰውን ቃል አንሥቶ አስቀድሞ፥ ከቁ. 1 እስከ 3 ድረስ፥ የመልከ ጼዴቅ ክህነት የኢየሱስን እንደ መሰለ፤ ቀጥሎም ይህን ነገር መሠረት አድርጎ፥ ከቁ. 4 እስከ 25 ድረስ፥ የኢየሱስ ክህነት ከአሮን (ከሌዊ) ክህነት እንደሚበልጥ ያሳያል።

ይህ መልከ ጼዴቅ ማን እንደ ሆነ መገንዘብ የሚያስፈልግ ነገር ነው። ታሪኩ በዘፍጥ. ም. 14 ላይ ተጽፎ ይገኛል። ሎጥ የተባለ የአብራም የወንድሙ ልጅ በሰዶም ሊኖር ሄዶ ጥቂት እንደ

ቆየ የሰዶም ንጉሥና 4 ጓደኞቹ ኮሎዶጎሞር የተባለውን ግዢቸውን ከድተው በእርሱ ዐመፁ። ኮሎዶጎሞር ከእርሱ ጋር የነበሩትም 3 ነገሥታት መጥተው የሰዶምን ንጉሥ ተዋጉና ድል አድርገው የሰዶምንና የገሞራን ከብት ሁሉ ወሰዱ፥ ሎጥን ደግሞ ማርከው ሄዱ። አብራም ወሬውን ቢሰማ በቤቱ የተወለዱትን 318 ሰዎች ሰብስቦ ተከታትሎአቸው ሄደ ከብቱንም ሁሉ ሎጥንም አስመለሰ። ወደ ቤቱ ተመልሶ ሲመጣ መልከ ጼዴቅ የተባለው የሳሌም (የኢየሩሳሌም፥ መዝ. 75፡2) ንጉሥ እንጀራንና የወይን ጠጅ ይዞ ሊገናኘው ወጣ፤ ንጉሥም ብቻ ሳይሆን የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነበረና፥ መባረክና አሥራትን መቀበል የካህን ሥራና መብት ነውና (ዘኁ. 6፡22-27፤ 18፡21፥26፤ ዘዳ. 21፡5) እርሱ አብራምን ባረከ አብራምም ለእርሱ አሥራት አወጣ። ታሪኩ ይህ ነው፥ በዚህም ታሪክ ላይ ደራሲው ከፍ ያለ ትምህርት ይመሠርታል።

«መልከ ጼዴቅ» የተባለው ስም ሲተረጎም «ንጉሠ ጽድቅ» ማለት ነው፥ መልከ ጼዴቅ የነገሠበት የሥፍራውም ስም «ሳሌም» ሲተረጎም «ሰላም» ማለት ነው። እንደዚሁም ስለ አባቱና ስለ እናቱ ስለ ትውልድም የተጻፈ ነገር የለም። የዘመንና የክህነቱም መጀመሪያና መጨረሻ አልተጠቀሰምና ለእኛ እንደሚመስል ሁሉ ለዘላለም ካህን ነበር። እንድግዲያውስ በዚህ ነገር ሁሉ የክርስቶስ ሥዕል ለመሆን በቃ። እንደምን? ቢሉ፥ ክርስቶስ ደግሞ «እግዚአብሔር ጽድቃችን» እና «የሰላም አለቃ» ይባላል። (ኤር. 23፡6፤ 33፡16፤ ኢሳ. 9፡6)። በሰማይ እናት፥ በምድር አባት የለውም፤ እግዚአብሔርም «አንተ ለዘላለም ካህን ነህ» ብሎታል። (መዝ. 109፡4)። በእነዚህ 5 ነገሮች፥ ማለት ከጽድቅ በመሆኑ፥ ከሰላም በመሆኑ፥ ንጉሣዊ በመሆኑ፥ በትውልድ ምክንያት ሳይሆን ከሰውየው የራሱ ተገቢነት የተነሣና ዘላለማዊ በመሆኑ፥ የመልከ ጼዴቅ ክህነት የክርስቶስን መሰለ፥ በእነዚህም 5 ነገሮች የክርስቶስ ክህነት ከአሮን (ከሌዊ) ክህነት ተለይቶአል።

<u>ማስገንዘቢያ</u>፡-

ሀ) «በመጀመሪያ የጽድቅ ንጉሥ፥ ኋላም ደግሞ የሰላም ንጉሥ።» (ቁ. 2)። ቅደም ተከተሉ ምን ጊዜም ይኸው ነው። (ኢሳ. 32፡17)። ጽድቅ አስቀድሞ ካልተገኘ ሰላም አይገኝም። የዚህ ዓለም ሰዎች ሰላምን ለማግኘት ይጣጣራሉ፤ ይሁን እንጂ አብዛኛውን ጊዜ በማይገኘው ዘንድ ይፈልጉታል። ከብስጭት እናመልጣለን ብለው አንዳንዶቹ ወደ ዳንስና ወደ ሲኒማ ወደ መጠጥም ቤት ይሄዳሉ። ነገር ግን ከዚህ ሁሉ የሚገኘው ሰላም ለጊዜ ነው እንጂ ነዋሪም አይደል። አንዳንዶችም «ኧረ! ችግሩን ያልተመለከትን እንደሆነ በሰላም እንኖራለን» ይላሉ ነገር ግን አለመመልከታቸው ያን ችግር አያስወግድም። ሌሎችም «መስማማት ነው እንጂ መታገልስ ምን ይጠቅማል?» ብለው ከክፉው ጋር በመስማማት ሰላምን የሚያገኙ ይመስላቸዋል፥ ነገር ግን በእውነቱ ይህ መንገዱ አይደለም (2 ቆሮ. 6፥14-18) ወደ ባሰም ብስጭት ያደርሳል። የለም፥ ልዑል እግዚአብሔር ሰላም በጽድቅ ላይ እንዲመሠረት፥ ሰላምም የጽድቅ ፍሬ እንዲሆን ወስኖአል። (ሮሜ 5፡1፤ 14፡17፤ ያዕ. 3፡18)። አስቀድመው በጽድቅ መሠረት ከእግዚአብሔር ጋር ሳይታረቁ ሰላምን የሚፈልጉ ሰዎች ሞልተዋል ነገር ግን አያገኙም። አስቀድሞ («በመጀመሪያ») እንደ ጽድቅ ንጉሥ ሳይቀበለው የሰላምን ንጉሥ የሚያውቅ ከቶ ማንም ሰው የለም። ሰው ሆይ፥ ሰላምን ብትፈልግ አስቀድመህ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቅ። (2ቆሮ. 5፡18-21)።

ለ) «አባትና እናት የትውልድም ቁጥር የሉትም፥ ለዘመኑም ጥንት ለሕይወቱም ፍጻሜ የለውም፥ ዳሩ ግን ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል።» (ቁ. 3)። እነዚህን ቃሎች ስናነብ መልከ

ጼዴቅ ሰው ሳይሆን መልአክ፥ ወይም ሌላ አንዳች ምስጢራዊ ነገር የሆነ ይመስለን ይሆናል። ነገር ግን «አባትና እናት የሉትም» ሲባል፥ እንደዚሁም «ለዘመኑ ጥንት ለሕይወቱም ፍጻሜ የለውም» ሲባል፥ በጹሑፍ (በታሪኩ) ላይ አልተጻፈም ማለት ነው እንጂ በፍጹም አልነበሩትም ማለቱ አይደለም። እነኝህ ነገሮች አልተጻፉምና መልከ ጼዴቅ በእግዚአብሔር ልጅ ተመስሎአል ማለት ነው። ሳይጻፉ የቀሩበትም ምክንያት መንፈስ ቅዱስ መልከ ጼዴቅ ክርስቶስን እንዲመስል፥ በእርሱም የክርስቶስን ሥዕል አግኝተን ክህነቱ ለዘላለም መሆኑን እንድናስተውል ስለ ወደደ ነው።

የትውልድ ቁጥር አለመኖሩ የሚያስደንቅና ታላቅ ምስጢር ያለበት ነገር ነው። ምክንያቱም እንደ ኦሪት ሕግ ሁሉ ክህነት የተሰጠ ለአሮን ልጆች ነው፤ ለእነርሱም ተወስኖአል። ትውልዱ በትውልድ መጽሐፍ ያልተገኘ ማንኛውም ሰው እንደ ካህን ሊያገለግል አልቻለም። (ዘኁ. 3፥10፤ 8፥19-22፤ 18፥1-7፤ ዕዝ. 2፥62፥63፤ ነህ. 7፥63-65)። ክህነት በዘር ተወስኖ ነበርና ዋና የሚያስፈልግ ነገር ሰው ከሌዊ ነገድ እንዲሆን ነበረ። ከሌዊ ነገድና ከአሮን ወገን የሆነ ወንድ ሁሉ፥ በጠባዩ መልካምም ቢሆን ክፉ፥ ቢወድም ባይወድ፥ ከዘሩ የተነሣ በዚያው ምክንያት ብቻ ካህን ነበረ። በተቃራኒው ግን ከዚያ ዘር ያልሆነ ማንኛውም ሰው፥ ቢፈልግና መልካም ሰው ቢሆንም፥ ንጉሥም ቢሆን፥ ካህን መሆን አልቻለም። (2ኛዜና. 26፥16-21።) ክህነት እንደ ሥጋ ትዕዛዝ ሕግ ነበረ። መልከ ጼዴቅ ግን የትውልድ ቁጥር የለውም። እንግዲያውስ ክህነቱ በዘር ላይ ሳይመሠረት በጠባዩና በእግዚአብሔር ልዩ ጥሪ ተመሥርቶአል፥ ይህም ስለሆነ ክህነቱ ከሌዊ ክህነት ልዩ ነው። ክህነቱም የክርስቶስን ክህነት ያመለክታልና የክርስቶስ ደግሞ ከሌዊ ልዩ መሆኑን እንገነዘባለን።

ሐዋርያው «ለዘመኑ ጥንት ለሕይወቱም ፍጻሜ የለውም፥ ዳሩ ግን ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል» ሲል መልከ ጼዴቅ ስለ ኖረበት ዘመን ብቻ ሳይሆን ስለ ክህነቱም ዘመን ጭምር ያሰበ ይሆናል። በኦሪት ላይ በተጻፈ በዚያ በሥጋ ትእዛዝ ሕግ ሌዋውያን አገልግሎታቸውን በ25፥ ወይም ሙሉ ሥራቸውን በ30 ዓመታቸው ጀምረው እስከ 50 ዓመታቸው ድረስ ያገለግሉ ነበር። (ዘኁል. 4፥46፥47፤ 8፥24-26)። ለክህነታቸው የተወሰነ መጀመሪያና መጨረሻ ነበረ ማለት ነው። ክህነታቸው «ለዘላለም» አልነበረም። መልከ ጼዴቅ ግን ክህነቱ የተወሰነ መጀመሪያና መጨረሻ የለውምና «ለዘላለም»፥ ማለት በእድሜው ዘመን ሙሉ ካህን ሆኖ ይኖራል። እንደ ፕሬዚዴንትና እንደ ንጉሥ ያለ ነገር ነው። «ፕሬዚደንድ» ተብሎ በአንድ አገር ላይ የሚሾመው ሰው ለ4 ወይም ለ5 ዓመት ይሾማል እንጂ ለዘላለም አይሾምም። ንጉሥ ግን የሚነግሥበት ዘመን አልተቆረጠምና (አልተወሰነምና) «ለዘላለም» ማለት የእድሜውን ልክ ያህል፥ ይነግሣል። እንደዚሁም መልከ ጼዴቅ፥ ክህነቱ የሚጅመርበትና የሚጨረስበት ዘመን አልተቆጠረምና «ለዘላለም» ካህን ሆኖ ይኖራል። በዚህም ደግሞ በእግዚአብሔር ልጅ ተመስሎአል፥ ስለ ክርስቶስ «አንተ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘላለም ካህን ነህ» ተብሎአልና።

ሐ) «ተመስሎ»። (ቁ. 3)። ኢየሱስ መልከ ጼዴቅን እንደ መሰለ ሳይሆን መልከ ጼዴቅ በኢየሱስ እንደ ተመሰለ፥ ማለት እንዲመስለው እንደ ተደረገ፥ ልብ እናድርግ። መልከ ጼዴቅ አስቀድሞ መጥቶ እንደ ሥዕል ሆኖ ኢየሱስ እንዴት እንደሚሆን እንደ ገለጠ ነው እንጂ ኢየሱስ በኋላ መጥቶ የመልከ ጼዴቅን ምሳሌ እንደሚፈጽም አይደለም።

ቁ. 4-10

4 የአባቶች አለቃ አብርሃም ከዘረፋው የሚሻለውን አሥራት የሰጠው ይህ ሰው
እንዴት ትልቅ እንደ ነበረ እስኪ 5 ተመልከቱ። ከሌዊ ልጆችም ክህነትን
የሚቀበሉት ከሕዝቡ ማለት ከወንድሞቻቸው፥ እነርሱ ምንም ከአብርሃም ወገብ
ቢወጡ፥ ከእነርሱ አሥራትን በሕግ እንዲያስወጡ ትእዛዝ 6 አላቸው፤ ትውልዱ
ከእነርሱ የማይቆጠረው ግን ከአብርሃም አሥራትን አውጥቶአል፥ የተስፋ ቃል
የነበረውንም ባርኮአል። 7 ትንሹም በታላቁ እንዲባረክ ክርክር የሌለበት ነገር ነው።
8 በዚህስ የሚሞቱ ሰዎች አሥራትን ያስወጣሉ፥ በዚያ ግን የሚያስወጣ በሕይወት
እንዲኖር የተመሰከረለት እርሱ ነው። 9 ይህንም ለማለት ሲፈቀድ አሥራትን
የሚያስወጣ 10 ሌዊ እንኳ በአብርሃም እጅ አሥራትን ሰጥቶአል፤ መልከ ጼዴቅ
በተገናኘው ጊዜ ገና በአባቱ ወገብ ነበረና።

እንዴት ትልቅ ነበረ! (ቁ. 4) በእነዚህ ቁጥሮች ላይ መልከ ጼዴቅ እንዴት ትልቅ እንደ ነበረ እናያለን። ከአብርሃም በለጠ፥ ስለዚህ ከሌዊና ከክህነቱ በለጠ፥ ስለዚህ ደግሞ ሹመቱ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ነውና የክርስቶስ ክህነት ከሌዊ ክህነት በለጠ። መብለጡን የምናይበት በቀደመው ክፍል ላይ ከተጠቀሱት 2 ነገሮች ነው። 1ኛ፥ አብርሃም ለመልከ ጼዴቅ አሥራትን በመክፈሉ፤ 2ኛ፥ መልከ ጼዴቅ አብርሃምን በመባረኩ። ነገር ግን ሐዋርያው አስቀድሞ የአብርሃምን የራሱን ታላቅነት ያሳስባል። አብርሃም ማን ኖሮአል? ተራ ሰው ነውን? ኧረ አይደለም! አብርሃምማ የአባቶች አለቃ ነው (ሮሜ 4፡1)፥ የእስራኤልን ሕዝብ የጀመረና የተስፋን ቃል የተቀበለ ነው። አብርሃምን የሚያክሉት እጅግ በጣም ጥቂቶች ናቸው። ቢሆንም አብርሃም ለዚህ ሰው፥ ለመልከ ጼዴቅ ከዘረፋው የሚሻለውን አሥራት ሰጠው! እንደ ብሉይ ኪዳን ሕግ ሌዋውያን ከቀሩት የእስራኤል ነገዶች አሥራትን ይቀበሉ ነበር (ዘኁል. 18፡21-24፤ ዘዳ. 14፡28፥29) ካህናትም ከዚያ አሥራት አሥራትን ተቀብለዋል። (ዘኁ. 18፡25-28)። ከፋዮቹ ከአብርሃም ወገብ የወጡ ነበሩና ይህን ሲያደርጉ የሌዋውያንና የካህናት ክብር ከፍ ያለ ነበረ፤ ይሁን እንጂ፥ አሥራትን የተቀበሉት በግዴታ ነው፥ የትእዛዝ ሕግ ነበርና። መልከ ጼዴቅ ግን ትውልዱ ከእነርሱ ምንም ባይቆጠር ከእስራኤል ሕዝብ ይቅርና ከአብርሃም ተቀበለ! አብርሃምም የከፈለው በሕግ ተገድዶ ሳይሆን የመልከ ጼዴቅን የተፈጥሮ ተገቢነት ታላቅነትም ተገንዝቦ በፈቃዱ ነው። መልከ ጼዴቅ የአብርሃምን አክብሮት ተቀብሎ፥ አብርሃም የተስፋ ቃል የነበረው ቢሆንም (ዘፍ. 12፡1-3፤ 22፡16-18) ባረከው፤ ትንሹ ምን ጊዜም በታላቁ ይባረካልና መልከ ጼዴቅ ይህን በማድረግ መብለጡን አሳየ፥ አብርሃምም አመነው። በዚህስ በኦሪት ሕግ አሥራት የሚያስወጡ ሞዋች ሰዎች ናቸው፥ በዚያ በመልከ ጼዴቅ ታሪክ ላይ ግን የሚያስወጣው ለዘላለም ካህን ሆኖ እንዲኖር የተምሰከረለት ነው። ደግሞእንደዚህ መናገር ትንሽ እንደ ስንፍና ምናልባት ቢመስልም እንኳ፥ ነገሩን በረቂቁ ብንመረምር አብርሃም አሥራት በሰጠ ጊዜ ልጁ ሌዊ ገና በወገቡ ነበረና ሌዊ በአብርሃም ሆኖ ለመልከ ጼዴቅ አሥራት አውጥቶአል፥ ከእርሱ መብለጡንም አምኖአል! እንግዲያውስ ይህ መልከ ጼዴቅ ምን ያለ ታላቅ ሰው ኖሮአል!

ማስገንዘቢያ፡-

ሀ) «ከሌዊ ልጆችም ክህነትን የሚቀበሉት።» (ቁ. 5)። «ከሌዊ ልጆች» የተባለበት ምክንያቱ የሌዊ ልጆች ሁሉ ክህነትን ስለ አልተቀበሉ ነው። ክህነትን የተቀበሉ ከሌዊ ነገድ ሆነው የአሮን ልጆች ብቻ ነበሩ። ሌዊ የተባለ የአብርሃም ልጅ የአሮን ቅድመ አያት ነበረ (1ኛ

ዘና. 6፡1-3)፤ እግዚአብሔርም የሌዊን ልጆች ሁሉ (ሌዋውያንን) የቤተ መቅደስ አገልጋዮች ይሆኑ ዘንድ ለያቸው (ዘኁ. 3፡5-9፤ 8፡5-22)፥ ከእነርሱም መካከል የአሮንን ልጆች ካህናት አደረጋቸው። (ዘጸ. 40፡12-15፤ ዘኁ. 3፡10፤ 18፡1-7)። በዚህ የተነሣ ክህነታቸው አንዳንድ ጊዜ «የሌዊ» አንዳንድ ጊዜም «የአሮን» ይባላል።

ለ) «በሕይወት እንዲኖር የተመሰከረለት።» (ቁ. 8)። ለመልከ ጼዴቅ የክህነቱን ብልጫ የሚመሰክር ይህ ተጨማሪ ማስረጃ ነው። በሌዊ ክህነት ዘንድ ወሰን ድንበር ነበረ። የካህናት አገልግሎት ከ30 እስከ 50 ዓመታቸው ተወስኖአል፥ ሞትም አቋርጦአቸው አገልግሎታቸውን እንዳይፈጽሙ ይከለክላቸው ነበረ። መልከ ጼዴቅ ግን፥ ቀደም ብለን እንዳየነው ሁሉ፥ ወሰን ድንበር ያለው ክህነት ሳይኖረው በሕይወት ዘመን ሁሉ፥ «ለዘላለም»፥ ካህን ነበረና የእርሱ ክህነት ከሌዊ ክህነት የተሻለ ነው። እንደዚሁም ክርስቶስ ለሕይወቱ ፍጻሜ የለውምና ለዘላለም ካህን ነው።

## ቁ. 11-19

11 እንግዲህ ሕዝቡ በሌዊ ክህነት የተመሠረተን ሕግ ተቀብለዋልና በዚያ ክህነት ፍጹምነት የተገኘ ቢሆን እንደ አሮን ሹመት የማይቆጠር፥ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ግን የሆነ ሌላ ካህን ሊነሣ ወደፊት ስለ ምን ያስፈልጋል? 12 ክህነቱ ሲለወጥ፥ ሕጉ ደግሞ ሊለወጥ የግድ ነውና። 13 ይህ ነገር የተነገረለት እርሱ በሌላ ወገን ተካፍሎአልና፥ ከዚያም መሠዊያውን ያገለገለ ማንም የለም፤ 14 ጌታችን ከይሁዳ ነገድ እንደ ወጣ የተገለጠ ነውና፥ ስለዚህም ነገድ ሙሴ ምንም እንኳ ስለ ክህነት አልተናገረም። 15፥16 በማይላፍም ሕይወት ኃይል እንጂ በሥጋ ትእዛዝ ሕግ ሳይሆን ሌላ ካህን በመልከ ጼዴቅ ምሳሌ ቢነሣ፥ 17 ይህ እጅግ አብልጦ የሚገለጥ ነው። አንተ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘላለም ካህን ነህ ብሎ ይመሰክራልና። 18፥19 ሕጉ ምንም ፍጹም አላደረገምና፥ ስለዚህም የምትደክም የማትጠቅምም ስለ ሆነች የቀደመች ትእዛዝ ተሽራለች፥ ወደ እግዚአብሔርም የምንቀርብበት የሚሻል ተስፋ ገብቶአል።

የሌዊ ክህነት ከተቋቋመ ከብዙ ዓመታት በኋላ እግዚአብሕር «አንተ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘላለም ካህን ነህ» ብሎ ክርስቶስን ካህን አድርጎ መሾሙን እንበበናል። አሁን በእነዚህ ቁጥሮች ላይ ደራሲው «ይህስ ስለምን ያስፈልጋል?» ብሎ ይጠይቃል። የሌዊ ክህነት ወደ ፍጻሜ፥ ማለት ወደ ታሰበው ግብ፥ ወደ ኅብረትና የእግዚአብሔርን ሕይወት ወደ መካፈል፥ ሊያደርስ ከቻለ ከዚያ ክህነት ያልሆነው ሌላ ካህን ይነሣ ዘንድ ስለምን አስፈለገ? ሌላ ተነሥቶአልና። የእስራኤል ሕዝብ የተቀበሉት ሕግ ለችሎቱ (ለመፈጸሙ) በሌዊ ክህነት ተንጠልጥሎአል፥ ወይም በላዩ ተመሥርቶአል። ማለት ያለ ክህነቱ ሕጉ ሊፈጸም አልቻለም። እንግዲያውስ ከሌዊ ክህነት ያልሆነ ሌላ ካህን ቢሾም ክህነት ተለውጦአልና በክህነቱ የተንጠለጠለው፥ ወይም በላዩ የተመሠረተው ሕግ አብሮ ተለውጦአል። ክህነቱም እንደ ተለወጠ የምንረዳበት፥ በመዝ. 109፥4 ላይ የተነገረው ቃል ስለ መሢሕ እንደ ተነገረ፥ መሢህም ከይሁዳ እንደሚሆን ስለምናውቅ ነው። (2ሳሙ. 7፡12፤ ኢሳ. 9፡6፥7፤ 11፡1-5፤ ሚክ. 5፡2)። ጌታችንም ከይሁዳ ነገድ እንደ ወጣ የተገለጠ ነው። (ማቴ. 2፡5፥6፤ ሮሜ 1፡3፤ ራእ. 5፡5)። ሙሴ ስለዚህ ነገድ ክህነት በአሪት ምንም አልተናገረምና እግዚአብሔር አሁን ኢየሱስን ቢሾም ክህነት ተለወጠ ማለት ነው።

ይህ የሌዊ ክህነት ወደ ፍጻሜ ለማድረስ ስለ አለመቻሉ የተነገረው ነገር እውነት መሆኑ እጅግ አብልጦ የሚገለጥበት፤ ሥጋዊ ነገሩን ሁሉ፥ ማለት ትውልዱን፥ እድሜውን፥ መብሉንና የሰውነቱን ሁኔታ ሁሉ (ዘሌ. 21፡16-23) በሚያዝዘ (በሚወስን) ሕግ መሠረት ሳይሆን እንደ መልከ ጼዴቅ ሆኖ በማያልፍ ሕይወት ኃይል መሠረት ካህን የሚሆን ቢነሣ ነው። እላይ እንደ ተባለው ሁሉ፥ የሌዊ ክህነት ወደ ፍጹምነት ለማድረስ በቻለ ኖሮ ሌላ ካህን ሊነሣ ባልተፈለገም ነበረ፤ ሆኖም ተነሣ። የሌዊ ክህነት ወደ እግዚአብሔር ሊያቀርበን አልቻለምና እግዚአብሔር እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት የሆነውን ሌላ አስነሣ። ሕጉ መንገዱንና የሚመጣውን የክርስቶስን ሥዕል አሳየን እንጂ እርሱ ራሱ ምንም ወደ ፍጹምነት ሊያድረስ አልቻለም። ካህናት የሚሞቱ ሰዎች ነበሩ፤ ለሕዝብ ሕግን የሚጠብቁበትን ኃይል ሊሰጡ አልቻሉም፤ መሥዋዕቶቻቸው በእውነት ኃጢአትን ሊያስወግዱ አልቻሉም (ም. 9፡9፥10፤ 10፡1፥4)፤ አገልግሎታቸውም፥ ወደ ታሰበው ግብ ሊያደርስ አልቻለም። ስለዚህ እግዚአብሔር በዚያ በመዝ. 109፡4 ላይ ስለ ክህነት የምትናገረውን የቀድሞች ትእዛዝ ሽሮ ሌላ ካህን ሾመ፥ እርሱም ክርስቶስ ነው። ካህናችንም እርሱ ሲሆን ወደ እግዚአብሔር እንድንቀርብ እጅግ የተሻለ ተስፋ ገብቶአል።

<u>ማስገንዘቢያ</u>፡-

ሀ) «ሕግ»። በዚህ ክፍል ውስጥ ተደጋግሞ የሚመጣው ይህ «ሕግ» የተባለው ቃል ኦሪት እንደ ሆነ ወይም የክህነት ሕግ እንደ ሆነ መለየት ያስቸግራል። ኦሪት የእግዚአብሔርን ፈቃድ እያስታወቀ ከኃጢአት ሲያስጠነቅቀን የክህነት ሕግ ሰው ኃጢአትን የሠራ እንደሆነ ነጽቶ ወደ ኅብረት እንዴት እንደሚመለስ ይነግረናል። በዚህ ክፍል ውስጥ ስለ የትኛው ሕግ እንደሚናገር ሊታውንት ባይስማሙም ቅሉ እኔ የሚመስለኝን ጻፍሁ።

ለ) «ሌላ ካህን ሊነሣ ስለምን ያስፈልጋል?» (ቁ. 11)። በዚያ በዱሮው ክህነት ፍጹምነት አልተገኘምና! ወንድም ሆይ አየህን? ፍጹምነት እንዲገኝ ታስቦአል! ማለት፥ ሰው ከኃጢአቱ፥ ሁሉ እንዲነጻና ወደ እግዚአብሔር ቀርቦ ከእርሱ ጋር የማያቋርጥ ኅብረት እንዲያገኝ ታቅዶአል። ለአንተ የሚሆን የእግዚአብሔር ፈቃድና ቁርጥ የሆነ ሐሳብ ነው። አገኘተኸዋልን? ካህን የተፈለገው ለዚህ ነው። ፍጹምነት ግን በሌላ በማናቸውም ክህነት አይገኝምና በዚህ ምክንያት እግዚአብሔር ኢየሱስን አስነሣ። የሚችል ካህን እርሱ ብቻ ነው። አትሳት፤ ለእርሱ የተሰጠ ሹመት ለዘላለም አያልፍም፥ ለሌላም ከቶ አይሰጥም። እግዚአብሔር የሾመው ካህን እርሱ ነውና «ካህናት» የምንላቸው ሌሎቹ የእርሱን ግዛት አይተላለፉ! ወደዚያ ወደ ታሰበው ግብ እንድትደርስ ነው። እንዲያደርስህ ብትለምነው፥ እንዲያደርስህም ብትታመንበት ሳትሰናከል ጠብቆ በክብሩ ፊት በደስታ፥ ነው የሌለህ አድርጎ ሊያቆምህ ይችላል። እነዚህን ጥቅሶች አውጥተህ እይ፡- ፊልጵ. 1፡6፤ 1ተሰ. 5፡23፥24፤ ይሁዳ ቁ. 24። ይህን የሚሻለውን ተስፋ ጨብጥ!

ሐ) «ጌታችን ከይሁዳ ነገድ ወጣ።» (ቁ. 14)። «ወጣ» ሲባል ግሪኩ የኢየሱስ መምጣት ፀሐይ እንደምትወጣ፥ ወይም ቁጥቋጥ ከግንድ እንደሚያቆጠቁጥ መሆኑን ያመለክታል። (ኢሳ. 11፡1፤ ኤር. 23፡5፥6፤ ዘካ. 3፡8፤ 6፡12)።

መ) «በማያልፍ ሕይወት ኃይል።» (ቁ. 16)። የሌዊ (የአሮን) ክህነት የተመሠረተበት ሕግ ደካማ የሆነ የሥጋ ትእዛዝ ሲሆን የክርስቶስ ክህነት በማያልፍ ሕይወት ኃይል ላይ ተመሥርቶአል፥ በዚያም ሕይወት ድካም ከቶ የለም። የእነርሱ ሕይወት በሞት ተቋረጠ፥

የክርስቶስ ግን የማያልፍ ነው። የማያልፍ ማለት የማይቋረጥ ማለት ነው። ሞት ስንኳ ሊያቋርጠው አልቻለም። ይሞት ዘንድ አስፈላጊ ነበረ፤ ሆኖም የያዘውን ሥራ ወደ ፍጹምነት ሊያደርስ ሕይወቱ እንዲቀጥል እንደዚሁም አስፈላጊ ነበር። ሕያው ነበረ፥ ሞተ፥ ሕያውም ሆነ። ሁለተኛም ለዘላለም ከቶ አይሞትም። (ራእ. 1፡17፥18፤ ሮሜ. 6፡9)። የአሮን ልጆች ካህናት የሆኑት ከትውልድ፥ ከእድሜ፥ ከሥጋ አኳኋናቸውም የተነሣ በትእዛዝ ስለ ተገደዱ ነው፥ ክርስቶስ ግን ካህን የሆነው ሞት እንኳ ሊያቋርጠው ያልቻለ ሕይወት ኃይል ስላደረበት ነው። (ዮሐ. 5፡26፤ 10፡17፥18)።

ሠ) «የምትደክም የማትጠቅምም።» (ቁ. 18)። የሌዊ ክህነት ለታሰበበት ጉዳይ፥ እርሱም ክርስቶስን ማመልከት ፍጹም ደኅና ነበረ፤ ነገር ግን ኃጢአትን የሚያስወግድ መሥዋዕትም ማቅረብ ሆነ፥ ወደ እግዚአብሔር አቅርቦ ኅብረትን ማስገኘት አልቻለም። የሌዊ ክህነት ድካም የሚገለጠው «አልቻለም» የሚለው ቃል በሁሉ ላይ በመጻፉ ነው። ሕሊናችንን ያነጻ ዘንድ፥ ሕጉን ለመጠበቅ ኃይልን ይሰጠን ዘንድ፥ ይልቁንም ወደ እግዚአብሔር ያቀርበን ዘንድ አልቻለም። ወደ ተሻለ ተስፋ አመልካችአልና መልካም ነበረ፥ ያን ተስፋ ግን ሊያስገኝ ባለመቻሉ ያቋቋመችው ትእዛዝ «የምትደክም የማትጠቅምም» ሆነች። ስለዚህ ስለ አሮን ክህነት የምትናገር ትእዛዝ ተሻረች፥ ሊያቀርብም የሚችል የተሻለ ክህነት ተተካ።

## ቁ. 20-25

20፥21 እነርሱም ያለ መሐላ ክህናት ሆነዋልና፤ እርሱ ግን፡- ጌታ፡- አንተ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘላለም ካህን ነህ ብሎ ማለ አይጸጸትም ብሎ በተናገረለት ከመሐላ ጋር ካህን ሆኖአልና ያለ መሐላ ካህን እንዳልሆነ 22 መጠን እንዲሁ ኢየሱስ ለሚሻል ኪዳን ዋስ ሆኖአል።

23 እነርሱም እንዳይኖሩ ሞት ስለ ከለከላቸው ካህናት 24 የሆኑት ብዙ ናቸው፤ እርሱ ግን ለዘላለም የሚኖር 25 ስለ ሆነ የማይለወጥ ክህነት አለው፤ ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል።

ሐዋርያው አሁን «እነርሱ ... እርሱ ግን ...» እያለ የዱሮ የሌዊ ካህናትና ኢየሱስን በማነጣጠር ልዩነታቸውን ያሳይና ከክርስቶስ ክህነት ዘንድ ያገኘነውን ታላቅ ጥቅም ይገልጣል። እነርሱ ያለ መሐላ ካህናት ሆነዋል፥ እርሱ ግን ከመሐላ ጋር ካህን ሆኖአል። መሾሙም ከመሾማቸው በሚሻል መጠን ዋስ የሆነለት የእርሱ ኪዳን እነርሱ ዋሶች ከሚሆኑለት ከዱሮ ኪዳን ይሻላል። እንደዚሁም ሁለተኛ እነርሱ እንዳይኖሩ ሞት ስላቋረጣቸው ክህነታቸውን ዘወትር ወደ ሌላ ካህን ያሳልፉ ነበር፤ እርሱ ግን የማይቋረጥ ሕይወት ኖሮት (ቁ. 15፡16) ለዘላለም ስለሚኖር ክህነቱ የማይለወጥ ነው። ስለዚህም እርሱ ሳይሰናከል ሳይከለከልም በእርሱ ካህንነት ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ፥ በመጠንም በዘመንም፥ ሊያድናቸው ይችላል።

<u>ማስገንዘቢያ</u>፡-

ሀ) «ማለ አይጸጸትም።» (ቁ. 20፡21)። እግዚአብሔር ይህን ብሎ የማለ የት ላይ ነው? ቢሉ፥ በመዝ. 109፡4 ላይ ነው። ሰው የሚምለው ጉዳዩ ትልቅ ሲሆን ብቻ ነውና እግዚአብሔር ከማለ ጉዳዩ እጅግ በጣም ትልቅ ቢሆን ነው። «አይጸጸትም» ይላልና ይህ የማይለወጥ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን እንገነዘባለን። እግዚአብሔር ኢየሱስ ለዘላለም ካህን

እንዲሆን ምሎአልና «ክህነቱ እንደ ሌዊ ክህነት ሆኖ ከዕለታት አንድ ቀን ያልፋል» ብለን መፍራት የለብንም። ክህነቱ የተረጋገጠ፥ ለመቼውም ቢሆን የማይለወጥ ነው። እስከ ዘላለም ድረስ ካህናችን እርሱ ነው።

ለ) «ያለ መሐላ ካህን እንዳልሆነ መጠን፥ እንዲሁ ኢየሱስ ለሚሻል ኪዳን ዋስ ሆኖአል።» (ቁ. 22)። የኪዳኑን መሻል የሚገልጥ፥ ዋሱ በመሐላ መሾሙ ነው። እግዚአብሔር የፊተኛውን ክህነት ሲያቋቁም መሐላ አስፈላጊ እንደ ሆነ አላሰበም (ዘጸ. 28፡1)፤ ይህን ግን ሲያቋቁም ምሎአል። እንግዲያውስ ይኸው ክህነት፥ እንደዚሁም ኪዳኑ፥ የበለጠ የተሻለ መሆኑም ተገልጦአል።

ሐ) «ኪዳን» (ቁ. 22)። ኪዳን በሁለት ሰዎች ወይም ወገኖች መካከል የተደረገ ስምምነት ወይም ውል ወይም ደግሞ ኮንትራት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ስለ ተደረጉ ስለ ሁለት ታላላቅ ኪዳኖች እናነባለን። በፊተኛው፥ «ብሉይ» በተባለው፥ እግዚአብሔር «ብታደርጉ (ወይም ባታደርጉ) እኔ አደርጋለሁ» ብሎአልና የተመሠረተበቱ በሰው ሥራ ላይ መሆኑ ታውቆአል። «የሚሻል ኪዳን» በተባለው በሁለተኛው «አዲስ» በተባለው ኪዳን ግን እግዚአብሔር «እኔ እንዲያው አደርጋለሁ» ብሎአልና የተመሠረተበት በእግዚአብሔር ጸጋ ላይ ብቻ ነው።

መ) «ዋስ» (ቁ. 22)። እዚህ ላይ በአማርኛ «ዋስ» ተብሎ የተተረጎመው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ እዚሁ ብቻ ተገኝቶአል። «መያዣ» ማለት ነው። ብሉይ ኪዳን እንደ ተሻረና ወደ እግዚአብሔር የምንቀርብበት የሚሻል ተስፋ እንደ ገባ የምናውቅበት፥ ኢየሱስ ለዘላለም ካህን እንዲሆን በመሾሙ ነው። ለዚህ ነገር እርሱ መያዣ ነው። ቢሆንም ቅሉ፥ ዋስ ደግሞ አንድ ነገር እንዲፈጸም የሚያረጋግጥ ነው። የተከሰሰ ሰው በቀጠሮ ቀን እንዲመለስ፥ ወይም አንድ ተበዳሪ ሰው ገንዘቡን እንዲከፍል የሚያረጋግጥ ዋስ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስም የሚገኙት የሁለቱ ኪዳኖች ዋሶች ካህናት ናቸው። ብሉይ ኪዳን እንዲፈጸም የእስራኤል ሕዝብ የእግዚአብሔርን ሕግ ሁሉ (አሪትን) እንዲጠብቁ ያስፈልግ ነበር። ከእነርሱ ዘንድ ሕግን የተላለፈ አንድ ሰው ቢኖር ከኪዳኑ ዋሶች፥ ማለት ከካህናት አንዱ መሥዋዕትን በማቅረብ ኃጢአቱን ያስተሰርይና በሁለቱ ወገኖች፥ በእግዚአብሔርና በሰውየው መካከል ኅብረትን ያስመልስ ነበር። እንደዚሁም ሁሉ ለአዲስ ኪዳን መፈጸም ዋስ የሆነው ካህን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

ሠ) «የማይለወጥ ክህነት።» (ቁ. 22)። እርሱ ሁልጊዜ እዚያ አለ። በብሉይ ዘመን አንድ ሰው ተቸግሮ ካህን ፍለጋ ምናልባት ይሄዳል። ሲደርስ ግን «ሉረ ሞቶአል! እሌላ ዘንድ መሄድ ያስፈልግሃል» ይባልና ሰውየው አዝኖ ይሄዳል። በኢየሱስ ግን እንደዚህ አይሆንም፤ ወደ ሌላ ወደ አዲስ መሄድ የለም፤ በፈለግህበት ጊዜ እርሱ እዚያ አለ።

ረ) «ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራል።» (ቁ. 25)። ኢየሱስ ዛሬ በመንግሥተ ሰማያት ከእግዚአብሔር ጋር እንደራሴአችን ነው። እዚያ የሆነው «ስለ እኛ» ነው። (ዎ. 9፡24)። እኛ ያቀረብነውን ጸሎት ተቀብሎ ለአባቱ ያስተላልፈዋል። ኃጢአትም ስንሠራ፥ ኃጢአት የማይሠራ የለምና (1ዮሐ. 1፡8፥10፤ 2፡1)፥ እርሱ የችንካሩ ምልክት ገና ያለባቸውን እጆቹንና እግሮቹን አሳየ ስለ እኛ ብሎ በጎልጎታ ላይ መከፈሉን ያስረዳና ከአባቱ ዘንድ ይቅርታ ይለምንልናል። እንደዚሁም በሰይጣን ስንፈተን፥ ከፈተና በታች እንዳንወድቅ ነገር ግን ኃይል ይላክልን ዘንድ ይለምናል። ከኃጢአት ፍርድና

ከኃጢአት ኃይል፡ ከሁለቱም፡ የሚያድነን አማላጃችን ኢየሱስ ነው። እስከ እድሜአችን ልክ ድረስ ዘወትር እንፈልገዋለን፡ እርሱም ዘወትር በግርማው ዙፋን ቀኝ ተቀምጦ ይማልድልናል። አባቱ ይነሣዋልን? ሉረ ከቶ አይነሣውም! (1ዮሐ. 1:9፤ ሮሜ 8:33:34)። የኢየሱስ የምልጃው መዓዛ አባቱን እንደምን ያስደስት ይሆን! (ዘፍ. 8:21፡ መዝ. 140:2፡ ራእይ 5:8፡ 8:3:4)። ይሁን እንጂ፥ ይለምንልናል ስንል በንጉሥ ፊት እንደ ቆመ ሰው ሆኖ ይለምንልናል ማለታችን አይደለም። እርሱ ለማኝ ሳይሆን በዙፋን ላይ የተቀመጠ ካህን ንጉሥ ነው። ልመናው ጸሎት ሳይሆን መኖሩ ነው። ማለት ከአባቱ ዘንድ የሚያገኝልን እዚያ በመኖሩ ወይም በመገኘቱ ብቻ ነው።

ሰ) «ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል።» (ቁ.25) ኢየሱስ ዘወትር በሕይወት ይኖራል፥ ስለዚህ በእርሱ በኩል ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል። እላይ እንዳልን ኢየሱስ ሁልጊዜ እዚያ አለ። እዚያም ያለው ካህናችን ሊሆን ነው። በእርሱ በኩል መምጣት ያስፈልገናል፥ ያለዚያ እግዚአብሔር አይቀበለንም። (ዮሐ.14:6) ነገር ግን በእርሱ በኩል ብንመጣ ፈጽሞ ሊያድነን ይችላል። በአማርኛ «ፈጽሞ» ተብሎ የተተረጎመው የግሪኩ ቃል ባለ ሁለት ፍች ነው። ብዛትንም ያመለክታል፥ ዘመንንም ያመለክታል። የሠራነው ኃጢአት ታላቅና የሚያስፈራ እንደ አለላም ቢሆን እንደ አመዳይ ሊያነጻው ይችላል፥ (ኢሳ.1:18)፤ ልንተወውም ከማንችል፥ ነገር ግን በአካላችን ተጎንጉኖ ባርያ ከሚያደርገንና ዘወትር ከሚጥለን ፈተናና መጥፎ ልማድ ፈጽሞ ሊያድነን ይችላል ያውም ለዘላለም! ወንድሜ ሆይ፥ ለመድኃኒትነቱ ወሰን እንደሌለ ታውቃለህን? ታላቅ ሊቀ ካህናታችን ኢየሱስ ፍጹም የሆነውን መሥዋዕት በማቅረብ ይቅርታን አስገኝቶ ከኃጢአት ፍርድ ያድነሃል፤ እንደዚሁም ዘወትር በሕይወት በመኖሩ ጸጋንና ኃይልን አስገኝቶ ከኃጢአት ኃይል ያድንሃል። ዛሬም ለመቻሉ ወሰን የለውም፥ ፈጽሞ ሊያድንህ ይችላል። ቃሉን አታሳንሰው። ኢየሱስ ከሁሉ፥ ያውም እስከ መጨረሻ ድረስ፥ ፈጽሞ ሊያድንህ ይችላል።

## ቁ.26-28

26 ቅዱስና ያለ ተንኮል ነውርም የሌለበት ከኃጢአተኞችም የተለየ ከሰማያትም
ከፍ ከፍ ያለ፥ እንደዚህ ያለ 27 ሊቀ ካህናት ይገባናል፤ እርሱም እንደነዚያ ሊቃነ
ካህናት አስቀድሞ ስለ ራሱ ኃጢአት በኋላም ስለ ሕዝቡ ኃጢአት ዕለት ዕለት
መሥዋዕትን ሊያቀርብ አያስፈልገውም፤ ራሱን ባቀረበ ጊዜ ይህን አንድ ጊዜ
ፈጽሞ አድርጎአልና። 28 ሕጉ ድካም ያላቸውን ሰዎች ሊቀ ካህናት አድርጎ
ይሾማልና፤ ከሕግ በኋላ የመጣ የመሐላው ቃል ግን ለዘላለም ፍጹም የሆነውን ልጅ
ይሾማል።

እንደዚህ ያለ ሊቀ ካህናት ተገቢያችን ነው። እግዚአብሔርን በፍጹም ልቡ እየወደደ (ዘዳግ.6:5) በባሕርዩና በአገልግሎቱ በእግዚአብሔር ዘንድ ቅዱስ የሆነ፤ ባልንጀራውን እንደ ራሱ እየወደደ በሰው ዘንድ ያለ ተንኮል የሆነ (ዘሌዋ.19:18። ዮሐ.1:48)። በሰውነቱና በባሕርዩ እድፍ ወይም ግድፈት ወይም ጎዶሎነት የሌለበት (ዘጸ. 12:5፤ ዘሌዋ. 22:19-24)፤ ሰው፥ ነገር ግን ኃጢአተኛ ሰው ያይደለ፤ አምላክም፥ ባለ ሙሉ ሥልጣንም የሆነ እንደዚህ ያለ ሊቀ ካህናት ያስፈልገናል። እንደዚህም ያለ በኢየሱስ ዘንድ ተገኘ፥ ኢየሱስ ይህን ሁሉ ነውና። (ማር. 1:24፤ ማቴ. 22:37-40፤ ኢሳ .53:9፤ ዮሐ. 8:46፤ 1ኛጴጥ. 1:18፥19፤ ዕብ. 4:15፤ ኤፌ. 1:20-23፤ ፊልጵ. 2:9፤ ማቴ. 28:18)

እርሱም ከእነዚያ የሌዊ ሊቃነ ካህናት እንደምን ይበልጣል! እነርሱ ኃጢአተኞች ስለነበሩ፥ ስለ ሕዝብ ኃጢአት መሥዋዕትን ሳያቀርቡ በፊት ስለ ራሳቸው ሊያቀርቡ ያስፈልጋቸው ነበር፤ (ዘሌዋ. 16፡6፥11፥15)፥ ያቀረቡትም ደጋግሞ ነበረ። ኢየሱስ ግን በአንድ ሰውነቱ መሥዋዕትና ካህን ሆኖ፥ ወይም ደጋግሞ ወይም ስለ ራሱ ሊያቀርብ አያስፈልገውም፤ ምክንያቱም፥ 1ኛ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ ባቀረበ ጊዜ (ኢሳ. 53፡10) ስለ ኃጢአት ሁሉ ለዘላለም በቂ የሆነውን መሥዋዕት ስላቀረበ፥ (ዕ. 9፡12፥28፤ 10፡10፥14) ሁለተኛ፥ ወይም ደጋግሞ፥ ማቅረብ ከቶ አያስፈልገውም። እንደዚሁም፥ 2ኛ ስለ ራሱ ሊያቀርብ አያስፈልገውም፤ ምክንክያቱም፥ የሕጉ ቃል ድካም ያላቸውንና ኃጢአተኞች የሆኑትን ብዙዎችን ሰዎች ካህናት ሲያደርግ በመዝ. 109፡4 ላይ የተጻፈው የመሐላው ቃል ያን የሕጉን ቃል ሽሮ ኃጢአት ከቶ ያልሠራውንና የማይሠራውን ለዘላለምም ፍጹም የሆነውን አንዱን የእግዚአብሔርን ልጅ ሾሞአል።

__ማስገንዘቢያ__፡-

ሀ) «እንደዚህ ያለ ሊቀ ካህናት ይገባናል።» (ቁ.26።) እምን የምንፈልገው ሁለመናው እንደዚህ ያለ ሊቀ ካህናት ነው፥ እርሱም ደግሞ ለእኛ ፈጽሞ ምቹ ነው። በመሞቱ ኃጢአታችንን አነጻ ወደ እግዚአብሔርም ሊያቀርበን ይችላል፤ በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነውና ሊራራልን ይችላል፤ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀምጦአልና አስፈላጊያችንን ሁሉ ሊሞላልን ይችላል! ዘወትር በሕይወት ይኖራልና፥ ፈጽሞ ሊያድነን ይችላል፥ በማማለዱም የእግዚአብሔርን ረድኤትና በረከት ሁሉ ያወርድልናል። ለዘላለም የሚኖር ፍጹም የሆነ ካህን በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦአል፥ እርሱም ወልደ እግዚአብሔር ነው። በእውነት እንደዚህ ያለ ሊቀ ካህናት እጅግ ይገባናል። ወደ ፍጻሜ ሊያደርሰን ያቅተው ይመስልሃልን? ሉረ አይመስልም! የሚሻል ተስፋ ገባ ማለት ነው፤ እንያዘው!

ለ) «ዕለት ዕለት።» (ቁ.27) ደራሲው «ዕለት ዕለት» ሲል በሐሳቡ ሁለት ነገሮች አጣምሮአል። ተራ ካህናት «ዕለት ዕለት» መሥዋዕትን ሲያቀርቡ (ዘጸ. 29፡38-42፤ ዳን. 8፡11-12) ሊቀ ካህናቱ «አስቀድሞ ስለ ራሱ ኃጢአት በኋላም ስለ ሕዝቡ ኃጢአት» በዓመት በዓመት ብቻ እርሱም በአስተሰርዮ ቀን ያቀርብ ነበር። (ዘሌዋ. 16፡6፥11፥15፥21፥29፥30)። ደራሲው በተለይ የሚያስበው ስለ ዘወትርነቱ ነውና ሁለቱን ነገሮች፥ የተራ ካህናትንና የሊቀ ካህናትን፥ አጣምሮ «ዕለት ዕለት» ይላል። «ተደጋግሞ» ማለቱ ነው። ይሁን እንጂ፥ ሊቀ ካህናቱ ከተራ ካህናት ጋር አብሮ ያቀረበ ሊሆን ይችላል። (ዘሌ. 6፡19-22፤ በግሪክ ትርጉም)።

ሐ) «ፍጹም የሆነውን» (ቁ.28) በዕ.2፡10፤ በዕ. 5፡9 ላይ የተጻፈውን እስኪ አስብ። ሊቀ ካህናት ይሆን ዘንድ በመከራ ተፈጸመ ከተፈጸመም በኋላ ሊቀ ካህናት፥ ተብሎ ተጠራ። በእርሱ ዘንድ ጉድለት የለም፥ ድካም የለም መደጋገም አያስፈልግም። ይገባናል! (ቁ. 26።)

# ምዕራፍ ስምንት

## የሚሻል ኪዳን መካከለኛ ስለ ሆነ

ከዕብራውያን ወገን የነበሩ የጥንት ክርስቲያኖች ወደ ማፈግፈግ ተቃርበዋል፥ ብዙዎች የዛሬ ክርስቲያኖችም እንደዚሁ ወደ ማፈግፈግ ይቃረባሉ። ምክንያቱም፥ የጥንትም ሆነ የዛሬ ሁለቱም በኢየሱስ ያለውን ጥቅም ስላላወቁ ወይም በሙሉ ስላልተገነዘቡት ነው። ዕብራውያን «መቅደስ፥ ክህነት፥ አገልግሎት፥ መሥዋዕትም ቀርተውብናልና ተጎዳን!» እያሉ አዝነዋል። የዛሬ ክርስቲያኖችም ከኃጢአት ፍርድ መዳናቸውን ቢያውቁም ቅሉ ዕለት ዕለት የሚደርስባቸውን ፈተና ለማሸነፍ ኃይልን ስላጡ «አልሆነልንም!» እያሉ ማፈግፈግን ጀምረዋል። ሐዋርያው ለሁለቱም ኢየሱስን አጉልቶ ያሳያል።

ዕብራውያን እንዲጽናኑ ከዱሮ ክህነት ይልቅ የኢየሱስ እንደሚሻል አስቀድሞ ያሳያቸዋል። (ም. 5-7።) ይህን አድርጎ ሲያበቃ በም. 8 ላይ የኢየሱስ አገልግሎት፥ ቀጥሎም በም. 9 ላይ ኢየሱስ የሚያገለግልበቱ መቅደስ፥ ቀጥሎ ደግሞ በም. 10 ላይ የኢየሱስ መሥዋዕት እንደሚሻል ያሳያቸዋል። አነስተኛው ነገር ቢቀርም እጅግ የሚሻለው መጥቶአል። ዕብራውያን እጅግ በጣም ተጠቀሙ እንጂ ከቶ አልተጎዱም። የዱሮ ካህናት ሊያደርጉላቸው ከሚችሉት ይልቅ ኢየሱስ አብልጦ ያደርግላቸዋል። ሐዋርያው እንዲህ አድርጎ በማስረዳት ዕብራውያንን ያጽናናል።

የዛሬ ክርስቲያኖችስ? አይ፥ እነርሱስ ኃጢአትን ለማሸነፍ ኃይልን ያጡት ኢየሱስ ዛሬ የሚሠራውን ሥራ ባለመገንዘባቸው ነው! ኢየሱስ ጥንት በድካም እንደ ሞተላቸው ያውቃሉ፤ ነገር ግን ዛሬ በኃይል በሕይወት እንደሚኖርላቸው አልተረዱም። ይህም ስለሆነ፥ ሐዋርያው ስለማያልፍ ሕይወት ኃይል (ም. 7፡15፥16) ይናገርና ኢየሱስ ፈጽሞ ሊያድናቸው መቻሉን እያስገነዘበ (ም. 7፡25) በሰማያት በግርማው ዙፋን ቀኝ መቀመጡን ያሳያል። (ም. 8፡6)

ደራሲው በም. 8 ላይ ከሌዊ ካህናት አገልግሎት የኢየሱስ አገልግሎት ይሻላል ብሎ ሲያስረዳ መሻሉ የተመሠረተበት በሁለት ነገሮች ላይ ነው:- 1ኛ፥ የሚሻል መቅደስ አገልጋይ በመሆኑ (ቁ. 2) 2ኛ፥ የሚሻል ኪዳን መካከለኛ በመሆኑ: (ቁ. 6) ነው ይላል። የሚሻል መቅደስ አገልጋይ በመሆኑ የዱሮ ካህናት በምሳሌና በጥላ ብቻ ያደረጉአቸውን ነገሮች ሁሉ እርሱ በእውነት ሊፈጽም ይችላል። የሚሻል ኪዳን መካከለኛ በመሆኑም በብሉይ ኪዳን ላይ ተሰጥተው ከነበሩት የተስፋ ቃሎች ይልቅ የሚሻሉትን ሊያስፈጽም ይችላል። ለጥንት ክርስቲያኖችም ሆነ ለዛሬ ኢየሱስ በእውነት የሚገባ ሊቀ ካህናት ነው።

### ቁ. 1-6።

1 ከተናገርነውም ዋና ነገሩ ይህ ነው፤ በሰማያት በግርማው ዙፋን ቀኝ የተቀመጠ
እንዲህ ያለ ሊቀ ካህናት 2 አለን፤ እርሱም የመቅደስና የእውነተኛይቱ ድንኳን
አገልጋይ ነው፥ እርስዋም በሰው ሳይሆን በጌታ የተተከለች ናት። 3 ሊቀ ካህናት
ሁሉ መባንና መሥዋዕትን ሊያቀርብ ይሾማልና፤ ስለዚህም ለዚህ ደግሞ
የሚያቀርበው አንዳች ሊኖረው የግድ ነው። 4 እንግዲህ በምድር ቢኖርስ፥ እንደ
ሕግ 5 መባን የሚያቀርቡት ስላሉ፥ ካህን እንኳ ባልሆነም፤ እነርሱም ሙሴ
ድንኳኒቱን ሲሠራ ሳለ እንደ ተረዳ፥ ለሰማያዊ ነገር ምሳሌና ጥላ የሚሆነውን

ያገለግላሉ። በተራራው እንደ ተገለጠልህ ምሳሌ ሁሉን ታደርግ ዘንድ ተጠንቀቅ ብሎት ነበርና። [6] አሁን ግን በሚሻል ተስፋ ቃል በተመሠረተ በሚሻል ኪዳን ደግሞ መካከለኛ እንደሚሆን፥ በዚያ ልክ እጅግ የሚሻል አገልግሎት አግኝቶአል።

«እንደዚህ ያለ ሊቀ ካህናት ይገባናል፤ እንዲህ ያለ ሊቀ ካህናት አለን!» (ም. 7፡26፤ ም. 8፡1) ከተነገረውና ከሚነገረውም ዋና ነገሩ ይህ ነው። እንዲህ ያለ ሊቀ ካህናት አለን፥ ሊቀ ካህናትም ብቻ ሳይሆን በግርማው ዙፋን ቀኝ የተቀመጠ ንጉሥ ነው። (ም. 1፡3) ባንድነት ንጉሥና ካህን የሆነው መልከ ጼዴቅ በዚህ ነገር ደግሞ ክርስቶስን መስሎአል። (ዘፍጥ. 14፡18።) ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተቀመጠውና የሚያገለግለውም በሰማያት ነው። በሰው እጅ የተተከለች መቅደስና ድንኳን (ማደሪያ) በምድር ላይ ኖረች (ዘጸአ. 25፡8፥9፤ 26፡1፤ 39፡32፥42፥43፤ ዕብ. 9፡1፥2)፤ ቢሆንም ኢየሱስ የእርስዋ አገልጋይ አይደለም። በማንኛውም ሥርዓት የተሾሙ ሊቃነ ካህናት ሁሉ የተሾሙት መባንና መሥዋዕትን ሊያቀርቡ ነውና «አንተ ካህን ነህ» ተብሎ ልዩ በሆነ በእግዚአብሔር ቃል የተሾመ ኢየሱስ (መዝ. 109፡3) የሚያቀርበው መሥዋዕት የግድ ይኖረዋል፤ እንዳለውም በም. 9፡11-14 ላይ ተጽፎ እናያለን። አገልግሎቱ በሰማያት ነው የተባለበት ምክንያት፥ የሚኖረው በምድር ላይ ቢሆን ኖሮ ካህን እንኳ ባልሆነም ነበርና ነው። ስለምን? ቢሉ፥ የምድራዊ መቅደስና ድንኳን አገልግሎት የተሰጠ ለሌዊ ነገድ ሰዎች ነው፥ ኢየሱስም ከሌዊ ሳይሆን ከይሁዳ ነገድ ወጥቶአልና።(ም. 7፡14) ዳሩ ግን በጌታ እንጂ በሰው እጅ ያልተተከለች መቅደስና ድንኳን አለች። (ም. 9፡11) መኖርዋን የምናውቅበቱ ምድራዊቱ ድንኳን በተሠራች ጊዜ እግዚአብሔር ሙሴን «በተራራው እንደ ተገለጠልህ ምሳሌ ሁሉን ታደርግ ዘንድ ተጠንቀቅ» ብሎት ነበርና። (ዘጸ. 25፡40፤ 26፡30፤ ዘኍል. 8፡4።) ስለዚህ በሙሴ እጅ የተሠራችው የእውነተኛ ነገር ምሳሌና ጥላ ብቻ እንደ ሆነች እንረዳለን። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሾመው በዚህች በእውነተኛይቱ እንዲያገለግል ነው። ኢየሱስ ትውልዱ ሌላ ነውና በዚያች፥ ምሳሌና ጥላ በሆነችው መቅደስ ሊያገለግል አልቻለም፤ ስለዚህ እግዚአብሔር «አንተ ካህን ነህ» ሲለው በእውነተኛ፥ በሰማያዊ መቅደስ እንዲያገለግል ማለቱ ነው። የምያገለግል ሊቀ ካህናት ነውና እንደሚያገለግሉ እንደ ሌሎች እንደ ሌዊ ሊቃነ ካህናት ሆኖ የኪዳን መካከለኛ ነው፥ ይህ ደግሞ የካህናት ሥራ ነውና። የሌዊ ካህናት የብሉይ ኪዳን መካከለኞች ሲሆኑ ኢየሱስ የአዲስ ኪዳን መካከለኛ ነው። አዲስ ኪዳንም በሚሻል ተስፋ ቃል ላይ ተመሥርቶ ከብሉይ ኪዳን የሚሻል ኪዳን ነውና የኢየሱስ አገልግሎት ከሌዊ ካህናት አገልግሎት እጅግ የሚሻል ነው።

<u>ማስገንዘቢያ</u>፡-

ሀ) ካህንና ንጉሥ። ጌታ በአብ በግርማው ዙፋን ቀኝ በመቀመጡ (ቁ.1) ፈጽሞ ንጉሥ እንደ ሆነ ታውቆአል፤ መሢህም ሊቀ ካህናትና ንጉሥ እንዲሆን በመዝ.109፡1 ና በዘካ.6፡13 ላይ ተጽፎአል። ኢየሱስ አስቀድሞ ሊቀ ካህናት ሆኖ መሥዋዕቱን አቅርቦአል፥ ቀጥሎም ንጉሥ ሆኖ በአባቱ ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአል። (ም. 1፡8፥ 2፡9፤ ፊል. 2፡9-11።) ሊቀ ካህናት ንጽሕናን ያመለክታልና፥ ንጉሥም ኃይልን ያመለክታልና፥ ከክርስቶስ ሞት ንጽሕናን ከሕይወቱም ኃይልን እናገኛለን። መሥዋዕቱን ሲያቀርብ በምድር ላይ የነበረውን ሥራ ፈጽሞአል፥ (ዮሐ. 17፡4፤ 19፡30) በግርማው ዙፋን ቀኝም ሲቀመጥ በሰማይ ያለውን ሥራ ጀምሮአል። መሥዋዕቱን ካቀረበ በኋላ «ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ» አለ (ማቴ. 28፡18) ዐርጎም በግርማው ዙፋን ቀኝ ተቀመጠ፤ ከዚያም አምላካዊ ኃይልን ለልጆቹ ያድላል። የምናሸንፍበትን ኃይል የምናገኘው ከእርሱ ከሚነግሠው

ንጉሣችን ዘንድ ነው። (ሮሜ 8:37።) ስለዚህ ኢየሱስ ነቢይና ካህን ንጉሥም መሆኑን እናያለን። ነቢይ ሆኖ የእግዚአብሔርን ነገር ተናገረን (ዕ. 1:2)፡ ካህን ሆኖ የምንድንበትን መሥዋዕት አቀረበ፡ ንጉሥም ሆኖ የምንኖርበትን ኃይል ይሰጠናል።

ለ) አገልጋይና መካከለኛ። ኢየሱስ የመቅደስ አገልጋይና የአዲስ ኪዳን መካከለኛ ነው። (ቁ. 2:6።) በምድራዊ መቅደስ በእስራኤላውያን ስም ሆነው አገልጋዮች የሆኑት የሌዊ ልጆች ነበሩ። (ዘጸ. 28: 41-43፡ ዘኁል. 8:23-26።) ሥራቸው መሥዋዕትን እያቀረቡ ሕዝብን ከኃጢአት ማንጻትና ወደ እግዚአብሔር ማቅረብ ነበረ። በሰማይ መቅደስ በእኛ ስም ሆኖ የሚያገለግል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። አስፈላጊውን መሥዋዕት ያቀረበው በምድር ላይ ሳለ ነውና ከእንግዲህ ወዲህ መሥዋዕት ማቅረብ አያስፈልገውም፡ ስለዚህ አገልግሎቱ ወደ እግዚአብሔር ማቅረብና መማለድ የምእመናንም ጸሎት ለእግዚአብሔር ማቅረብ ነው። (ዕ. 7:25፡ 9:24፡ ሮሜ 8:34፡ ራዕይ 8:3፥4።)

መካከለኛም በሁለት ወገኖች መካከል ገብቶ የሚቆምና እያገናኘ ከአንዱ ተቀብሎ ለሌላው የሚሰጥ ነው። (ኢዮብ 9:33፡ ገላ. 3:19።) የሌዊ ካህናት የዱሮ ኪዳን መካከለኞች እንደ ሆኑ ሁሉ እንዲሁም ኢየሱስ የአዲስ ኪዳንን መካከለኛ ነው። የሌዊ ካህናት ብሉይ ኪዳንን እያገለገሉ መሥዋዕትንና ምልጃን በማቅረብ ኪዳንን ተስፋዎች ለእስራኤል እንዳስገኙ ሁሉ እንዲሁም ኢየሱስ አዲስ ኪዳንን እያገለገለ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ በማቅረብና በመማለድ የአዲስ ኪዳንን ተስፋዎች ለክርስቲያኖች ያስገኛል። (ቁ. 8-12።)

ሐ) «ምሳሌና ጥላ» (ቁ. 5) እውነተኞቹ በሰማይ ነበሩ፤ በምድር ያሉትም በምሳሌና እንደ ጥላም አድርገው እነርሱን ያመለክቱናል። ምሳሌ ከቶ ፍጹም አይደለም (ዕ. 10:1)፥ ጥላም የነገርን ወይም የዛፍን ወይም የቤትን ወይም የሰውን ዙሪያ ዙሪያውን ብቻ ያሳያል እንጂ ነገሩን በሙሉ አያሳይም። እንደዚሁም ሁሉ በምድር ላይ ያሉ የሰማያትን ነገሮች ዙሪያ ወይም ዓይነታቸውን ያመለክቱናል እንጂ እነዚያ ነገሮች በእርግጥ እንዴት እንደ ሆኑ አናውቅም። መንፈሳውያን ነገሮች ግዙፍ በሆኑ ምሳሌዎች ይመሰላሉ ማለት ነው። (1ቆሮ. 13:12።) አሁን በተሰጠን አንጎላችን የሰማያትን ነገሮች ልናስተውል አንችልምና እነዚያ ነገሮች እኛ በምንችልበቱ እንደሚተረጉሙልን ይሆን ይሆናል።

መ) «የሚሻል ኪዳን።» (ቁ. 6) «ከብሉይ ኪዳን አዲሱ በምን ይሻላል?» ቢሉ፥ ብሉይ በእግዚአብሔር ላይና በሰውም ጭምር ሲመሠረት አዲሱ በእግዚአብሔር ላይ ብቻ ስለተመሰረተ ነው። በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር «እናንተ አድርጉ እኔም አደርጋለሁ» ሲል (ዘጸ. 23:22-33፤ 24:7፥8) በአዲስ ኪዳን እግዚአብሔር «እንዲያው እኔ አደርጋለሁ» ይላል። (ኤር. 31:31-34።) ብሉይ የወደቀው ከሰው ድካም የተነሣ ነው። አዲሱ እንደዚህ ባለ ምክንያት አይወድቅምና የሚሻል ኪዳን ነው። ለመሆኑ፥ አንተ ብዙ ጊዜ «እኔ አልችልም አቤቱ፤ አንተ አድርግልኝ!» ብለህ የለምን? ኧረ ይህ ኪዳን ይሻላል! የሚሻለው ደግሞ ዋስና መካከለኛ የሆነው የሚሻል በመሆኑ ነው። (ዕ. 7:22።)

ሠ) ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰማያት ያለፈውና ከሰማያት ከፍ ከፍ ያለው፥ በአብ በግርማው ዙፋን ቀኝም የተቀመጠው (ዕ. 4:14፤ 7:26፤ 8:1) መንግሥተ ሰማያትን እንዲከፍትልን ነው። በመንግሥተ ሰማያት ኑሮ መኖር የእግዚአብሔር ሕይወት ተካፋዮችም መሆን አስችሎናል ማለት ነው። ከዚህ በፊት እንዳየነው ሁሉ ኢየሱስ እንደ መልከ ጼዴቅ ካህን ሆኖ ኃጢአታችን ለማሸነፍ ኃይልን ይሰጠናል። ከምድር ዐርጎ በሰማያዊ

መቅደስ ገብቶ በተቀመጠ ጊዜ በዚያን ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ከሰማይ ወደ ምድር ወርዶ በሥጋዊ፥ ማለት በሰው ልብ መቅደስ ገባ። (1ቆሮ. 3፡16።) ምክንያቱን እናስተውል። ኢየሱስ ስለ ሰው ሆኖ ወደ ሰማያዊ መቅደስ ገብቶ የዚያን ስፍራ አቀማመጥ ወይም ኑሮ ለሰው ብሎ ከተቀበለ በኋላ፥ እንደራሴአቸው በሰማያት ተቀብሎ የነበረውን ኑሮ ለሰው እንዲሰጥ መንፈስ ቅዱስ ወደ ሰው ልብ መቅደስ ገብቶአል። መንፈስ ቅዱስ ወደ ዓለም የመጣው ወልድ የሰው እንደራሴ ሆኖ በመጋረጃ ውስጥ (ም. 6፡19፥20) ይኖርበት የነበረውን የንጽሕናና የኃይል ኑሮ ሰው እንዲካፈል ነው። እንደራሴአችን በሰማያት ያገኘውንና የሆነውን ሁሉ መንፈስ ቅዱስ ለሰው ይሰጠዋል ያስፈጽመዋልም።

## ቁ. 7-13

7 ፊተኛው ኪዳን ነቀፋ ባይኖረው፥ ለሁለተኛው ስፍራ ባልተፈለገም ነበር።

8 እነርሱን እየነቀፈ ይላቸዋልና፡-

9 እነሆ፥ ከእስራኤል ቤትና ከይሁዳ ቤት ጋር አዲስ ኪዳን የምገባበት ወራት
ይመጣል ይላል ጌታ፥ ከግብፅ አገር አወጣቸው ዘንድ እጃቸውን በያዝሁበት ቀን
ከአባቶቻቸው ጋር 10 እንደ ገባሁት ኪዳን አይደለም፤ እነርሱ በኪዳኔ አልጸኑምና፥
እኔም ቸል አልኋቸው ይላል ጌታ። ከዚያ ወራት በኋላ ከእስራኤል ቤት ጋር
የምገባው ቃል ኪዳን ይህ ነውና ይላል ጌታ፤ ሕጌን በልቡናቸው አኖራለሁ
በልባቸውም እጽፈዋለሁ፥ እኔም አምላክ እሆንላቸዋለሁ እነርሱም ሕዝብ
ይሆኑልኛል።

11 እያንዳንዱም ጎረቤቱን እያንዳንዱም ወንድሙን፡- ጌታን እወቅ ብሎ
አያስተምርም፥ ከታናሹ 12 ጀምሮ እስከ ታላቁ ድረስ ሁሉ ያውቁኛልና።
ዓመፃቸውን እምራቸዋለሁና፥ ኃጢአታቸውንም ደግሜ አላስብም።

13 አዲስ በማለቱ ፊታኛውን አስረጅቶአል፤ አሮጌና ውራጅ የሆነውስ ሊጠፋ
ቀርቦአል።

«አዲስ ኪዳን እገባለሁ» ብሎ እግዚአብሔር ካሰበ፥ ምክንያቱ በፊተኛው ኪዳን ነቀፋን ወይም ጉድለትን ቢያገኝበት ነው። ነቀፋን (ጉድለይን) አግኝቶበታልና እርሱን ትቶ አዲስን መግባት አስቦአል። «ነቀፋውስ ምን ኖሮአል?» ቢሉ፥ ነቀፋውማ በቁ. 9 ላይ ተጽፎ እንደተመለከተ «በኪዳኔ አልጸኑምና» የተባለው የሕዝቡ አለማቻል ነበረ። ሕጉ ቅዱስ ነበር ትእዛዚቱም ቅድስትና ጻድቅት በጎም ነበረች (ሮሜ 6፡12)፥ ሕዝቡ ግን ሊጠብቁት አልቻሉም (በመጠበቅ አልጸኑም)፥ ሕጉም የሚጠብቁበትን ኃይል ለሕዝብ አልሰጠም። በዚህ ምክንያት ነው «በዚያ ክህነት ፍጹምነት አልተገኘም» እና «ሕጉ ምንም ፍጹም አላደረገም» የተባለው። (ም. 7፡11፥18፥19) ጉድለቱ በእውነት የኪዳኑ ሳይሆን በልባቸው አለመታዘዝ ምክንያት የሕዝቡ አለመቻል ነበረና (ሮሜ 8፡3) እግዚአብሔር እርሱን ሳይሆን እነርሱን እየነቀፈ «አዲስ ኪዳን እገባለሁ» አለ። ይሁን እንጂ ኪዳኑ ሰው ማድረግ የሚገባውን እያሳየ ያን ነገር ለማድረግ ኃይል አልሰጠውምና በኪዳኑ ደግሞ ነቀፋ ተገኝቶአል። ስለዚህም እግዚአብሔር አዲስ ኪዳን ሊገባ አስቦአል። ይህም ያሰበው ኪዳን እንደ ፊተኛው በሙሴ ዘመን እንደ ገባው ያለ ኪዳን (ዘጸአይ 24፡1-11) አይሆንም ነበር። ያ ኪዳን የአባትና የልጅ የሕግና የትዕዛዝ የተግሣጽና የቅጣት ኪዳን ነበር። በልባቸው ክፋት ምክንያት የእስራኤል ሕዝብ ሊጠብቁት አልቻሉም፥

እግዚአብሔርም ስለቸው ለእነርሱ መጠንቀቁም ወደ መቆጣት ተለወጠ። እንግዲያውስ በነቢዩ በኤርምያስ ዘመን አዲስ ኪዳን ሊገባ ማሰቡን አስታውቆአል። (ኤር. 31፡31-34)

በአዲስ ኪዳን እግዚአብሔር ሕጉን ከሰው ውጭ ባሉት በድንጋይ ጽላቶች ላይ ሳይጽፍ (ዘጸአት 32፡15-16፣ 34፡29፣ 2ቆሮ. 3፡7) በሰው ውስጥ፡ በልቡ ላይ ይጽፈው ነበር። በብሉይ ጊዜ ሕጉ በሰው አንጻር ሲቆም ልቡ የማይታዘዝ በመሆኑ አልተነካም ነበርና ሰው ለሕጉ መታዘዝ አልቻለም፡ አሁን ግን ሕጉ በልቡ ላይ ስለሚጻፍ ልቡ ታዛዥ ይሆንና ሕጉን በደስታ ይፈጽመዋል። (ፊልጵ. 2፡13) አለመቻል ተወግዶአል፤ መጽናትም ተገኝቶአል ማለት ነው።

በዚህ ኪዳን ደግሞ እግዚአብሔር ልዩ በሆነ ዓይነት የሕዝቡ አምላክ፤ እነርሱም ልዩ በሆነ ዓይነት የእርሱ ሕዝብ ይሆኑ ነበርና በመካከላቸው ልዩ የሆነ መግባባትና መስማማት ይሆናል። (ከዘጸአት 6፡7ና 19፡5 ጋር ኤፌ. 1፡14ንና 1ጴጥ.2፡9ን አነጣጥር) ይህስ እንደምን ነው? ቢሉ፥ ነገሩ ከዚህ እንደሚከተለው ነው። አዳም ኃጢአት ከመሥራቱ በፊት በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ልዩ ዓይነት መተዋወቅ፤ ማለት መግባባትና መስማማት፤ ግኑኙነትና ዝምድና ነበር፤ አዳም ግን ኃጢአት በሠራ ጊዜ ይህ ሁሉ ተበላሸ። በአዲሱ ኪዳን የተስፋ ቃል ይህ ልዩ መተዋወቅ ይመለስ ነበር። እግዚአብሔር ለስኛ አሁን የሚሆነው ለአዳም የነበረው ዓይነት አምላክ ነው፤ እኛም ለእግዚአብሔር የምንሆነው አዳም ለእግዚአብሔር በነበረው ዓይነት ሕዝቡ እንሆናለን። ኃጢአተኛ በሆነ ሰውና በእግዚአብሔር መካከል ከነበረው መተዋወቅ ሁለመናው ልዩ የሆነ፣ ማለት ኃጢአት ከመግባቱ በፊት የነበረው ዓይነት መተዋወቅ አሁን ይመለስልናል ማለት ነው። አዲስ ኪዳን በሚገቡ ወገኖች፥ በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል መከፋፋትና መለያየት ከእንግዲህ ወዲህ የለም፣ ለመቸውም ቢሆን መተዋወቃቸው የተቀራረበና የተሳሰረ ነው።

ሦስተኛ ደግሞ እግዚአብሔርን የሚያውቁት ከሌሎች ሰዎች ተምረው ሳይሆን እርሱ ራሱ በመንፈስ ቅዱስ ያስተምራቸው ነበር። (ኢሳ. 54፡13፥ ዮሐ. 6፡45፥ 1ዮሐ. 2፡27) ዱሮ እግዚአብሔርን የማወቅ መብት ለካህናት ተወስኖ ነበር፥ ያለ እነርሱም የእግዚአብሔርን ቃል ሊተረጉም የሚችል አልነበረም፤ ተሰጥቶአልና አዲስ ኪዳን ግን መብቱ ለሁሉም (2ኛ ጢሞ. 3፡15) እግዚአብሔርን በማወቅ ነገር በካህናትና በተራ ሕዝብ መካከል ልዩነት እይኖርም ነበር። የግሪኩም ቃል እንደሚያመልክትና አግርኛው እንድሚለው ሁሉ ይህ መብት ስለ እግዚሰብሔር እንዲያውቁ ብቻ ሳይሆን ራሱን እግዚአብሔርን እንዲያውቁት ነው።

ይህም ሁሉ የሚሆነው «ዓመፃቸውን እምራቸዋለሁና፥ ኃጢአታቸውንም አላስብምና።» (ኤር.31፥34።) «ና» የተባለችው ቅጽል ምክንያትን ታስታውቃለችና ቁ.12፥ ከእርሱ በላይ የተጻፉት የተስፋ ቃሎች የሚፈጹሙበትን ምክንያት ያስረዳል። እነርሱ የሚሆኑት እግዚአብሔር ዓመፅን ስለሚምርና ኃጢአትን ስለማያስብ ነው። ስለዚህም መሠረታዊ የሆነ የአዲስ ኪዳን ተስፋ ይኸው ነው፥ እርሱም ወደ ቀሩት የተስፋ ቃሎች ሁሉ ዘንድ የሚያደርስ በር ነው።

ይህ ኪዳን በእግዚአብሔር ቃል «አዲስ» ተባለ። እንግዲያውስ «አሮጌ» አለ! «አሮጌውስ ማናቸው ኪዳን ነው? ቢሉ፥ የፊተኛው፥ «ብሉይ» የተባለው ነዋ! ያስረጀውም እግዚአብሔር ነው። «ይሻራል፥ ይጠፋል» ያለው እግዚአብሔር ራሱ ነው፥ ያውም ከብዙ ዓመታት በፊት፥ የተናገረውም ከሚያከብሩዋቸው ነቢያታቸው በአንዱ ነው! አሮጌና ውራጅ የሆነ ነገር በቅርቡ የሚጠፋ ነውና መልእክቱ የተጻፈላቸው ዕብራውያን ያስተውሉ። እነርሱ ሊጠብቁ የሚግተረተሩበትን እግዚአብሔር «አርጅቶአል፥ አይረባም»። ብሎ ነቅፎታልና ዕብራውያን (ክርስቲያኖችም) መጥፋቱ ከዱሮ ዘመን እንኳ መነገሩን ተገንዝበው አዲሱን አሁን ይጨብጡ።

ማስገንዘቢያ፡-

ሀ) «ከእስራኤል ቤትና ከይሁዳ ቤት ጋር» (ቁ. 8) እነኚህ የእስራኤል አገር ሁለቱ ክፍሎች ናቸው። (1ኛነገ. 12፡19-24) እግዚአብሔር ከአሕዛብ ጋር ኪዳን ገብቶ አያውቅም አይገባም። እንግዲያውስ አዲስ ኪዳን የገባ ከእስራኤል ጋር ነው። ይህ ሲባል አንባቢው «ይህስ ከሆነ ለእስራኤል መቼ ተፈጸመ? እኛስ? ከአሕዛብ ወገን ብንሆን በኪዳኑ እንደ ምን እንገባለን?» ብሎ ይጠይቅ ይሆናል። ለእነዚህ ለሁለት ጥያቄዎች መልሱ አንድ ሆኖ ከዚህ እንደሚከተለው ነው። ዋና መገንዘብ የሚያስፈልገን ነገር ያለ መካከለኛ የሚፈጽም ኪዳን እንደሌለ ነው። ማለት የኪዳኑ መፈጸም የሚንጠለጠለው በመካከለኛው ነው። የመቅደስ አገልጋይ ሆኖ በኪዳኑ መሠረት ከእግዚአብሔር ዘንድ ተስፋዎችን ተቀብሎ ለሰው የሚሰጥ መካከለኛ ነውና ኪዳኑ የሚፈጸም ከመካከለኛው ጋር መንፈሳዊ ግንኙነት ላለው ሰው ነው። «መንፈሳዊ ግንኙነትስ ምን ማለት ነው? የሚገኘውስ እንዴት ነው?» ቢሉም አንድ ሰው እግዚአብሔር መካከለኛ አድርጎ በሾመው ሲያምን ነው። (ዘጸ. 14፡31፤ ዩሐ. 11፡45) ማለት ኢየሱስ ክርስቶስን የግል መድኀን አድርገን ስናምንበትና ስንቀበለው (ዩሐ. 1፡12) በዚያን ጊዜ በእርሱና በእኛ መካከል ልዩ ስሜት ይፈጠርና በመካከላችን ሕያው ግንኙነት ይገኛል። እስራኤላውያን ከአዲስ ኪዳን መካከለኛ ጋር ይህን ግንኙነት እስከ አሁን አላገኙምና ኪዳኑ አልተፈጸመላቸውም ተስፋዎቹንም አልተቀበሉም። «መቼ ይፈጸምላቸዋል? መቼ ይቀበላሉ?» ቢሉ፥ በዳግም ምጽአት ጊዜ፥ እስራኤል በክርስቶስ ሲያምኑና እንደዚሁም ከኪዳኑ መካከለኛ ጋር ግንኙነትን ሲያገኙ ነው። (ዘካ. 12፡10 ም. 13፡1፥ ሮሜ 11፡25-32) እንደዚሁ ደግሞ ከአሕዛብ ወገን የሆነ ሰው በክርስቶስ ሲያምን ከምድራዊ እስራኤል ባይሆን እንኳ ከመንፈሳዊ እስራኤል ነውና (ገላ. 3፡7፥9፥6፥16፥ ሉቃ. 19፡9፥ ዩሐ. 1፡47) ኪዳኑ ይፈጸምለታል እርሱም ተስፋዎቹን ይቀበላል። በመካከለኛው ላመነ ሰው፥ በዚያ ባመነበቱ ጊዜ፥ ኪዳኑ ይፈጸምለታል ማለት ነው።

ለ) በይቅርታ ላይ የተመሠረቱት 3 የአዲስ ኪዳን ተስፋዎች። (ቁ. 10፡11) በአዲስ ኪዳን እንደምናገኘው ሁሉ በይቅርታ ላይ ተመሥርተው ለክርስቲያኖች ሁሉ የተሰጡ ሦስት የተስፋ ቃሎች አሉ። አዲሱ ኪዳን የተሠራው የፊተኛውን ጉድለት ለመሙላት ነውና፤ ማለት፥ አለመቻላችንን አስወግዶ መቻልን ለመስጠት ነውና 1ኛው የተስፋ ቃል የታዛዥ ልብ ተስፋ ነው። እግዚአብሔር ሕጉን በልቡናችን ያኖረዋል በልባችንም ይጽፈዋል። ኃጢአትን (ፈተናን) የምናሸንፍበት ኃይል እነሆ! ቀድሞ በውጭ የነበረው አሁን በውስጥ ሊሆን ነው። ቀድሞ ፊት ለፊታችን ሆኖ እናየውና ልንፈጽመው እንጥር ነበር፤ ብንጥርም ቅሉ አብዛኛውን ጊዜ ልንፈጽመው ሳንችል እንወድቅ ነበር። አሁን ግን በአዲስ ኪዳን የተሰጠው የተስፋ ቃል ያ ሕግ በልባችን እንዲኖር ነው፤ ማለት፥ ከእኛ የተለየ ነገር ሳይሆን ከሰውነታችን ክፍሎች አንዱ ሊሆን ነው። ቀድሞ ከመቆም ይልቅ መውደቅ ቀላላችን ነበረ፥ አሁን ግን ከመውደቅ ይልቅ መቆም ይቀለናል። የባሕር ዛፍን ዘር ነገር እናስተውል። የባሕር ዛፍ ሕግ በዘሩ ልብ ውስጥ ስላለ ዘሩ ሲያድግ የባሕር ዛፍ ይሆናል፥ የባሕር ዛፍንም በሙሉ መስሉ ሕይወቱ (ባሕርዩ፥ አመሉ) የባሕር ዛፍ ይሆናል። እንደዚሁም የእግዚአብሔር ሕግ በልቡናችንና በልባችን፥ ማለት በፈቃዳችንና በምኞታችን ውስጥ ተጽፎ ሲኖር የእግዚአብሔርን ባሕርይ እንይዛለንና ሕጉን እንዲያው በደስታ እንፈጽመዋለን። (መዝ. 39፡8፥ 1ዮሐ. 3፡9) ክፉ የነበረው ልባችን የእግዚአብሔር ሕግ ተጽፎበት ኖሮ አሁን ፈጽሞ ታዛዥ ልብ ነውና ከአለመታዘዝ ይልቅ መታዘዝ ይቀለናል። በአዲስ ኪዳን ይህ

በተስፋ ቃል ተሰጥቶናል፣ እንወርሰውም ዘንድ ኢየሱስ ዋሳችንና ተያዣችን ነው። (ዕ. 7:22) «የእግዚአብሔር ሕግስ ወደ ልባችን እንደምን ይገባል?» ቢሉ፣ መንፈስ ቅዱስ ሲገባ ነው፤ የእግዚአብሔር ሕግ የእግዚአብሔር መንፈስ ነውና።

2ኛው የተስፋ ቃል እግዚአብሔር አምላክ እንዲሆንልን፣ እኛም ሕዝብ እንድንሆንለት ነው። ይህም ማለት እርሱ የእኛ አምላክ ይሆናልና አምላካችን ይሆንልን ዘንድ ይምንወደውን ሁሉ እርሱ ይሆንልናል፤ እኛም የእርሱ ሕዝብ እንሆናለንና ህዝቡ ይሆኑለት ዘንድ የሚወደውን ሁሉ እኛ እንሆንለታለን። ከጥንት ጀምሮ የእግዚአብሔር ሐሳብ ይኸው ነው፤ ሰውን የፈጠረበትም ምክንያቱ ይህ ነው። «እኔ አምላክ እሆናቸዋለሁ እነርሱም ሕዝብ ይሆኑኛል» የተባሉ ቃሎች በመጽሐፍ ቅዱስ ተደጋግመው ይገኛሉ። (ዘጸ. 6:7፤ ዘሌዋ. 26:12፤ ዘዳግ. 29:13፤ ኤር. 30:22፤ 31:33፤ ሕዝ. 11:20፤ 36፤ 28:37፤ 27፤ ሆሴ. 2:23፤ ዘካ. 8:8፤ 2ኛቆር. 6:16:18፤ ራእ. 21:3) እግዚአብሔር ራሱን የሚሰጥላቸውንና ያለማቋረጥ ከእርሱ ጋር በመኖር ዓይነተኛ ደስታቸውን የሚያዩትን ሕዝብ ፈልጎአል። እንዲህ ያለውንም ህዝብ የሚያገኘው ከእርሱ ጋር በአዲስ ኪዳን ውስጥ በሚገቡት ሰዎች፣ ማለት በእኛ፤ በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በምንገኝ ሰዎች ዘንድ ነው። (መዝ. 49:5)

ለእርሱ የሆነ ሁሉ የእኛ ይሆናልና በእና ዘንድ የታጣ ወይም የጎደለ ሁሉ በእርሱ ሀብት ይሞላል። (ሉቃ. 15:31፤ ፊሊጵ. 4:19) ለእኛ አስፈላጊ የሆነውን ሁሉ እርሱ ይሆንልናል ማለት ነው። በአጸፋው ደግሞ፤ በእርሱ ደስ እንደሚለው እንደሚወደው ልጁ ያደርገናልና (ማቴ. 3:17፤ ሮሜ 8:29) እርሱ የሚፈልገውን ሁሉ እኛ እንሆንለታለን። ይህ ደግሞ በአዲስ ኪዳን በተስፋ ቃል ተሰጥቶናል፤ እንወርሰውም ዘንድ ኢየሱስ ዋሳችንና ተያዣችን ነው።

3ኛው የተስፋ ቃል የአብሮ መኖር ወይም የኅብረት ተስፋ ነው። እንደ ፊተኛው፤ እንደ ብሉይ ኪዳን ሕግ፤ ካህናቶቹ ብቻ፤ እነርሱም በዓመት፤ አንድ ጊዜ ብቻ በዓመት ወደ እግዚአብሔር ፊት ይገቡ ነበር። (ዘጸአ. 30:10) እንደ አዲሱ ኪዳን የተስፋ ቃል ግን ሁላችን ሁልጊዜ በእግዚአብሔር ፊት ልንኖር እንችላለን። ስለዚህ «እግዚአብሔርን እወቅ!» አይባልልንም፤ እግዚአብሔርን እናውቃለንና! ሰውም እንዲያስተምረን አያስፈልግም፤ ራሳችን ገብተን ከእግዚአብሔር ጋር ተዋውቀን አውቀነዋልና፤ ያውም ወዳጅንና ባልንጀራን እንደምናውቅ። በአዳም ዘመን እግዚአብሔር ቀኑ በመሸ ጊዜ ከአዳም ጋር ሊገናኝ ይመጣ ነበርና አዳም እግዚአብሔርን አውቋል፤ ይሁን እንጂ፤ መገናኘታቸው በየጊዜው የሚቋረጥ ነበር።(ዘፍጥ. 3:8) እኛ ግን በማይቋረጥ ኅብረት ከእግዚአብሔር ጋር እንኖራለንና ከዚያ እጅፍ በበለጠ አኳኋን እናውቀዋለን። መጋረጃው ከላይ እስከ ታች በሁለት ተቀድዶአል (ማቴ. 27:51 ዕ. 10:19-20)፤ በሩ ክፍት ነው፤ ዛሬ ሁላችን ገብተን ከእግዚአብሔር ጋር አብረን ልንኖር እንችላለን፤ ኖረንም እናውቀዋለን። በአዲሱ ኪዳን የተሰጠ ለሁላችን የሚሆን የተስፋ ቃል ነው፤ ይህንኑም እንወርስ ዘንድ ኢየሱስ ዋሳችንና ተያዣችን ነው።

ሐ) ኪዳኑ የተሰጣቸው ሰዎች የተስፋ ቃሎቹን እንዲወርሱ ዋስ የሚሆን የኪዳኑ መካከለኛ መሆኑን ልብ እናድርግ። መውረስ ከእኛ ሳይሆን ከእርሱ ነው። የአዲስ ኪዳን መካከለኛ የሆነው ኢየሱስ እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩትን ተስፋዎች ሁሉ አንድ በአንድ እንድንወርስ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጠን ተያዣችን ነው። እርሱ በመንፈስ ቅዱስ እየሠራ እያንዳንዱ የተስፋ ቃል እንዲፈጸምልን ለማድረግ ዋስ ነው። እስኪ እናስብ! እንዲህ ያለ የካህናት አለቃ አለን፤ ሦስቱን የተስፋ ቃሎች፤ አራተኛውንም እርሱም የይቅርታን ተስፋ፤ ሊያስፈጽምልን ተዘጋጅቶ ተቀምጦአል። እኛ ምንም ማድረግ አያስፈልገንም፤ እርሱ «እኔ

አደርጋለሁ» ብሎ ቃሉን ሰጥቶአል። ያደርግልን ዘንድ ብቻ በጸሎት እንጠይቀው፤ በዚያንም ጊዜ «ዓይን ያላየችው ጆሮም ያልሰማው በሰውም ልብ ያልታሰበው እግዚሰብሔር ለሚወዱት አዘጋጅቶአል» ተብሎ በ1ኛ ቆሮ. 2፡9 ላይ የተጻፈው ቃል እውነት እንደሆነ እናገኛለን። «ሰማይና ምድር ያልፋሉ፥ ቃሌ ግን አያልፍም።» (ማቴ. 24፡35) « እርሱ ያለውን አያደርገውምን? » (ዘኁል. 23፡19)

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## (የኢየሱስ አገልግሎት የተሻለ ነው)

### በሚሻል መቅደስ ውስጥና በሚሻል ደም ስለሚያገለግል

ምዕራፍ ከምዕራፍ በመለያየ ቁጥር ይለያይ እንጂ የመልእክቱ ሐሳብ የተያያዘ ነው። ደራሲው የሌዊን ሥርዓትና የክርስቶስን ሥርዓት እያነጻጠረ በሁሉም በኩል የክርስቶስ እንደሚሻል በማሳየት ላይ ነው። ከም. 5 እስከ ም. 7 ድረስ በክህነት ረገድ የክርስቶስ እንደሚሻል እንዳሳየ ሁሉ እንዲሁም አሁን ከም. 8 እስከ ም. 10 ድረስ በአገልግሎት ረገድ እንደሚሻል ያሳያል። በም. 8 ላይ የክርስቶስ አገልግሎት እጅግ አድርጎ የሚሻልበቱ ክርስቶስ በሚሻል ተስፋ ቃል በተመሠረተ የሚሻል ኪዳን መካከለኛ በመሆኑ ነው ብሎአል። በዚያ ምዕራፍ ላይ ክርስቶስ የእውነተኛይቱ ድንኳን አገልጋይ ስለ መሆኑና ሙሴም ስለ ሠራት ድንኳን በአጭሩ ተናግሮአል፤ ነገር ግን ስለ ኪዳን መናገር ወድዶ እስከ ጥቂት ጊዜ ድረስ እነዚያን ነገሮች ትቶአል፤ አሁን ግን እንደገና ያነሣቸዋል። ምዕራፉ በ2 ክፍል ይከፈላል። በመጀመሪያው ክፍል (ቁ. 1-14) ስለ መቅደስ ሲናገር በሁለተኛው ክፍል (ቁ. 15-28) ስለ ደም ይናገራል።

ከቁ. 1 ጀምሮ እስከ ቁ. 14 ድረስ ሙሴ መቅደስ እንድትሆን የሠራት ድንኳን ምሳሌ ብቻ እንደ ነበረችና የሌዊ ካህናት ያቀረቡት መባና መሥዋዕት የሚጠፋ የሥጋ ብቻ በመሆናቸው የሚያመልከውን በሕሊና ፍጹም ሊያደርጉ እንዳልቻሉ፥ ክርስቶስ ግን ያገለገለባት ድንኳን እውነተኛይቱ እንደ ነበረችና ያቀረበው መሥዋዕት የዘላለም መንፈስ ያደረበት በመሆኑ ሕያውን እግዚአብሔርን እንድናመልክ ሕሊናችንን ሊያነጻ እንደቻለ በማስረዳት የክርስቶስ አገልግሎት ከሌዊ ካህናት አገልግሎት እንደሚሻል ይገልጣል።

ከቁ. 15 እስከ ቁ. 28 ደግሞ ስለ ደም ይናገራል። ኪዳንም ሆነ ኑዛዜ የሚጸና በደም መሆኑንና እንደ ኦሪት ሕግ ከጥቂቶች በቀር ነገር ሁሉ በደም እንደሚነጻ ካሳሰበ በኋላ እነዚያ የዱሮ ምሳሌዎች በደም እንዲነጹ አስፈላጊ ከሆነ እውነተኞቹ ነገሮች በደም፥ ይልቁንም በሚሻል ደም፥ ይነጹ ዘንድ አስፈላጊ መሆኑን ያስረዳል። እስከዚህ ድረስ ምሳሌና እውነተኛ ነገር ተመሳስለዋል፥ እዚህ ላይ ግን የማይመሳሰሉበት ነገር ተገኝቶአል። እነዚያ የሌዊ ሊቃነ ካህናት በየዓመታቱ ሁሉ ወደ ድንኳኒቱ የሚገቡ ሲሆኑ፥ ክርስቶስ አንድ ጊዜ ብቻ ገብቶአል። የእነርሱ ሥራ ምንም ፍጹም አላደርገምና በዓመት በዓመት መድገም ሆነባቸው፤ የክርስቶስ ደም ግን ጉዳዩን ለዘላለም ፈጽሞአልና መግባቱ እንዲደገም አላልፈለገም። እንዲያውስ ከሌዊ ካህናት አገልግሎት የክርስቶስ የሚሻል አይደለም? እጅግ ይሻላል!

#### መጀመሪያ ክፍል ቁ. 1-14

#### ቁ. 1-5

1 ፊተኛይቱም ደግሞ የአገልግሎት ሥርዓትና የዚህ ዓለም የሆነው መቅደስ
ነበራት። 2 የመጀመሪያይቱ ድንኳን ተዘጋጅታ ነበርና፥ በእርስዋም ቅድስት
በምትባለው ውስጥ መቅረዙና ጠረጴዛው የመሥዋዕቱም ኅብስት ነበረባት፤
3 ከሁለተኛውም መጋረጃ ወዲያ ቅድስተ ቅዱሳን የምትባለው ድንኳን ነበረች።
4 በዚያም ውስጥ የወርቅ ማዕጠንት ነበረ ሁለንተናዋም በወርቅ የተለበጠች የኪዳን
ታቦት፤ በእርስዋም ውስጥ መና ያለባት የወርቅ መሶብና የበቀለች የአሮን በትር
የኪዳኑም ጽላት ነበሩ፤ 5 በላይዋም ማስተስሪያውን የሚጋርዱ የክብር ኪሩቤል
ነበሩ፤ ስለ እነዚህም ስለ እያንዳንዳቸው ልንናገር አሁን አንችልም።

ደራሲው የፊተኛውንና የሁለተኛውን ኪዳን አገልግሎት በማነጣጠር ላይ ነው። (በአማርኛ ትርጉማችን «ፊተኛይቱ» ተብሎ ጾታው ሴት የሆነው ቃል የመጣው ከግሪክ ግልባጮች ከአንዳንዱና ከግዕዝ ትርጉም ነው። ሐዋርያው በግሪክ ቋንቋ ሲጽፍ «ፊተኛ» ብሎ ስምን ጠቅሶ ሳያገባ በመቅረቱ ፊተኛው ኪዳን፥ ወይም ፊተኛይቱ ድንኳን እንደሆነ ያስጠረጥራል። ዮሐንስ አፈወርቅ ግን «ፊተኛ ሲል ምን ማለቱ ነው? ኧረ ፊተኛ ኪዳን ማለቱ ነው!» ይላል፥ ይህም እውነት ሳይሆን አይቀርምና እንዲህ አድርገን ተርጉመነዋል።) ያ ፊተኛው ኪዳን፥ ብሉይ ማለት ነው የተመደበ የአገልግሎት ሥርዓትና ያ ሥርዓት የሚፈጸምበት መቅደስ ነበረው፤ ስለ መቅደስም አሠራር በዘጸ. ም. 25ና ም.26 ላይ፥ ቀጥሎም ከም.36 ጀምሮ እስከ ም. 39 ድረስ እናነባለን። መቅደሱ ባለ ሁለት ክፍል የሆነ የድንኳን ማደሪያ ነበር፤ ወይም በሁለት የተያያዙ ድንኳኖች የተሠራ እንደ ማደሪያ ያለ ነገር ነበር ልንል እንችላለን። (ዘጸ.25፡8-9፥ 26፡1)። ካህናት በውጭው መጋረጃ በኩል ገብተው ያገለገሉባት መጀመሪያይቱ ድንኳን (ወይም መጀመሪያይቱ የማደሪያ ክፍል) «ቅድስት» ትባል ነበር። በእርስዋ ውስጥ በስተ ደቡብ በኩል መቅረዝ፥ በስተ ሰሜን በኩል 12 የገጽ ኅብስቶች ያሉበት ጠረጴዛ ወይም ገበታ ነበረ። (ዘጸአ. 25፡31-39፥ 23-28፥ 30፤ ዘሌዋ. 24፡5-8) በቅድስት ውስጥ፥ ያውም በታቦቱ አንጻር፥ ጥዋትና ማታ ዕጣን ይታጠንበት የነበረ የዕጣን መሠዊያ ደግሞ ነበረ።(ዛጸአ. 30፡1-10) ድንኳንን ከድንኳን (ወይም ክፍልን ከክፍል) የሚለያይ ሁለተኛ መጋረጃ ደግሞ በውስጥ ነበረ፤ ከመጋረጃም ወዲያ የነበረችው ድንኳን ወይም ክፍል «ቅድስተ ቅዱሳን» ትባል ነበር። (ዘጸአ. 26፡31-33)። እግዚአብሔር የሚገኝበቱ ስፍራ ሆኖ ይህ ከሁሉ ይልቅ ቅዱስ ስፍራ ነበረ። በቅድስት ውስጥ እንደ ነበሩ ሁሉ እንዲሁም በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ የማገልገያ ዕቃዎች ነበሩ። የወርቅ ማዕጠንት ነበረ፥ የኪዳን ታቦት ነበረ። (ዘጸአ. 25፡10-22)። በኪዳን ታቦት ሣጥን ውስጥ 3 ነገሮች የቀምጠዋል፡- 1ኛ፥ የእስራኤል ነገዶች በምድረ በዳ ሳሉ የበሉት መና የተባለ ከሰማይ የወረደው ኅብስት የነበረበት መሶበ ወርቅ (ዘጸአ. 16፡12-15፤ 31-34)፥ 2ኛ ያቆጠቆጠች የአሮን በትር (ዘኁል. 17፡1-11)፤ 3ኛ፥ ብሉይ ኪዳን የተጻፈባቸው ሁለቱ የድንጋይ ጽላቶች። (ዘጸ. 32፡12፤ 23፡15-16፤ ዘዳ. 10፡1-2) በኪዳን ታቦት ላይም የስርየት መክደኛ ወይም «ማስተስሪያ» ነበር፥ የስርየት መክደኛውንም በክንፎቻቸው የሚጋረዱ ሁለት ኪሩቤል ነበሩ። (ዘጸአ. 25፡17-22)።

መቅደስ እንድትሆን በዚህ ዓለም ላይ የተሠራች ይህችው ድንኳን በሰማይ ያለችው የእውነተኛይቱ መቅደስ ምሳሌ ነበረች እንጂ ራስዋ ነዋሪ አልነበረችም። ደራሲው ዓይነተኛ ሐሳቡ በብሉይ ኪዳንና በአዲስ፥ በሌዊ ክህነትና በክርስቶስ፥ በሌዊ ካህናትና አገልግሎትና በክርስቶስ አገስግሎት መካከል ያለውን ልዩነትና በሁሉም በኩል የክርስቶስን መሻል ለማመልከት ነውና አሁን ስለተዘረዘሩት የማገልገያ ዕቃዎች እምብዛም መናገር አይፈልግም። ስለዚህ ወደ አገልግሎት ነገር፥ በተለይም ሁለቱ ዓይነት ማለት የሌዊ ካህናትና የክርስቶስ አገልግሎት የሚፈጽሙትን ነገር ወይም የሚያሳዩትን ጥቅም ወደ ማስረዳት አሁን ይመለሳል።

<u>ማስገንዘቢያ</u>፡-

ሀ) «ቅድስት» (ቁ. 2) በዚህ ቁጥር ላይ እንደምናየው ሁሉ «ቅድስት» የምትባለው የማደሪያ መጀመሪያ ድንኳን ናት። ይሁን እንጂ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ አንዳንድ ጊዜ፥ ማለት በቁ. 8፡12፡24፡25 ላይ፥ «ቅድስት» ሲባል «ቅድስተ ቅዱሳን» የምትባልዋን ሁለተኛይቱን ድንኳን፥ ወይም ውስጠኛውን ክፍል ማሰብ እንደሚገባን ግልጥ ነው። ለ) «የወርቅ ማዕጠንት» (ቁ. 4) መምህራን ይህን ለመተርጎም ይቸገራሉ፤ ምክንያቱም ርዝመቱ 1

ከንድ፥ ስፋቱም 1 ክንድ፥ ከፍታውም 2 ክንድ የሆነ፥ ገበታ መሳይ የሆነ፥ በብሉይ ኪዳን መቅደስ ውስጥ የነበረ የዕጣን መሠዊያ በቅድስት ውስጥ ቆሞአል እንጂ በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ አልቆመም። (ዘጸአ. 30፡6-7፤ 40፡5-26)። ደራሲው ግን እዚህ በዕብ.9፡4 ላይ በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ያቆመው ይመስላል። ይህን ነገር ለማስረዳት ልዩ ልዩ ሐሳቦች ቀርቦዋል። ይሁን እንጂ፥ ሌሎቹ ካህናት በየጊዜው ሁሉ ይጠቀሙባቸው የነበር የብረት ጥናዎች ሲኖሩ (ዘሌዋ. 10፡1፤ ዘሁል.16፡6) «በትልቁ በማስተስረያ ቀን ምን ሥርዓት ጊዜ ሊቀ ካህናት ልዩ የሆነ የወርቅ ጥና ይዞ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ይገባ ነበር» የሚል «ምሽና» የሚባል የአይሁድ የሕግ መጽሐፍ አለ። ይህም በዘሌዋ. 16፡12-13 ላይ ከተጻፈው ነገር ጋር ይስማማልና የእውነት ሳይሆን አይቀርም። ስለዚህ ሐዋርያው በዚህ ምዕራፍ ላይ የሚያስበው በተለይ ስለዚያ ስለ ማስተስረያ ቀን ሥርዓት ነውና፥ «በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ የወርቅ ማዕጠንት ነበር» ሲል ስለዚያ ስለ ሊቀ ካህናት ማዕጠንት ያሰበ ይመስላል። የሆነ ሆኖ ነገሩ የተጣራ አይደለም።

## ቁ. 6-10

6 ይህም እንደዚህ ተዘጋጅቶ ሳለ፥ ካህናት አገልግሎታቸውን እየፈጸሙ ዘወትር
በፊተኛይቱ ድንኳን ይገቡባታል፤ 7 በሁለተኛይቱ ግን ሊቃ ካህናት ብቻቸውን
በዓመት አንድ ጊዜ ይገቡባታል፤ እርሱም ስለ ራሱና ስለ ሕዝቡ ስሕተት
የሚያቀርበውን ደም ሳይዝ አይገባም፤ 8 ፊተኛይቱም ድንኳን በዚህ ገና ቆማ ሳለች፥
ወደ ቅድስት የሚወስደው መንገድ ገና እንዳልተገለጠ መንፈስ ቅዱስ ያሳያል።
9፥ 10 ይህም ለአሁኑ ጊዜ ምሳሌ ነው። እንደዚህም መባና መሥዋዕት ይቀርባሉ፤
እነዚህም እስከ መታደስ ዘመን ድረስ የተደረጉ፥ ስለ ምግብና ስለ መጠጥም ስለ
ልዩ ልዩ መታጠብም የሚሆኑ የሥጋ ሥርዓቶች ብቻ ናቸውና የሚያመልከውን
በሕሊና ፍጹም ሊያደርጉት አይችሉም።

በዚህ ምዕራፍ በቁ. 1 ላይ ደራሲው ስለ አገልግሎት ሥርዓትና የዚህ ዓለም ስለ ሆነው መቅደስ ተናግሮአል። ከቁ. 1 እስከ ቁ. 5 ድረስ የመቅደስን ነገር ሲያስረዳ ከቁ. 6 እስከ ቁ.10 ድረስ ስለ አገልግሎት ሥርዓት ይናገራል፤ በተለይም የሚያነሣው በዘሌዋ. ም. 16 ላይ የተጻፈውን እስራኤላውያን (ዕብራውያን) ከሁሉ ይልቅ ያከብሩት የነበረውን የማስተረያ ቀን ሥርዓት ነው። በአመት አንድ ጊዜ ብቻ በሚፈጸመው በዚያ ስርዓት ሊቀ ካህናቱ ለእስራኤል ሰዎች በሞላ ስለ ኃጢአታቸው ሁሉ ያስተሰርይ ነበር። (ዘሌዋ. 16፡33-34) ይሁን እንጂ፥ ሐዋሪያው በእነዚህ ቁጥሮች ላይ የሌዊ ካህናት አገልግሎት ከሚዳዊ ርኵሰት እንጂ ከውስጣዊ ኃጢአት ሊያነጻ አለመቻሉን ያስረዳል።

ከቁ. 1 እስከ ቁ. 5 ድረስ እንደ ተዘረዘረው ሁሉ መቅደሱ ተዘጋጅቶ ሳለ ተራ ካህናት በየጊዜው ሁሉ ወደ ቅድስት ይገቡ ነበር። ጥዋት መብራትን ሊያዘጋጁ ማታም ሊያበሩ፥ ጥዋትና ማታ ዕጣን ሊያጥኑ ቅዳሜ ቅዳሚም የገጽ ኅብስት ሊያኖሮና ሊለውጡ ይገቡ ነበር። (ዘጸአ. 27፡20-21፤ 30፡7-8፤ ዘሌዋ. 24፡8)። በሁለተኛይቱ ድንኳን ግን አይገቡም ነበር። የእርስዋ ነገር ልዩ ነው። ከሕዝብም ሆነ ከተራ ካህናት ወደዚያ የገባ ሰው የለም። ሊቀ ካህናቱ ብቻ ወደዚያ ይገባ ነበር፥ እርሱም የገባው በዓመት አንድ ጊዜ በማስተሰርያ ቀን ብቻ ነው። በዚያ ቀን ሊቀ ካህናቱ ለራሱና ለቤተሰቡ ኃጢአት ያሚሆነውን፥ በገዛ ገንዘቡ የተገዛውን አንድ ወይፈን፥ የእስራኤልም ሕዝብ ለእነርሱ ኃጢአት የሚሆኑትን ሁለት አውራ ፍየሎች ያቀርቡ ነበር። ሊቀ ካህናቱ አስቀድሞ የራሱን ወይፈን አርዶ (ም. 5፡3) ደሙን ይዞ ወደ መቅደሱ ውስጠኛው ክፍል ወደ ቅድስተ ቅዱሳን፥ ይገባና ደሙን በስርየቱ መክደኛ ላይና በፊቱም በጣቱ

ሰባት ጊዜ ይረጨው ነበር። ቀጥሎም ከመቅደሱ ወጥቶ ከሁለቱ አውራ ፍየሎች አንዱን ያርድና ደሙን ይዞ ተመልሶ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ገብቶ እንደዚሁ በመክደኛው ላይና በፊቱ ይረጨው ነበር። (ዘሌዋ. 16፡6-15)። ይህም የቅድስተ ቅዱሳን መንገድ ተወስኖ፥ ያለ ደምም መግባት የለም ማለት ነው። ሰው ሁሉ ሊገባ አልቻለም፤ ያለ ደምም የገባ ማንም የለም።

ይህ የአገልግሎት ሥርዓት ለሚመጣው ዘመን ምሳሌ ብቻ ነበር። ነዋሪ ነው ተብሎ አልታሰበም፤ ለጊዜው፥ እስከ መታደስ ዘመን፥ ማለት እስከ አዲስ ኪዳን ዘመን ብቻ ነበረ። እንደዚህ ሥርዓት የቀረቡ መባና መሥዋዕት አቅራቢዎችን በሕሊናቸው፥ ማለት በልባቸው ወይም በውስጥ ውስጣቸው፥ ፍጹም ሊያደርጉ አልቻሉም፤ ምክንያቱም የሥርዓቱ ጉዳይ ከምግብና ከመጠጥ ከገላም መታጠብ ጋር በመሆኑ (ዘሌዋ. ም. 11፤ ም. 14፤ ዘኍል. ም. 19) ሥጋን እንጂ ልብን ሊነካ አልቻለም።

<u>ማስገንዘቢያ</u>፡-

ሀ) «መንፈስ ቅዱስ ያሳያል» (ቁ. 8) መንፈስ ቅዱስ አሳይቶአል ሲባል ምን ማለት ነው? ቢሉ፥ ይህ ሥርዓት ሁሉ ለሙሴ የተሰጠው በመንፈስ ቅዱስ ነውና መንፈስ ቅዱስ እንደዚህ ሲያዝዝ ሁሉ እግዚአብሔር ወዳለበቱ ዘንድ የሚያደርስ መንገድ ገና እንዳልተከፈተ ያመለክታል ማለት ነው።

ለ) «ወደ ቅድስት የሚወስደው መንገድ ገና አልተገለጠም» (ቁ. 8) በቅድስትና በቅድስተ ቅዱሳን መካከል የነበረው መጋረጃ ወደ ውስጠኛው ክፍል መንገዱን ከለከለ። ያ መጋረጃ እስኪገለጥ ድረስ ወደ እግዚአብሔር ዘንድ መግባት የለም። የተገለጠው ክርስቶስ ለኃጢአታችን ሲሞት ነው። (ማቴ. 27፡51) ከዚያ ጊዜ ወዲህ በክርስቶስ የሚመጣ ማንም ሰው ሊገባ ይችላል። (ም. 10፡20፤ ዮሐ. 14፡6)

ሐ) «የሥጋ ሥርዓቶች ብቻ» (ቁ. 9፡10) እነኝህ ሥርዓቶች «የሥጋ ብቻ» የተባሉበት ምክንያት፡-1ኛ፥ መሥዋዕቶቹ እንስሶች እየሆኑ የምዋች ሥጋ ብቻ ነበሩ። 2ኛ፥ የመብልንና የመጠጥን የመታጠብንም ነገር፥ የሥጋን ነገር ብቻ ያስቡ ነበር። 3ኛ፥ ጥቅማቸው ለሚያመልከው ሰው ሥጋ ብቻ ነበር፥ ለመንፈሱ ምንም ሊያደርጉ አልቻሉም። መ) «የሚያመልከውን በሕሊና ፍጹም ሊያደርጉት አይችሉም» (ቁ. 9፡10) ሰው ወደ እግዚአብሔር ዘንድ ገብቶ ኅብረትን እንዲያገኝ የሚከለክል የረከሰ ሕሊና ነው። የክርስቶስ ደም የፈሰሰው ለእርሱ እንደሆነ ተገንዝቦ እግዚአብሔርን የሚያመልክ ማናቸውም ሰው ለሠራው ኃጢአት ሁሉ ይቅርታን እንደ ተቀበለ ያውቃል፤ ይሁን እንጂ፥ ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚሠራው ኃጢአት ሕሊናውን ያረክሰበታል፥ ሕሊናውም እንደረከሰ ስለሚሰማው ወደ እግዚአብሔር መቅረብና ኅብረትን ማግኘት የእግዚአብሔርንም ሕይወት መካፈል ይሳነዋል። ብዙዎች ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረትን የሚያጡ በዚህ ምክንያት ነው። የሚመኙቱ ዳዊት የተመኘውን ነገር ነው፥ እርሱም ንጹሕን ልብና የቀናውን መንፈስ ነው። (መዝ. 50፡10) እነኝህ የብሉይ ኪዳን ሥርዓቶች ይህን ሊሰጡ አይችሉም። ከዚህ ከሕሊና መርከስ ጋር የተያያዘ የደም ነገር ነው። ለሚመጣው ጊዜ ምሳሌ የሆነው የወይፈንና የፍየል ደም አስቀድሞ ከድንኳኒቱ ውጭ እንደ ፈሰሰ፥ ቀጥሎም በውስጥ እንደ ተረጨ ማስታወስ የሚገባን ነገር ነው። (ዘሌዋ. 16፡11፤14፤15) እንደ ምሳሌው እንዲሁም በእውነተኛው ነው። ጎልጎታ በሚባል ቦታ ላይ የክርስቶስ ደም ፈሰሰ፤ ያም ደም ለኃጢአታችን ይቅርታን አስገኘልን። ይቅርታን ካገኘን በኋላ ግን ሕሊናችን አንዳንድ ጊዜ

ይረክሳል። ይህ ሲሆን የክርስቶስ ደም በውስጥ፡ በልባችን ላይ ይረጭና ሕሊናችንን ከኃጢአት ርኩሰት ያነጻል። (1ኛ ዮሐ. 1፡7) እንዲሁም ኅብረትን ዳግመኛ እናገኛለን። ደሙ የፈሰሰው ለይቅርታ፣ የተረጨውም ለንጽሕና ነው። መፍሰሱ ወደ እግዚአብሔር ነው፤ መረጨቱ ወደ እኛ ነው። መፍሰሱ ከፍርድ፤ መረጨቱ ከርኩሰት ያድነናል። ከቁ. 11 እስከ ቁ. 14 ድረስ የምናገኘው ትምህርት ይህ ነው።

ቁ. 11-14

> [11] ነገር ግን ክርስቶስ ይመጣ ዘንድ ላለው መልካም ነገር ሊቃ ካህናት ሆኖ፥
> በምትበልጠውና በምትሻለው በእጆችም ባልተሠራች ማለት ለዚህ ፍጥረት
> ባልሆነች ድንኳን፥ የዘላለምን ቤዛነት አግኝቶ። [12] አንድ ጊዜ ፈጽሞ ወደ ቅድስት
> በገዛ ደሙ ገባ እንጂ በፍየሎችና በጥጆች ደም አይደለም። [13] የኮርማዎችና
> የፍየሎች ደም በረከሱትም ላይ የተረጨ የጊደር አመድ ሥጋን ለማንጻት የሚቀድሱ
> ከሆኑ፥ ነውር የሌለው [14] ሆኖ በዘላለም መንፈስ ራሱን ለእግዚአብሔር ያቀረበ
> የክርስቶስ ደም እንዴት ይልቅ ሕያውን እግዚአብሔርን ልታመልኩ ከሞተ ሥራ
> ሕሊናችሁን ያነጻ ይሆን?

ከቁ. 6 እስከ ቁ. 10 ድረስ ነገራቸው ተጽፎ ከተገኘው ከድሮ ሊቃነ ካህናት የክርስቶስ ነገር ምንኛ ይሻላል! እነርሱ በሚመጣ ዘመን ለሚሆነው ነገር ምሳሌ ብቻ ያገለገሉ ነበር (ቁ. 9፡10) ክርስቶስ ለዚያው፥ ራሱ እውነተኛ ለሆነው ነገር እያገለገለ ሊቀ ካህናት ሆኖአል። (ቁ. 11) እነርሱ የዚህ ዓለም በሆነው መቅደስና ለዚህ ፍጥረት በሆነችው ድንኳን ያገለግሉ ነበር (ቁ.1፡11) ክርስቶስ ግን በምትበልጠውና በምትሻለው ድንኳን፥ ማለት በሰማይ፥ ያገለግላል። (ቁ. 24) እነርሱ ተመላለሰው ወደ ቅድስት ይገቡ ነበር፥ ክርስቶስ ግን አንድ ጊዜ ለዘላለም ገብቶአል። እነርሱ ቢሞካከሩ እንኳ ሊያድኑ አልቻሉም፥ ክርስቶስ ግን የዘላለምን ቤዛነት አግኝቶአል። እነርሱ የእንስሶችን ደም ይዘው ይገቡ ነበር፥ ክርስቶስ በገዛ ደሙ ገብቶአል። (ቁ. 11፡12)

ይህ ሁሉ የሆነው በክርስቶስ ደም ክብር (ወይም ዋጋ) ምክንያት ነው። (1ኛ ጴጥ.1፡18-20) ምሳሌ በሆነው በብሉይ ኪዳን ሥርዓት የእንስሶች ደም ከኃጢአት፥ ደም የነበረበትም የጊደር አመድ ከርኩሰት እያነጻ ቅዱስ ከሆነ ሁሉ፥ ማለት ከመቅደስ አገልግሎትና ከተቀደሰ ሕዝብ ኅብረት፥ ተለይቶ የነበረውን ሰው ተመልሶ እንዲገባ ያስፈቅድ ነበር። (ዘሌዋ. ም. 4፤ ዘኍል. ም. 19) ያ ደም ካነጻና ሰውዬው ተመልሶ ገብቶ እግዚአግሔርን ሊያመልክና ኅብረትን ሊያገኝ የሚያስፈቅድ ከሆነ (በቂ ከሆነ)፥ የከበረ የክርስቶስ ደም እንዴት ይልቅ እግዚአብሔርን በአገልግሎታችን ልናመልክና በኅብረቱ ልንኖር ከኃጢአትና ከርኩሰት ውስጥ ውስጣችንን ሊያነጻ ይበቃ ይሆን! ለሕግ ያልተቻለው (ቁ. 9፡10) ለክርስቶስ ተችሎአል። (ቁ. 13፡14፤ ሮሜ 8፡3)

<u>ማስገንዘቢያ</u>፡-

ሀ) «የዘላለምን ቤዛነት አግኝቶ» (ቁ. 12) «ቤዛነት» የተባለው ቃል አንድን ባርያ ነፃ ለማውጣት የሚከፈለውን ገንዘብ ያመለክታል። በዚህ ረገድ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብፅ ባርነት ተቤዣቸው፤ እስራኤላውያንም ርስታቸውንና መኖሪያ ቤቶቻቸውን ይቤዡ ነበር። (ዘጸአ. 6፡6፤ 15፡13 ዘሌዋ. 25፡25-29) ኃጢአተኞች የኃጢአት ባርያዎች ናቸው እነርሱንም ነፃ ለማውጣት የሚከፈለው ዋጋ ሞት ነው። (ዮሐ. 8፡34-44፤ ሮሜ

6፡16-23) ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ዋጋ ከፈለና አርነት አወጣን። (ቁ. 15) ይህ ቤዛነት «የዘላለም ቤዛነት» ነው። የሌዊ ሊቀ ካህናት በማስተስረያ ቀን ባቀረበው መሥዋዕት እስከ 1 ዓመት ድረስ አስፈላጊውን ከፍሎ ይሆናል። መቸስ በእውነቱ መሥዋዕቱ ምሳሌ ብቻ ነበረና ለኃጢአት ሊከፍል አልቻለም። ይሁን እንጂ በዓመት በዓመት 1 ጊዜ ብቻ አቅርቦታልና እስከ 1 ዓመት ድረስ ይጠቅም ነበር ብንል አንስትም። የክርስቶስ መሥዋዕት ግን የዘላለም ቤዛነትን አግኝቶአል። ይህም ማለት የክርስቶስ ሥራ ለእርሱ እንደ ሆነ የሚቆጥረው ሰው ለዘላለም ድኖአል እንጂ ከቶ ሊጠፋ አይችልም። (ዩሐ. 10፡27-29) አንድ ልጅ አባቱን ሲበድለው እንደሚሆን ነገር ነው። በኃጢአቱ ምክንያት ኅብረቱ ይጠፋል እንጂ ልጅነቱ አይጠፋም።

ጌታ ይህን የዘላለምን ቤዛነት «አግኝቶአል» ሲባል ፈልጎ ተከታትሎ የደረሰበትና ያገኘው ማለት ነው። የተገኘ በቀላሉ አይደለም፤ ሊያገኘው ከሰማየ ሰማያት እስከ ጎልጎታ መሄድ ሆነበት።

ለ) «በገዛ ደሙ ገባ» (ቁ. 12) «የገዛ ደሙን ይዞ ገባ» አለማለቱን እስኪ አስተውሉ። በዱሮ ሥርዓት ሊቀ ካህናቱ የታረደውን የመሥዋዕቱን ደም ይዞ ወደ መቅደስ ይገባ ነበር። ክርስቶስ ግን ደሙን በጎልጎታ አፍስሶ ሲያበቃ በዚያ ደም መሠረት ወደ ሰማያዊ መቅደስ ገባ። « ደሙን ይዞ» ሳይል «በደሙ»፥ ማለት በደሙ ክብር መሠረት ወይም ምክንያት ይላል።

ሐ) «በዘላለም መንፈስ» (ቁ. 14) «በዘላለም መንፈስ» ሲል «በመንፈስ ቅዱስ» ማለቱ አይደለም። ለምን አይደለም? ቢሉ፥ «ጌታ በመንፈስ ቅዱስ ራሱን ለእግዚአብሔር አቀረበ» መባሉ መልካም ፍች አይሰጥምና። ራሱ ወልድ ነውና በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት እንዲያቀርብ ለምን ያስፈልጋል? አይደለም። ደራሲው ስለ መሥዋዕት መጻፉ ነው። ባለፉት ቁጥሮች ላይ ስለ እንስሶች፥ እነርሱም ሥጋ ብቻ ስለ መሆናቸው ተናግሮአል። አሁን ወደ ክርስቶስ ተዘውሮ ልዩነቱን ያመጣል። «እንስሶች ምዋች በሆነ ሥጋ ቀረቡ፤ ክርስቶስ ግን በዘላለም መንፈስ ቀረበ» እያለ ከአሁን ብዙ ጊዜ በፊት የጀመረውን ማነጣጠር ይቀጥላል። ክርስቶስ የሠዋው መሥዋዕት የእንስሶች፥ ወይም እንኳ የተራ ሰው መሥዋዕት ሳይሆን የመለኮት ባሕርይ ያለበት መሥዋዕት ነበረ፥ ያፈሰሰውም ደም የእንስሳ ወይም የተራ ሰው ደም ሳይሆን የእግዚአብሔር ሕይወት ያለበት ደም ነበረ። በም. 1 ላይ በተለይም እዚያ በቁ. 3 ላይ የተጻፈውን እስኪ እናስብ። ክርስቶስ በዚያ ላይ የተጻፈውን ሁሉ ነው እኮ! እንግዲያውስ የፈሰሰው ደም የወልደ እግዚአብሔር ደም ነበረ እንጂ የተራ ሰው ደም አልነበረም። እግዚአብሔር በክርስቶስ ነበረ፤ ክርስቶስም ከእመቤታችን ማርያም በተወለደ ጊዜ ከእኛ ጋር የነበረው እግዚአብሔር ነበር። በሥጋም የተገለጠው እግዚአብሔር ነበር። (2ኛ ቆሮ. 5፡19፤ ማቴ. 1፡22-23፤ 1ኛ ጢሞ. 3፡16) ኢየሱስ ከድንግል ተወለደ ለሚለው ትምህርት ኃይሉን አስገላጊነቱንም የሚሰጥ ይኸው ነገር ነው። ይህን ከተገነዘብን ከእነዚያ እንስሶች ደም ይልቅ የክርስቶስ ደም ምንኛ እንደሚከብር፥ ዋጋውም ምንኛ ከፍ እንደሚል ስንገምት እስከዚህ ድረስ ነው ማለት ከቶ አይቻለንም። እነዚያ እንስሶች በሚዳዊ ሰውነታቸው ነውር የሌላቸው ይሆኑ ይሆናል፥ ክርስቶስ ግን በውስጥ ውስጡ ስንኳ ነውር በፍጹም አልነበረውም። (ዘጸአ. 12፡5፤ ዘሌዋ. 22፡19-21፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡18፥19፤ 2፡22፤ 1ኛ ዮሐ. 3፡5) እንግዲያውስ የክርስቶስ ደም ምንኛ የከበረ ነው! የእንስሶች ደም ሥጋን ለማንጻት የሚቀድስ ከሆነ፥ የክርስቶስ ደም እንዴት ይልቅ ሕሊናችንን ያነጻ ይሆን?

መ) «ሊታመልኩ ያነጻል» (ቁ. 14) የምንነጻ እንድናገለግል ነው። (ዩሐ. 15፡2) በአማርኛችን «ሊታመልኩ» ተብሎ የተተረጎመ የግሪኩ ቃል «እያገለገለ ማምለክ» ማለት ነው። በማገልገል እናመልከዋለን። ሕይወት፥ «የዘላለም የተባለው ሕይወት፥ እውነተኛ ሕይወት፥ ደስታ የሞላበት ሕይወት፥ በእግዚአብሔር ፊት በኅብረት እየኖረ ማገልገል ነውና፥ ርኩሰትም ከዚያ ኅብረት ይለያልና፥ ርኩሰት ወደ አፍረትና ወደ መንፈሳዊ መካንነት ያደርሳል። የረከሰና ወቃሽ የሆነ ሕሊና እግዚአብሔርን ከማገልገል ይከለክላል። የረከሰ ሕሊና ኖሮት ወደ እግዚአብሔር ፊት የሚገባና በደስታ የሚያገለግል ማን ነው? ሉረ አይቻልም! ነገር ግን የክርስቶስ ደም ከዚያ ርኩሰት ሲያነጻን እንደ ገና ወደ ቅድስተ ቅዱሳን፥ ወደ እግዚአብሔር ፊት ገብተን ኅብረትን ልናገኝና እንደ ገና በደስታ ልናገለግለው እንችላለን፥ አገልግሎታችንም ፍሬያማ ይሆናል። በእግዚአብሔር ፊት እየኖርን እርሱን በማገልገል ከምናገኘው ደስታ የበለጠ ደስታ ከቶ የለም። አገልግሎታችንስ ምን ኖሮአል? ቢሉ የካህናት አገልግሎት ነዋ! ክርስቶስ ለአባቱ ካህናት እንድንሆን አደረገ። (ራእ. 1፡6፤ 5፡10) አገልግሎታችንም የዱሮ ካህናት ሥራ ሆኖ ሰውን ወደ እግዚአብሔር ማቅረብ ነው። ይሁን እንጂ የአዲስ ኪዳን ካህናት ነንና ሰውን ወደ እግዚአብሔር የምናቀርበው ሥጋዊ መሥዋዕትን በማቅረብ ሳይሆን ወንጌልን በማስተማር ነው። (ሮሜ 15፡16፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡5-9)

ሠ) «ከሞተ ሥራ» (ቁ. 14) ይህን ቃል ከዚህ በፊት በም. 6፡1-2 ላይ አግኝተነዋል። እዚያ ላይ ወደ ሞት የሚያደርስ ወይም ወደ ሕይወት ለማድረስ የማይችል ሥራ ነው ብለናል። እዚህ በም. 9፡14 ላይ መጀመሪያውን የሆነ ይመስላል። የጊደር አመድ ያለበት ውኃ በላዩ የተረጨ ሰው የሞተውን ነገር የነካ ሰው ነበረ። የሞተውን መንካት ሰውዮውንና የእግዚአብሔርን ማደሪያ ያረክስ ነበር። ሞት አረከሰ ማለት ነው። (ዘኁ. 19፡11-16) ሐዋርያው አሁን ወደ ዕብራውያን ሲጽፍ ይህ ነገር ትዝ ይለዋልና ሕሊናን የሚያረክስ ነገር «የሞተ ሥራ» ይለዋል። በቁ. 13 ላይ የተጠቀሰው የኮርማዎችና የፍየሎች ደም ሥጋን ከኃጢአት፥ የጊደር አመድ የነበረበትም ውኃ ሥጋን ከርኩሰት ያነጻ ነበርና ሐዋርያው አሁን «እንደዚሁ የክርስቶስ ደም ሥጋን ሳይሆን ሕሊናን ከኃጢአትና ከርኩሰት ያነጻል» ብሎ ደሙ እግዚአብሔርን ልናመልክ እንደሚፈታን ያስተምረናል።

ረ) «ሕሊናችሁን ያነጻል» (ቁ. 14) ይህን ስናነብ ሕሊናን ከልብ አንለይ። ሕሊና ከልብ መንጭቶ የልብ ስሜት ወይም የልብ ሐሳብ ነው። ደሙ በሕሊና ላይ ሲረጭ ልቡ ይነጻል። ም. 10፡22ን ተመልከቱ። መንጻትም ከይቅርታ (ከስርየት) የተለየ ነገር ነው። ስርየትና መንጻት ሁለት ነገሮች እንደሆኑ በቲቶ 2፡14ና ነ1ኛ ዩሐ. 1፡9 ላይ እናገኛለን። እንደዚሁም እዚህ በዕብ. 9፡14 ላይ ሐዋርያው የሚናገረው ስለ ሕሊናችን መንጻት ነው እንጂ ስለ ኃጢአታችን ስርየት አይደለም።

ሰ) ወቃሽ ሕሊና! ወቃሽ ሕሊና ክርስቲያንን ምንኛ ያስቸግርና ያሳዝነዋል! ቀኑን ከሥራ ሌሊቱን ከእንቅልፍ ይለየዋል። መጸለይ ሲሞክር፥ የክርስትና አገልግሎቱን ሲያዘጋጅ ያስቸግረዋል። ደስታን ከልቡ፥ ምስክርነትን ከአፉ ያሳጣዋል። በእግዚአብሔር ፊት በኅብረት በመኖር ፋንታ እፍረትና ፍርሃት ይይዘዋል። (መዝ. 31፡3-4፤ 50፤68) ሁኔታው ምንኛ አሳዛኝ ነው! ያን ሕሊና ያንንም ልብ ከኃጢአት ርኩሰትና ከእፍረት ስሜት የሚያነጻ የኢየሱስ ደም ብቻ ነው። (1ኛ ዩሐ. 1፡7) በእንዲህ ያለ ችግር የተቸገረ ክርስቲያን ከዛሬ ስንት ዓመታት በፊት ለይቅርታው የፈሰሰለትን ያን የክርስቶስ ደም አንሥቶ ልቡን

ይረጭበት ዘንድ «እርጨኝ፥ እጠበኝ!» ብሎ እግዚአብሔርን ይለምነው። (መዝ. 50፡7) ሰላምን የሚያገኝና ወደ ኅብረት ወደ ደስታኛም አገልግሎት የሚመለሰው ይህን ሲያደርግ ብቻ ነው። ሆኖም በእውነቱ ይህ ምሳሌ ብቻ ነው። የክርስቶስ ደም በመንግሥተ ሰማያት የለም፤ በጎልጎታ ፈሰሶ ከዚያ ቀረ። ይሁን እንጂ፥ ሕሊናችን የሚነጻው በዚያው ደም መሠረት ነው፥ በዚያውም ደም በማመን ነው። (የሐዋ. 15፡9) ሥራው የተፈጸመው በጎልጎታ ነው፥ በዚያንም ጊዜ ከኃጢአት ፍርድና ከርኩሰት ሁሉ ድነናል። ሆኖም እኛ ሰዎች በዚያ ደም የምንጠቀም አስፈላጊነቱን በምንረዳበት ጊዜና ቁጥር ነው። ወንድሜ ሆይ፥ ይህን ቁጥር 14 ተመልከት። የኢየሱስ ደም ሕያው እግዚአብሔርን አንተ ልታመልክ ሕሊናህን ያነጻል ይል የለምን? ይላል!

## ሁለተኛ ክፍል። ቁ. 15-28

### ቁ. 15-22

15 ስለዚህም የፊተኛው ኪዳን ሲጸና ሕግን የተላለፉትን የሚቤዥ ሞት ስለሆነ፥
የተጠሩት የዘላለምን ርስት የተስፋ ቃል እንዲቀበሉ እርሱ የአዲስ ኪዳን መካከለኛ
ነው። 16 ኑዛዜ ያለ እንደሆነ የተናዛዡን ሞት ማርዳት የግድ ነውና 17 ሰው ሲሞት
ኑዛዜው ይጸናልና ተናዛዡ በሕይወት ሲኖር ግን ከቶ አይጠቅምም። 18 ስለዚህም
ፊተኛው ኪዳን እንኳ ያለ ደም አልተመረቀም። 19-20 ሙሴም ትእዛዛትን ሁሉ
እንደ ሕጉ ለሕዝቡ ሁሉ ከተናገረ በኋላ፥ የጥጆችንና የፍየሎችን ደም ከውኃና
ከቀይ የበግ ጠጉር ከሂሶጵም ጋር ይዞ፡- እግዚአብሔር ያዘዘላችሁ የኪዳን ደም ይህ
ነው ብሎ በመጽሐፉና በሕዝቡ ሁሉ ላይ ረጨው። 21 እንዲሁም በድንኳኒቱና
በማገልገያው ዕቃ ሁሉ ደምን ረጨ። 22 እንደ ሕጉም ከጥቂቶች በቀር ነገር ሁሉ
በደም ይነጻል፥ ደምም ሳይፈስ ስርየት የለም።

ደራሲው በም. 8፡6 ላይ ኢየሱስ በሚሻል ተስፋ ቃል የተመሠረተ የሚሻል ኪዳን መካከለኛ እንደሚሆን ተናግሮአል፥ አሁንም ኢየሱስ የአዲስ ኪዳን መካከለኛ የሆነበትን ምክንያት ያስረዳል። ምክንያቱ፥ የተጠሩት የዘላለም ርስት የተስፋ ቃል እንዲቀበሉ» ነው። ይሁን እንጂ አዲስ ኪዳን እንዲገባና ኢየሱስ መካከለኛው እንዲሆን ኢየሱስ ይሞት ዘንድ የግድታ ሆነ፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ሕግ የሆነ የፊተኛው ኪዳን እንዲፈጸም አስፈላጊ ነበር። ብሉይ ኪዳን «ሕግ የተላለፈ ሰው ይሙት» ብሎ አዝዞ ነበርና ያ ኪዳን ጸንቶ ሳለ ሕግን የተላለፉት ሰዎች እንዳይሞቱ ታስበ እንደሆነ የሚቤዣቸው አንድ ሞት እንዲገኝ ተፈልጎአል። ክርስቶስ መጥቶ ተቤዣቸው፥ በመሞቱም ብሉይ ኪዳንን ፈጸመ። (ማቴ. 5፡17-18፤ ሮሜ 10፡4) እንግዲያውስ አዲስ ኪዳን ሊጸና እርሱም መካከለኛው ሊሆን ቻለ። ደራሲው «ርስት» የሚለው ቃል አሁን ጽፎ ነበርና ሐሳቡ ወደ ኑዛዜ ነገር ያልፋል፤ ይልቁንም ይህ የሆነው በአማርኛ «ኪዳን» እና «ኑዛዜ» የተባሉት ሁለቱ ቃሎች እርሱ በጻፈበቱ በግሪክ ቋንቋ በአንድ ቃል ብቻ ስለሚተረጎሙ ነው። የኑዛዜውንም ነገር ሲያስብ ልክ እንደ ኪዳን ነገር መሆኑን አስተውሎአል። ኪዳንም ሆነ ኑዛዜ የሚጸናው ሞት ሲሆን ወይም ደም ሲፈስ ብቻ ነውና፥ ደም ሞትን ያመለክታልና (ዘሌዋ. 17፡11) ብሉይ ኪዳን እንኳ ያለ ደም አልተመረቀም። በዘጸ. 24፡6-8 ና በዘጸ. 29፡12-21 ላይ የተጻፈው ታሪክ ይህን ይገልጣል። ሙሴ የጥጆችንና የፍየሎችን ደም ይዞ «ኪዳኑን የሚያጸና ደም ይህ ነው» ብሎ ሕጉ በተጻፈበት መጽሐፍና ሕጉን በተቀበሉት ሕዝብ ላይ፥ እንዲሁም በድንኳኒቱና በማገልገያው ዕቃ ሁሉ ላይ ረጨው፤ ኪዳኑም ጸና። ይህ

የደም መርጨት ሥርዓት የብሉይ ኪዳን ዋና ሥርዓት ነበረ። በውኃ ወይም በእሳት ከነጹት ከጥቂቶች ነገሮች በስተቀር (ዘሌዋ. 14:1-9፤ ዘኍል. 19:17-19፤ 31:22-24) ሁሉ በደም ይነጻ ነበር፥ ደምም ሳይፈስ ስርየትን ያገኘ አልነበረም።

<u>ማስገንዘቢያ</u>:-

ሀ) «የዘላለም ርስት የተስፋ ቃል» (ቁ. 15) ይህስ ምን ኖርአል? ቢሉ፥ ለአብርሃም የተሰጠው የተስፋ ቃል ነው። (በም. 6:11-12 ላይ የተጻፈውን ማስገንዘቢያ ለ) ተመልከት።) በዚህ ቃል ለአብርሃምና ለሥጋውያን ልጆቹ ከነዓን የተባለችው አገር ስትሰጥ ለእኛ ለመንፈሳውያን ልጆቹ የዘላለም ሕይወት ይሰጣል። ይህም «የዘላለም» የተባለው ሕይወት ማለት ከእግዚአብሔር ጋር በሕብረት እየኖርን የእግዚአብሔርን ሕይወት ተካፋዮች እንድንሆን ነው። እንዲሁም ሕይወታችን የበቃኝ ማለት የደስታና የኃይል ሕይወት ይሆናል፥ አገልግሎታችንም ፍሬያማ ይሆናል። ይህን የተስፋ ቃል ከዚህ በፊት አግኝተነዋል፥ ወደፊትም በም. 10:36ና በም. 11:13፥39 ላይ እናገኘዋለን። (በተለይ በገጽ 45 ላይ በማስገንዘቢያ መ) ውስጥ ስለዚህ ነገር የተጻፈውን ተመልከት።)

ይሁን እንጂ፥ ተስፋው ለዚህ ለምድራዊ ሕይወታችን ብቻ አይደለም፥ በዚህ ዓለም ላይ ሳለን በከፊል እናገኘዋለን። በድንግዝግዝም እናየዋለን። (1 ቆሮ. 13:9-12) ፍጹምነቱን፥ ሙላቱን፥ የምናገኝ በመንግሥተ ሰማያት ነው። በዚያን ጊዜ ወደ ተፈጠርንበት መልክና ምሳሌ ተመልሰን ከእርሱ ጋር ተቀምጠንና በፊቱ ኖረን የኅብረትን ሙሉ ጣዕም እናጣጥማለን። የምንጠባበቀው «አገር» ይኸው ነው። (ም. 11:14-16)፥ የደኅንነታችንን ማግር በፊት ለፊቱ የምናየው እዚያው ነው። ይህ የአሁኑ የዚያ የሚመጣውን ጥላ ወይም ምሳሌ ብቻ ነው። የወደፊቱ የተስፋችን ፍጹምነት ነው፥ እርሱም የክብር ተስፋ ይባላል። ዛሬ አለን፥ እዚያ ግን በእጥፍ እናገኘዋለን።

ለ) «የተጠሩት» (ቁ. 15) የተስፋ ቃል ሊቀበሉ የተጠሩት የአብርሃም ልጆች ናቸው። እላይ እንዳልነው ሁሉ ሥጋውያን ልጆቹ ከነዓንን፥ መንፈሳውያን ልጆቹ የዘላለምን ሕይወትና በዚያ ቃል ውስጥ ተጠቅልሉ የሚገኘውን ሁሉ ለመውረስ ተጠርተዋል። መንፈሳውያን ልጆቹ ክርስቲያኖች ናቸውና እኛ ሁላችን ከሰማያዊው ጥሪ ተካፋዮች ነን። (ዕብ. 3:1) የኢየሱስ ክርስቶስ ልንሆንና ቅዱሳን ለመሆን ተጠራን። (ሮሜ 1:6-7፤ 1ኛ ቆሮ. 1:2) በቅዱስ አጠራር ተጠራን። (2ኛ ጢሞ. 1:9) ወደ እግዚአብሔር ልጅ ወደ ጌታችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ኅብረት ተጠራን። (1ኛ ቆሮ. 1:9) ወደ መንግሥቱ ወደ ክብሩም ተጠራን። (1ኛ ተሰ. 2:12) የዘላለምን ርስት የተስፋ ቃል እንድንቀበል ተጠራን። (ዕብ. 9:15) አንባቢ ሆይ ተጠርተህ የለምን? ከተጠራህም ልትቀበል ቀርበሃልን? ታላቅና አስደሳች የሆነ ርስት እኮ ልትቀበል ተጠርተሃል። ችል ብለኸዋልን? ለዘላለም ሕይወት ከነበረከቱ ሁሉ ለመቀበል ተጠርተሃል። መቀበያም መንገድ ተከፍቶልሃል። ችል ትለዋለህን? እስኪ በል፥ የጳውሎስን ቃል ስማ። ሐዋርያው እንዲህ አለ:- «አንድ ነገር አደርጋለሁ፤ በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴም ወዳለው እየተጣጣርሁ፥ በክርስቶስ ኢየሱስ ከፍ ከፍ ያለውን የእግዚአብሔርን መጥራት ዋጋ እንዳገኝ እከታተላለሁ።» (ፊልጵ. 3:13-14) ወንድሜ ሆይ፥ እንዲህ አታደርግምን? በፊትህ እንደዚህ ያለ ታላቅ በረከት ሲኖር እስከ አሁን ድረስ ያገኘኸው ጥቂቱ ይበቃሃልን? አይብቃህ! የተጠሩት እኮ እንዲቀበሉ ነው፤ ስለዚህ ለመቀበል እንቅረብ ወደ ፍጻሜም እንሂድ። (ም. 6:1)

ሐ) «እግዚአብሔር ያዘዘላችሁ የኪዳን ደም ይህ ነው» (ቁ. 19-20) ሙሴ የጥጆችንና የፍየሎችን ደም ይዞ እንደዚህ ቢናገር እስራኤላውያን የብሉይ ኪዳንን ተስፋዎች ሁሉ ይወርሱ ዘንድ አረጋገጠላቸው። እንደዚህም ሁሉ የአዲስ ኪዳን ዋስና መካከለኛ የሆነ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር እራት ሲበላ ጽዋውን አንሥቶ «ይህ ስለ ብዙዎች የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ነው» ብሎ ክርስቲያኖች የአዲስ ኪዳን ተስፋዎች ይወርሱ ዘንድ አረጋገጠ። (ዘጸአ. 24፡6-8፤ ማር. 14፡24)

ክርስቶስ ኪዳኑን ሊያጸናልንና ለእርሱ የሆነውን ሁሉ፥ ማለት ያገኘልንን ሁሉ ሊያወርሰን ሞተ። መሞቱም አስፈላጊ ነበረ። ምክንያቱም ተናዛዡ ካልሞተ ወራሾቹ ሊቀበሉ አይችሉም።

መ) «ነገር ሁሉ በደም ይነጻል፥ ደምም ሳይፈስ ስርየት የለም» (ቁ. 22) በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ስለ ደም ነገር ብዙ እናነባለን። እዚሁ ላይ ከቁ. 12 ጀምሮ እስከ ቁ. 22 ድረስ ደም የተባለ ቃል 10 ጊዜ ተጽፎ ይገኛል። ክርስትናን እናስተምራለን ብለን ስለ ደም ባንናገር ማስተማራችን ጎዶሎ ነው። ስለ ደም ማስተማር ከሁሉ ይልቅ አስፈላጊያችን ነው።

ደም ያነጻል፥ ደምም የስተሰርያል። እነኝህ ሁለት ነገሮች ማለት መንጻትና ይቅርታ፥ በእኛ ዘንድ ልዩ ቢሆኑም ሁለቱም የሚሆኑ በዚያ ደም ነው። ክርስቶስ ደሙን ባፈሰሰ ጊዜ የኃጢአት ነገር በሞላ፥ ርኩሰቱንም ፍርዱንም፥ ፈጽሞአል። ያ ደም ስርየትን አስገኘልን፥ ያም ደም እንደ ተከፈተ ምንጭ ሆኖ ከኃጢአትና ከርኩሰት ሁሉ ያለማቋረጥ ያነጻናል። (ዘካ. 13፡1)

## ቁ. 23-28

23 እንግዲህ በሰማያት ያሉትን የሚመስለው ነገር በዚህ ሊነጻ እንጂ በሰማያት ያሉቱ ራሳቸው ከእርሱ ይልቅ በሚበልጥ መሥዋዕት ሊነጹ የግድ ነበረ።
24 ክርስቶስ በእጅ ወደ ተሠራች፥ የእውነተኛይቱ ምሳሌ ወደምትሆን ቅድስት አልገባምና፥ ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት ስለ እኛ አሁን ይታይ ዘንድ ወደ እርስዋ
ወደ ሰማይ ገባ። 25 ሊቀ ካህናትም በየዓመቱ የሌላውን ደም ይዞ ወደ ቅድስት
እንደሚገባ፥ ራሱን ብዙ ጊዜ ሊያቀርብ አልገባም፤ 26 እንዲህ ቢሆንስ፥ ዓለም
ከተፈጠረ ጀምሮ ብዙ ጊዜ መከራ ሊቀበል ባስፈለገው ነበር። አሁን ግን በዓለም
ፍጻሜ ራሱን በመሠዋት ኃጢአትን ሊሽር አንድ ጊዜ ተገልጦአል። 27 ለሰዎችም
አንድ ጊዜ መሞት ከእርሱ በኋላም ፍርድ እንደ 28 ተመደበባቸው እንዲሁ ክርስቶስ
ደግሞ፥ የብዙዎችን ኃጢአት ሊሸከም አንድ ጊዜ ከተሠዋ በኋላ፥ ያድናቸው ዘንድ ለሚጠባበቁት ሁለተኛ ጊዜ ያለ ኃጢአት ይታይላቸዋል።

በእነዚህ ቁጥሮች ላይ የደራሲው ሐሳብ ከቁ. 6 ጀምሮ እስከ ቁ. 10 ድረስ እንደ ተጠቀሰው ወደ ማስተስረያ ቀን ሐሳብ ይመለሳል። በማስተስረያ ቀን ሊቀ ካህናቱ መቅደሱንና የመገናኛው ድንኳንን መሠዊያውንም ከሕዝብ ርኩሰት ለማንጻት የወይፈንንና የፍየልን ደም ይዞ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ይገባ ነበር። (ዘሌዋ. 16፡14-22) ይህን ያደረገው ኅብረትን ለመመለስ ነው። በሕዝብ ርኩሰት ምክንያት በእግዚአብሔርና በእስራኤል መካከል ኖሮ የነበረው ኅብረት ተቋረጠ፤ ያም ኅብረት የሚመለስ ከሆነ ደም እንዲፈስና የሕዝቡ ኃጢአት እንዲሰረይ ያስፈልግ ነበር። ሊቀ ካህናቱ የሞት ምልክት የሚሆነውን ደም ይዞ ወደ መቅደስ ገብቶ ያን ደም ቢረጭ የእግዚአብሔር መኖሪያ ከሕዝብ ርኩሰት ነጻ፥ ኅብረትም ሊመለስ ቻለ።

በቁ. 22 ላይ ሐዋርያው በብሉይ ኪዳን ዘመን የተገኙ ምሳሌዎች ነገሮች ማለት በሰማያት ያሉትን የሚመስሉት ነገሮች፥ ሊነጹ የጥጆች (የወይፈኖች) እና የፍየሎች ደም የግድ ነበር

ብሎአልና አሁን በቁ. 23 ላይ እነዚያ ምሳሌዎች ነገሮች በዚያ ደም ከነጹ እውነተኞቹ ነገሮች ከዚያ በሚበልጥ መሥዋዕት፥ ወይም በሚሻል ደም፥ ሊነጹ የግድ ነው ይላል። ምክንያቱም፡- 1ኛ፤ ክርስቶስ የገባው ወደሚሻል መቅደስ ነውና፤ 2ኛ፤ ክርስቶስ የሠራው ሥራ ለበለጠ ዘመን ስለሚጸና ነው።

የሊቀ ካህናቱ ሥራ ዝቅተኛ ነበረና ዝቅተኛ ደም በቂ ሆኖአል። እርሱ ምሳሌ የሆነውን ደም ይዞ መሳሌ ወደ ሆነችው ቅድስተ ቅዱሳን ገብቶ ለአንድ ዓመት የሚሆን ምሳሌ ኅብረትን አገኘ። ክርስቶስ በአይሁድና በብሉይ ኪዳን ዘመን ፍጻሜ ላይ ም. 1፡2፥ ገላ. 4፡4) ራሱን መሥዋዕት አድርጎ፥ በዚያ ደም ክብር መሠረት ወደ እውነተኛይቱ ቅድስት ወደ ሰማያት ገብቶ ለዘላለም የሚሆን እውነተኛ ኅብረትን አገኘልን። የገባውም ከርኩሰት ለማንጻት ብቻ ሳይሆን ኃጢአትን ሁሉ በሁሉ ለመሻር ነው። የሚበልጥ መስዋዕት፥ የሚሻል ደም፥ የግድ የሆነው በዚህ ምክንያን ነው። በሰዎች ዘንድ ሞት ፍጻሜ ነገር ነው። ከዚያ ወዲያ ወደ ፍርድ መሄድ እንጂ ወደ ዓለም ተመልሶ መጥቶ ዳግመኛ መሞከር የለም። በክርስቶስ ዘንድ ነገሩ እንደዚሁ ነው። እርሱ አንድ ጊዜ ከተሠዋ በኋላ የኃጢአትን ጉዳይ ሊያነሣ ተመልሶ አይመጣም፤ መሞቱ ፍጻሜ ነገር ነበር። ሊቃነ ካሃንቶቹ ያደረጉትን እርሱ አያደርግም። እነርሱ ወደ መቅደስ ይገቡና ጉዳዩን በሚመጣው ዓመት ሊደገሙ ተመልሰው ይወጡ ነበር። አልጨረሱምና ሁለተኛ ጊዜ ሊሞክሩ ወጥተዋል። ክርስቶስ ግን የሠራው ሥራ ሞትን መስሎ ፍጻሜ ነገር ነበርና ኃጢአትን ጉዳይ ሊያነሣ አይመለስም። ሥራው ተፈጸመ (ዩሐ. 19፡30) ጉዳዩ አለቀ። እርግጥ ነው፤ ክርስቶስ ከሞት እንደተነሣ እንዲሁም ሰው ከሞት ይነሣል። ቢሆንም ሰው የሚነሣው ሊፈረድበት ነው፤ ክርስቶስ ግን የተቤዡትን ወደ ተዘጋጀላቸው ሙሉ መዳን ሊያደርስ ይገለጣል።

<u>ማስገንዘቢያ</u>፡-

ሀ) «የግድ ነበር» (ቁ. 23) ስለምን የግድ ነበረ? ቢሉ፥ የግድ የሆነበት ምክንያት እግዚአብሔር እንዲያው ይቅር ሊል ስለማይችል ነው። መሀሪና ይቅር ባይ ይሁን እንጂ ጻድቅና ቅዱስ ነውና ኃጢአትን መጥላቱን እንዲያሳይና ተገቢ ፍርድን እንዲፈርድበት የግድ ያስፈልጋል። ኃጢአት እንዲሰርይ የግዴታ ነው፥ የሚሰረይም በደም ነው፤ እግዚአብሔርም ይቅር እንዲለን ይህን ዋጋ ለአያንዳንዳችን ከፍሎአል። (ሮሜ 3፡26፤ 1ኛ ዩሐ. 2፡12፤ 3፡16)

ለ) «በእግዚአብሔር ፊት ስለ እኛ አሁን ይታይ ዘንድ» (ቁ. 24) ኢየሱስ እዚያ ያለው «ስለ እኛ» ነው። (ም.2፡9፤ ሮሜ 8፡34) ምሳሌነታችን ነው። የሥቃዩ ምልክቶች በከበረ ሰውነቱ ታይተው ሳሉ (ራእ. 5፡6) በእግዚአብሔር ፊት ስለ እኛ ይታያል። ሰው ሆኖ ስለ ሰው ተቀምጦአል፤ በታውንም ስለ ሰው ይዞአል። እግዚአብሔር እርሱን ሲያይ እኛን የሚነሣ ይመስላልን? (ም. 7፡25) ኧረ አይመስልም! የዱሮ ሊቀ ካህናት ወደ እግዚአብሔር ፊት ሲገባ እንዳይሞት ዕጣንን ይዞ የጢስ ደመና ያስነሣ ነበር (ዘሌዋ. 16፡12-13)፥ ኢየሱስ ግን ባቀረበው መሥዋዕት እግዚአብሔርን ከሰው ጋር አስታርቆአልና የጢስ ደመና አያስፈልገውም። መንግሥተ ሰማያት ስፍራ ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊ አኗኗር ነውና፥ ኢየሱስም እዚያ ያለው «ስለ እኛ» ነውና፥ እርሱ በአባቱ ፊት በሚኖርበት ሞገስና ኅብረት እኛም ተደስተን እንድንኖር መንገዱ አሁን ተገልጦአል። (ቁ. 8) ሰው በዚያ በመንግሥተ ሰማያት ሕይወት (አኗኗር) ይኖር ዘንድ ሊቀ ካህናታችን ተቀምጦአል። ዋና የመልእክቱ ትምህርት ይህ ነው፥ ሊቀ ካህናችን የሚያደርሰን ወደዚህ ነው።

ሐ) «ኃጢአት ሊሽር» (ቁ. 26) በቁ. 22 ላይ ደም እንደሚያስተሰርይ እናያለን። እዚሁ ላይ ግን የክርስቶስ ደም ኃጢአትን እንደሚያስተሰርይ ብቻ ሳይሆን ፈጽሞ እንደሚሽረው እናያለን፤ ይህን «መሻር» የተባለውን ቃል በም.7፡18 ላይ አግኝተነዋል። ሥልጣኑንና ኃይሉን አስወግዶ ከቶ እንዳልኖረ ማድረግ ማለት ነው። የኃጢአት ቃል (ክስ) ከእንግዲህ ወዲህ ኃይል የለውም፤ በእርሱም ምክንያት በሰው ላይ አይፈረድም። በሰው ዘንድ ተሽሮአል (ሮሜ 8፡3-4)፥ በእግዚአብሔርም ዘንድ ተሽሮአል። እንደ ተከፈለ ዕዳ ሆኖ ተዘንግቶአል፤ ዛሬ ኃጢአት አይቆጠርብንም። (መዝ. 31፡2) ኢየሱስ ራሱን በመሠዋት ኃጢአትን እንደ ሻረ ስናምን መንፈስ ቅዱስ በእኛ ዘንድ በእውነት እንደተሻረ ያረጋግጥና «ኃጢአት አይገዛችሁም» የሚለውን የተስፋ ቃል ያወርሰናል። (ሮሜ 6፡14)።

መ) «አንድ ጊዜ» (ቁ. 26) አንድ ጊዜ ብቻ ኃጢአትን ሊሽር መገለጡ ያቀረበው መሥዋዕት ለዘላለም የሚበቃና ፍጹም መሆኑን ያስረዳል። እንዲደገም አያስፈልግም። በዚህ ነገር በርትተን እናስብ። ለሌላ መሥዋዕት ቦታ ከቶ የለም፥ ክርስቶስ ሁሉን ፈጽሞአል። የተሠራ ኃጢአት ሁሉ የሚሠራም ሁሉ የሚሰረይ በዚያ በአንዱ መሥዋዕት መሠረት ነው። የኃጢአት ጉዳይ ባላለቀ ኖሮ የካህናት አለቃ በየዓመቱ መሥዋዕትን ባቃረበው ምሳሌ ክርስቶስ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ብዙ ጊዜ መከራ ሊቀበል ባስፈለገው ነበር። ይሁን እንጂ ክርስቶስ የሞተው አንድ ጊዜ ብቻ ነው። አንድ ጊዜ ብቻ በመሞቱም ኃጢአት ሁሉ፥ ያለፈውና ያሁኑ የሚመጣውም፥ በዚያ አንድ መሥዋዕት እንደ ተሰረየ እንረዳለን። ኃጢአትን የሚሰርይ ደም ብቻ ነውና (ቁ. 22) የኢየሱስ መሥዋዕት ከአዳም ዘመን ጀምሮ እስከ ዕለተ ስቅለት ድረስ የተሠራውን ኃጢአት ብቻ በሰረየ ኖሮ ከዚያ ዕለት ወዲህ የተሠራውን ኃጢአት ይሰረይ ዘንድ እንደ ገና እንዲሞት ባስፈለገው ነበር። ዳግመኛ አልሞተም፥ አይሞትምም። (ቁ. 28) ስለ ኃጢአት አንድን መሥዋዕት ለዘለዓለም አቅርቦአል። (ም. 10፡12) ደሙ ለኃጢአት ሁሉ ለዘመንም ሁሉ በቅቶአል።

ሠ) «የብዙዎችን ኃጢአት ሊሸከም» (ቁ. 28) ደራሲው በኢሳ. 53፡12 ላይ የተጻፈውን የሚጠቅስ ይመስላል። «የብዙዎችን» እንጂ «የሁሉንም» አለመጻፉ በምን ምክንያት ነው? ቢሉ፡- እርግጥ ነው፥ እግዚአብሔር የሁላችንን በደል በኢየሱስ ላይ አኖሮአል። (ኢሳ. 53፡6)፤ ሆኖም እንዳንዶች ሰዎች ኃጢአታቸውን በሌላ ዓይነት ሊያደራጁ ይወዳሉ። ኢየሱስ ራሱን ለሁሉም ቤዛ ሰጥቶአል። (1ኛ ጢሞ. 2፡6)፤ ይሁን እንጂ፥ የሠራው ሥራ የሚጸና ለተቀበለው ወይም ላመነበቱ ሰው ብቻ ነው። (ዮሐ. 1፡11-12፤ 3፡36፤ 1ኛ ጢሞ. 4፡10)። ክርስቶስ አስፈላጊውን ሁሉ አድርጎአል፤ ቢሆንም፥ ሰው ያን ሥራ የሚቀበለው በፈቃዱ ነው እንጂ በግድ አይደለም። ሰው ካልወደደ ሥራው አይጸናለትም። ውልን የመሰለ ነገር ነው። ዉሉ ለሁሉም ሲሆን የሚጸናለት ፊርማውን ለሚጨምርበት ብቻ ነው። «የብዙዎችን ኃጢአት ተሸከመ» የተባለው በዚህ ምክንያት ነው።

ረ) «ለሚጠባበቁት» (ቁ. 28) እነኝህስ እነማን ናቸው? ቢሉ፥ የሚጠባበቁቱ አማኞች ክርስቲያኖች በሞላ ናቸው እንጂ በአንዳች ልዩ አጠባበቅ የሚጠባበቁት ጥቂቶች ክርስቲያኖች ብቻ አይደሉም። (ሮሜ 8፡19፥23፥25፤ 1ኛ ቆሮ. 1፡7፤ 1፡52-58፤ ፊል. 3፡20-21፤ ገላ. 5፡5፤ 1ኛ ተሰ. 4፡17)

ሰ) «ያለ ኃጢአት» (ቁ. 28) ክርስቶስ በዚያ ጊዜ የሚመጣው «ያለ ኃጢአት» ነው፤ ማለት የሚመጣው የኃጢአትን ጉዳይ ሊያነሣ አይደለም። የኃጢአትን ጉዳይ በመሞቱና በመነሣቱ

ጩርሶአል፤ አሁን የሚያነሣው የደኅንነትን ነገር ነው። የሚመጣው ለሚጠባበቁት የመዳንን ፍጻሜ ለማውረስ ነው፥ እርሱም ማለት የሰውነታቸውን ቤዛ የሆነውን ልጅነት ሊሰጣቸውና ወዳዘጋጀላቸው ስፍራ ሊወስዳቸው ነው። (ሮሜ 8፡23፤ ዮሐ. 14፡3)

ሸ) «ይታይላቸዋል» (ቁ. 28) በዚህ ክፍል (ቁ. 23-28) ላይ ክርስቶስ 3 ጊዜ ተገልጦ እንደሚታይ እናነባለን። መጀመሪያ፥ ኃጢአትን ሊሽር ከእመቤታችን ሲወለድ ተገልጧል። (ቁ. 26) ሁለተኛ፥ በእግዚአብሔር ፊት ስለ እኛ ይታያል። (ቁ. 24) ያድናቸው ዘንድ በሚጠባበቁት ይታይላቸዋል። ይህ ሦስተኛ መገለጡ፥ ማለት ዳግም ምጽአቱ ከሁሉ ይልቅ የተረጋገጠ ነገር ነው። ራሱ ኢየሱስ ከመሞቱ በፊትና ከመሞቱ በኋላ (ቁ. 28) «እመጣለሁ» ብሎአል። (ዮሐ. 14፡3፤ ራእ. 22፡20)፤ መላእክት «ይመጣል» አሉ። (የሐዋ. 1፡11)፤ ሐዋርያትም «ይመጣል» አሉ። (ቲቶ 2፡13) ታላቁ የቤተ ክርስቲያን ተስፋ ነው። ይሁን እንጂ፥ ያ ቀን ለአማኞች ክርስቲያኖች ለደኅንነት ሲሆን ለቀሩቱ ሁሉ ለፍርድ ይሆናል። አንባቢ ሆይ፥ ያ ቀን ለአንተ የትኛው ይሆን ይሆን? ለደኅንነትን ወይስ ለፍርድ? ክርስቶስ በሕይወትህ ዘመን እንደ ተወደደ ባልንጀራ ተቆጥሮ ይመጣልህ እንደሆነ (መኃ. 5፡9-16) የታላቅ ክብርና የደስታ ቀን ይሆንልሃል። በሕይወትህ ዘመን እንደ ተናቀና እንደ ተጠላ እንግዳ ተቆጥሮ (ኢሳ. 53፡3) ይመጣብህ እንደሆነ ግን የሚያስፈራ የፍርድ ቀን ይሆንብሃል። ለዚያ ቀን ተዘጋጅተሃልን? ያልተዘጋጀህ እንደሆነ ሁለተኛ ጊዜ መጥቶ ሲገለጥ በእርሱ ፊት እንዳታፍር (1ኛ ዮሐ. 2፡28) ዛሬውኑ ተመልሰህ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቅ። (2ኛ ቆሮ. 5፡20፤ 6፡1-2)።

# ምዕራፍ አሥር

## (የኢየሱስ አገልግሎት የተሻለ ነው።)

### የሚሻለውን መሥዋዕት ስላቀረበ

የኢየሱስ አገልግሎት ከሌዊ ካህናት አገልግሎት የሚሻልበቱ ደግሞ በመሥዋዕቱ ነው፤ ይህም የዚህ ምዕራፍ መጀመሪያ ክፍል ትምህርት ነው። (ቁ. 1-18) ይህም ክፍል የዶክትሪን (የመልእክቱ ዓይነተኛ ትምህርት) መጨረሻ ክፍል ነው፤ ከዚህ በኋላ፥ ከቁ. 19 ጀምሮ እስከ መልእክቱ ፍጻሜ ድረስ የምናገኘው ሊቀ ካህናቱ ክርስቶስ የሆነለት ሰው እንዴት መኖር ወይም መመላለስ እንደሚገባው ነው።

እነዚያ የዱሮ መሥዋዕቶች ምንም ቢደጋገሙ ቢበዙም ኃጢአትን ሊያስወግዱ አልቻሉም፤ የክርስቶስ አንዱ መሥዋዕት ግን የዘላለም ፍጹማን አድርጎናል። ይህ ነገር እንደሚሆን እንደ ሆነም የሚያስረዱ 3 ምስክሮች አሉ፤ እነርሱም የዳዊት ትንቢት የክርስቶስ መቀመጥና የመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት ናቸው። (ቁ. 1-18) በዚህ ክፍል ውስጥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ፥ የክርስቶስን ሥራ፥ የመንፈስ ቅዱስንም ምስክርነት እናገኛለን።

ይልቁንም በምዕራፉ ሁለተኛ ክፍል (ቁ.19-39) የምናገኘው እግዚአብሔር ወዳለበቱ ዘንድ እንድንቀርብና ሳናፈገፍግ በእምነታችን እንድንጸና ማደፋፈሪያ ምክር ነው። በምክሩ መካከል ሐዋርያው 4ኛውን የማስጠንቀቂያ ክፍል አግብቶ ሰው በገዛ ፈቃዱ ክርስቶስን እንደ መካድ የሚመስለውን ኃጢአት ቢሠራ ምን ያለ ፍርድ እንደሚቆየው እያስረዳ በብርቱ ብርቱ ቃል ያስጠነቅቃል። የሚያስጠነቅቀው ግን ለመጽናት ሊያደፋፍር ነውና ዕብራውያንን የቀድሞውን መጽናታቸውንና የወደፊት ክብራቸውን እያሳሰባቸው በማደፋፈሪያ ምክር ምዕራፉን ይዘጋል።

### ቁ. 1-4

> 1 ሕጉ ሊመጣ ያለው የበጎ ነገር እውነተኛ አምሳል ሳይሆን የነገር ጥላ አለውና፥ ስለዚህም በየዓመቱ ዘወትር በሚያቀርቡት በዚያ መሥዋዕት የሚቀርቡትን ሊፈጽም ከቶ አይችልም። 2 እንደዚያማ ባይሆን የሚያመልኩት አንድ ጊዜ ነጽተው ከዚያ በኋላ በሕሊናቸው ኃጢአትን ስላላወቁ ማቅረብን በተዉ አልነበረምን?
> 3 ነገር ግን በዚያ መሥዋዕት በየዓመቱ የኃጢአት መታሰቢያ አለ፤ 4 የኮርማዎችና የፍየሎች ደም ኃጢአትን እንዲያስወግድ የማይቻል ነውና።

የምዕራፉ መለያያ ቁጥር እንደ ገና አስቸግሮናል። ሐዋርያው መልእክት (ደብዳቤ) ይጽፋልና ሐሳቡ የተከታተለ ነው። እዚህ በም. 10 መጀመሪያ ላይ ደርሲው ወደ አዲስ ሐሳብ ሳይዘል የም. 9ን ሐሳብ ይቀጥላል። እንዲያውም ቁ. 1 የም. 9፡28 ተቀጣይ ነው። በም. 9 ላይ የብሉይ ኪዳንን ምሳሌዎች ከክርስቶስ ከእውነተኞቹ ነገሮች ጋር ሲያነጻጥር ነበር። «የማስተስረያ ቀን መሥዋዕት በየዓመቱ ሲቀርብ የክርስቶስ አንድ ጊዜ ብቻ ቀርቦአል» አለ። አሁንም ሕጉ (ኦሪት) ከእውነተኛው ነገር ጋር ፍጹም ትክክለኝነት ሳይኖረው ምልክቱን ብቻ ስላሳየ ራሱ ወደ ፍጻሜ ለማድረስ አለመቻሉን ያስረዳል። ሕጉ አመልክቶአል እንጂ አልፈጸመም። ለዚሁም ማስረጃ የሚሆን የሕዝብ ዘወትር መሥዋዕትን ማቅረብ ነው። እነዚያ መሥዋዕቶች የታሰበውን በእውነት ከፈጸሙና የሕዝብንም ሕሊና ካነጹ እነርሱን የሚያቀርቡቱ ካቀረቡ ወዲያ ርኩስነታቸው ባልተሰማቸውም ነበርና ማቅረብን በተዉ ነበር። አልተዉምና አለመንጻታቸው ታውቆአል። ይህም ይቅርና ራሱ ሕጉ «መሥዋዕቶቹ በዓመት በዓመት

ይቅረቡ» በማለቱ በእውነቱ አለመፈጸማቸውን ገልጦአል። (ዘሌዋ. 16፡29፥ 30፥ 34) ሕዝቡ በየዓመቱ ሁሉ ኃጢአታቸው ይሰማቸው ነበር፤ የማስተሰርያም ቀን ሥርዓት አሳሰባቸው እንጂ ከቶ ኃጢአታቸውን አላዘነጋቸውም። ምክንያቱም፥ የእንስሶች ደም ኃጢአትን ሊያስወግድ አይችልምና። (ም. 9፡9-10) የእንስሳ ደም የሰውን ኃጢአት እንደምን ይከፈል? አይቻልም።

<u>ማስገንዘቢያ፡-</u>

ሀ) «ሕጉ ሊመጣ ያለው የበጎ ነገር እውነተኛ አምሳል ሳይሆን የነገር ጥላ አለውና»። (ቁ. 1) በአዲስ ኪዳን ዘመን የመጣው በጎ ወይም እውነተኛ ነገር ያደረገውን ሕጉ ሊያደርግ አልቻለም ማለት ነው። ሕጉ እውነተኛውን ነገር መሰሎአል እንጂ ከእርሱ ጋር ሁለመናው ትክክል አልነበረም። ለምሳሌ፥ በሕጉ ምሳሌ ብዙዎች ሊቃነ ካህናቱ ነበሩ። በእውነተኛው ግን አንድ ብቻ ነበር። በሕጉ፥ ሊቀ ካህናቱ ለራሱ ኃጢአት ማቅረብ ነበረበት፤ በአዲስ ኪዳን ማለት በእውነተኛው ግን ሊቀ ካህናቱ ኢየሱስ ለራሱ መቅረብ የለበትም። በብሉይ ኪዳንም መሥዋዕቶቹ ብዙ ነበሩ። በእውነተኛው ግን መሥዋዕቱ አንድ ብቻ ነው። ከዚህም የምንማረው አንድ ነገር አለ። ይኸውም በብሉይ ኪዳን ምሳሌዎችም ሆነ ክርስቶስ በተናገራቸውም ምሳሌዎች ዘንድ ጥቃቅኑ ነገር ሁሉ የሚተረጎም እንዳይደለ ነው። ምሳሌዎቹ የተሰጡት ወይም የተነገሩት ጠቅላላውን ነገር ለማስረዳት (ለማሳየት ወይም ለማመልከት) ሲሆን እኛ በእነዚያ ምሳሌዎች ውስጥ የሚገኙትን ታናናሽ ነገሮች በገዛ ራሳችን መተርጎም አይገባንም። ራሱ መጽሐፍ ቅዱስ የሚተረጉማቸውን ነገሮች ሁሉ ልናምን እንችላለን፤ የቀሩት፥ የሰው ልብ ወለድ የሆኑት ነገሮች ሁሉ ግን ከሃይማኖት አይቆጠሩም።

ለ) «መፈጸም፥ መንጻት፥ ኃጢአትን ማስወገድ» (ቁ. 1፡2-4) እነኚህ 3 ነገሮች የአንድ ነገር ልዩ ልዩ ደረጃዎች ናቸው። ኃጢአት ሲወገድ ሰው ይነጻል፥ የነጻም ሰው ወደ እግዚአብሔር ዘንድ ሊገባ ፈጽሞ ተገቢና ቻይ ነው። (ይህን ከም. 2፡10ና ከም. 5፡9-10 ጋር አነጣጥሩ) በቁ. 10 ላይም «ተቀድሰናል» የሚለው ቃል በዚህ ዓይነት ነው። ወደ እግዚአብሔር ፊት ሊገባ የተፈጸመ ሰው ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ነው። (1ኛ ጴጥ. 2፡9)

ሐ) «በዚያ መሥዋዕት በየዓመቱ የኃጢአት መታሰቢያ አለ» (ቁ. 3) እንደ አንድ ቢልቃጥ መድኃኒት ያለ ነገር ነው። መድኃኒቱ በሽተኛውን ፈውሶት ቢሆን ኖሮ መጠጣቱን በተወ ነበር፤ አልተወምና በሽታ ገና እንዳልደረበት ታውቆአል። ይህም ብቻ ሳይሆን፥ ቢልቃጢቱን በተመለከተ ቁጥር በሽታው ይታወሰዋል። እንደዚሁም እነዚያ የማስተስረያ ቀን መሥዋዕቶች ኃጢአታቸውን ያሳስቡዋቸው ነበር፤ የክርስቶስ መሥዋዕት ግን ከቀረበበት ጊዜ ውዲያ የኃጢአት መታሰብ የለም። (ቁ. 17)

## ቁ. 5-10

5 ስለዚህ ወደ ዓለም ሲገባ፡- መሥዋዕትንና መባን አልወደድህም ሥጋን ግን
አዘጋጀህልኝ፤ በሙሉ በሚቃጠል መሥዋዕትና 6 ስለ ኃጢአት በሚሠዋ መሥዋዕት
ደስ አላለህም። 7 በዚያን ጊዜ፡- እነሆ፤ በመጽሐፍ ጥቅልል ስለ እኔ እንደ ተጻፈ፥
አምላኬ ሆይ፥ ፍፈቃድህን ላደርግ መጥቼአለሁ አልሁ ይላል። 8 በዚህ ላይ፡-
መሥዋዕትንና መባን በሙሉ የሚቃጠል መሥዋትንም ስለ ኃጢአትም የሚሠዋ
መሥዋዕትን አልወደድህም በእርሱም ደስ አላለህም ብሎ፥ እነዚህም እንደ ሕግ
የሚቀርቡት ናቸው፥ 9 ቀጥሎ፡- እነሆ አምላኬ ሆይ፥ ፈቃድህን ላደርግ

መጥቼአለሁ ብሎአል። ሁለተኛውን ሊያቆም የፊተኛውን ይሽራል። [10] በዚህም ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋ አንድ ጊዜ ፈጽሞ በማቅረብ ተቀድሰናል።

በብሉይ ኪዳን መሥዋዕቶች የክርስቶስ መሥዋዕት እንደ ተተካና እነርሱ ሊያደርጉ ያልቻሉትንም የክርስቶስ አንዱ መሥድዋዕት እንደደረገ የሚያስረዳ የብሉይ ኪዳን ምስክርነት እነሆ! የኮርማዎችና የፍየሎች ደም ኃጢአትን እንዲያስወግድ የማይቻል ስለሆነ (ቁ. 4) ክርስቶስ ቀድሞውንም በዳዊት አፍ በመዝ. 39፡6-8 ላይ ሲናገር «በእነርሱ ፋንታ እኔ ተተክቻለሁ» ይላል። እነዚያ የብሉይ ኪዳን መሥዋዕቶች ጉዳዩን ሊፈጽሙ አልቻሉምና እግዚአብሔርን አላስደሰቱም ልቡንም አላጠገቡም። የእግዚአብሔር ፈቃድ ኃጢአት እንዲወገድ ስለዚህም ሰው ነጽቶ ተፈጽሞ ለእርሱ እንዲቀደስ ነበር። እነዚያ መሥዋዕቶች መንገዱን አሳዩ እንጂ ሥራውን ሊሠሩ አልቻሉምና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሳይፈጽሙ ቀሩ፤ እግዚአብሔርም በመሥዋዕቶቹ ዳስ አላለውም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ «ኃጢአትን የሚያስወግድ ይመጣል» ተብሎ በቃልና በምሳሌ በልዩ ልዩ በኩል ተጠቅሶ ነበርና ጊዜው ሲደርስ ክርስቶስ መጣ። (ዘጸአ. 12፡10-13፤ ዘኁል. 21፡8-9፤ ዘዳ. 18፡15-18፤ ዮሐ. 5፡46፤ 12፡41፤ ገላ. 4፡4-5) በመዝሙረ ዳዊት በተጠቀሰው በታ ላይ የክርስቶስ ሥልጣን ሊቆም ሕጉ፥ ብሉይ ኪዳን፥ እንደሚሻር ተመልክቶአል። ኢየሱስ ነፍሱን መሥዋዕት በማድረጉ ኃጢአትን አስወግዶአል፥ ይህንም በማድረጉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ፈጽሞአል። (ኢሳ. 53፡10፤ ዩሐ. 1፡29) እንግዲያውስ፥ የእርሱ ሥጋ መሥዋዕት ሆና ቢቀርብ እኛ ተቀድሰናል። በእግዚአብሔር ፊት አድንገባ ፈጽሞ ተገቢዎች ተደረግን ማለት ነው። (ም. 9፡13፥14)

ማስገንዘቢያ፡-

ሀ) «ሥጋን አዘጋጀህልኝ» (ቁ. 5) ክርስቶስ ከሥላሴዎች አንዱ ስለ ሆነ እርሱ ከጥንት ከዘላለም ነው። ወደ ዓለም ከመምጣቱ በፊት ከአብ ጋር ነበረ። (ዮሐ. 1፡1-2) በእግዚአብሔር ሕግ ኃጢአትን የሚያስተሰርይ ሞት ብቻ ነውና ክርስቶስ ኃጢአትን የሚያስወግድ ከሆነ ይሞት ዘንድ እንዲሞትም ሥጋ ይዘጋጅለት ዘንድ፥ ያስፈልግ ነበር። ስለዚህ «ቃል ሥጋ ሆነ» (ዮሐ. 1፡14) ከዕለታት አንድ ቀንም ከዘላለም የነበረው ከእመቤታችን ማርያም ተወልዶ ወደ ዓለም መጣ. (ገላ. 4፡4)

ለ) «በመጽሐፍ ጥቅልል» (ቁ. 7) የዱሮ መጻሕፍት እንደ ዛሬ መጽሐፎቻችን ሳይሆኑ በብራና ወይም በደንገል እየተሠሩ ረዥም የሆኑ የተጠቀለሉ ጥቅልሎች ነበሩ። ጽሕፈቱ በዓምድ በዓምድ ይጻፍና እንደ ተፈለገው መጠን ብራና ወይም ደንገል እየተቀጣጠለ ይጨመርና ዳር ዳሩን ይሰፋ ነበር። መጽሐፉ ሲያልቅ ሁለቱ ዳሮቹ፥ መጀመሪያውና መጨረሻው፥ ክብ በሆኑ በሁለት እንጨቶች ይታሰሩና መጽሐፉ ይጠቀለል ነበር።

## ቁ. 11-14

[11] ሊቀ ካህናትም ሁሉ ዕለት ዕለት እያገለገለ ኃጢአትን ሊያስወግዱ ከቶ የማይችሉትን እነዚያን መሥዋዕቶች ብዙ ጊዜ እያቀረበ ቆሞአል፤ [12] እርሱ ግን ስለ ኃጢአት አንድን መሥዋዕት ለዘላለም አቅርቦ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ፥ [13] ጠላቶቹም የእግሩ መረገጫ እስኪደረጉ ድረስ ወደፊት ይጠብቃል። [14] አንድ ጊዜ በማቅረብ የሚቀደሱትን የዘላለም ፍጹማን አድርጎአቸዋልና።

ትንቢይ ላይ ነው። ነቢዩ የአዲስ ኪዳንን የተስፋ ቃሎች ሲገልጥ በፍጻሜው ላይ «ኃጢአታቸውንና ዓመፃቸውንም ደግሜ አላስብም» ብሎ የጌታን ቃል ይጠቅሳል። (ኤር. 31፡31-34) እግዚአብሔር የማያስባቸው በፍጹም ቢወገዱ ነው፤ ከተወገዱም መሥዋዕት ስለ እነርሱ ማቅረብ ምን ያሻል? የክርስቶስ መሥዋዕት ኃጢአት የተባለውን ነገር በሙላ አስወግዶአልና ከእንግዲህ ወዲህ መሥዋዕት አያስፈልግም። ይህ በእውነት የመልእክቱ 2ኛ ክፍል መጨረሻ ነው። ከእንግዲህ ወዲህ የምናገኘው «የአማኞች አመላለስ» ክፍል ነው።

<u>ማስገንዘቢያ፡-</u>

ሀ) «መንፈስ ቅዱስ ስለዚህ ይመሰክርልናል» (ቁ. 15) ይህን በቁ. 17ና 18 ላይ የተጠቀሰውን ቃል የጻፈው ነቢዩ ኤርምያስ ሲሆን ወደ ዕብራውያን የሚጽፈው ደራሲ «መንፈስ ቅዱስ እንዲህ ብሎ ይመሰክርልናል» ይላል። ይህም መገንዘብ የሚገባን ነገር ነው። ነቢያት የጻፉአቸው ቃሎች የመንፈስ ቅዱስ ቃሎች ነበሩ፤ ወይም ደግሞ፥ መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ በኩል ጽፎአል ልንል እንችላለን። ይህም የሆነው ነቢያት በምንላቸው ዘንድ ብቻ አይደለም። ሙሴ «እግዚአብሔር እንዳስተምራችሁ ያዘዛት ትእዛዝና ሥርዓት ፍርድም ይህች ናት» ብሎ ኦሪትን በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተናገረ መስክሮአል። (ዘዳግ. 6፡1-2) በዚህም በዕብራውያን መልእክታችን ውስጥ እግዚአብሔር በዳዊት አፍ እንደተነገረ አግኝተናል። (ም. 4፡7፤ 10፡5-7) መጽሐፍ ቅዱስ የሰው ቃል ሳይሆን የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ ማስተዋል የሚገባን ነገር ነው። (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ 2ኛ ጴጥ. 1፡20-21፤ 1ኛ ተሰ. 2፡13)

ለ. «ከዚህ ወዲህ ስለ ኃጢአት ማቅረብ የለም» (ቁ. 18) «መሥዋዕት አያስፈልግም» መባሉን ሰምታችኋልን? ተገንዝባችሁታልን? እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያው በቅዱስ ጳውሎስ አፍ ሲናገር «ከዚህ ወዲህ ስለ ኃጢአት ማቅረብ የለም» ብሎአል። «ከዚህ ወዲህ» ሲል ጊዜው ከመቼ ጀምሮ ነው? ክርስቶስ አንዱን መሥዋዕት ካቀረበበት ቀን ወዲህ ነዋ! እኛሳ? ገና ዛሬ ልናቀርብ እናስባልንን?

## ቁ. 19-25

19፤20 እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ በመረቀልን በአዲስና በሕያው መንገድ ወደ
ቅድስት 21 በኢየሱስ ደም በመጋረጃው ማለት በሥጋው በኩል እንድንገባ ድፍረት
ስላለን በእግዚአብሄርም ቤት ላይ የሆነ ታላቅ ካህን ስላለን፥ ከክፉ ሕሊና ለመንጻት
ልባችንን 22 ተረጭተን ሰውነታችንንም በጥሩ ውኃ ታጥበን በተረዳንበት እምነት
በቅን ልብ እንቅረብ፤ 23 የተስፋን ቃል የሰጠው የታመነ ነውና እንዳይነቃነቅ
የተስፋችን ምስክርነት እንጠብቅ፤ 24 ለፍቅርና ለመልካምም ሥራ እንድንነቃቃ
እርስ በርሳችን እንተያይ፤ 25በአንዳንዶችም ዘንድ ልማድ እንደሆነው
መሰብሰባችንን አንተው፥ እርስ በርሳችን እንመካከር እንጂ፤ ይልቁንም ቀኑ
ሲቀርብ እያያችሁ አብልጣችሁ ይህን አድርጉ።

ሐዋርያው ታላቁ የክርስቶስ ሊቀ ካህንነት ትምህርት የተጻፈበትን የመልእክቱ 2ኛውን ክፍል ጨርሶአል፥ እነዚህም ቁጥሮች «እንግዲህ እንቅረብ» በማለታቸው በ1ኛ የመልእክቱ ክፍል መጨረሻ ላይ ከተጻፉት ጋር ይመሳሰላሉ። (ም. 4፡14-16) እዚህ ላይ ሐዋርያው ያስረዳቸውን ሁሉ በአጭሩ እያስታወሳቸው ከመጀመሪያ ጀምሮ ዓላማው የነበረውን ነገር አንደገና በዕብራውያን አንባቢዎቹ ፊት ያኖረዋል። ክርስቶስ ሊሠልና በክርስቶስ ያገኙትን ሀብት

ሊገልጥላቸው ጥሮአል፤ (ገላ. 3፡1) ይህንስ ያደረገው የሚደፍሩበትንና የሚመኩበትን ተስፋ እስከ መጨረሻው አንጽተው እንዲጠብቁ ለማደፋፈር ነበር። (ዕ. 3፡6፥14) ዕብራውያን ወደ ኋላ ወደ ይሁዳዊ ሃይማኖት፥ ሊያፈገፍጉ ከጅለዋል፥ ሐዋሪያውም ክርስቶስንና በክርስቶስ የምናገኘውን ሁሉ ከገላለጠ በኋላ «እንግዲህ .... እንቅረብ» ይላል። በዚህም በመልእክቱ 3ኛ ክፍል ላይ መደፋፈሪያንና ማስጠንቀቂያን እያፈራረቀ ሊያጸናአቸው ይሞክራል።

«እንግዲያውስ እንቅረብ» በዚያ በከበረ በኢየሱስ ደም መሠረት (ዕ. 9፡12-14፤ ኤፌ.2፡13፡18) ይከለክል በነበረው መጋረጃ በኩል ወደ እግዚአብሔር ፊት የምንገባበት መንገድ አሁን ስለ ተገለጠ (ዕ. 9፡8) በሙሉ መተማመን እንቅረብ። እንድንቀርብ የሚፈቅድልንም ያ ደም ብቻ ሳይሆን በልዑል እግዚአብሄር ቤት ላይ ተሾሞ የሚያቀርብ ታላቅ አጋፋሪ፥ ኢየሱስ፥ ስላለን ነው፤ ስለዚህ ሕሊናችንን በሚያነጻ በመሥዋዕቱ ደም ልባችንን ተረጭተን (ዕ. 9፡14)፥ አገራችንንም ከርኩስ አካሄድ ሁሉ በሚያነጻ ውኃ ታጥበን (ዮሐ. 13፡10)፥ ደጆ ሰላሙንና መድረኩን አልፈን እግዚአብሔር ወዳለበቱ፥ ወደ ቅድስት፥ በማይነቃነቅ እምናትና በእውነተኛ ልብ (ዮሐ. 4፡24) እንቅረብ። በክርስቶስ ለተገኘ ተስፋችን መስክረናልና፥ ያንም ተስፋ የሰጠን የማይዋሽ ነውና (ዘኁል. 23፡19፤ ማቴ. 24፡35)፥ ከምስክርነት ቃላችን ትንሽራትተን አናፈገፍግ፥ ዳሩ ግን ራሳችንን ብቻ ሳንመለከት ሌሎችን ደግሞ ለፍቅርና ለመልካም ሥራ እንድንቀሰቀስ እንመልከታቸው። ይልቁንም ይህም ማድረግ የሚመችን አንድ ላይ ስንሰበሰብ ነውና ከመሰብሰብ አንቅር፤ የምንሰበሰበው በፊታችን ያለው ጊዜ አጭር እንደ ሆነ በተለይ ስለ ተገነዘብን ነው።

<u>ማስገንዘቢያ</u>፡-

ሀ) «በመረቀልን» (ቁ. 19፡20) መንገዱ የተከፈተው፥ በንጉሥ ወይም በሌላ ባለ ሥልጣን ሲሆን አዲስ መንገድ፥ ለምሳሌ በድልድይ ላይ ወይም በከተማ ውስጥ እንደሚከፈተው ነው። ይህም መከፈት «መመረቅ» ይባላል። ይህ ወደ ቅድስት የሚወስደው መንገድ የተመረቀው ወይም የተከፈተው ከላይ የቆመው እግዚአብሔር ያን ይከለክል የነበረው መጋረጃ ከሁለት ሲቀደው ነበረ። (ማቴ. 27፡51)

ለ) «በአዲስና በሕያው መንገድ» (ቁ. 19፤20) መንገዱ ክርስቶስ ነው። (ዮሐ. 14፡6) መንገዱ «አዲስ» የተባለበቱ በመታደስ ዘመን ስለ ተከፈተ ነው። (ዕ. 9፡8-10) «ሕያው» የተባለበቱም ሊቀ ካህነቱ ይረግጥ የነበረው መንገድ ሕይወት የሌለበት መድረክ ሲሆን የዛሬ ምእመን የሚቀርብበት በህያው ክርስቶስ ስለ ሆኔ ነው። ደግሞ፥ ሊቀ ካህናቱ ይቀርብበት የነበረው መንገድ ለሌላ ሰው የሞት መንገድ በሆነ ነበር፤ ዳሩ ግን በክርስቶስ የሚሄድ ማንኛውም ሰው ሕይወትን ያገኛል።

ሐ) «በመጋረጃው ማለት በሥጋው» (ቁ. 19፤20) ሰው ወደ እግዚአብሔር ዘንድ እንዳይገባ የከለከለው ኃጢአት ያደረበቱ ሥጋው ነበረ። ይህን እንቅፋት ለማስወገድ ክርስቶስ ሥጋ ለበሰ። (ዕ. 10፥5፤ ዮሐ. 1፡14፤ ሮሜ 8፡3-4።) ይሁን እንጂ፥ ከድንግል ማርያም በመወለዱ ምክንያት ሥጋው ንጹሕ ቅዱስም ሥጋ ነበረ። ይህም ቅዱስ ሥጋውን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርጎ ሲያቀርብ፥ ማለት ሥጋው በጎልጎታ በተቆረሰ ጊዜ (1ኛ ቆሮ. 11፡24) ከልካዩ መጋረጃ ተቀደደና መንገዱ ተከፈተ። ስለዚህ የምንገባው «በመጋረጃው ማለት በሥጋው» ነው።

መ) «ድፍረት ስላለን» (ቁ. 19፤20) በልብ መተማመን ላይ የተመሠረተ ድፍረት ነው። የእግዚአብሔር ወልድ ሕይወት ያለበትን ደም ስናይና ያ ደም የፈሰሰው ስለ እኛ ኃጢአት መሆኑን ስንረዳ «ይበቃል፥ እግዚአብሔር ይቀበለናል!» ብለን በድፍረት እንቀርባለን።

ሠ) «ስላለን .... ስላለን»› (ቁ. 19፤ 20፤ 21)˜˜˜ አለንና በንብረታችን መጠቀም ይገባናል። አለንና እንቅረብ። (ቁ. 22) አለንና እንጠብቅ። (ቁ. 23) አልንና እንተያይ። (ቁ. 24) በእምነት እንቀርባለን፥ በተስፋ እንጠብቃለን፥ ለፍቅርም እንተያያለን።

ረ) «በእግዚአብሔር ቤት ላይ የሆነ ታላቅ ካህን» (ቁ. 21) ይህ ቤት ሞላ የምእመናን ቤት ሊሆን ይችላል (ም. 3:6) ዳሩ ግን ደራሲው እዚህ ላይ ስለዚያ ሰማያዊ መቅደስ ወይም ስለ እውነተኛይቱ ድንኳን የሚናገር ይመስላል። (ም. 8:1-2፤ ም. 9:24) በዚህ ቤት ላይ እንደ መልከ ጼዴቅ የሆነ ታላቅ ካህን አለ።

ሰ) «ከክፉ ሕሊና ለመንጻት ልባችንን ተረጭተን ሰውነታችንንም በጥሩ ውኃ ታጥበን» (ቁ. 22) ሐዋርያው ወደ ቤተ መቅደስ ስለ ገቡት ስለ ብሉይ ኪዳን ካህናት ያስባል። እነኚህ ካህናት በተካኑበት ጊዜ በደም ይረጩና በውኃ ይታጠቡ ነበር። (ዘጸ. 29:4፤ 20:21፤ ዘሌዋ. 8:6፤30) ደግሞ፥ ወደ ቤተ መቅደስ ከመግባታቸው በፊት 1ኛ፤ በመሠውያ (በደም)፥ 2ኛ፤ በመታጠቢያ ሰን (በውኃ) ማለፍ ያስፈልጋቸው ነበር። (ዘጸ. 30:17-22፤ ዘሌዋ. 16:4) በዚህ መሠረት እኛም ዛሬ እግዚአብሔር ወዳለበቱ ወደ እውነተኛ መቅደስ ልንገባ ብንወድ 1ኛ፥ ከክፉ ሕሊና ለመንጻት በዚያ በክርስቶስ ደም ልባችን እንዲረጭ (ም. 9:14)፥ ማለት ያ ደም ከኃጢአት ሁሉ እንዲያነጻን መተማመን፥ እና ሰውነታችን በጥሩ ውኃ እንዲታጠብ፥ ማለት አካሄዳችንን ከሚያርክስ ሁሉ ማንጻት ያስፈልገናል። የምንገባ እንደሆነ ንጹሕ ልብ ንጹሕም አካሄድ ያሻናል። የደም መረጨት በእግዚአብሔር ዘንድ መበጀታችንን፥ የውኃ መታጠብ በሰው ዘንድ መበጀታችንን ያሳስባል። አስቀድመን በደሙ ማንጻት እንተማመናለን፥ ቀጥሎም የምንሄድባቸውን ስፍራዎችና የምንተባበራቸውን ጓደኞች የእረፍት ጊዜአችንንም የምናሳልፍባቸውን ጨዋታዎች መርምረን ተመራምረን አካሄዳችንን በሁሉ ንጹሕ እናደርገዋለን፤ ከዚያም በኋላ እንገባለን።

ሐዋርያው «ጥሩ ውኃ» ሲል የሚናገርበቱ ስለ ጥምቀት ነው የሚሉ ሰዎች አሉ። ይህማ ይቻላል፤ ሆኖም ሐዋርያው የሚጽፍላቸው ሰዎች ክርስቲያኖች፥ እንዲሁም የተጠመቁ ስለ ሆኑ ክርስቲያንም ወደ እግዚአብሔር ሲቀርብ መጠመቅ ስለሌለበት፥ ሐዋርያው የሚናገረው ሥጋንና መንፈስን ከሚያረክስ ሁሉ ራሳችንን እንድናነጻ ይመስላል። (2ኛ ቆሮ.7:1) ወደ እግዚአብሔር ልንቀርብ ብንወድ ከኃጢአት ሁሉ እንድንርቅ በእውነቱ ያስፈልገናል። በቁ. 26 ላይ የተጻፈውም ቃል ይህን ትርጉማችንን የሚደግፍ ይመስላል።

ሸ) «በተረዳንበት እምነት» (ቁ. 22) እንዲህ ያለ ነገር፥ እንዲህም ያለ ስፍራ እንዳለልን በጽኑ እምነት ማመን ያስፈልግናል። በጥርጥር ወደ የትም አንደርስም። (ም. 11:6፤ ያዕ. 1:6-8) በዚያ በፈሰሰው ደም ክብር (ዋጋ) ብቃትና በዚያ በታላቁ ክህን ችሎታ ማመን ያስፈልገናል። የደሙን ዋጋ ወይም የካህኑን ሥልጣን የሚጠራጠር ሰው ወደ ተነገረለቱ ግብ ከቶ አይደርስም። እምነትስ በደሙና በካህኑ እንዲሆን ያስፈልጋል እንጂ በሌላ ቢሆን አያደርስም። አንባቢ ሆይ፥ አንተው በዚያ ደምና በዚያ ካህን መሠረት ልትቀርብ እንደምትችል የተረጋገጠ ጽኑ እምነት አለህን?

ቀ) «እንቅረብ» (ቁ. 22) ይህ ታላቁ የመልእክቱ ትምህርት ነው፥ ባለፉት ምዕራፎች ውስጥ የተጻፈውም ሁሉ ወደዚህ ዓላማ ሊያደርሰን ተጽፎአል። «እንቅረብ!» ለአንድ ዕብራዊ ሰው ሐሳቡ ምንኛ ግሩም ነው! ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ያስፈራ የለምን? አሪት «ኃጢአትን እንዳይሸከሙ እንዳይሞቱም የእስራኤል ልጆች ወደ መገናኛው ድንኳን አይቅረቡ» ብሎ የለምን? (ዘኁ. 18፡22) ያዛ የሚባልም ሰው ታቦትን ቢነካ አልሞተምን? (2ኛ ሳሙ. 6፡6-7) ካህን አልነበረም እንጂ ንጉስ የሆነ ዖዝያን ገብቶ ዕጣን ቢያጥን ለምጻም ሆኖ የለምን? (2ኛ ዜና 26፡16-21) ሊቃነ ካህናትስ፥ በዓመት በዓመት ወደ እግዚአብሔር ፊት ሲገቡ እውጭ የቆመው ሕዝብ ሁሉ «ይሞት ይሆንን?» በማለት እጅግ በጣም ይፈራ አልነበረምን? አሁንም ሐዋርያው «እንቅረብ» ይላል! ምድራዊ ካህን በመካከል ሳይኖር ኃጢአተኛ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ፥ የልቡን በእግዚዘብሔር ፊት መናገር (1ኛ ሳሙ. 1፡15) በእግዚአብሔርም ዘንድ እንደ ወዳጅ መኖር፥ ይህስ በእውነት ድንቅና ግሩም የሆነ ሐሳብ ነው! ይህንስ በማድረግ ምን ያለ አንዋንዋር ለዕብራውያንና ለእኛ ተሰጥቶአል! ሄኖክ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ እግዚአብሔርንም ደስ አሰኘ (ዘፍጥ. 5፡22-24፤ ዕብ. 11፡5)፤ እኛም እንዲሁ እናደርግ ዘንድ ተጋበዝን። የዚህ መልእክት ደራሲ «ያን ደም ያንም ታላቅ ካህን እያያችሁ በድፍረት ቅረቡ» ይለናልና እንደነዚያ አሥሩ ለምጻሞች ሆነን በሩቅ እየቆምን «ማረን፥ አቤቱ፥ ማረን» ሳንል (ሉቃ. 17፡12-13) እግዚአብሔር በዚያ በክቡር ደም ምክንያት ቀድሞ እንደ ማረን ተገንዝበን፥ ልዩ በሆነ የእግዚአብሔር ፈቃድና ትእዛዝ በተሾመው አጋፋሪ ካህን እጅ ተይዘን፥ ወደ ጸጋው ዙፋን በድፍረት እንቅረብ። መንገዱ ክፍት ነው፤ እግዚአብሔርም «ቅረቡ» ይለናል። አንቀርብምን? እንቅረብና ከቶውንም ከዚህ በፊት ያወቅን ከሆነ እጅግ በበለጠ አንዋንዋር እንኑር።

በ) «እንዳይነቃነቅ የተስፋችንን ምስክርነት እንጠብቅ» (ቁ. 23)። በእኛ ስላለ ተስፋ፥ ራሱ እግዚአብሔር ስለ ሰጠን ተስፋ፥ መስክረን ይሆናል፤ አሁን እንዳይነቃነቅ የተስፋችንን ምስክርነት እንጠብቅ። (1ኛ ጴጥ. 3፡15፤ ዕብ. 3፡6) እዚህ ላይ ሸቦ የተገተረበት የምሰሶ ሥዕል አለን። ያ ምሰሶ በመሬት ውስጥ ተተክሎአል፤ ሸቦው ግን ይስበውና ከመሠረቱ ያስለቅቀዋል። በልባቸው ወደ ግብፅ እንደ ተመለሱ እንደ እስራኤላውያን ያለ ነገር ነው። ከግብፅ ባርነት ቢድኑም የግብፅ ነገር ገና ይስባቸው ነበር። (የሐዋ. 7፡39፤ ዘኁል. 11፡5፤ 14፡3-4) ወደ ፊት እንዳይሄድ ወደ ኋላ የሚስብ ነገር አለ ማለት ነው። እንደዚሁ እነኝህ ዕብራውያን በጽኑ ፈተና ምክንያት ከክርስትና መሠረት ተነቃንቀው ወደ ኋላ፥ ወደ አይሁድ ሥርዓት፥ ለመመለስ ተሳቡ። ስለዚህ ሐዋርያው «እንዳይነቃነቅ የተስፋችንን ምስክርነት እንጠብቅ» ይላል።

ከመሠረታቸው ተነቃንቀው ወደ ኋላ የሚመለሱ ስንቶቹ ናቸው ዛሬ! በዓለም፥ በሥጋ፥ በዲያብሎስም ወደ ኋላ ይሳቡና ከመሠረታቸው ይነቃነቃሉ። የሚያስፈራውም ጨርሶ እንዳይወድቁ ነው። ወደ ኋላ መመለስ ከክርስቶስ እያወጣንም ይሆናል፤ ነገር ግን ወደ ኋላ መመለስ ወደ ፍጹም መካድ ሊያደርሰን ይችላል። ለምሳሌ፥ ቅዱስ ጴጥሮስ «ሩቅ ሆኖ» ጌታን መከተል ሲጀምር ሰይጣን በመካከላቸው ገብቶ ወደ መካድ ጴጦሮስን አድርሶት የለምን? (ማቴ. 26፡58፤69፤70) ሉረ ማፈግፈግስ እጅግ በጣም ያስፈራል! ለምንስ ወደ ኋላ እንመለሳለን? በፊታችን ግሩም የሆነ ተስፋ አለ እኮ! ያንም ተስፋ የሰጠን ራሱ እግዚአብሔር ነው። ይኸው የማይነቃነቅ ነገር! እግዚአብሔር አይዋሽም። ስለ አንድ መብል በኩርነቱን እንደ ሸጠ እንደ

ማለት ጨናችንን፥ ልንጠብቅ ብንፈልግ፥ ከማፈግፈግ ተጠብቀን ጸንተን ወደ ፍጻሜ ለመሄድ ብንወድ መሰብሰባችን አንተው።

በዕብራውያን ዘንድ አንዳንዶች መሰብሰብን የተውት ስደትንና መከራን ስለ ፈሩ ነው። እኛሳ? እኛ ለምን ተውን? መጽሐፍ ቅዱስን ይዘን ስንሄድ ሰው አይቶ «ጸረ ማርያም!» ብሎ ስለሚሰድበን ነውን? ወይስ የተማርን ስንሆን «በእውቀት እኔ እበልጣቸዋለሁ፥ በእነርሱ ዘንድ ብሰበሰብ ምን እጠቀማለሁ?» ስለምንል ነውን? ወይስ «አይ! እኔማ ጽኑ ክርስቲያን ነኝና መሰብሰብ ምን ያስፈልገኛል?» ስለምንል ነውን? ማናቸውንም ቢሆን ሐዋርያው «የተስፋችንን ምስክርነት እንድንጠብቅ መሰብሰባችንን አንተው» ይለናልና ልማዳችንን እናሻሽለው።

በጥንት ዘመን ክርስቲያኖች ባንድነት ይሰበሰቡበት የነበር በግሪክ ቋንቋ «አጋፔ» የተባለ የፍቅር ገበታ ነበረ። የዛሬ የየወሩ ማኅበሮቻችን መነሻቸው ምናልባት ይህ ይሆን ይሆናል። የሆነ ሆኖ ከዛሬ ማኅበሮቻችን ይህ በመንፈሳዊ ረገድ የእርስ በርስ መጽናናት የቀረ ይመስላል። የእኛ የማኅበራችን ጨዋታ ዛሬ ስለ ዓለምና ስለ ገበያ ነው! ሰውንም ማማት ሁለመናው አልጠፋም ይሆናል። ምነው ማኅበሮቻችን ወደዚያ ወደ ተገባው ደንብ በተመለሱና የማኅበርተኞቹ ዓይነተኛ ጉዳይ ለፍቅርና ለመልካምም ሥራ ለመነቃቃት እርስ በርሳችን መተያየት በሆነ!

ነ) «ቀኑ ሲቀርብ» (ቁ. 25) «ሐዋርያው የሚነገረው ስለ የትኛው ቀን ነው?» ቢሉ፥ ብዙዎች መምህራን ኢየሩሳሌም በሮማዊው በቲቶ እጅ ስለምትፈርስበት ቀን ነው ይላሉ፥ ምክንያቱም ይህ መልእክት በተጻፈ ጊዜ ያ ቀን በእውነት ተቃርቦ ነበር። ለዕብራውያንም ያ ቀን ሳይሆን አይቀርም። ይሁን እንጂ መልእክቱ ለዛሬ ደግሞ ነውና ቀኑ ለእኛ በ1ኛ ተሰ. 5፡2፣ በ2ኛ ተሰ. 2፡1-3ና በ2ኛ ጴጥ. 3፡10 ላይ የተነገረለት «የጌታ ቀን» የተባለውም ቀን ይሆን ይሆናል። ያም ሆነ ይህ ቀኑን በደኅና ለማሳለፍ መጽናት ያሻልና ክርስቲያኖች መሰብሰባቸውን እንዳይተዉ ተመክረዋል።

## ቁ. 26-31

> 26 የእውነትን እውቀት ከተቀበልን በኋላ ወደን ኃጢአት ብናደርግ ከእንግዲህ 27 ወዲህ ስለ ኃጢአት መሥዋዕት አይቀርልንምና፥ የሚያስፈራ ግን የፍርድ መጠበቅ ተቃዋሚዎችንም ሊበላ ያለው የእሳት ብርታት አለ። 28 የሙሴ ሕግ የናቀ ሰው ሁለት ወይም ሦስት ቢመሰክሩበት ያለ ርኅራኄ ይሞታል፤ 29 የእግዚአብሔርን ልጅ የረገጠ ያንንም የተቀደሰበትን የኪዳኑን ደም እንደ ርኩስ ነገር የቆጠረ የጸጋውንም መንፈስ ያክፋፋ፥ እንዴት ይልቅ የሚብስ ቅጣት የሚገባው ይመስላችኋል? 30 በቀል የእኔ ነው፤ እኔ ብድራትን እመልሳለሁ ያለውን እናውቃልንና፤ ደግሞም፡- ጌታ በሕዝቡ ይፈርዳል። 31 በሕያው እግዚአብሔር እጅ መውደቅ የሚያስፈራ ነው።

የመጽናታችን ዋና አስፈላጊነት የሚታየው ያልጸናን እንደ ሆን ከሚመጣብን ነገር ነው። «ለምን እንጽና?» የሚል ጥያቄ ቢቀርብ መልሱ «ከእንግዲህ ወዲህ ስለ ኃጢአት መሥዋዕት አይቀርልንምና» የሚል ነው። ባለፉት ቁጥሮች ላይ ሐዋርያው በልመናና በምክር ዕብራውያን የተስፋቸውን ምስክርነት እንዲጠብቁ አደፋፍሮአቸው ነበር፥ በሚከተሉትም ቁጥሮች ላይ ልመናውንና ምክሩን ሳይቀበሉ ወደ ኋላ የተመለሱ እንደሆን የሚደርስባቸውን ፍርድ በመግለጽ በዚህ በ4ኛው የማስጠንቀቂያ ክፍል ላይ ያስጠነቅቃቸዋል። ይሁን እንጂ አሳቡ አንድ ነው ገና ሊያጸናቸው ይጣጣራል።

በአራት ምሳሌ በሞላ ክርስቶስ መተካቱን ሰምተው ተረድተው ካወቁ በኋላ (ዕ. 6:4) ወደው ፈቅደው ክርስቶስን ቢጠሉና በመጥላታቸውም ጸንተው ወደ አይሁድ ሥርዓት ቢመለሱ ስለ ኃጢአት መሥዋዕት አይቀርላቸውም። የአራት መሥዋዕቶች ምሳሌዎች ብቻ እንደ ሆኑና ኃጢአትን ሊያስወግዱ ከቶ እንዳልቻሉ ተረድተዋል። (ቁ. 11) እንግዲያውስ ክርስቶስን አሁን ቢጠሉት እግዚአብሔርን የሚያስታርቅ ምን መሥዋዕት ቀረ? ሉረ የቀረ ከቶ የለም! የለምና የሚቀረው ፍርድ ብቻ ነው፤ ለመዳንም ተስፋ የለም። በኢሳ. 26:12 ላይ «እሳት ጠላቶቹን ትበላለች»፥ በመዝ. 89:11 ላይ «የቁጣህን ጽናት ማን ያውቃል? ከቁጣህም ግርግ የተነሣ አለቁ»፥ በዕብ. 12:29 ላይም «አምላካችን በእውነት የሚያጠፋ እሳት ነው» ተብሎ ተጽፎአልና የከሐዲዎች ፍጻሜ በእውነት የሚያስፈራ ነው።

የሙሴን ሕግ የናቀ ሰው ይገባኝ ማለት ሳይችል ከሞተ ይልቁንም እግዚአብሔር በልጁ የተናገረውን ቃል ቸል የሚለው ሰው እንዴት ይሞት ይሆን? (ዕ. 1:2፤ 2:1-4) እግዚአብሔርን ክዶ ሌሎችን አማልክት ያመለከው ሰው በድንጋይ ከተወገረ (ዘዳግ. 17:2-7) ኢየሱስን ክዶ ተመልሶ ለምሳሌዎች የሚገዛ ሰው ከዚያ በባሰ ይቀጣ የለምን? ወድዶ ፈቅዶ ኢየሱስን የሚክድ ሰው የሚያደርገውን እስኪ እንመልከት። ሦስት ነገር ያደርጋል። 1ኛ፤ የገዛ አገሩን ሰንደቅ ዓላማ እንደሚረግጥ ሰው ነፍሱን ስለ እርሱ ብሎ የሰጠውን፥ «ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ አምላክ» የተባለውን ወልደ እግዚአብሔርን ይረግጣል፥ ይህንም በማድረግ የእግዚአብሔርን ፍቅር ይረግጣል። (ዮሐ. 3:16) 2ኛ፥ መዝና አመዛዝና ኃጢአትን በማስወገድ በእግዚአብሔር ዘንድ እንዲኖር ተገቢ ያደረገውንና አዲስ ኪዳንን የጸናለትን ደም፥ የእግዚአብሔር ወልድ ሕይወት የነበረበትን ደም (ዕ. 9:14)፥ የአታላይና የውሸታም ደም ነው በማለት ስርየት ለዘላለም የማይገኝለትን ኃጢአት ይሠራል። (ማር. 3:22፤ 28-30) 3ኛ፥ በጸጋ ወደ ጸጋም የሚጠራውን የመንፈስ ቅዱስን ድምፅ ባለመስማት መንፈስ ቅዱስን ይወርፋል። ይህ ሰው ሥላሴዎችን፥ አብን ወልድንና መንፈስ ቅዱስን አውቆ በድሎአል። ውጤቱሳ? ውጤቱማ ኃጢአትን በሚበቀል በሕያው እግዚአብሔር እጅ መውድቅ ነው፤ እርሱም እጅግ በጣም የሚያስፈራና የሚያስደነግጥ ነገር ነው። በዘዳግ. 32:35-36 ላይ «በቀልና ፍርድ የእኔ ነው፤ እግዚአብሔር በሕዝቡ ይፈርዳል» የሚል አምላክ ታላቅና ኃያል ቀናተኛም መሆኑን አውቀናልና (ዘጸአ. 20:5-6) «ማዳንህን አልቀበልም» ብሎ እልከኛ በሆነ ከሐዲ ላይ የሚወርደውን መዓት እስከዚህ ድረስ ነው ብሎ መገመት የማይቻል ነገር ነው።

<u>ማስገንዘቢያ</u>:-

ሀ) «ወደን ኃጢአት ብናደርግ» (ቁ. 26) «ይህስ ምን ዓይነት ኃጢአት ነው?» ብለው ቢጠይቁኝ፥ ማንኛውም ዓይነት ኃጢአት ሊሆን ይችላል። የእውነትን እውቀት ከተቀበልን በኋላ ወደን ፈቅደን ተደስተን አዘውትረን ኃጢአት ብናደርግ ክርስቲያኖች በፍጹም አይደለምና ሙሉ የሆነ የእግዚአብሔር ፍርድ እንደሚወድቅብን የታወቀ ነው። «ክርስቲያኖች በፍጹም አይደለንም» ያልሁበት ምክንያት አማኝ ክርስቲያን ኃጢአትን እንደዚህ ስለማይሠራ፥ እንደዚህም መሥራት ስለማይችል ነው። (1ኛ ዮሐ. 3:6-10) አማኝ ክርስቲያን ኃጢአትን ያደርግ ይሆናል (1ኛ ዮሐ. 1:8-10፤ 2:1)፥ ይሁን እንጂ የሚያደርገው ፈቅዶ በደስታ ሳይሆን በሰይጣን ተገድዶ ነው፥ ካደረገውም በኋላ በታላቅ ኀዘን ይጸጸትበታል።

ሆኖም እዚህ በክፍላችን ላይ ሐዋርያው የሚናገርበቱ ኃጢአት በተለይ ክሕደት የሆነ ይመስላል። «ስለምን?» ቢሉ፥ ከዘዳግ. 17:2-7 የሚያቀርበው ነገር ይህንኑ ያመለክታል፤ በቁ. 35 ላይ

(1ኛ ጴጥ. 5፡9፤ ራእ. 1፡6፤ ዮሐ. 8፡34) ወንጌልን ሰምተው በአእምሮአቸው ተረድተው «አምነናል» ይላሉ፤ እምነታቸው ግን ከአጋንንት እምነት በምንም አይበልጥም። (ያዕ. 2፡19) «ክርስቲያኖች ነን» ይላሉ፥ ነገር ግን በእውነቱ ክርስቲያኖች አይደሉም። በአንጎላቸው የእውነትን እውቀት ተቀብለዋል፥ ያ እውቀት ግን ሕይወታቸውን፥ ማለት አመላለሳቸውን፥ በፍጹም አልነካም። በስም ክርስቲያኖች ናቸውና ሌሎቹ ሰዎች እንደ ክርስቲያኖች ሆነው ይቆጥሩአቸዋል፤ ሕይወታቸው (አመላለሳቸው) ግን የአረመኔዎች ነው። አስፈላጊ ፍሬዎች በፍጹም የሉበትም። (ሉቃ. 3፡8፤ ገላ. 5፡22-25) ዋና የቤተ ክርስቲያን እንቅፋት እነኝህ ሰዎች ናቸው። አንተም አማኝ ክርስቲያን ሆይ፥ በአንተ ሰበብ፥ አንተ በምትኖርበት ሕይወት (አመላለስ) ምክንያት የእግዚአብሔር ስም በአሕዛብ (ባላመኑቱ) መካከል ይሰደባልን? (ሮሜ 2፡24) ወደ ኋላ ማፈግፈግህ ታናሽ ነገር ከቶ አይምሰልህ። ያንተ ሕይወት (አመላለስ) ሌሎችን በማርከስ ላይ ነውና አብጀው! ያልተመለስህ እንደሆነ ዋጋህን ልንገርህን? 1ኛ ቆሮ. 3፡13ን እይ። «ባዶ እጁን!» አወይ ጉዳት! አወይ ቁጭት!

ሠ) «ጌታ በሕዝቡ ይፈርዳል» (ቁ. 30) ይህ ጥቅስ ከመጣበት በዘዳ. 32፡36 ላይ «በሕዝቡ» ሳይል «ለሕዝቡ» ይላል። ሁለቱም እውነት ናቸው። እግዚአብሔር በእስራኤል ጠላቶች ፊት ለሕዝቡ ይፈርዳል፤ በትልቁ በፍርድ ቀን ግን ከሁሉ አስቀድሞ በሕዝቡ ይፈርዳል። (ሮሜ 2፡9፤ 1ኛ ጴጥ. 4፡17)

ረ) «በሕያው እግዚአብሔር እጅ መውደቅ የሚያስፈራ ነው» (ቁ. 31) «እግዚአብሔር የፍቅርና የምሕረት አምላክ ከሆነ «በቀል የእኔ ነው እኔ፥ ብድራትን እመልሳለሁ» ብሎ እንደምን ይናገራል?» ቢሉ፥ እውነት ነው፥ እግዚአብሔር የፍቅርና የምሕረት አምላክ ነው። ይህማ ባይሆን አንድያ ልጁን ለኃጢአተኞች ይሞት ዘንድ በመላክ ፈንታ ወደያውኑ ባጠፋቸው ነበር። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የላከው የእግዚአብሔር ፍቅር ነው። (ዮሐ. 3፡16፤ ሮሜ 5፡8) እግዚአብሔር በኃጢአተኞች ላይ የሚመጣውን ገሃነመ እሳት አውቆአልና በዚህ ምክንያት የፍቅርና የምሕረት አምላክ ነውና፥ ኃጢአተኞች ወደ ገሃነመ እሳት እንዳይገቡበት የተቻለውን ሁሉ አድርጎአል፤ የደኅንነትም መንገድ ለሁሉም ከፍቶአል።

ሰው ግን ያን የእግዚአብሔርን ሥራ ደኅንነቱንም ካወቀ በኋላ ጀርባውን መለስ አድርጎ «አልቀበልም በዚያ መንገድ አልሄድም፥ ከለላውን አልፈልግም!» ቢል እግዚአብሔር ቅዱስ በመሆኑ ምክንያት በኃጢአተኛ ላይ የግዴታ የሚወርደው መዓት ያለ ጥርጥር እምቢተኛውን ሰው ያገኘዋል። እድል ፈንታው የተረጋገጠ ነው፥ ለተስፋ አንድም መሠረት የለውም። ፍርዱ በእውነት የሚያስፈራ ነው። (ሉቃ. 12፡4-5)

አረመኔም ኃጢአትን ቢሠራ መጥፎ ነገር ነው፥ ክርስቲያን ቢሠራው ግን የባሰ ነው፤ ምክንያቱም ክርስቲያኑ እግዚአብሔርን «አባት» ይለዋል በበለጠም ያውቃል። ቅጣቱም በመጠኑ የባሰ ይሆናል። (1ኛ ጴጥ. 1፡14-17፤ ዮሐ. 9፡40-41፤ ሉቃ. 12፡47) አትሳቱ፤ እግዚአብሔር የሚዘበትበት አምላክ አይደለም። (ገላ. 6፡7-8)

## ቁ. 32-39

32፥33 ነገር ግን ግማሽ በነቀፋና በጭንቅ እንደ መጫወቻ ስለ ሆናችሁ ግማሽም
እንዲህ ካሉት ጋር ስለ ተካፈላችሁ፥ ብርሃን ከበራላችሁ በኋላ መከራ በሆነበት
በትልቅ ተጋድሎ የጸናችሁበትን የቀደመውን ዘመን አስቡ። 34 የሚበልጥና
ለዘወትር የሚኖር ገንዘብ በሰማይ ራሳችሁ እንዳላችሁ አውቃችሁ፥ በእስራቴ
ራራችሁልኝ የገንዘባችሁምን ንጥቂያ በደስታ ተቀበላችሁ። 35 እንግዲህ ታላቅ
ብድራት ያለውን ድፍረታችሁም አትጣሉ። 36 የእግዚአብሔርን ፈቃድ
አድርጋችሁ የተሰጣችሁን የተስፋ ቃል እንድታገኙ መጽናት ያስፈልጋችኋልና።

37 ገና በጣም ጥቂት ጊዜ ነው፥ ሊመጣ ያለውም ይመጣል 38 አይዘገይምም፥
ጻድቅ ግን በእምነት ይኖራል ወደ ኋላ ቢያፈገፍግ፥ ነፍሴ በእርሱ ደስ አይላትም።

39 እኛ ግን ነፍሳቸውን ሊያድኑ ከሚያምኑቱ ነን እንጂ ወደ ጥፋት ከሚያፈገፍጉ
አይደለንም።

ዕብራውያን ተስፋ ወደ መቁረጥ ደርሰው ነበር፥ ወደ አይሁድም ሥርዓት ሊመለሱ አስበዋል። ሐዋርያው በክርስቶስ ለመጽናት ሲያደፋፍራቸው ከቁ. 26 ጀምሮ እስከ ቁ. 31፤ ድረስ ሰው ያልጸና እንደሆነ የሚደርስበትን ፍርድ በአሉታ አስተያየት ካስረዳ በኋላ አሁን በሚከተሉት ቁጥሮች ላይ ወደ አዎንታ አስተያየት ተመልሶ ዕብራውያን የጸኑ እንደሆነ የሚያገኙትን ብድራት ያመለክታቸዋል።

«ነገር ግን» በማለቱ የሚጽፍላቸውን ዕብራውያን ከእነዚያ፥ ባለፈው ክፍል ላይ ከጻፋቸው ከሐዲዎች ይለያቸዋል፤ ይህም በም. 6፡9 ላይ እንዳደረገው ነገር ነው። ከቁ. 32 እስከ ቁ. 34 ድረስ ወደ ኋላ እየተመለከተ ከዚያ በፊት የቻሉትን ሁሉ ያሳስባቸዋል፤ ቀጥሎም ከቁ. 35 እስከ ቁ. 39 ድረስ ወደ ፊት እየተመለከተ የሚቆያቸውን ክብር ያመለክታቸዋል። በሁሉ፥ ዓይነተኛ አሳቡ ሊያስጸናቸው ነው።

ዕብራውያን የክርስቶስን ነገር ከሰሙና ከመኑ ወዲህ ብዙ ጭንቀት ደርሶባቸው ነበር። የዚህ ጭንቀት እኩሌታው፥ ሰዎች ቲያትር መሳይ አድርገዋቸው ስማቸውን እንደ ከፉ፥ ያውም በንቀትና በመቀለድ፥ ሲያወጡ ግፍንም ከየዓይነቱ ሲያደርጉባቸው ነበር። እኩሌታው ደግሞ እንዲህ ያለው ነገር በሌሎቹ ላይ ሲደረግ ዕብራውያን ክርስቲያኖቹ በፈቃዳቸው ከእነርሱ ጋር ተሳታፊዎች ሆነው ስለ ነበር ነው። ይህን ሁሉ መከራ ታግሠው በክርስቶስ ጸንተው ነበር። ይህም ብቻ ሳይሆን የበለጠና ማንም ሊነጥቅባቸው የማይችለው ርስት ራሳቸው በሰማይ እንዳላቸው ተገንዘበው በምድር ላይ የነበረ ንብረታቸው ቢወረስባቸው እንኳ ንጥቂያውን በደስታ ተቀብለውት ነበር እንጂ አላዘኑም ነበር። (1ኛ ጴጥ. 1፡3-5) ባለፈው ዘመን ይህን ሁሉ ከታገሡ ከቻሉም አሁን በዚህ ለምን ያፈገፍጋሉ? ይልቁንም እንዲህ ያለ ታላቅ ብድራት ሲኖርበት፥ ሉረ መተማመናቸውን እንደ ውራጅ ልብስ አድርገው አይጣሉት! (ም. 11፡25-26፤ ማቴ. 5፡11-12፤ ሮሜ 8፡18፤ 1ኛ ቆሮ. 2፡9) እግዚአብሔር የሰጣቸውን ታላቁን ተስፋ፥ እርሱም መዳን በሙላቱ፥ እንዲቀበሉና እንዲጠቀሙበት ከፈለጉ የተመደበላቸውን መከራ እንኳ እንዲታገሡ እንዲጸኑም ያስፈልጋቸዋልና። (ም. 6፡11-12፤ ፊልጵ. 1፡29) ከዚህ በፊት መጽሐፍ ቅዱስ በእምባ. 2፡3፥4 ላይ ስለዚህ ነገር መስክሮአል። ነቢዩ እምባቆም እስራኤል ከከለዳውያን እጅ በቅርቡ መዳንዋን አይቶ «ወደ ፍጻሜው ይቸኩላል፥ እርሱም አይዋሽም ቢዘገይም በእርግጥ ይመጣልና ታገሠው፥ እርሱ አይዘገይም» እንዳለው ሁሉ

ደራሲው አሁም የጌታን መምጣት አይቶ «ሊመጣ ያለው (ማቴ. 11፡3) በቅርቡ ይመጣልና ጽኑ» ይላል። ጻድቅ የሚኖረው በማይቋረጥ እምነት ነውና ይጽኑ፤ ወደ ኋላ ያፈገፍጉ እንደ ሆነ ግን እግዚአብሔርን አያስደስቱም። (ም.11፡6።) ሐዋርያውና ዕብራውያንም የደኀንነታቸውን ፍጹምነት ለመቀበል በእምነት የሚኖሩ ናቸው እንጂ፥ ወደ ኋላ አፈግፍገው እግዚአብሔርን አስመርረው ባለማስደሰት ጠንቅ ወደ ጥፋት የሚደርሱ አይደሉም። (ም. 3፡16-19፤ 1ኛ ቆሮ. 10፡5)

<u>ማስገንዘቢያ</u>፡-

ሀ) «እንዲህ ካሉት ጋር ስለ ተካፈላችሁ» (ቁ. 32፡33) የተከሰሱት ተከስሰዋል፥ የተያዙት ተይዘዋል፥ የተፈረደባቸው ተፈርዶባቸዋል፥ የታሰሩትም ታስረዋል፥ ሌሎችን ክርስቲያኖች በነገሩ ምን ያገባቸዋል? እነርሱስ አልተከሰሱም፥ ገና በደኅና ናቸው፤ በአንድ ዳር ቆመው በራሳቸው አለመያዝ እየተደሰቱ ራሳቸውን በጥንቃቄ ሁሉ ቢጠብቁ አይሻልምን? የዓለም ሰው «ይሻላል» ይላል፥ እነኝህ ዕብራውያን ግን ከተጠሉት ጋር መካፈል ወደዋል። ይህም እኮ ትልቅ ነገር ነው! ከእነርሱ ጋር እንደ ታሰሩ ሆነው እስሮችን አሰቡ፥ ከተጨነቁም ጋር ተጨነቁ። (ም. 13፡3፤ ሮሜ 12፡15) ይህም ለእኛ የሚሆን መልካም ማስረጃ ነው። ከተወደዱት ጋር መሳተፍ ቀላል ነገር ነው፤ ከተጠሉት ጋር መሳተፍ ግን ማን ይወዳል? ሆኖም ለክርስቲያን የሚገባ ነገር ነው። ለወንጌልም ሆነ ለክርስቶስ፥ በዚህም አገር ቢሆን በዚያ፥ ወንድሞች ቢታሰሩ ወይም ቢሰደዱ (1ኛ ጢሞ. 4፡16) እኛ የቀረነው በመከራቸው ሁሉ መሳተፍ ይገባናል። እንደ ምን? ቢሉ፥ በጸሎት፥ ቀጥሎም በገንዘባችን በመረዳት፥ ወደ ቤታችን በመቀበል፥ ምግብ በማቅረብ፥ ቤተ ሰቦቻቸውንና ከብቶቻቸውን በመጠበቅ፥ እርሻዎቻቸውን በማረስና በማረም ሰብልንም በማከማቸት፥ በዚህም በሌላም ልናግዛቸውና ልናጽናናቸው ክርስቲያናዊ ተግባራችን ነው።

ለ) «ድፍረታችሁም አትጣሉ» (ቁ. 35) አማኞች ክርስቲያኖች የመጀመሪያ እምነታቸውን እስከ መጨረሻው የማይጠብቁት በምን ምክንያት ነው? እነኝህ ዕብራውያን መተማመናቸውን ሊጥሉት የጀመሩት መከራ ስለበዛና የክርስቶስ መምጣት የዘገየ ስለ መሰላቸው ነው። (2ኛ ጴጥ. 3፡4) «መጥቶ ከመከራችን ያድነናል» ብለው ተጠባብቀውት ነበር፤ አልመጣም፤ ስለዚህ ሰለቻቸው፥ ወደ ኋላም ሊያፈገፍጉ ጀመሩ። እንደዚሁም ዛሬ ችግር ስለሚበዛባቸው አንዳንዶች ክርስቲያኖች ያፈገፍጋሉ፤ ይሁን እንጂ ምክንያቱ ምን ጊዜም መተማመንን መጣል ነው። በፊታቸው ያለው ደስታ ይጨልምባቸዋል (ም. 12፡1-2)፥ ተስፋቸው ይደክማል፥ ወደ ኋላም ያፈገፍጋሉ። ምክንያቱስ? በሰማያት ያለው ነገር የረቀቀ፥ የተስፋውም ቃል የማይታመንበት ሆኖ ስለ ታያቸው አይደለምን? መተማመናቸውን ጥለዋል ማለት ነው።

ለእያንዳንዳችን የሚያስፈልጉ ሦስት ነገሮች አሉ፡-

1ኛ፥ ተስፋችንን በፊት ለፊታችን ማኖር ነው። በእሽቅድድም ውስጥ፥ የሚሽቀዳደም ሰው ትኩር ብሎ የመድረሻውን ገመድና ከመድረሻው ገመድ ቀጥሎ የሚቆየውን ሽልማት በአሳቡ እያየ ይሮጣል። ያ አሳብ ያም ተስፋ ወደ ፊት ይገትተዋል። እኛም በፊታችን ያለውን አክሊል በማስታወስ በመንገድ ላይ ከመለገም፥ ወይም ወደኋላ ከማፈግፈግ እንጠበቃለን። 2ኛ፥ የማይቋረጥ የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ መፈለግ ነው። መሮጥስ እንችል ይሆናል፥ ቀስ ብሎ መራመድሳ? ታላቅ ነገር በፊታችን ሲኖር በርትተን በሩጫ እንችለዋለን፤ እንሮጣለን

እንታክትም። በፊታችን ያለው ግን የዕለት ዕለት ታናሽ ነገር ሲሆንሳ? እምብዛም የሚጥለን ይኸው አይደለም? እኛ አብዛኛውን ማፈግፈግ የምንጀምረው ሰው በማያይበት ቦታ ብቻችንን ስንሆንና ሥራችን ያ የተለመደው ሲሆን ነው። ሳይደከሙ መሄድ (መራመድ) ይህ ነው ችግራችን። መድኃኒቱስ? ዕለት ዕለት እግዚአብሔርን በመተማመን መጠባበቅ ነው። (ኢሳ. 40:27-31)

3ኛ፥ መጽናት እንደሚያስፈልገን መገንዘብ ነው። ዋናው ነገር መጀመር ሳይሆን መጨረስ ነው። መጀመርስ መልካም ነገር ነው፥ ሰው የጀመረውን ባይጨርስስ? አይጠቅምም። የምንድነው እስከ መጨረሻ ብንጸና ነው። (ማቴ. 10:22፤ 24፥13) የተሰጠንን የተስፋ ቃል የምናገኝ የእግዚአብሔር ፈቃድ ካደረግን በኋላ ነው። (ም. 10:36) ስለዚህ እንጽና! ክርስቲያን መሆን እኮ ቀላል ነገር አይደለም። ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የምንገባው በብዙ መከራ መሆኑ ተነግሮናል (የሐዋ. 14:21-22)፥ ዓለም እንደሚጠላን ተነግሮናል (ዮሐ. 15:18-21)፥ ክርስቶስ እስኪመጣ ድረስ ዘመኑ የረዘመ እንደሚሆንም ተነግሮናል። (ማቴ. 25:5-19)፥ እነዚህም ነገሮች አውቀናል። ታዲያስ ወገባችንን እንታጠቅና ለመቆም አሳባችንን እንቁረጥ። (ኤፌ. 6:10-13) «ንቁ፥ በሃይማኖት ቁሙ ጎልምሱ፥ ጠንከሩ!» (1ኛ ቆሮ. 16:13)

ይሁን እንጂ፥ አንድ ነገር አለ። ደራሲው በእነዚህ ቁጥሮች ላይ የሚናገርበቱ ብዙ ጊዜ በአማኞች ክርስቲያኖች ዘንድ ስለሚገኝ ስለዚህ ዓይነት ማፈግፈግ ሳይሆን «ወደ ጥፋት» (ቁ. 39) ስለሚያደርስ ዓይነት ይናገራል። ይህም እላይ እንዳየነው ሁሉ ፈጽሞ ሌላ ነገር ነው። ከአንባቢዎች መካከል እንደዚህ ያለ ማለት ወደ ጥፋት የሚያደርስ ዓይነት ማፈግፈግ እንደሌለ እተማመናለሁ።

ሐ) «የተሰጣችሁ የተስፋ ቃል» (ቁ. 36) ስለዚህ የተስፋ ቃል ከዚህ በፊት በእያሌው እንብበናል። (ም. 6:11-12፤ ም. 9:15) ለአብረሃምና ለዘሩ የተሰጠ የተስፋ ቃል ነው፥ አንዳንድ ጊዜም «የእስራኤል ተስፋ» ይባላል። ይሁን እንጂ መንፈሳውያን የአብርሃም ልጆች ክርስትያኖች ናቸውና ደግሞ «የቤተ ክርሲያን የተስፋ ቃል» ይባላል። እስራኤላውያን አብዛኛውን ስለ ሙታን መነሣት ይተረጉሙት ነበር። (የሐዋ. 23:6፤ 24:15፤ 26:6-8፤ 28:20) ይሁን እንጂ፥ ከዚያ የበለጠ ነገር ነበር። በአሪት ዘፍጥረት በልዩ ልዩ ቦታ ላይ እንደምናየው ሁሉ ይህ የተስፋ ቃል ወሰንና ዳርቻ የማይገኝለት፤ እስከ የሌለው ሁሉን ነገር በውስጡ የያዘና ያከማቸ የበረከት ቃል ነበረ። የሙሉ መዳን ተስፋ፥ ፍጹም የሆነ ድኅንነት የሚሰጥ ተስፋ ነው እንጂ የትንሣኤ ሙታን ተስፋ ብቻ አይደለም። የተስፋው ቃል ሰው አዳም ከወደቀበቱ ሁሉ እንዲመለስና እግዚአብሔር በፈጠረው ጊዜ ያቀደለትን ነገር ሁሉ በሞላ እንዲያገኝ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ «ስፋቱና ርዝመቱ ከፍታውም ጥልቅነቱም ምን ያህል መሆኑን ለማስተዋል፥ ከመታወቅም የሚያልፈውን የክርስቶስ ፍቅር ለማወቅ ትበረቱ ዘንድ፥ እስከ እግዚአብሔርም ፍጹም ሙላት ደርሳችሁ ትሞሉ ዘንድ፥ እጸልያለሁ» ብሎ እንዳመለከተው ያለ ነገር ነው። (ኤፌ. 3:18-19) እንደ ፍቅሩ እንዲሁም የተስፋ ቃሉ ነው። ሰፋፊ ሆኖ በውስጡ ሁሉን ጠቅልሎአል። በውስጡ የመድኅን መምጣት የኃጢአት መወገድ፥ ሰው የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖና ከእርሱ ጋር ሕብረትን አግኝቶ በዘላለም ሕይወት መኖር፥ መንግሥተ ሰማያትን መውረስ፥ ትንሣኤ ሙታንና የሥጋ መነሣት፥ ለዘላለም ከእግዚአብሔር ጋር በክብር መቀመጥ፥ ሁሉም በዚህ ተስፋ ቃል ተጠቅልሎአል። (ምሳ. 10:22) በአጭር ቃል፥ ሰው ወደ ጥንቱ የእግዚአብሔር አሳብ ተመልሶ እንዲገባ ነው። ማለት፥ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር በክብርና በኅብረት ለዘላለም

እንዲኖር በመልኩ እንደ ምሳሌውም እንደ ተፈጠረ እንዲሁ እንዲሆን ነው። (ም. 2፡5-9፤ ሮሜ 8፡18-24)

በም. 6፡15 ላይ «አብርሃም ከታገሠ በኋላ ተስፋውን አገኘ» ከተባለ በኋላ በም. 11፡13 ላይ «አለገኙም» ይልና በም. 11፡39-40 ላይ «እነዚህ ሁሉ የተሰጠውን የተስፋ ቃል አላገኙም፥ ያለ እኛ ፍጹማን እንዳይሆኑ እግዚአብሔር ስለ እኛ አንዳች የሚበልጥ ነገርን አስቀድሞ አይቶ ነበር» የተባለበቱ በዚህ ምክንያት ነው። የተሰጠው የተስፋ ቃል የፍጹምነት ተስፋ ነበረ፤ ፍጹማን ግን የምንሆነው ሥጋችን ከተነሣ በኋላ ነውና፥ ሥጋችንም የሚነሣ ክርስቶስ በዳግም ምጽአት ሲመጣ ነውና፥ ስማቸው በም. 11 ላይ የተጻፈ ቅዱሳን ሁሉ ፍጹማን ገና አልሆኑም። የተስፋውን ምሳሌ፥ ምድራዊውን ነገር፥ ተቀብለው ይሆናል፤ ግን እውነተኛውን ነገር በሞላ ገና አልተቀበሉም።

መ) «ጻድቅ በእምነት ይኖራል» (ቁ. 38) እርግጥ ነው፥ ሐዋርያው እዚህ ላይ የሚናገረው ዕለት ዕለትና ዓመት በዓመት ስለምንኖርበት እምነት ነው እንጂ ጥቅሱ በተጠቀሰበት በሌላው ቦታ ላይ እንደሚሆን ስለምንድንበቱ መንገድ አይናገርም። (ሮሜ 1፡17) ይሁን እንጂ፥ ይኸን ነገር ብናጣራ የሚከፋ አይመስለኝም። የምንድንበቱ በእምነታችንም ሆነ በመልካም ሥራችን አይደለም፥ የምንድንበቱ በክርስቶስ ሥራ ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ የሥራው ትሩፋትም ወደ እኛ ዘንድ የሚመጣው በእምነታችን መስኖ ነው፥ እምነታችንም የሚገለጠው በመልካም ሥራችን ነው። (ኤፌ. 2፡8፤ ያዕ. 2፡18) ያዳነን ጸጋው ነው፥ ያንም ጸጋ የምንቀበለው በእምነት እጅ ወይም በእምነት መስኖ ነው። ማስተስሪያው በደሙ ሆነ፥ በእምነትም ይገኛል። (ሮሜ 3፡25)

# 3ኛ ክፍል የአማኞች አመላለስ (ም. 11-ም. 13)

## ምዕራፍ አሥራ አንድ

### አማኝ በእምነት ይኖራል

መልእክቱን በጻፈ ጊዜ የሐዋርያው ዓይነተኛ ዓላማ ዕብራውያንን ወደ ኋላ ከማፈግፈግ ለመከልከል ነው። ይህን ለማድረግ፣ ከም. 1 ጀምሮ እስከ ም. 10 ድረስ ኢየሱስን ሥሉአል። የራሱን የኢየሱስን ታላቅነት አስቀድሞ አስረድቶአል፥ ከዚያም በኋላ ኢየሱስ ወዴትና ወዴት ዘንድ ሊያስገባቸው እንደሚችል ገልጦአል። አሁንም በመልእክቱ መጨረሻ በም. 11፤ ም. 12ና ም.13 ላይ ዓይነተኛ ዓላማውን ተከታትሎ ማስረጃ ማስረጃን እያቀረበ የመጀመሪያ እምነታቸውን እስከ መጨረሻው አጽንተው እንዲጠብቁ በልመናና በማስጠንቀቂያ ያደፋፍራውቸዋል።

በም. 10፡22-24 ላይ እስከዚያ ድረስ በተሰጠው ትምህርት ላይ የተመሠረቱት ማድረግ የሚገባን 3 ነገሮች ተጠቅሰዋል፤ እነዚህም በተረዳንበት እምነት እንድንቀርብ፥ የተስፋችንን ምስክርነት እንደጠብቅ፥ ለፍቅርም እንደንነቃቃ እርስ በርሳችን እንድንተያይ ናቸው። አሁን በሚከተሉት 3 ምዕራፎች ላይ ደራሲው እነዚህን 3 ነገሮች በተራ በተራ እያነሣ ዕብራውያንን በእምነትና በተስፋ በፍቅርም እንዲመላለሱ ይመክራቸዋል፤ ይህንም በማድረጉ እኛንም ይመክረናል።

ም. 11 ስለ እምነት የሚናገር ምዕራፍ ነው። ደራሲው እምነት ምን እንደሆን አስቀድሞ ያስረዳል። ቀጥሎም ከዕብራውያን (ከእስራኤላውያን) ታሪክ ውስጥ የብዙዎቹን የዕብራውያንን አበው ስም ጠቅሶ እነኝያ የዱሮ ዕብራውያን ከእግዚአብሔር ዘንድ የተስፋን ቃል ተቀብለው ከእምነታቸው የተነሣ የተጋደሉትን ተጋድሎ ያሳይና በምዕራፉ መጨረሻ ላይ የተስፋን ቃል ለመውረስ የታገሡትን መከራና ሥቃይ ይተቻል። ሐዋርያው እነርሱ የመጀመሪያ እምነታቸውን እስከ መጨረሻ አጽንተው እንደጠበቁ በማስታወስ የሚጽፍላቸው ዕብራውያንም ቀንተው (ሮሜ 11፡14) በእምነታቸው እንዲጸኑ ያነቃቃቸዋል። ለእነርሱም በተሰጠው ምክር እኛ ደግሞ እንመከራለን። «በእምነትና በትዕግሥትም የተስፋውን ቃል የሚወርሱትን እንድትመስሉ እንጂ ዳተኞች እንዳትሆኑ ተስፋ እስኪሞላ ድረስ እያንዳንዳችሁ ያን ትጋት እስከ መጨረሻ እንድታሳዩ እንመኛለን» ተባለ (ም. 6፡11-12)፤ ይህም ምዕራፍ የዱሮ ሽማግሌዎች እንዴት እንዳመኑና እንዴት እንደ ታገሡ ያሳየናል።

#### ቁ. 1-3

> 1 እምነትም ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያረጋግጥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ
> ነው። 2 ለሽማግሌዎች የተመሰከረላቸው በዚህ ነውና። 3 ዓለሞች በእግዚአብሔር
> ቃል እንደ ተዘጋጁ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት
> እናስተውላለን።

«ጻድቅ በእምነት ይኖራል» ተብሎአልና (ም. 10፡38) እምነት ምን እንደ ሆነ ሐዋርያው አሁን ያስረዳናል። እምነት፥ ተስፋ የተደረገበትን ነገር እንደ ሆነ ነገር ቆጥሮ መኖር፥ ወይም የማይታየውን ነገር እንደምናየው አድርገን መኖር ነው። ለምሳሌ፥ የተስፋ ቃል ይሰጣል፤ ያ ነገር ምናልባት የማይቻል ይመስላል፥ መፈጸሙም የማይታይ ነው፤ ሆኖም እምነት ገብቶ ነገሩን ያረጋግጥና «ነው!» ይላል፥ የማይታየውንም ነገር ከአሁን አሁን በፊታችን እንደሚሆን

ያደርጋል። እግዚአብሔር ለሽማግሌዎች፥ ማለት ለብሉይ ኪዳን አበው የመሰከረላቸው በእንዲህ ያለ እምነት ስለ ኖሩ ነው። እኛም ዓለማትና ዘመናት በእግዚአብሔር ቃል ተዘጋጁ እንላለን፤ ይህም እምነት ነው፥ ይህንም ስንል የማይታየው ነገር የሚታይ ሆኖ ተገኘ ማለታችን ነው።

<u>ማስገንዘቢያ</u>:-

ሀ) በሐዋርያት ዘንድ እምነት የተባለው ነገር በአንድ ሰው ወይም አንድ ሰው በተናገረው ቃል፥ ተማምኖ መኖር፥ «ቃሉ እንደሚፈጸም እርግጠኛ ነኝ» ብሎ መኖርም ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እምነት ይኸው ነውና ይህን መገንዘብ ይገባናል። ምክንያቱም፥ ስለ እምነት ስንናገር አንዳንድ ጊዜ አንግባባም። «እምነት» ሲባል አንዱ ሰው ስለ ራስ እውቀት ብቻ ያስባል ለማረጋገጫም ያዕ. 2:14ን ይጠቅሳል፤ አንዱም ስለጽኑ መተማመን ያስባል፥ ለማረጋገጫም ሮሜ 4:5ን የጠቅሳል፤ በቅዱስ ጳውሎስና በቅዱስ ያዕቆብም መካከል አለመስማማት ያለ ይመስላል። ይህ ግን በፍጹም ስሕተት ነው። ቅዱስ ጳውሎስ ስለ እውነተኛ እምነት፥ ስለ መተማመን፥ ሲናገር ቅዱስ ያዕቆብ የሚናገረው ስለ ራስ እውቀት ብቻ ነው።

እዚህ በዕ. 11:1 ላይ እውነተኛ እምነት ምን እንደ ሆነ እናያለን ምዕራፉም በሞላ ይህን እውነተኛ እምነት ያብራራል። የሽማግሌዎች እምነት ሁሉ ወደ ሥራ አድርሶአቸዋል። አብርሃም የተሰፋን ቃል ስላመነ ሥራ ሠራ። ረዓብም እግዚአብሔር አገሪቱን ለእስራኤላውያን ሰጥቶ እንደ ነበረ ስላመነች የተላኩትን መልእክተኞች ሸሸገች። አብርሃም በእምነት አቀረበ፥ ረዓብም በእምነት አልጠፋችም ተባለ። (ቁ. 17፥18፥31) ማለት፥ ሁለቱም የዳረጉትን ነገር ያደረጉቱ ስላመኑ ነው፤ ወይም ሥራቸውን የመነጨው ከእምነታቸው ነው ሊባል ይቻላል። እንደዚሁም ሥራቸው ለእምነታቸው መስክሮአል ይባላል፤ ስለምን? ቢሉ ያላመኑ ከሆነ ባልሠሩም ነበርና። ስለዚህ፥ መልካም ሥራ የእውነተኛ እምነት ማረጋገጫ መሆኑን እንረዳለን። በጎቹ በቀኝ የቆሙት በዚህ ምክንያት ነው። መልካም ሥራቸው እምነታቸውን አረጋግጦአል። (ማቴ. 25:31-40) መልካም ሥራ የሌለው እምነት በመጽሐፍ ቅዱስ ሐሳብ እምነት አይደለምና ቅዱስ ያዕቆብ «የሞተ ነው» ይለዋል። ስለዚህ ሁሉ «እምነት ያድናል» ሲባል አጋንንት የሚያምኑበት ዓይነት እምነት፥ የራስ ብቻ እምነት ሳይሆን (ያዕ. 2:19) በዕብ. ም. 11 ላይ የተነገረለት ዓይነት፥ ማለት መተማመን መሆኑን መገንዘብ ይገባናል። ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነገር ነውና ሕይወትን ሊሰጥ አይችልም። እንደዚሁም ከእምነት ያልመነጨ መልካም ሥራዎችም አሉ፤ እነኝህም እንደዚሁ ሁሉ ከእምነት የተለዩ ናቸውና የሞቱ ናቸው፥ ሕይወትንም ሊሰጡ አይችሉም። የሚያድን በዕብ. 11 ላይ የተነገረለት የሚሠራ፥ እምነት ነው።

ለ) በዚህ መልእክት ሐዋርያው በጠቅላላ በማደፋፈርም ሆነ በማስጠንቀቅ ዕብራውያንን ወደ ኋላ ከማፈግፈግ ሊጠብቃቸው ጥሮአል፤ እዚህም በም. 11 ላይ ሐሳቡን በመቀጠል «ጥንታውያኑን አበው እስኪ ተመልከቱ፤ እነርሱ እንደምን እንደጸኑና እንደ ታገሡ እዩ። ታዲያ፥ አሁን እናንተ ወደ ኋላ ትመለሳላችሁን?» ይላቸዋል።

ለመሆኑ ወደ ኋላ፥ የምንመለሰው በምን ምክንያት ነው?

1ኛ ምክንያት:- መንፈሳዊ ጤናችንን ስለማንጠብቅ ነው። «የዚህ ዓለም ሐሳብና የባለጠግነት ማታለል የሌላውም ነገር ምኞት» ገብተውብንም ሆነ (ማር. 4:19) እንቅልፍ ወደን ከአልጋችን መነሣት አስቸግሮንም ሆነ መንፈሳዊ ምግባችንን ማለት መጽሐፍ ቅዱስን

እንብበን በማሰላሰልና የግል ጸሎትንም በማድረግ ስለማንጠግብ ነው። ዳዊትን ሳንመስል ከመንፈሳዊ ቁርስ ይልቅ ሥጋዊን ወደናል! (መዝ. 18:10፤ 118:103) ይህ ወደ መድከም እንደሚያደርሰን የታወቀ ነው። መድኃኒቱስ? «ለእናንተ የምነግራችሁን ለሁሉ እላለሁ፤ ትጉም ጸልዩም» (ማቴ. 28:41፤ ማር. 13:37)

2ኛ ምክንያት፡- ከዚህ ዓለም ሰዎች ጋር ስለምንተባበር ነው። «አትሳቱ፤ ክፉ ባልንጀርነት መልካሙን አመል ያጠፋል» (1ኛ ቆሮ. 15:33) የእግዚአብሔር ሕዝብ ነው ብንልም የተለየን ልንሆን አንወድም። (1ኛ ጴጥ. 2:9) ለሁለት ጌቶች መገዛት እንወዳለን፤ እግዚአብሔርን ልንወድ እንፈልጋለን፥ በዓለም ያሉትንም ልንወድ እንፈልጋለን። ይህ ግን የማይቻል ነገር ነው፥ ከሁለቱ አንዱ እያነሰ የግድ ይሄዳል። (ማቴ. 6:24፤ 1ኛ ዮሐ. 2:15-16፤ ያዕ. 4:4) መድኃኒቱስ? «ከመካከላቸው ውጡና የተለያችሁ ሁኑ» (2ኛ ቆሮ. 6:14-18ን ተመልከቱ)

3ኛ ምክንያት፡- ዓለማዊ መሻሻልን ስለምንከታተል ነው። እንዲህ ያለ መሻሻል ዘወትር መጥፎ ነውን? ቢሉ፥ አይደለም፥ ነገር ግን መሻሻላችን ከክርስቶስ ቢለየን መጥፎ ነው። ክርሲትያኖች ሩጫ፥ አሽቅድድም፥ የሚሮጡ ሩዋጮች ናቸውና ሽክምን ማብዛት ወይም ግቡን መርሳት አይገባቸውም። (ዕብ.12:1-2) ጽድቅንና እግዚአብሔርን መምሰል እነኝህንም የሚመሳሰሉትን እንድንከታተል እንጂ ገንዘብና ምቾችን ማዕረግንም እንድንከታተል አልታዘዘንም። (1ኛ ጢሞ. 6:9-11) ሐዋርያቶቹን እንጂ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖችን እንምሰል። (1ኛ ቆሮ. 4:8-13) መድኃኒቱስ? «አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ» (ማቴ. 6:33) «ከደቀ መዛሙርቱ ብዙዎች ወደ ኋላ ተመለሱ። ኢየሱስም ለ12ቱ፡- እናንተ ደግሞ ልትሄዱ ትወዳላችሁን? አለ» (ዮሐ. 6:66-69) እኛላ?

## ቁ. 4-6

4 አቤል ከቃየል ይልቅ የሚበልጥን መሥዋዕት ለእግዚአብሔር በእምነት አቀረበ፥
በዚህም፥ እግዚአብሔር ስለ ስጦታው ሲመሰክር እርሱ ጻድቅ እንደሆነ
ተመሰከረለት፤ ሞቶም ሳለ በመሥዋዕቱ እስከ አሁን ይናገራል። 5 ሄኖክ ሞትን
እንዳያይ በእምነት ተወሰደ፥ እግዚአብሔርም ስለ ወሰደው አልተገኘም።
6 ሳይወሰድ እግዚአብሔርን ደስ እንዳሰኘ ተመስክሮለታልና፤ ያለ እምነትም ደስ
ማሰኘት አይቻልም፤ ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ
ለሚፈልጉትንም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና።

እምነት ምን እንደ ሆነ አይተናል። ወደ ሥራ የሚያደርስ መተማመን ነው። በም. 10:38፥39 ላይ ሐዋርያው የነቢዩን ቃል እየጠቀሰ «ጻድቅ በእምነት ይኖራል ወደ ኋላም ቢያፈገፍግ እግዚአብሔር በእርሱ ደስ አይሰኝም» ብሎአልና የማፈግፈግ ተቃራኒ የሆነው እውነተኛ እምነት እግዚአብሔርን ደስ እንደሚያሰኝና ወደ ጽድቅ እንደሚያደርስ ለማሳየት 2 ማስረጃዎችን፥ ማለት አንደኛ የአቤልን ሁለተኛም የሄኖክን አሁን ያቀርባል።

አቤል በእምነት መሥዋዕትን አቀረበ (ዘፍጥ. 4:3-5)፤ እምነቱ ሥራ አፈራ ማለት ነው። ይህ እውነተኛ እምነቱ እግዚአብሔርን ደስ አሰኘ። «እግዚአብሔር ወደ አቤልና ወደ መሥዋዕቱ ተመለከተ» ሲባል (ዘፍጥ. 4:3-5) እግዚአብሔር ተደስቶ «ይኸውላችሁ የፈለግሁት መሥዋዕት!» ብሎ እንደ መሰከረ ያስረዳል። የአቤል መሥዋዕት ለእምነቱ እውነተኛነት መስክር እግዚአብሔርን አስደስቶአል፥ ጽድቅ የሚቆጠርልንም ስናምን ነውና በዚህ፥ ማለት

በመሥዋዕቱ መቅረብ፥ አቤል ጻድቅ እንደ ሆነ ተመሰከሮአል። (ከዚህ ጋር ሮሜ 4፡18-25ንና ያዕ. 2፡21-23ን አነጦሩ) በተጨማሪ ደግሞ አቤል ቢሞት እንኳ እግዚአብሔር የሚፈልገውና የሚቀበለው መሥዋዕት እንዲይ ያለ መሆኑን እስከ አሁን ድረስ ያስረዳል።

የሄኖክም ነገር እንደዚሁ ነው። (ዘፍጥ. 5፡24) ሄኖክ በእግዚአብሔር ስላመነ አካሄዱን ከእርሱ ጋር አደረገ፤ እግዚአብሔርም በእውነተኛ እምነቱ ተደስቶ ወሰደው፥ አልተገኘምም። እግዚአብሔር በሄኖክ እምነት እንደ ተደሰተ በምን ይታወቃል? ቢሉ፥ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንዲሄድ በመፍቀዱ ነዋ! እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘው የአቤልና የሄኖክ እምነት ነበር፤ ያለ እምነትም ደስ ሊያሰኘው የሚችል የለም። ምክንያቱም፥ የሚሰግድለት ሰው እግዚአብሔር እንዳለ፤ ለሚለምነውም መልስ እንደሚሰጥ ካላመነ እንዴት አድርጎ ያስደስተዋል? እንግዲያውስ ዕብራውያን ከሚያምኑቱ ይሁኑ እንጂ ወደ ኋላ ከሚያፈገፍጉት አይሁኑ።

<u>ማ ስገንዘቢያ</u>፡- «አቤል ከቃየን ይልቅ የሚበልጥን መሥዋዕት አቀረበ።(ቁ. 4) የአቤል መሥዋዕት በምን በለጠ? ቢሉ፥ ብልጫው በእምነት መቅረቡ ነው። የኦሪት ዘፍጥረት ታሪክ እግዚአብሔር በአቤል መሥዋዕት እንደ ተደሰተ፥ በቃየን መሥዋዕት ግን እንዳልተደሰተ ግን ይነግረናል እንጂ ምክንያቱን አያስረዳንም። ወደ ዕብራውያን የተጻፈ መልዕክት ግን የእምነቱ ነገር ይጨምራልና እግዚአብሔር የተደሰተበቱ በአቤል እምነት መሆኑም እንረዳለን። ሁለቱ ወንድማማቾች ያቀረቡአቸው መሥዋዕቶች ከመልካሙ እንደ ነበረ አያጠራጥርም፤ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር በቃየን መሥዋዕት ደስ አልተሰኘም። ምክንያቱስ? በመሥዋዕቱ ዘንድ ጉድለት ስለ ተገኘ ነው። ጉድለቱስ ምን ኖሮአል? ቢሉ፥ ይኸው የዕብራውያን መልዕክት የሚያስታውቀን ነገር ነው፥ እምነት ጎደለበት። መቼ እንደ ሆነ አናውቅም እንጂ «ብዙ ቀን» ከተባለው ጊዜ ውስጥ (ዘፍጥ. 4፡3) እግዚአብሔር የመሥዋዕትን ነገር አስተምሮአቸው «የምቀበለው መሥዋዕት የደም መሥዋዕት ነው» ብሎአቸው ይሆናል። (ይህም ከዚህ በፊት፥ እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ካለበሳቸው ከቁርበት ልብስ ነገርና ከዚህ በኋላ፥ ከተደነገገው ከበግ መሥዋዕት ነገር ጋር ይስማማል።) አቤል የእግዚአብሔርን ቃል አምኖ በግን አቀረበ፤ ቃየን ግን አላመነውምና ከምድር ፍሬ አቀረበ፥ እግዚአብሔርም በቃየን መሥዋዕት ደስ አልተሰኘም።

የቃየን መሥዋዕት ከእምነት ያልመነጨ የመልካም ሥራ (ምግባር) እውነተኛ ምሳሌ ነው። ቃየን ለእግዚአብሔር መናኛ ነገርን ባላቀረበም ነበርና ከሁሉ ይልቅ መልካም የሆነውን ነገር ኖሮአል ልንል እንችላለን። ይሁን እንጂ፥ ያ ነገር እግዚአብሔርን ደስ አላሰኘም። እንደዚሁም የቃየንን መሥዋዕት የመሳሰሉ ከእምነት ያልመነጩ መልካም ሥራዎች ሁሉ እግዚአብሔርን ደስ አያሰኙም። ምክንያቱም፥ «ያለ እምነት ደስ ማሰኘት አይቻልምና» (ዕብ. 11፡6)

## ቁ. 7-12

7 ኖኅ ገና ስለማይታየው ነገር ተረድቶ እግዚአብሔርን እየፈራ ቤተ ሰቦቹን ለማዳን መርከብን በእምነት አዘጋጀ፥ በዚህም ዓለምን ኮነነ፥ በእምነትም የሚገኘውን ጽድቅ ወራሽ ሆነ።

8 አብርሃም የተባለው ርስት አድርጎ ሊቀበለው ወዳለው ስፍራ ለመውጣት
በእምነት ታዘዘ፥ ወዴትም እንደሚሄድ ሳያውቅ ወጣ።
9 ለእንግዶች እንደሚሆን
በተስፋ ቃል በተሰጠው አገር በድንኳን ኖሮ፥ ያን የተስፋ ቃል አብረውት
ከሚወርሱ ከይስሐቅና ከያዕቆብ ጋር፥ እንደ መጻተኛ በእምነት ተቀመጠ፤
10 መሠረት ያላትን፥ እግዚአብሔር የሠራትንና የፈጠራትን ከተማ ይጠብብቅ
ነበርና።
11 ተስፋ የሰጠው የታመነ እንደ ሆነ ስለ ቆጠረች፥ ሣራ ራስዋ ደግሞ

> ዕድሜዋ እንኳ ካለፈ በኋላ ዘርን ለመፀነስ ኃይልን በእምነት አገኘች። 12 ስለዚህ ደግሞ በብዛታቸው እንደ ሰማይ ኮከብ እንደማይቆጠርም በባሕር ዳር እንደአለ አሸዋ የነበሩት የሞተን ሰው እንኳ ከመሰለው ከአንዱ ተወለዱ።

እምነት በእግዚአብሔር ወይም በቃሉ መተማመንና አካሄዳችንን በዚሁ እምነት ማደራጀት ነው፤ ሐዋርያውም አሁን ይህንኑ ያደረጉትን የ3 ጥንታውያን ሰዎችን ታሪክ ይጠቅሳል።

ኖኅ እንደ ሄኖክ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረገ ሰው ሆኖ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምቶ ስላመነ ከባሕር በራቀና በደረቅ ምድር ላይ ከጥፋት ውኃ የሚድንበትን ታላላቅ መርከብ ሠራ። (ዘፍጥ. 6፡13-22) ውኃው አልታየም፤ ወደዚያ ቦታ የሚመጣ ከቶ አልመሰለም፤ ሆኖም ኖኅ «እግዚአብሔር ከተናገረ ይሆናል» ብሎ ተማምኖ ያላመኑትን ሰዎች ፌዝ እየቻለ መርከብን ሠራ፤ እንደ አቤልም ሆኖ በእምነት የሚገኘውን ጽድቅ ወራሽ ሆነ።

አስቀድሞ አብራም በኋላ ግን አብርሃም የተባለውም (ዘፍጥ. 17፡5) እንደዚሁ አደረገ። እግዚአብሔር ተናገረው የተስፋንም ቃል ሰጠው፤ አብራምም በቃሉ ተማምኖና ተስፋ የተደረገበትን ነገር እንደ ሆነ ነገር ቆጥሮ ወዴት እንደሚሄድ ስንኳ ሳያውቅ በእምነት ወጣ። (ዘፍጥ. 12፡1-4) በእምነት ወጣ በእምነትም ተቀመጠ። እግዚአብሔር «ለአንተና ለዘርህ ለዘላለም እሰጠዋለሁ» ብሎ ተስፋ በሰጠው አገር የእግር ጫማ ስንኳ የሚያህልን ርስት ሳይቀበል መሠረት በሌለው ድንኳን እድሜውን ሙሉ ኖሮ እንደ መጻተኛ፤ የውጭ አገር ሰዎች ያገር መኖሪያ ፈቃድ እየተሰጠው አብረውት ከሚወርሱት ከልጁና ከልጅ ልጁ ጋር የተስፋን ቃል መፈጸም እየተጠባበቀ በእንግድነት ተቀመጠ። (መዝ. 104፡8-13፤ የሐዋ. 7፡5) ይህንም ያደረገው እግዚአብሔርን ስላወቀና ከእርሱ ዘንድ ታላቅን ነገር ለማግኘት ስላሰበ፤ የተስፋንም ቃል እንደሚፈጽም ሙሉ መተማመንና ዋስትና ስላደረበት ነው። ምድራዊና አላፊ የሆነውን ዝቅተኛ ነገር ሳይሆን የሚበልጠውን፤ ሰማያዊና ነዋሪ የሆነውን ከፍተኛ ነገር ይፈልግ ነበር። መሠረት የሌለውንና እርሱ ዕለት ዕለት እንደ ተከለው ድንኳን ሳይሆን መሠረት ያላትን፤ እግዚአብሔር የሠራትንና የፈጠራትን ከተማ ይጠብቅ ነበር።

ሣራ የተባለችው የአብርሃም ሚስት ደግሞ በመጀመሪያ ላይ ምንም ብትጠራጠር ብትስቅም (ዘፍጥ. 18፡10-15) የተስፋን ቃል የሰጠው እግዚአብሔር መኖሩን በተረዳች ጊዜ ተስፋ የሰጠው የታመነ እንደ ሆነ ስለ ቆጠረች በማይቻለው አመነች፤ እምነትዋም ግሩም የሆነውን ውጤት አገኘ። በብዛታቸው እንደ ሰማይ ከዋክብት የሆኑት መንፈሳውያን ልጆችም፤ እንደማይቆጠር በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋ የነበሩት ሥጋውያን ልጆችም የሞተ ሆኖ ከታየው ከአንዱ ሰው ተወለዱ። (ሮሜ 4፡19-21)

ማስገንዘቢያ፡- ሀ) «ኖኅ . . . በዚህም ዓለምን ኮነነ» (ቁ. 7) ኖኅ ዓለምን እንዴት ኮነነ? ቢሉ፤ በእውነተኛ እምነቱ ኮነነው። አምኖአልና ሠራ። እግዚአብሔር «የጥፋተን ውኃ አመጣለሁ የምትድንበትን መርከብ ለአንተ ሥራ» ብሎ ቢያዝዘው ኖኅ አምኖ ሠራ። (ዘፍጥ. 6፡13-22) በ2ኛ ጴጥ. 2፡5 ላይ ኖኅ ጽድቅን እንደ ሰበከ ተጽፎአል። መርከብን ሲሠራ ሳለ ጎረቤቶቹና የአገሩ ሰዎች ሁሉ ተሰብስበው «ይህን የምታደርገው ለምንድር ነው?» ብለው ጠይቀውት ይሆናል፤ እርሱም እግዚአብሔር የተናገረውን ቃል ሰበከላቸው። እነርሱ ግን አላመኑምና ጠፉ። ኖኅ በእምነቱ በመተማመኑና በሥራው የሚያመካኙበትን ሁሉ ስላስወገደ፤ ዓለምን ኮነነ። (ማቴ. 12፡41)

## ቁ. 13-16

13 እነዚህ ሁሉ አምነው ሞቱ፥ የተሰጣቸውን የተስፋ ቃል አላገኙምና፤ ዳሩ ግን
ከሩቅ ሆነው አዩትና ተሳለሙት፥ በምድሪቱም እንግዶችና መጻተኞች እንዲሆኑ
ታመኑ። 14 እንዲህ የሚሉት ለእነርሱ የሚሆነውን አገር እንዲፈልጉ
ያመለክታሉና። 15 ያን የወጡበትን አገር አስበው ቢሆኑ ሊመለሱ ጊዜ በሆነላቸው
ነበር፤ 16 አሁን ግን የሚበልጠውን እርሱም ሰማያዊ አገር ይናፍቃሉ። ስለዚህ
እግዚአብሔር አምላካቸው ተብሎ ሊጠራ በእነርሱ አያፍርም፤ ከተማን
አዘጋጅቶላቸዋልና።

እነዚህ ሁሉ፥ ማለት አብርሃም ይስሐቅ ያዕቆብና ሣራ፥ የተስፋ ቃል ተሰጥቶአቸው እድሜአቸውን ሁሉ መፈጸሙን እየተጠባበቁ ኖሩ፥ እያመኑም ሞቱ። ይሁን እንጂ አብርሃም ከመሞቱ በፊት ይስሐቅ ተወልዶ ነበርና፥ ያዕቆብም ወደ ግብፅ በወረደ ጊዜ የአብርሃም ቤተሰብ በቁጥራቸው 70 ሰዎች ሆኖ ነበርና፥ (ዘፍጥ. 46:27) የመፈጸሙን መጀመሪያ አይተው ነበር የተሰጣቸውን የተስፋ ቃል ባያገኙ እንኳ መፈጸሙን ከሩቅ ሆነው አዩት። ጭው ባለ ሜዳ ላይ የሚጓዙት ነጋዴዎች የሚሄዱበትን ከተማ ከሩቅ ሆነው አይተውት «ዛሬ ባንደርስ እንኳ ግድ የለም፥ ነገ እንደርሳለን» እያሉ እንደሚሳለሙት እንዲሁም እነኝህ አበው የማይታየውን በእምነት ዓይን እያዩ በተስፋው ቃል መፈጸም እየተማመኑ ኖሩ እየተማመኑም ሞቱ። እግዚአብሔር ምድሪቱን ሊሰጣቸው መሐላ እየጨመረ የተስፋ ቃል ሰጥቶአቸው ነበር (ዘፍጥ. 12:7፤ 13:14-17፤ 24:7)፥ እነርሱም እግዚአብሔር በምሳሌ የሚያሳየውን በእውነተኛ ነገር እንደሚፈጽም አውቀዋልና ከነዓንን መውረስ ብቻ ሳይሆን ከከነዓን ምድር የምትበልጠውን፥ «መሠረት ያላትን፥ እግዚአብሔር የሠራትንና የፈጠራትን ከተማ» (ቁ. 10) ለመቀበል አምነው በነበሩባት ምድር ዘላኖችን መስለው ድንኳንን እየተከሉ ኖሩና በዚያች ምድር እንግዶችና መጻተኞች መሆናቸውን አመኑ። (ዘፍጥ. 23:4: 47:9) እንዲህም በማለት፥ እኛ «ኢትዮጵያችን» እንደምንለው ሁሉ እነርሱም ለእነርሱ የሚሆነውን የግል አገር እንደ ፈለጉ አመልክተዋል። ወደ እርሱ ሊመለሱ ምን ጊዜም በተቻላቸው ነበርና «አገራችንን እንፈልጋለን» ሲሉ በምድር ላይ፥ «በሁለት ወንዞች መካከል»፥ አብርሃም የወጣበትን አገር (የሐዋ. 7:5) ማለታቸው አልነበረም፤ ዳሩ ግን የተሰጣቸውን የተስፋ ቃል ተመልክተው የሚበልጠውን አገር፥ እርሱም በሰማይ፥ ሊቀበሉ ናፈቁ። እግዚአብሔር በተስፋ ቃሉ፥ «እኔ አምላካቸው እሆናለሁ» ብሎ ነበርና (ዘፍጥ. 17:7-8) የዚያን ተስፋ ፍጻሜ በልዩ አኳኋን መቀበል፥ ተማምነው ከእርሱ ጋር በኅብረቱ ለዘላለም ሊኖር አሰቡ። እያመኑ እንደዚህ አስበዋልና ኢየሱስ ያመኑትን ሰዎች «ወንድሞቼ» ብሎ ሊጠራቸው እንዳላፈረ (ዕ. 2:11-13) እንዲሁም እግዚአብሔር በዕብራውያን አበው እምነት ተደስቶ «የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ» ተብሎ ሊጠራ በእነርሱ አላፈረም። (ሉቃ. 20:37-38) እንደ ተስፋ ቃሉ፥ እንደ እምነታቸውም፥ አብልጦ አድርጎ ከተማን አዘጋጅቶላቸዋልና በዚህ ምክንያት ደግሞ አምላካቸው ሊባል አያፍርም። (ማቴ. 25:34፤ ዮሐ. 14:2)

<u>ማስገንዘቢያ</u>፡-

ሀ) «ከቁ. 8 ጀምሮ እስከ ቁ. 16 ድረስ «አገር» ወይም «ከተማ የተባለው ምንድር ነው?» ቢሉ፥ ያ ከመጀመሪያ ጀምሮ ስለ እርሱ ተጽፎ ያገኘነው፥ ምሳሌው ከነዓን የሆነው፥ ወተትና ማር የሚያፈስሰው «አገር» ነው። (በዕ. 3:19 ላይ መ) የተባለውን ማስገንዘቢያ፥ ደግሞ በዕ. 9:15 ላይ ሀ) የተባለውን ማስገንዘቢያ ተመልከት።) ሆኖም እኛ «አገር» ወይም

«ከተማ» ስንል እንደምናስበው ያለ ግዙፍ የሆነ ቦታ ሳይሆን ኑሮ ነው። ይህ «አገር» ይህም «ከተማ» በዳዊት ዘንድ «የእግዚአብሔር ከተማ» ይባላል (መዝ. 45፡4፤ 47፡1፥8፤ 96፡3) በአዲስ ኪዳንም «አዲሲቱ ኢየሩሳሌም» ይባላል። (ዕብ. 12፡22፤ ራእ. 3፡12፤ 21፡2) ኅብረትን በማግኘት የእግዚአብሔርን ሕይወት መካፈል ነው፤ ወደ ጥንቱ መልክ ምሳሌ መመለስ ነው፤ በሙሉ በፍጹምም መዳን ነው፥ የሰንበት ዕረፍት ነው፤ የምንቀበለው ርስት ነው፤ የሰውነታችን መቤዠት ነው፤ ዘላለማዊ ክብር ነው። እነኝህን ነገሮች ሁሉ ነው፥ በጠቅላላውም «የዘላለም ሕይወት» ይባላል። ይህ ሁሉ በእግዚአብሔር ተስፋ ቃል ተሰጥቶናል (1ኛ ዮሐ. 2፡25) መከራ የምንታገሥና በእምነት የምንጸና ይህንኑ በሙላቱ ለማግኘት ነው። ይህ አገር ወይም ከተማ ገና ነው፤ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር አዘጋጅቶታልና ይሆናል፥ ከዕለታት አንድ ቀንም ፍጹማን እንሆናለን። (ቁ. 39፡40)

ለ) «እግዚአብሔር አምላካቸው ተብሎ ሊጠራ በእነርሱ አያፍርም»። (ቁ. 16) ይህን ቃል ከም. 10 እና ከራእይ 3፡ 12 ጋር አንጣጥሩ። አንድ ተማሪ በደብተሩና በልብሱ ላይ ስሙን እንደሚጽፍ ያለ ነገር ነው። ይህን የሚያደርገው ዕቃው እንዳይጠፋበት፥ ሌላም ሰው ገንዘቤ ነው ቢል እርሱ «ሉሬ የእኔ ነው እንጂ፥ ስሜ ተጽፎበታል!» ሊል እንዲችል ነው። እንደዚሁ፥ ሁሉ እግዚአብሔር ስሙን በላያችን አድርጎ «እነርሱ የእኔ ናቸው፥ ባለቤታቸውም እኔ ነኝ» ይላል። እርሱ «የአብርሃም አምላክ የይስሐቅ አምላክ የያዕቆብም አምላክ» ተብሎ እንደ ተጠራው ሁሉ እንደዚሁም እያንዳንዳችን ስም ስማችንን አግብተን «የ (እገሌ) አምላክ ነው» ልንል እንችላለን። (መጋ. 2፡ 16) ይህም ምን ያለ መጽናናትን ይሰጠናል!

ሐ) እነዚህ ሁሉ አምነው ሲሞቱ እኛ ወደ ኋላ ተመልሰን ባለማመን ልንሞት ነውን? ሐዋርያው የሚጽፈው ለዕብራውያን ነው፤ ሆኖም ቃሉ ወደ እኛ ደርሶአል።

ሐዋርያው የእነዚህን ሰዎች ሁሉ ታሪክ ያቀረበው ዕብራውያን በፊታቸው ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንዲሮጡ ለማደፋፈር ነው። በአይሁድ ሥርዓትና በክርስቶስ ያመኑት ነበር። በመከራ ቀን ላልተው ወደ ኋላ ለመመለስ አሰበዋል። (ምሳሌ 24፡ 10) ሐዋርያው ግን የጥንቱን ሰዎች ጉልበት እያሳያቸው የመጀመሪያ እምነታቸውን እስከ መጨረሻው አጽንተው እንዲጠብቁ ይጎተጉታቸዋል። ዕብራውያን ከአይሁድ ሥርዓት ወጥተው ወደ ክርስትና እንዲመጡ እንደ ተጠሩ ሁሉ አብርሃም ከከለዳውያን ዑር ወጥቶ ወደ ከነዓን እንዲመጣ ተጠርቶአል። (ዘፍጥ. 15፡7) አብርሃም ሳያመነታ ወጣ፤ ዕብራውያንም እንዲሁ ያድርጉ። የተሰጠው የተስፋ ቃሉ መፈጸሙ የማይቻል ሆኖ ታያቸውን? እስኪ ሣራን ያስታውሱ። ለእርስዋ የተሰፍጠው የተስፋ ቃል እርስዋ አስቀድማ እስከትስቅ ድረስ፥ የማይቻል ሆኖ አልታያትምን? (ዘፍጥ. 18፡9-15) ይሁን እንጂ ተስፋ የሰጠው የታመነ እንደ ሆነ ስለ ቆጠረች እምነትዋ ታላቅ ውጤትን አገኘ። ዕብራውያንም እንደዚሁ ይመኑ የተስፋን ቃል የሰጠው በእርግጥ የታመነ ነውና። (ም. 10፡23)

እነዚያ አበው ወደው ቢሆኑ ሊመለሱ ጊዜ በሆነላቸው ነበር፤ ነገር ግን አልተመለሱም። ዕብራውያን አይመለሱ፥ እኛም አንመለስ።

ይህ ሁሉ የተጻፈ እኛን ለማስተማር ነው። (ሮሜ 15፡4) የተስፋ ቃል የማይቻል ወይም ለመቀበል የሚያደገት መሆኑ ይታየን ይሆናል። ይሁን እንጂ ተስፋ ቆርጠን ወደ ኋላ አፈግፍገን አንመለስ። እነዚያ አምነው ሞቱ፥ ይኸውላችሁ መጽናት! በዚህ ሕይወታቸው

አልተቀበሉትም፤ ባይቀበሉ እንኳ «ይሆናል!» ብለው እየፎከሩ ሞቱ። እምነት ማለት ይህ ነው። እኛስ ደካማዎች ነንን? ሣራን እናስታውስ! ተስፋ የሰጠውም የታመነ እንደ ሆነ እየቆጠርን የመጀመሪያ እምነታችንን እስከ መጨረሻው አጽንተን እንጠብቀው።

ጌቶቼ ሆይ፥ ለመሆኑ የዛሬ ሰው ምንኛ ሞኝ ነው! አንድ ጭልፋ ወጥ የሚመስለውን ታናናሽ ነገርን ለማግኘት እንዲህ ያለውን የዘላለም ርስት በቶሎ ይለቃል እኮ! (ም. 13፡16)

## ቁ. 17-31

[17-18] አብርሃም በተፈተነበት ጊዜ ይስሐቅን በእምነት አቀረበ፥ የተስፋን ቃል [19]
የተቀበለው፡- በይስሐቅ ዘር ይጠራልሃል የተባለለት እርሱም አንድ ልጁን አቀረበ፤
[20] እግዚአብሔር ከሙታን እንኳ ሊያስነሣው እንዲቻላቸው አስቦአልና፥ ከዚያም
ደግሞ በምሳሌ አገኘው። [21] ይስሐቅ ሊመጣ ስላለው ነገር ያዕቆብንና ዔሳውን
በእምነት ባረካቸው፥ ያዕቆብ ሲሞት በእምነት የዮሴፍን ልጆች እያንዳንዳቸው
ባረካቸው፥ በዘንጉም ጫፍ ተጠግቶ ሰገደ። [22] ዮሴፍ ወደ ሞት ቀርቦ ሳለ
በእምነት ስለ እስራኤል ልጆች መውጣት አስታወሰ ስለ አጥንቱም አዘዛቸው።

[23] ሙሴ ከተወለደ በኋላ ወላጆቹ ያማረ ሕፃን መሆኑን አይተው በእምነት ሦስት
ወር ሸሸጉት የንጉሥንም አዋጅ አልፈሩም። [24] ሙሴ ካደገ በኋላ የፈርዖን የልጅ
ልጅ እንዳይባል በእምነት እምቢ አለ፥ [25፥26] ከግብፅም ብዙ ገንዘብ ይልቅ ስለ
ክርስቶስ መነቀፍ እጅግ የሚበልጥ ባለ ጠግነት እንዲሆን አስቦአልና ለጊዜው
በኃጢአት ከሚገኝ ደስታ ይልቅ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራ መቀበልን
መረጠ፤ ብድራቱን ትኩር ብሎ ተመልክቶአልና። [27] የንጉሡን ቁጣ ሳይፈራ
የግብፅን አገር የተወ በእምነት ነበር የማይታየውን እንደሚያየው አድርጎ
ጸንቶአልና። [28] አጥፊው የበኩሮችን ልጆች እንዳይነካ ፋሲካንና ደምን መርጨትን
በእምነት አደረገ።

[29] በደረቅ ምድር እንደሚያልፉ በኤርትራ ባሕር በእምነት ተሻገሩ፥ የግብፅ ሰዎች
ግን ሲሞክሩ ተዋጡ። [30] የኢያሪኮ ቅጥር ሰባት ቀን ከዞሩበት በኋላ በእምነት
ወደቀ። [31] ጋለሞታይቱ ረዓብ ሰላዮችን በሰላም ስለ ተቀበለቻቸው ከማይታዘዙ
ጋር በእምነት አልጠፋችም።

በዚህ ክፍል ውስጥ ደራሲው አባታቸው ከሆነ ከአብርሃም ጀምሮ በተስፋው ቃል መሠረት ወደ ተሰጣቸው ወደ ከነዓን አገር እስኪገቡ ድረስ የእስራኤልን ሕዝብ ታሪክ ይከታተልና ተስፋው እስኪሞላላቸው ድረስ የእስራኤል መሪዎች ሁሉ እምነታቸውን እንደ ጠበቁና በእምነት እንደ ኖሩ ይተርካል።

አብርሃምን እግዚአብሔር ፈተነው፤ ይኸውም በእውነት የፈራው እንደሆን ለማወቅ ነው። (ዘፍጥ. 22፡1-19) የተስፋው ቃል የሚፈጸመው በይስሐቅ በኩል መሆኑን ራሱ እግዚአብሔር አስታውቆት ነበር። (ዘፍጥ. 17፡19፤21፤21፡12)፥ ቢሆንም «ይስሐቅን መሥዋዕት አድርገህ ሠዋው» እያለ አብርሃምን አሁን ያዝዛል። ይህማ ከተደረገ የተስፋው ቃል እንደምን ይፈጸም? ይሁን እንጂ፥ አብርሃም በእምነቱ ሳይደክም «እግዚአብሔር የተስፋውን ቃል ከመፈጸም ከቶ አይቀርም፥ ይስሐቅን ከሙታን ሊያስነሣው ቢያስፈልግ እንኳ ሊያስነሣው ይችላል፥ ያስነሣዋልም» ብሎ በእምነት ቆጥሮአልና ልጁን ወደ ሞት አቀረበው፤ ከዚያም እንደ ሆነ ደግሞ ተቀበለው።

ይስሐቅ የተሰጠውን የተስፋ ቃል መሠረት አድርጎ ልጆቹን በእምነት ባረካቸው። (ዘፍጥ. 27፡27-29፥39፥40፤ ዘፍጥ. 12፡2፥3፤ 13፡15፥16)

ያዕቆብም ሊሞት ነው። ብዙ ዓመት፥ መቶ አርባ ሰባት ዓመት፥ ኖሮአል (ዘፍጥ. 47፡28)፥ የተስፋውን ቃል ግን አላገኘም። ቢሆንም እምነቱ ያው የጸና ነው። እንደ ተስፋው ቃል ሁሉ የአብርሃም ልጆች እንደሚበዙና ምድሪቱም የእነርሱ እንደምትሆን ተማምኖአልና የዮሴፍን ልጆች በተስፋው ቃል መሠረት ባረካቸው፤ ራሱም የተስፋውን ቃል ባለመቀበሉ ሳይቀየም ለመገበውና ከክፉ ነገር ሁሉ ለጠበቀው አምላክ ምስጋናና ስግደትን እያቀረበ ሞተ። (ዘፍጥ. 48፡9-22፤ 47፡31)

ዮሴፍ እንደ አባቱ እንደ ያዕቆብ ሆኖ ለሞት ተቃርቦአል። የአብርሃም ቤተ ሰብ በሞላ በተስፋ ቃል ከተሰጠው አገር ወጥቶ በምድረ ግብፅ ተገኝቶአል። ይሁን እንጂ ዮሴፍ የተስፋውን ቃል አስቦ «ትወጣላችሁ፥ እግዚአብሔር ተናግሮአልና 400 ዓመት ያህል ብትቆዩ እንኳ ትወጣላችሁና አጽሜን እንድትወስዱ አደራችሁን!» ብሎ ወንድሞቹን አማላቸው። (ዘፍጥ. 15፡13፤ 50፡22-26)

ሙሴ በጭንቀት ጊዜ ተወለደ። ለአብርሃም የተባለለቱ 400 ዓመት አልፎአል፥ ቤተ ሰቡም ታላቅ ሆኖአል። የግብፅ ንጉሥ «የእስራኤል ልጆች ሕዝብ በዝተው በጦርነት ጊዜ እንዳያሸንፉን» ብሎ የሚወለደው የእስራኤል ወንድ ልጅ ሁሉ ወደ ወንዝ እንዲጣል አዘዞአል። በተስፋው ቃል ላይ ያረፈ የእስራኤላውያን እምነት ግን አልበረደም፥ የሙሴ ወላጆችም የእምነት ሰዎች ነበሩ። ተስፋውን እያዩ ተማምነዋል፥ የንጉሥን አዋጅ ሳይፈሩ ሙሴን 3 ወር ሸሸጉት። እንደ ወላጆቹ ሁሉ እንዲሁም ሙሴ የእምነት ሰው ነበረ። ያደረገው ሁሉ በእምነቱ ተገዝቶአል። የተስፋን ቃል አምኖአል፥ ስለዚህ ያደረገውን ሁሉ አድርጎአል። የፈርዖን የልጅ ልጅ እንዳይባል እምቢ ያለው፥ የግብፅን አገር የተወው፥ ፋሲካንም ያደረገው በእምነት ነው። በተስፋው ቃል ስለ ተማመነ፥ ብድራቱን ትኩር ብሎ ስለ ተመለከተና የማይታየውን አምላክ እንደሚያየው አድርጎ ስለ ጸና፥ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ሆኖ ባሪያ መሆንንና መነቀፍን መከራ መቀበልንም መረጠ እንጂ ከግብፃውያን ጋር ሆኖ ክብርንም ሆነ ባለጠግነትን ደስታንም መቀበል አልፈለገም። በእርሻ ውስጥ የተሰወረን መዝገብ አግኝቶ፥ ወይም ዋጋዋ እጅግ የበዛ መልካምን ዕንቁ አግኝቶ ከደስታው የተነሣ ሄዶ ያለውን ሁሉ የሸጠውን ሰው መስሎ የዓለምን ነገር ሁሉ ንቆአል። (ማቴ. 13፡34-36፤ ዕብ. 12፡2) እንደዚሁም «እኔ በዚያች ሌሊት በግብፅ አገር አልፋለሁ በኩርንም ሁሉ እገድላለሁ፤ ደሙም ባላችሁበት ቤት ምልክት ይሆንላችኋል፤ ደሙንም ባየሁ ጊዜ ከእናንተ አልፋለሁ» የተባለው የእግዚአብሔርን ቃል አምኖ አጥፊው መልአክ ሲያልፍ እንዳይነካቸው ፋሲካንና የደምን መርጨትን አደረገ። (ዘጸአ. 12፡12፥13፥21-24) ይሁን እንጂ፥ ፋሲካንና ደም መርጨትን ሲደነግግ ያመነበቱ እግዚአብሔር ስለሚመጣው መልአክና ስለሚያድነው ደም በተናገረው ቃል ብቻ ሳይሆን ስለ ምድሪቱ በተናገረው ቃል ጭምር አምኖአል። (ዘጸአ. 12፡25) የአባቶች አለቆችና የሙሴ እምነት ወደ እስራኤል ሕዝብ ተላልፎአልና የኤርትራን ባሕር የተሻገሩት በተስፋ ቃል በማመን ነው፤ የኢያሪኮንም ኃይል ያሸነፉት እንደዚሁ ነው። (ዘጸአ. 14፡15-18፥ 21፥ 22፤ ኢያ. 6፡2-5፤ 8-21) በዚያው እምነት ደግሞ ጋለሞታይቱ ረዓብ ራስዋን ከሞት አዳነች። እንደምን? ቢሉ፥ «እኔ በእግዚአብሔርና እርሱ በሰጣችሁ የተስፋ ቃል አምናለሁ፥ እግዚአብሔር ይህችን አገር እንደሚሰጣችሁ አውቃለሁ» እያለች (ኢያ. 2፡9-11) ሁለቱን ሰላዮች ስለ ተቀበለችና በደኅና ስለ ሰደደች ነው። በተነገረው ቃል አመነች ሠራችም። ስለዚህ ከማይታዘዙት ሕዝብ

ሳትቆጠር ከእስራኤል ሕዝብ ተቆጠረችና በተቀደሰ ትውልድ ውስጥ ገባች። (ኢያ. 6፡25፤ ማቴ. 1፡5፤ ኤፌ. 2፡11-13፥19)

__ማስገንዘቢያ__፡-

ሀ) «አብርሃም . . . ይስሐቅን በእምነት አቀረበ፥ ከዚያም (ከሙታን) ደግሞ በምሳሌ አገኘው።» (ቁ. 17-19) በዘፍጥ. 22፡2 ላይ እንደ ተጻፈው ሁሉ እግዚአብሔር የአብርሃምን እምነት በፈተነ ጊዜ «ይስሐቅን ይዘህ ወደ ሞሪያም ምድር ሂድ፥ እኔም የምነግርህ በአንድ ተራራ ላይ በዚያ መሥዋዕት አድርገህ ሠዋው» ብሎ አዘዘው። አብርሃምም ሳይጠራጠር ማለዳ እንደ ተነሣና እግዚአብሔር ወዳለው ቦታ ሄዶ መሠውያውን እንደ ሠራ፥ እንጨትንም እንደ ረበረበ ልጁንም ይስሐቅን አስሮ በመሠውያው ላይ እንዳጋደመውና ያርደው ዘንድ ቢላዋን እንዳነሣ እናውቃለን። ነገር ግን የእግዚአብሔር መልአክ ስለ ከለከለው ይስሐቅን አልሠዋውም አላረደውም። እዚህ በዕብራውያን መልእክት ክፍላችን ላይ «አብርሃም ልጁን አቀረበ» ይላል፤ ማለቱም፥ መሥዋዕት አድርጎ ሠዋው መሆኑ አይጠረጥርም። አብርሃም ግን ልጁን መሥዋዕት አድርጎ አልሠዋውም። ይሁን እንጂ፥ በአብርሃም ልብና ሐሳብ ውስጥ በሥዋዕቱ ተሠውቶአል። ይስሐቅ አልሞተም እንጂ አብርሃም እስከ ሞት ጫፍ ድረስ አቀረበው። ልጁ በእርግጥ አልሞተምና በዚህ ምክንያት ደራሲው «ከዚያ (ከሙታን ደግሞ በምሳሌ አገኘው» ይላል። አልሞተምና ከሙታን አገኘው» ሊል አይችልም። ሆኖም ይስሐቅ ልክ እንደ ሞተ ነበርና አብርሃም ልክ ከሙታን እንዳገኘው እውነት ነው። እንግዲያውስ «በምሳሌ አገኘው» ማለት ልክ ከሙታን እንዳገኘው ተቀበለው ማለት ነው።

ለ) «ያማረ ሕፃን መሆኑን አይተው» (ቁ. 23) በሙሴ ዘንድ ልዩ የሆነ አንዳች ነገር የነበረ ይመስላል፤ ምክንያቱም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ማማሩ 3 ጊዜ ተጠቅሶአል። (ዘጸአ. 2፡2፤ የሐዋ. 7፡20፤ ዕብ. 11፡23) 3 ጊዜ መጠቀሱም መገንዘብ የሚገባን ነገር መሆኑን ለማመልከት ነው። (የሐዋ. 10፡16) ነገሩን እንድናስተውል የተስፋውን ቃል መመርመር ነው። በዚያ በተስፋው ቃል ውስጥ «የምድር ነገዶች ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ» የሚሉ ቃሎች ተገኝተዋል። (ዘፍጥ. 12፡3፤ 22፡18) በዚህ ምክንያት የተስፋውን መፈጸም በእምነት ይጠባበቁ የነበሩ የእስራኤል ሕዝብ የሚያድናቸውን ሰው ከጥንት ጀምሮ ይጠባበቁ ነበር። በብሉይ ኪዳን ዘመን ፍጻሜ ላይ አንዳንዶች የእስራኤል ሰዎች የእስራኤልን መጽናናት ይጠባበቁ እንደ ነበር (ሉቃ. 2፡25፥38፡ 23፡51፤ 24፡21) እንዲሁም የክርስቶስ ምሳሌ የሆነ ሙሴ በተወለደበቱ ዘመን የእስራኤል ሕዝብ የእግዚአብሔር መድኃኒት የሚሆንላቸውን ይጠባበቁ ነበር (ዘፍጥ. 49፡18)፤ ይህንም አብዝተው ያደረጉት በጽኑ መከራ ተይዘው ስለ ነበር ነው። እንግዲያውስ የሙሴ ወላጆች ልዩ የሆነ ማማሩን ባዩ ጊዜ «በተስፋው ቃል የተነገረለት ይኸው ነው» እያሉ እግዚአብሔር እንደሚጠብቀውና ለታላቅ ሥራ እንደሚያበቃው አምነው የንጉሡን አዋጅ ሳይፈሩ 3 ወር ሸሸጉት። (ይሁን እንጂ ኢሳ. 52፡14፤ 53፡2 ተመልከት) ሐ) «ስለ ክርስቶስ መነቀፍ» (ቁ. 26) «በሙሴ ዘመን ክርስቶስ አልመጣም ነበርና ስለ እርሱ ብሎ መነቀፍ እንደምን ችሎአል?» ቢሉ፥ አይደለም ሙሴ ስለ ክርስቶስ ብሎ እንደ ተነቀፈ አይደለም። ደራሲው የሚጽፈው ለዕብራውያን ነው፥ እነርሱም ስለ ክርስቶስ መነቀፍን በጣም አውቀዋል። (ም. 10፡32፥33) እንግዲያውስ ሙሴ «እስራኤላዊ ነኝ እንጂ የፈርዖን የልጅ ልጅ አይደለሁም» ሲል የደረሰበቱ ነቀፋና ዕብራውያን «ክርስቲያኖች ነን እንጂ የአይሁድን ሥርዓት የምንከተል አይደለንም» ሲሉ የደረሰባቸው ነቀፋ ተመሳስለዋልና ሐዋርያው በእነርሱና በሙሴ መካከል

ለ) ወንድሜ ሆይ ስማ ልንገርህ። በክርስቲያን ኑሮ ወደ ፊት፥ ወደ ፍጻሜ፥ እንዳትሄድ የሚከለክልህ እንደ ኤርትራ ባሕርና እንደ ኢያሪኮ ያለ እንቅፋት በፊትህ ተቀምጦአልን? ከተቀደሰ ሕዝብስ እንዳትቆጠር የሚቃወም ረዓብን የተቃወመ ብርቱ ብርቱ ምክንያት አለን? እስኪ ተመልከት። የእስራኤል ልጆች የኤርትራን ባሕር ተሻገሩ፥ በኢያሪኮ ቅጥርም ላይ ቆሙ፤ ረዓብም ጋለሞታና ከነዓናዊት ብትሆንም ከእስራኤል ሕዝብ ለመቆጠር ደረሰች። «በምን?» ትላለህን? በእምነት! የበቂት በእግዚአብሔር ቃል እያመኑ በመራመድ ብቻ ነው። አንተም እንደዚሁ በእምነት ተራመድ፥ ባሕርም ይከፈላል፥ ቅጥርም ይወድቃል፥ ከተቀደሰም ሕዝብ ትቆጠራለህ።

## ቁ. 32-38

32 እንግዲህ ምን እላለሁ? ስለ ጌዴዎንና ስለ ባርቅ ስለ ሳምሶንም ስለ ዮፍታሔም
ስለ ዳዊትና ስለ ሳሙኤልም ስለ ነቢያትም እንዳልተርክ ጊዜ ያጥርብኛልና።
33 እነርሱ በእምነት መንግሥታትን ድል ነሡ፥ ጽድቅን አደረጉ፥ የተሰጠውን
የተስፋ ቃል አገኙ፥ 34 የአንበሶችን አፍ ዘጉ፥ የእሳትን ኃይል አጠፉ፥ ከሰይፍ
ስለት አመለጡ፥ ከድካማቸው በረቱ፥ በጦርነት ኃይለኞች ሆኑ፥ የባዕድ ጭፍሮችን
አባረሩ። 35 ሴቶች ሙታናቸውን በትንሣኤ ተቀበሉ፤ ሌሎችም መዳንን ሳይቀበሉ
የሚበልጠውን ትንሣኤ እንዲያገኙ እስከ ሞት ድረስ ተደበደቡ፤ 36 ሌሎችም
መዘበቻ በመሆንና በመገረፍ ከዚህም በላይ በእስራትና በወኅኑ ተፈተኑ፤
37 በድንጋይ ተወግረው ሞቱ፥ ተፈተኑ፥ በመጋዝ ተሰነጠቁ፥ በሰይፍ ተገድለው
ሞቱ፥ ሁሉን እያጡ መከራን እየተቀበሉ እየተጨነቁ የበግና የፍየል ሌጦ ለብሰው
ዞሩ፥ 38 ዓለም አልተገባቸውምና በምድረ በዳና በተራራ፥ በዋሻና በምድር ጉድጓድ
ተቅበዘበዙ።

ማስረጃዎቹ በዝተዋል! በእስራኤል ታሪክ ውስጥ በእምነታቸው የተመሰከረላቸው ብዙ ናቸው፥ ስለ ሁሉም፥ ለመተረክ ጊዜ ያጥራል። በቁ. 32 ላይ ከመሳፍንትና ከነገሥታት ከነቢያትም ጥቂቶች ቢጠቀሱም እነኝህ ምሳሌዎች የሚሆኑት ናቸው እንጂ እነርሱን የመሳሰሉት ብዙዎች አሉ። እነኝህ ሁሉ ከእምነታቸው የተነሣ ታላላቅን ነገር አደረጉ። በመካከላቸው ከባዕድ መንግሥታት ጋር ታግለው ድል የነሡ እነጌዴዎንና ባርቅ፥ እነዮፍታሔና እነዳዊት አሉ፤ በቅን ፍርድ የፈረዱ መሳፍንቶቹና ዳዊትም አሉ (1ኛ ሳሙ. 12፡3-5፤ 2ኛ ሳሙ. 8፡15)፤ የተሰጣቸውን የተስፋ ቃል ያገኙ እነኢያሱና እነጌዴዎን እነዳዊትም አሉ (ዘዳግ. 31፡7፤ መሳ. 6፡14-16፤ 1ኛ ሳሙ. 16፡13)፤ የአንበሶችን አፍ የዘጉ እነዳዊትና እነዳንኤል አሉ (1ኛ ሳሙ. 17፡34-36፤ ዳን. 6፡16-23)፤ ሽታው እንኳ እስከማይደርስባቸው ድረስ የእሳትን ኃይል ያጠፉ እነ3ቱ ደቂቅ አሉ (ዳን. 3፡19-28)፤ በሰይፍ ከመገደል የዳኑ እነዳዊትና እነኤልሳዕ አሉ (1ኛ ሳሙ. 17፡45-51፤ 2ኛ ነገ. 6፡14-17)፤ በሰውነታቸው ደካማዎች የሆኑት ነገር ግን እጅግ የበረቱ እነሳምሶንና እነመቃብያን አሉ (መሳ. 16፡28-36)፤ በጦርነቱ የጀብዱ ሥራ የሠሩና የባዕድ ጭፍሮችን ያባረሩ በመጽሐፍ ቅዱስ የምናነብላቸውና በመቃብያን ዘመንም የተገኙቱ አሉ። ሴቶች እንኳ በእምነት ስለ በረቱ የሞቱትን ልጆቻቸውን በትንሣኤ ተቀበሉ (1ኛ ነገ. 17፡17-24፤ 2ኛ ነገ. 4፡32-37)፤ ሌሎች ሰዎችም አሁንም በተለይ ወደ መቃብያን ዘመን እንሻገራለን፥ የሚበልጠውን ትንሣኤ፥ ማለት ሁለተኛ ሊሞቱ ተነሥተው ወደዚህ ዓለም መመለስን ሳይመኙ ለዘላለም ሊኖሩ በመንግሥተ ሰማያት መነሣትን ወድደው ከሥቃይ ሊድኑ ሳይፈቅዱ በመኪና ላይ ተገትረው ሲደበደቡ እስከ ሞት ድረስ ታገሡ። ከእነዚህም ሌሎች ስለ ሃይማኖታቸው ብለው መዘበቻ በመሆንና በልዩ ልዩ አኳኋን በመገረፍና

በመታሰር የተፈተኑ እነመቃብያን እነሐዋርያት እነጳውሎስም አሉ (ም. 10፡32-33፤ የሐዋ. 5፡40-41፤ 2ኛ ቆሮ. 11፡23-27) በድንጋይ ተወግረው የሞቱ እነዘካርያስና እነእስጢፋኖስ አሉ፤ (2ኛ ዜና 24፡20-21፤ የሐዋ. 7፡59)፤ «ይህን ትናገር ወይም ታደርግ እንደ ሆነ ከሥቃይ አርፈህ ተፈትተህ ትለቀቃለህ» እየተባሉ ሃይማኖታቸውን ይክዱ ዘንድ የተፈተኑ በመቃብያን ዘመን ብዙዎች አሉ፤ የታሪክ መጽሐፍ ነቢዩ ኢሳይያስ በምናሴ ዘመን በመጋዝ እንደ ተሰነጠቀ ይነግረናል፤ እንደ ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ በሰይፍ ተገድለው የሞቱ አሉ (የሐዋ. 12፡2)፥ ሁሉም ተዘርፎባቸውና ሰው ከሚኖርበት አገር ተሰድደው ቤትም ሆነ ልብስ እያጡ የበግና የፍየል ሌጦ ለብሰው በምድረ በዳና በተራራ እየዞሩና በዋሻና በምድር ጉድጓድ እየኖሩ የተቅበዘበዙ አሉ። ይህን ሁሉ የታገሡቱ እግዚአብሔር በሰጠው በተስፋ ቃል ስላመኑና መፈጸሙን ለመቀበል ስለ ተማመኑ ነው።

<u>ማስገንዘቢያ፡-</u>

ሀ) ስለ መቃብያን። መቃብያን የተባሉቱ ክርስቲያኖች አይደሉም፤ ቢሆንም ለሃይማኖት ብለው ታላቅ ተጋድሎ የተጋደሉ ናቸው። የኖሩበት ዘመን ከክርስቶስ በፊት 150 ዓመት ያህል፥ ማለት በብሉይ ኪዳን ዘመንና በአዲስ ኪዳን ዘመን መካከል ነው። በዚያ ዘመን እጅግ በጣም ጨካኝ የሆነ የሶርያ ንጉሥ የእስራኤልን አገር ይገዛ ነበር፥ እነርሱም አይሁድ ሁሉ እግዚአብሔር የሰጠውን ሥርዓት ትተው ርኩስን ሥጋ እንዲበሉና እርሱ ባሠራቸው መሠውያዎች ላይ መሥዋዕትን ለሶርያ አማልክት እንዲያቀርቡ ትእዛዝ አወጣ። እንዳይገረዙም ሰንበትን እንዳያከብሩ አዘዘ። እሺ የማይሉም ሁሉ፥ ወንዶችም ሴቶችም፥ በማይነገር ጭካኔ ተሠቃዩ። ይህ ሲሆን ሞዲን በሚሉት ለኢየሩሳሌም ቅርብ በሆነ ከተማ ውስጥ 5 ወንዶች ልጆች የነበሩት ማታትዩ የሚባል አንድ ካህን ነበረ። ይህ ሰው ለእግዚአብሔር ሕግ እጅግ ይቀና ነበር፥ ከዕለታትም አንድ ቀን አይሁዳዊ የሆነ ሰው እሺ ብሎ መሥዋዕት በንጉሡ መሠዊያው ላይ ማቅረቡን አይቶ ተናደደና አይሁዳዊውን የንጉሡንም መኮንን ገድሎ «ለእግዚአብሔር ሕግ የምትቀኑ ሁሉ ከእኔ ጋር ሁኑ» እያለ 5ቱን ልጆች አስከትሎ ወደ በረሃ ሄደ። በተጨማሪ የተሰጠው ስም በግሪክ ቋንቋ ሲተረጎም መቃባዩስ የሆነ ይሁዳ የተባለው 3ተኛ ልጁ አለቃቸው ሆነና ወደ እነርሱ የተሰበሰቡቱ አገራቸውን እስኪያስለቅቁ ድረስ በሶርያ ንጉሥ ላይ ብርቱ ጦርነት አደረጉ። እንግዲያውስ መቃብያን የተባሉቱ ይሁዳና ወንድሞቹ ተከታዮቻቸውም ናቸው።

ለ) «የበግና የፍየል ሌጦ ለብሰው ዞሩ» (ቁ. 37) ይህንም ያደረጉቱ ነቢያት ወይም ተማሪዎች እንደሚያደርጉት በልማድ ሳይሆን ከሰው መኖሪያ እንደ አውሬዎች ስለ ተሰደዱና ሁሉን ስላጡ ነው። ቤት ስላጡ ለጊዜው የሚሆንላቸውን መኖሪያ ፈልገው መዞር፥ ልብስም ስላጡ የበግና የፍየል ሌጦ መልበስ የግድ ሆነባቸው።

ሐ) «ዓለም አልተገባቸውም» (ቁ. 38)። በዓለም ግምትና በእግዚአብሔር ግምት መካከል ያለውን ልዩነት ተመልከቱ። የዓለም ሰው «በዓለም ሊኖሩ አይገባቸውም» ብሎ ከዓለም አሳደዳቸው። የእግዚአብሔር ቃል ግን «ዓለም አልተገባቸውም» ይላል! (ዮሐ. 15፡18-21)

መ) ሐዋርያው «አባቶቻችሁ የተጋደሉትን ተጋድሎ የታገሡትን መከራ ሁሉ አስታውሱ። እነርሱ እምነታቸውን እስከ መጨረሻው አጽንተው እንደ ጠበቁ እናንተም ጠብቁት» ሲል ነው። ለዕብራውያንም ሆነ ለእኛ በእምነት መኖር ምን ጊዜም ቀላል ነገር አይደለም። ይሁን

እንጂ እነዚያ የጥንት ሰዎች ምንኛ ቻሉ! የተሰጠውን የተስፋ ቃል አዩ አመኑበትም፥ «እስከንቀበል ድረስ አንለቅም» ብለው ጸኑ። (ዘፍጥ. 32፡26) የተወደድህ እንባቢ ሆይ፥ አንተስ? ትለቀዋለህን? እስከ አሁን ድረስ ቻልህ፤ አንሁን ወደ ኋላ ታፈገፍግ ጀምረኃልን? አፈግፍገህ እንደ ሆነ «ጻድቅ በእምነት ይኖራል ወደ ኋላም ቢያፈገፍግ ነፍሴ በእርሱ ደስ አይላትም» የተባለውም ቃል አስበህ አረግመድህን አጽና። (ም. 10፡38)

## ቁ. 39፡40

39፡40 እነዚህም ሁሉ በእምነታቸው ተመስክሮላቸው ሳሉ የተሰጠውን የተስፋ ቃል አላገኙም፤ ያለ እኛ ፍጹማን እንዳይሆኑ እግዚአብሔር ስለ እኛ አንዳች የሚበልጥ ነገርን አስቀድሞ አይቶ ነበርና።

እግዚአብሔር በዚህ ምዕራፍ ላይ የተጠቀሱትን ሰዎች ሁሉ እምነት አይቶ ደስ አለው፥ መሰከረላቸውም። ይሁን እንጂ የተሰጠውን የተስፋ ቃል አላገኙም። ምነው? ቢሉ፥ እነርሱ የደኅንነትን ፍጹምነት ከማግኘታቸው በፊት አብረናቸው እንድንገባረከ እግዚአብሔር አስቀድሞ ስላሰበ ነው።

ማስገንዘቢያ፡-

ሀ) «የተሰጠውን የተስፋ ቃል አላገኙም» የተሰጠውን የተስፋ ቃል መቀበልና ፍጹማን መሆን ያው ነው። ሁለቱም ቃሎች አንድ ናቸው። እነዚያ በም. 11 ላይ የተጠቀሱቱ ሁሉ የተስፋ ቃል አላገኙም፥ ባያገኙም ቅሉ መፈጸሙን ከሩቅ ሆነው አዩ በእምነትም ሞቱ። አንባቢዎቼ የተሰጠው የተስፋ ቃል ምን እንደ ሆነ ከዚህ በፊት ሳይረዱ አልቀሩም። የተስፋው ቃል ፍጹም የሆነ መድኅን ያገኘልን ፍጹም የሆነውን መዳንና የዚያን መዳን ፍጹምነት ነው። ያንም መዳን መቀበል ፍጹም መሆን ማለት ነው። ከዚህ በፊት እንደ ተባለው ሁሉ፥ ከሁሉ መዳን ነው። በቁ. 13-16 ላይ በማስገንዘቢያ ሀ) እንዳየነው ሁሉ በዚህ መልእክት ውስጥ በልዩ ልዩ ነገር ተመስሎአል። ወተትና ማር የምታፈስስ፥ ከነዓን የተባለችው፥ ያች የዕረፍት አገር ናት (ም. 4፡1-16)፤ ያ የዘላለም ርስት ነው (ም. 9፡15)፤ ሽማግሌዎቹ ይናፍቁ የነበሩት ያን ከተማ ነው (ም. 11፡13-16)፤ በሌላ መጽሐፍ ተጽፎ እንደምናገኘው ያ ሰውነታችን ቤዛ ነው (ሮሜ. 8፡23)፤ ያ የሥጋችን መለወጥ ነው (ፊልጵ. 3፡21፤ 1ኛ ቆሮ. 15፡51-54)፤ ወደ ቀድሞ መልክ ምሳሌ መመለስ ነው (1ኛ ዮሐ. 3፡1)፤ የዘላለም ክብር ነው። (ሮሜ 8፡30፤ ቆላ. 3፡4፤ 2ኛ ጢሞ. 2፡10) ሙሉ መዳን ወይም የመዳን ፍጹምነት ይኸው ነው፤ የተሰጠውም የተስፋ ቃል ይኸው ነው። እነዚያ የአባቶች አለቆች በከፊል በምሳሌ ተቀብለውታል እንጂ ፍጹምነቱን እስከ አሁን አልተቀበሉም፤ የሚቀበሉት ክርስቶስ በዳግም ምጽአት ሲመጣ ነው።

ለ) «ስለ እኛ አንዳች የሚበልጥ ነገርን አስቀድሞ አይቶ ነበር» ምኑን አይቶልን ይሆን? ብለው ቢጠይቁ እኛ አብረናቸው እንድንፈጸም ነው። በማቴ. 20፡1-16 ላይ ተጽፎ እንደሚገኘው ያለ ነገር ነው። በዚያ ክፍል ላይ ባለቤት ሰው ለወይኑ አትክልት ሠራተኞችን ሊቀጥር ማለዳ፥ በ3 ሰዓት በ6፥ በ9፥ በ11 ሰዓትም ወጣ። በመሸ ጊዜ አዛዡን ጠርቶ «እኩል አድርገህ አንድ አንድ ብር ስጣቸው» አለው። ፊተኞቹ ሲቀርቡ ከኋለኞቹ አብዝተው የሚቀበሉ መሰላቸው፤ ባለቤትዮው ግን ለኋለኞቹ አንዳች የሚበልጥ ነገርን አስቦ ነበርና ኋለኞቹ ከፊተኞቹ ጋር አስተካከለ። እግዚአብሔር ስለ እኛ ያየው ነገር እንደዚሁ ነው። እኛ

ከእነርሱ ጋር ያን የክብር ቀን እንድንካፈል እግዚአብሔር እነርሱን አዘግይቶአል። (ራእ. 6፡9-11) (ሮሜ 11፡33-36)

እንግዲያውስ ከእነርሱ ጋር አብረን ልንካፈል ነንና የላሉትን እጆች የሰለሉትን ጉልበቶች አቅንተን ያን የመጀመሪያ እምነታችንን አጽንተን እስከ መጨረሻው እንጠብቀው እንጂ ወደ ኋላ አናፈገፍግ፤ እንጠብቀውም እንደሆነ የምናገኘው መዳን እንዲህ ያለውን መዳን ከሆነ በቀላሉ አንጣለው። (ዕ. 12፡12፥16)

# ምዕራፍ አሥራ ሁለት

## አማኝ በተስፋ ይታገሣል

ም. 11 ስለ እምነት የሚናገር ምዕራፍ እንደ መሆኑ መጠን ም. 12 ደግሞ ስለ ተስፋ የሚናገር ምዕራፍ ነው። ደራሲው የሽማግሌዎችን እምነት በማስታወስ ዕብራውያን ክርስቲያኖችን እስከ መጨረሻው እንዲጸኑ እንዳደፋፈራቸው ሁሉ እንዲሁም አሁን በፊታቸው ያለውን ተስፋ በማስታወስ እንዲታገሡ ያደፋፍራቸዋል።

ተስፋ ትዕግሥትን ይፈጥራል፥ ክርስቲያኖችም ይታገሡ ዘንድ በዚህ ምዕራፍ ላይ ብዙዎች ተስፋዎች ተዘርዝረዋል። በክርስትና እሽቅድድም ገብተው በትዕግሥት ለሚሮጡት ክብር ይቆያቸዋል (ቁ. 1፥2)፤ የአባት ቅጣት ለሚታገሡት ታላቅ ጥቅም ይገኛል (ቁ. 3-11)፤ የደረሱበት ስፍራ ከፊተኛው ስፍራ እጅግ በጣም አስደሳች ነው (ቁ. 18-24) የሚቀበሉትም መንግሥት እንደዚህ ዓለም ሳይሆን ለመቼም የማይናወጥ መንግሥት ነው። (ቁ. 26-29)

ደራሲው እንደዚህ በዕብራውያን ፊት ተስፋን በመዘርጋት ለትዕግሥት ያደፋፍራቸዋል፥ አልፎ አልፎም፥ በተለይ በምዕራፉ መጨረሻ ላይ፥ እንደ ልማዱ ሁሉ ማደፋፈሩን በማስጠንቀቂያ ያጸናል።

### ቁ. 1፥2

> 1፥2 እንግዲህ እነዚህም የሚያህሉ ምስክሮች እንደ ደመና በዙሪያችን ካሉልን፥ እኛ ደግሞ ሸክምን ሁሉ ቶሎም የሚከበንን ኃጢአት አስወግደን፥ የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልክተን፥ በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ፤ እርሱ ነውርን ንቆ በፊቱም ስላለው ደስታ በመስቀል ታግሦ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአልና።

«እንግዲህ ... እኛ ደግሞ» ይህ ከም. 11 የመነጨው ትምህርት ነው። በም. 11 ላይ ሽማግሌዎች (አበው) በእምነት ያደረጉትን ማለት እስከ ዕለተ መሞታቸው ድረስ እያመኑ መታገሣቸውን አይተናል! አይተናልና በእነዚህ ቁጥሮች ላይ «እንግዲያውስ እኛ እንዲህ እናድርግ» ተባለ። ሽማግሌዎቹ በእግዚአብሔር ቃል ስላመኑና በፊታቸው ያለውን ብድራት ስለ ተመለከቱ (ም. 10፡35፤ ም. 11፡26) በሕይወት ዘመናቸው ያጋጠማቸውን ችግርና ሥቃይ ሁሉ ታገሡ፥ ገናም እያመኑ ሞቱ። እነርሱ ያደረጉትን እኛም እናድርግ። ሕይወታችን ኦሊምፒያ በተባለው የግሪክ አገር ከተማ ላይ ከተፈጸሙት እሽቅድድሞች አንዱን ይመስላል። በኦሊምፒያ ብዙ ሰዎች የእነርሱን እሽቅድድም ጨርሰው አሁን በተራቸው የሚሮጡትን ተወዳዳሪዎች እንደ ተመለከቱና ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዳደፋፈሩአቸው ሁሉ እንዲሁም ዛሬ በጥንት ዘመናት የሮጡት ቀጥራቸው የብዙ ብዙ የሆነ አበው በእኛ ዙሪያ ቆአምው መሮጣችንን ይመሰክራሉ! እኛም መመስከራቸውን በማሰብ እንበረታታለን። ሩዋጭም ሲሮጥ ሳለ በሰውነቱ ላይ ክብደት የሚጨምርበትን ነገር ሁሉና በነፋስ ተውለብልቦ በእግሮቹ የሚጠመጥምበትን ልብስ እንደሚያስወድግ እንዲሁም እኛ መንፈሳዊ እሽቅድድማችንን የሚያሰናክለውን ሁሉ ማስወገድ ይገባናል።

ሩዋጭም ሲሮጥ ወዲያና ወዲህ ሳይመለከት ወደ ፊቱ ወደ መድረሻው ገመድ ብቻ እንደሚመለከት ሁሉ እኛም ክርስቲያኖች ዓይናቻችንን በመሪ አለቃችን (ም. 2፡10)፤ ሽልማትንም በሚያበረክትልን ዳኛ (ማቴ. 25፡21፥23፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡3-5) በኢየሱስ ላይ ተክለን በትዕግሥት (በጽናት) እንሩጥ። ኢየሱስም እንድንቀበል ዋሳችን እንደ መሆኑ መጠን

(ም. 7፡22) ምሳሌአችን ይሁን፤ ምክንያቱም እርሱ እንደ እነዚያ ዕብራውያን እንደ እኛም ሁሉ ተነቀፈ ተጨነቀ ተሣቀየም (ም. 4፡14-16፤ ም. 10፡32-34)፥ ቢሆንም በፊቱ ያለውን ደስታ አይቶ እርሱ ሁሉን ታገሠ፥ አሸንፎም ተቀምጦአልና። እርሱን እየተመለከትን እያሰብንም (ቁ. 3) በትዕግሥት ጸንተን እንሩጥ።

<u>ማስገንዘቢያ</u>፡-

ሀ) «እነዚህን የሚያህሉ ምስክሮች» (ቁ. 1) በእነዚህ ቁጥሮች ላይ ሐዋርያው በም. 11 ላይ ስለ ተነገረላቸው ሽማግሌዎች እንደሚናገር ግልጥ ነው። ይህም ሲሆን «በዙሪያችን አሉ» ማለቱ እንዴት ነው? ሙታን በምድር ላይ ዛሬ የሚደረገውን ነገር ያያሉን? መላእክት እንጂ ሙታን በዚህ ዓለም ላይ የሚደረገውን ያያሉ የሚል ጥቅስ በመጽሐፍ ቅዱስ የለም። በዚህ አንጻር እንደማያዩ ይመስላል። (2ኛ ነገ. 22፡20) በዕረፍት ላይ አይደሉምን? በዚህ ዓለም ጣጣ ሁሉ ይጨነቃሉን? አይመስልም። ታዲያስ «በዙሪያችን አሉ» ሲባል እንዴት ነው? ቢሉ ሁለት መልስ እናቀርባለን።

1ኛ፥ ይህ ነገር ሁሉ ሥዕል ወይም ምሳሌ ነው። እኛ በእሽቅድድም የምንሮጥ ሰዎች በእውነት አይደለንም፥ እነኝህም ምስክሮች በእውነት በዙሪያችን የሉም። እኛ እንደምንሮጥ ዓይነትና እነርሱ በዙሪያችን እንደሚቆሙ ዓይነት ነው እንጂ እኛ በእውነት እንድንሮጥ ወይም እነርሱ በዙሪያችን እንዲቆሙ አይደለም። ነገሩ በሞላ እኛን ለማደፋፈር የተሰጠ ሥዕል ወይም ምሳሌ ነው።

2ኛ፥ መመስከር የተባለው ቃል ሁለት ፍች አለው። «እገሌ መስክሮአል» ሲባል እገሌ ነገሩን በዓይኑ አየ፥ ወይም ደግሞ እገሌ ለነገሩ በቃሉ መሰከረ ማለት ነው። «ምስክር» የተባለውም ቃል እንደዚሁ ነው። እንግዲያውስ ሽማግሌዎቹ ምስክሮች ናቸው ሲባል በዓይናቸው መስክረዋል ማለቱ ሳይሆን ለነገሩ መስክረዋል ማለቱ ይሆናል። «ተመሰከረላቸው እንጂ እነርሱ መቼ መስክረዋል?» ቢባል በሕይወታቸው መስክረዋል። የሕይወታቸው ምስክርነት በም. 11 ላይ ተጽፎ አግኝተነዋል። ሕይወታቸው ለእኛ የሚሆን ምስሌ (ማስረጃ) ነው። የሕይወታቸው ምስክርነት፥ ማመናቸው፥ መታገሣቸውም በፊታችን ነው፤ የሚከብበንም ይመስላልና ተደፋፍረን እንሮጣለን።

ለ) «ሸክምን ሁሉ ቶሎ የሚከበንንም ኃጢአት አስወግደን» (ቁ. 1፥2) የምናስወግዳቸው ሁለት ነገሮች ናቸው፤ እነርሱም ሸክምና ኃጢአትን። ሸክምና ኃጢአት ለየብቻቸው ናቸው። ሸክም የሆነ ነገር መሮጣችንን የሚያሰናክል ነገር ነው እንጂ ኃጢአት አይደለም። (ማቴ. 18፡7-9) እሽቅድድም የሚሽቀዳደሙ ሰዎች ፈቅደው ራሳቸውን ከብዙ ነገር ይከለክላሉ። (1ኛ ቆሮ. 9፡25) ነገሩ ለሌሎች ሰዎች ፈጽሞ ደግ ይሆናል፤ ለሩዋጭ ግን የማይጠቅም ይሆናልና ይተውዋል። እነርሱ ሰውነታቸውን ከሚያለሰልስና ከሚያወፍር፥ ከትርፍ ልብስና ዕቃ ሁሉ ራሳቸውን እንደሚከለክሉ እንዲሁም እኛ መሮጣችንን ከሚያሰናክል ነገር ሁሉ ራሳችንን መከልከል ይገባናል። የሚያሰናክለን ምንና ምን ነገር ነው? ቢሉ፥ መንፈሳዊ ሕይወታችንን የሚያባክን (የሚያደክም) ነገር ሁሉ ነው። ብልጥግና ሊሆን ይችላል (ማር. 10፡21-25) አጉል ልማድ፥ የምንደሰትባቸው ጨዋታዎች፥ የምናነባቸው መጻሕፍት፥ የለመድናቸው ሱሶች፥ ወይም ያበጀናቸው ባልንጀሮች እንኳ፥ እነኝህ ሁሉ ማሰናከያዎች ሊሆኑ ይችላሉ። እነኝህ ነገሮች እኮ ለብዙዎች ክርስቲያኖች ዛሬ ማሰናከያዎች ነቸው። ክርስቲያን ሆይ፥ ሸክምን ሁሉ ከሰውነትህ አስወግድ!

ኃጢአትማ ማንኛውም ኃጢአት ይሆናል። ኃጢአት ቶሎ ይከበናል፥ ሩጫችንንም ከቶኛ ያስተጓጉላል። የክርስትናን እሽቅድድም ዋና ከልካይ ኃጢአት ነው። ማንኛውም ኃጢአት ይሆናል አልሁኝ እንጂ ሐዋርያው ደጋግሞ ስለ አለማመን ተናግሮአልና እዚህ ላይ የሚናገርበቱ ኃጢአት አለማመን ሳይሆን አይቀርም። (ም. 10፡26) ልብስ በሩዋጩ እግር ላይ ተጠምጥሞ ከመሮጥ እንደሚከለክለው እንዲሁም ጥርጥር ወይም አለማመን፥ እሳትን የሚያጠፉ ቀዝቃዛ ውኃን መስሎ የክርስትና ሩጫችንን ያሰናክላል። ሩጫችንን የሚያሰናክለው ኃጢአት አብዛናውን ይኸው የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሎች መጠራጠር ነው። ክርስቲያን ሆይ፥ ጥርጥርን (አለማመን) ከሰውነትህ አስወግድ!

ሐ) «እርሱ በፊቱ ስላለው ደስታ በመስቀል ታግሦ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀመጠ» (ቁ. 2) ክርስቶስ፥ ያን ያህል መከራ ይታገሥ ዘንድ ያጽናናው በፊቱ የቆየው ደስታ ነው። በእምነት ዓይን እርሱን እየተመለከተ ታገሠ ሩጫውንም ጨረሰ፥ በክብርም ተቀመጠ። (መዝ. 15፡8-11፤ ዮሐ. 17፡4፤ 2ኛ ጢሞ. 4፡7፥8) ወንድም ሆይ፥ አሁን ስትሮጥ እጅግ በጣም ተቸግረሃልን? ተስፋው ከዓይንህ ፊት አይጥፋ፥ ብድራቱን ከመመልከት አትሰልች፥ በትዕግሥት ጸንተህ ሩጥ። ብንጸና ከእርሱ ጋር ደግሞ እንነግሣለን። (2ኛ ጢሞ. 2፡13) ደግሞ አንድ ነገር ልብ አድርግ፡- እርሱ የተቀመጠው አንተን ሊረዳህ ነው! (ም.1፡3፤ ም. 8፡1)

መ) ከእኛ ከክርስቲያኖች ብዙዎቹን ብትመለከቱ ሽርሽር የምንሄድ እንጂ ከቶ እሽቅድድም የምንሽቀዳደም አንመስልም! መንፈሳዊ ሕይወታችንን ወይም ክርስትናችንን በቀላል አስተያየት እንመለከተዋለን። ከቶ አንቸኩልም፤ «ጊዜው ሲደርስ እንደርስ የለምን?» ብለን የምናስብ ይመስላል። ራሳችንን አንጠብክም፤ እንደ ሌሎች፥ እንደ ዓለም ሰዎች ሁሉ ልንሆን የምንችል ይመስለናል። ሉረ እንዲህ አይደለም! መጽሐፍ ቅዱስ ክርስትና በብርቱ የምንታገልበት ሕይወት እንጂ የምንሰንፍበት ሕይወት አለመሆኑን በብዙ ቦታ ላይ ያስጠነቅቀናል። (ሉቃ. 13፡24፤ ማቴ. 10፡22፤ ማር. 13፡37፤ 2ኛ ቆሮ. 13፡5፤ 2ኛ ጴጥ. 1፡10) ስለዚህ ከእንቅልፍ እንነሣ፡- ዳተኞች አንሁን፤ ዳሩ ግን ተስፋው እስከሚሞላልን ድረስ እያንዳንዳችን እስከ መጨረሻው ትጋትን እናሳይ። (ም. 6፡11፥12፤ ሮሜ 13፡11-14) ወንድም ሆይ፥ ያንተስ? ሽርሽር ነውን ወይስ እሽቅድድም?

## ቁ. 3-11

3 በነፍሳችሁ ዝላችሁ እንዳትደክሙ፥ ከኃጢአተኞች በደረሰበት እንዲህ ባለ
መቃወም የጸናው አስቡ። 4 ከኃጢአት ጋር እየተጋደላችሁ ገና ደምን እስከ ማፍሰስ
ድረስ አልተቃወማችሁም፤ እንደ ልጆችም ከእናንተ ጋር፡-

5፥6 ልጄ ሆይ፥ የጌታን ቅጣት አታቅልል፥ በሚገሥጽህም ጊዜ አትድከም፤ ጌታ
የሚወደውን ይቀጣዋልና፥ የሚቀበለውንም ልጅ ሁሉ ይገርፈዋል

7 ብሎ የሚያነጋግረውን ምክር ረስታችኋል። ለመቀጣት ታገሡ፤ እግዚአብሔር
እንደ ልጆች ያደርግላችኋልና፤ አባቱ የማይቀጣው ልጅ ማን ነው? 8 ነገር ግን
ሁሉ የቅጣት ተካፋይ ሆኖአልና ያለ ቅጣት ብትኖሩ ዲቃላዎች እንጂ ልጆች
አይደላችሁም። 9 ከዚህም በላይ የቀጡን የሥጋችን አባቶች ነበሩን እናፍራቸውም
ነበር፤ እንዴትስ ይልቅ ለመናፍስት አባት አብልጠን ልንገዛና በሕይወት ልንኖር

በተገባል? 10 እነርሱ መልካም ሆነ እንደ ታያቸው ለጥቂት ቀን ይቀጡን ነበርና፥ እርሱ ግን ከቅድስናው እንድንካፈል ለጥቅማችን ይቀጣናል። 11 ቅጣት ሁሉ ለጊዜው የሚያሳዝን እንጂ ደስ የሚያሰኝ አይመስልም፥ ዳሩ ግን በኋላ ለለመዱት የሰላምን ፍሬ እርሱም ጽድቅን ያፈራላቸዋል።

በዕብራውያን መካከል ጥቂቶች በኢየሱስ ቢያምኑ የሚበዙቱ አላመኑምና በአማኞቹ ላይ መለየትና መቃወም በብዙ ተነሥቶአል። ቤተ ዘመዶቻቸው ጠልቶአቸዋል፥ ተቃዋሚዎችም እየነቀፉአቸውና ስማቸውን እንደ ክፉ እያጠፉ አስጨንቀዋቸዋል። (ማቴ. 10:36፤ ሉቃ. 6:22፤ ዕብ. 10:32-34) አማኞቹ ክርስቶስ በቶሎ መጥቶ ከዚህ መከራ ሁሉ የሚያድናቸው መስሎአቸው ነበር፥ ነገር ግን አልመጣም፥ ተስፋቸውም ቀዝቅዞአል እነርሱም ደክመዋል ወደ ኋላም ማፈግፈግ ጀምረዋል። ሐዋርያው ሊያበረታታቸው ሲጥር በዚህ ክፍል ላይ ሁለት ነገሮችን ያሳስባቸዋል። በተቀዳሚ ኢየሱስን ያስቡ። (ም. 3:1) እርሱ ምንና ምን የሚያህለውን መቃወም ታገሦአል! ዕብራውያን እርሱ ግን እንደ ሆነ ያስቡ፤ ቀጥሎም ኃጢአተኞች ሰዎች ያሉትንና ያደረጉበትን ያስቡ። (ም. 1:2፥3፤ ማቴ. 3:17፥ 10:25፥ 11:19፥ 26:67-68፥ 27:63፤ ማር. 15:15-20) ቢሆንም፥ እርሱ ሁሉን ታገሠ እንጂ በነፍሱ አልዛለም አልደከመም። ለመሆኑ፥ የተፈጸመው በመከራ አይደለምን? (ም. 2:10) ዕብራውያን የእርሱን ያህል ከቶ አልተጋደሉም። በነቀፋና በጭንቅ እንደ መጫወቻ በመሆንና ገንዘባቸውን በመነጠቅ ተቸገሩ እንጂ እርሱን መስለው ደማቸውን እስከ ማፍሰስ ድረስ አልተጣቀዩም። ይህን ያስቡና ይበርቱ።

ሁለተኛ ደግሞ፥ በምሳ. 3:11፥12 ላይ የተጻፈውን ነገር ምነው ረሱ? ልጅ በአባቱ ተግሣጽ አይመረር ተብሎ የለምን? የደረሰባቸው እኮ የአባታቸው አስተዳደግ ወይም አመራር ወይም ተግሣጽ ነው! እግዚአብሔር እንደ ተወደዱ ልጆች ያደርግላቸዋል፥ ለጥቅማቸውም ነው። ልጅ የሆነ ሁሉ ቅጣትን ይቀበላል። አባት ዲቃሎቹንና ሠራተኞቹን መቅጣት አይጭነቅ ይሆናል፥ ለልጆቹ ግን ይጨነቃል ይቀጣቸዋልም። የወለዱን አባቶቻችን ሲቀጡን የምናፍራቸው ከሆነ በመንፈስ የወለደን አባታችን ሲቀጣን ለቅጣቱ መገዛትና የግል ልጆቹ ሆነን በእውነተኛ ሕይወት ከእርሱ ጋር መኖር አይገባንምን? እረ ይገባናል! የሥጋ አባቶቻችንም የቀጡን በጨኸታችንም ሆነ በጨዋታችን እነርሱን ስላስቸገረን ነው፥ ያውም በሕፃንነት ወራታችን ብቻ ነው፤ እግዚአብሔር ግን ሳይሰለቸው በሕይወታችን ዘመን ሁሉ ይቀጣናል፥ ዓላማውም ከቅድስናው እንድንካፈል፥ ማለት ልክ እርሱን እንድንመስል፥ ፍጹማን እንድንሆን ነው። (ዘሌዋ. 11:44፥45) እውነት ነው፥ በተቀጣንበት ጊዜ ቅጣቱ መራራ ነገር ይመስለናል፤ ይሁን እንጂ፥ ሩዋጭ ሰውነቱን የሚያጠነክረውን ጅምናስቲክ (የሰውነት ማጠንከሪያ)፥ አስጨናቂ ቢሆንም ቅሉ፥ በእሺታ መንፈስ አድርጎት እንደሚጠቀምበቱ ሁሉ፥ እኛም ያን ቅጣት በበጎ ፈቃድ ተቀብለን ብንጠቀምበት፥ ከግዕበሉ ታላቅ መናወጥ ቀጥሎ ታላቅ ጸጥታ (ሰላም) እንደ ተገኘ ሁሉ (ማቴ. 8:24-26)፥ ያ መራራ ቅጣትም ጣፋጭን ነገር፥ እርሱም በእግዚአብሔር ዓይን ፊት ቅን የሆነውን ሕይወት፥ ያፈራልናል።

<u>ማስገንዘቢያ</u>:-

ሀ) «ከናንተ ጋር የሚነጋገረውን ምክር ረስታችኋል» (ቁ. 5:6) የሚነጋገረው ምክር የመጽሐፍ ቅዱስ ምክር ነው። ይህስ የተለምዶ ነገር ነው እንጂ ልዩ ነገር አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ ይነጋገረናል (ማር. 15:28፤ ዮሐ. 7:38፥42፤ 19:37፤ ሮሜ 4:3፤ 9:17፤ 10:17፤ 10:11፤ 11:2፤ ገላ. 4:30፤ 1ኛ ጢሞ. 5:18፤ ያዕ. 4:5)፥

የሚለውምን ባናውቅ ወይም ብንረሳ በእግዚአብሔር ነገር ብዙ ስሕተት እናደርጋለንና ድምፁን መስማት ይገባናል። እንግዲያውስ መጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪአችን ይሁን!

ለ) «እርሱ ለጥቅማችን ይቀጣናል» (ቁ. 10) እኛ በእውነት፥ ያውም በሁለተኛ ልደት፥ የእግዚአብሔር ልጆች ከሆንን (ዮሐ. 1፡12፥13፤ 1ኛ ዮሐ. 3፡1) መከራም ሆነ ችግር የሚመጣብን ከአፍቃሪ አባት ዘንድ ነው እንጂ ከሌላ አይደለም። አባታችን ያልፈቀደው አንዳች ነገር ሊመጣብን አይችልም፤ ስለዚህ የሚመጣ ሁሉ ከእርሱ እጅ እንደ መጣ ልንቆጥረው እንችላለን። ይህም ከሆነ የሚመጣው ሁሉ ለጥቅማችን እንጂ ለጉዳታችን አልመጣም። ወይኑን ያደባለቀው አስቆሮቱ ይሁዳ እንደ ሆነ ቢመስልም «አብ የሰጠኝ ጽዋ» ነው። (ዮሐ. 18፡11) ወደ ባርነት የሸጡን ወደሞቻችን እንደ ሆኑ ይመስል የሆናል፤ ይሁን እንጂ «እግዚአብሔር ነው በታላቅ መድኃኒት አድናችሁ ዘንድ የላከኝ» (ዘፍጥ. 45፡4-8) የሰይጣን መልእክተኛ እንደ ሆነ ይመስል ይሆናል፤ ይሁን እንጂ «የተሰጠ ስጦታ» ነው። (2ኛ ቆሮ. 12፡7) እንግዲያውስ የሚመጣብን ማንኛውም ነገር ሁሉ ከአባታችን ከእግዚአብሔር መምጣቱንና ለጥቅማችን መሰጠቱን ተገንዝበን እንጠቀምበት እንጂ አናቃልለው አንናቀውም። አንዳንድ ጊዜ ችግርና መከራ ኃዘንም በምን ምክንያት እንደሚመጣብን አናውቅም ይሆናል፤ ይሁን እንጂ፥ ሁኔታችንን በሞላ ከሚያውቅ ከአባት ዘንድ መምጣቱን እንወቅ። (ሮሜ 8፡28)

ወንድም ሆይ፥ ዛሬ ምን ችግር ገጥሞሃል? ጤናን ማጣት ነውን፥ ወይስ ኀዘን፥ ወይስ ድህነት፥ ወይስ ፈተና? የአባት ተግሣጽ ነው እኮ ሌላ አይደለም። ጠንክርና ተጠቀምበት እንጂ አትመረርበት። «እግዚአብሔር እንዲህ ያለውን ነገር የጣለብኝ በምን ምክንያት ነው፥ ልጁ አይደለሁምን?» ትላለህን? ያውልህ ምክንያቱ! ልጅ በመሆንህ ነዋ! የአባት አስተዳደግ ነገር ነው። «እግዚአብሔር ቢጠላኝ ነው» ትላለህን? ሎረ፥ ስሕተት ነው! ቢወድህ ነው እንጂ ቢጠላህስ አይደለም። «እግዚአብሔር ጨካኝ ነው» ትላለህን? ኧረ ተው እባክህ! ጨካኝስ አይደለም፥ ከቅድስናው እንድትካፈል ቢያስብልህ ነው እንጂ። ልብህን ሳታደነድን «እሺ አባቴ ሆይ!» ብለህ ተገዛለትና በመከራው ተጠቀም። ይሁን እንጂ፥ ልብህን መርምር። በኃጢአት ምክንያት መጥቶ ይሆንን? ይህስ ሊሆን ይቻላል። ያለመታዘዝ ወይም ያለመጠንቀቅ ጉዳይ ያለ እንደ ሆነ፥ ወይም ምናልባት ያማስቀረት ነገር ቢኖር (የሐዋ. 5፡2) አባትህ ወደ መልካሙ መንገድ ይመልስህ ዘንድ ቢጥር ይሆናል፤ ልጁንም በፍቅር ሊመልስ ባይችል በበትር ይሞክረው ይሆናል።

ለታላቅ በረከት ታላቅ ፈተና ብዙ ጊዜ አስፈላጊ ነው፤ ማለት፥ በተፈጥሮው ካለ ድንጋይ የተዋበ ሐውልት ከመውጣቱ በፊት የቀራጺ መሮ፥ እጅግ ጥሩ የሆነ የአንገት መስቀል ከመገኘቱም በፊት የአንጥረኛ እሳት አስፈላጊ እንደ መኖኑ መጠን እኛ ከቅድስናው የምንካፈል ከሆንን የአባታችን ተግሣጽ ብዙ ጊዜ ያስፈልግ ይሆናል። «መከራን አትላክብኝ፥ አቤቱ» ብለህ እግዚአብሔርን ትለምናለህ? አትለምነው። «እንደ ዲቃላ ቁጠረኝ» ማለትህ ነው እኮ! ምነው፥ አባትህ ሳይገሥጽህ ቢተውህ ትወዳለህን? እርሱን መምሰል፥ ፍጹምም መሆን፥ አትፈልግምን? ይልቁንም መከራ ሲገጥምህ «ከአባቴ ዘንድ የመጣ ነው፥ ለጥቅሜ ተሰጥቶአል፤ አባቴ ፍጹም ሊያደርገኝ ቢወድ ነው» ብለህ በትሕትና በደስታም ተቀበለው እንጂ ከመከራ ነጻ መሆን አትመኝ።

ቁ. 12-17

[12] ስለዚህ የላሉትን እጆች የሰለሉትንም ጉልበቶች አቅኑ፤ [13] ያነከሰውም
እንዲፈወስ እንጂ እንዳይናጋ፥ ለእግራችሁ ቅን መንገድ አድርጉ። [14] ከሰው ሁሉ
ጋር ሰላምን ተከታተሉ ትቀድሱም ዘንድ ፈልጉ፥ ያለ እርሱ ጌታን ሊያይ የሚችል
የለምና። [15] የእግዚአብሔር ጸጋ ለማንም እንዳይጎድለው፥ ብዙዎቹም
የሚረከሱበት አንድ መራራ ሥር ወደ ላይ በቅሎ እንዳያስጨንቅ ሴሰኛም የሚሆን
እንዳይገኝ፥ [16] ወይም ስለ አንድ መብል በኩርነቱን እንደ ሸጠ እንደ ዔሳው ለዚህ
ዓለም የሚመች ሰው እንዳይሆን ተጠንቀቁ። [17] ከዚያ በኋላ እንኳ በረከቱን ሊወርስ
በወደደ ጊዜ እንደ ተጣለ ታውቃላችሁና፤ በእንባ ተግቶ ምንም ቢፈልገው ለንስሐ
ስፍራ አላገኘምና።

ከደረሰባቸው መከራ የተነሣ ዕብራውያን በነፍሳቸው ዝለው ደክመው ነበር። (ቁ. 3) እጆቹ እንደ ላሉት፥ ጉልበቶቹም እንደ ሰለሉት በእሽቅድድም እንደሚሽቀዳደም እንደ ደከመ ሩዋጭ፥ ወይም የድካም መንፈስ አድሮባት ኖሮ ጎባጣ ሆና ቀንታ ልትቆም እንዳልተቻላት ሴት (ሉቃ. 13፡10-13) ሆነዋል። አሁን ግን መከራው ለጥቅማቸው የተሰጠ የአባት ተግሣጽ መሆኑን ተረድተዋልና በኢሳ. 35፡3፥4 ላይ የተጻፈውን ቃል እያሰቡ ሰውነታቸውን ሰብሰብ አድርገው በተሠመረላቸው መሥመር በቀጥታ ይሩጡ። ራሳቸውን (ቁ. 12-14)፥ በማኅበራቸው (በቤተ ክርስቲያን) የሚገኙትንም ሌሎች (ቁ. 15-17) ማሰብ ይገባቸዋል። ራሳቸው፥ 1ኛ፥ በሚዳዊ አካሄዳቸው ይጠንቀቁ፤ ምክንያቱም እያነከሱ የሚሄዱ፥ ማለት በክርስትናና በይሁዲነት የሚያመነቱ (1ኛ ነገ. 18፡21) በማኅበራቸው አሉ። እነኝህ የባሰ ተጎድተው እንዲያውን እንዳይከፉ ክርስቲያኖቹ ማሰናከያን ሁሉ ከመንገድ አስወግደው፥ ሸካራውን ትክክል አድርገው ራሳቸው በርትተው ይሩጡ። (ሉቃ. 3፡3-6) 2ኛ በውስጣዊ አኳኋናቸው ይጠንቀቁ፤ ማለት በሰው ዘንድ ሰላምን በእግዚአብሔር ዘንድ ቅድስናን እያጠናቀቁ ይሩጡ።

ቀጥሎም ሌሎችን ያስቡ፤ ይህም የእያንዳንዳቸው ጉዳይ ነው። እንደ እረኞችና እንደ ኤጲስ ቆጶሳት ሆነው የምእመናንን መንጋ ይጠብቁ፥ ይህንም ሲያደርጉ በመንጋው ውስጥ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ሰዎች ይገኙ እንደሆነ ይመረምሩ። (1ኛ ጴጥ. 5፡1-4፤ ፊልጵ. 1፡1፤ ዮሐ. 21፡15-17) በመካከላቸው የእግዚአብሔርን ጸጋ በሙሉ ሳይጠቀምበት ቀርቶ ወደ ኋላ የቀረ ዳተኛ አለን? ወደ ሙላቱ እንዲደርስ ያጽናኑትና ያደፋፍሩት። በምካከላቸው በዘዳግ. 29፡18 ላይ «ሐሞትና እሬት የሚያበቅል ሥር» ተብሎ በሰበቡ ሌሎች ብዙዎች የሚረከሱበት ሰበበኛ ሰው ይገኛልን? ወይስ ንጽሕናን የማይጠብቅ ሕገወጥ ሰው አለን? (1ኛ ቆሮ. 5፡1፥6-12) ወይስ እፀድ የሌለው ማለት መንፈሳዊ ስፍራ ወይም ክፍል በሕይወቱ የሌለበት፥ ዔሳውን መስሎ ከዚህ ዓለም ብቻ የሆነ ሰው አለን? የዚህ ሰው የበረከት ሰዓት እንደሚያልፍና ከዚያ በኋላ በብዙ ቢቆጭም ቅሉ ሳያገኝ እንደሚቀር ያታወቀ ነው። ይህን ሁሉ ይመርምሩ።

<u>ማስገንዘቢያ</u>፡-

ሀ) ራሳችንን ሌሎችንም መጠበቅ። ራሳችንን የምንጠብቀው ሌሎች እንዲበረቱ እንጂ እንዳይሰናከሉ ነው። በማኅበር (በቤተ ክርስቲያን) ውስጥ የሚገኙቱ ሁሉ እኛን ያያሉ እንደሚያዩም ይሆናሉ። እኛ በርትተን ብንሮጥ እነርሱ ተጽናንተው ይሮጣሉ፤ እኛም ደክመን ብንለግም እነርሱም እንዲሁ ያደርጋሉ። በእኛ ምሳሌ ሌሎች ይመራሉና ራሳችንን መጠበቅ ይገባናል። ሌሎችን የምንጠብቅበት ምክንያት ማኅበሩ እንዲበረታ ነው። ይህም የእርስ በርስ መጠባበቅ አስፈላጊ መሆኑም በም. 3፡13 ላይ አይተናል፥ 1ኛ ቆሮ.

12፡24፥25ና በ1ኛ ተሰ. 5፡14፤ በያዕ. 5፡16ም ላይ እናያለን። እንርሳው እናጓድለውም።

ለ) «ከሰው ሁሉ ጋር ሰላምን ተከታተሉ፥ ትቀደሱም ዘንድ ፈልጉ» (ቁ. 14) የክርስትናን ሩጫ እንደሚገባ ሁሉ ልንሮጥ ብንፈልግ እነዚህን ሁለት ነገሮች መፈጸም ያስፈልገናል። የጥል ወይም የመለያየት መንፈስ መሮጣችንን ያስተጓጉላል ማኅበሩን ይበጠብጣል፤ እንግዲያውስ እንዳይገኝብን እንጠንቀቅ። እንደዚሁም፥ ሰው ወደ መድረሻ ገመድ ደርሶ ጌታን ሊያይ ይወድ እንደሆነ፥ ያለ ቅድስና የሚያየው የለምና በእሽቅድድም ዘመኑ ሁሉ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ (የተለየ) እንዲሆን ያስፈልጋል። በዓለም ነንና በሚቻለን ሁሉ ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ለመኖር እንጣር፤ ይሁን እንጂ ከዓለም እይደለንምና ለእግዚአብሔር ተለይተን እንኑር እንጂ ከሚገባ በላይ በዓለም ውስጥ እንደባለቅ። (ዮሐ. 17፡11፥14፥16) ቅድስናም ማለት ለእግዚአብሔር መለየት (የተለየ መሆን) ብቻ ሳይሆን ከኃጢአትም መለየት ማለት ነውና ጌታን ልናይ ብንወድ በእሽቅድድም ዘመናችን ሁሉ ራሳችንን ከኃጢአት መጠበቅ ያሻል።

ሐ) «በእንባ ተግቶ ምንም ቢፈልገው» (ቁ. 17) ዔሳው በረከቱን ለማግኘት ያልቻለበት ምክንያቱ ሽጦት ስለ ነበረ ነው! (ዘፍጥ. 25፡27-34) በረከቱና ብኩርናው ተቆራኝተው ነበር፥ እርሱም ብኩርናውን ሲሸጥ በረከቱን አብሮ ሸጠ። ከሸጠው በኋላና በረከቱ እንደተለየው ሲረዳ አዘነ አለቀሰም። (ዘፍጥ. 27፡38) ለንስሐ ግን ስፍራ አልተገኘም በረከቱ ተሽጦ ሄዶ ነበርና።

ኧረ እንጠንቀቅ! ከቶ የማይመለሱ ነገሮች አሉና። ለምሳሌ ልጅግር ልጃገረድም ክብርናቸውን ቢያጠፉ በምን ይመለስ? እኛም አንድ መብልን የሚመስል ነገር ለማግኘት ታላቅ በረከት እንዳንሸጥ እንጠንቀቅ። «ስንፍና አድርጌአለሁ፥ እጅግ ብዙም ስቻልቻሁ» ያለው ሳኦል አንሰማምን? (1ኛ ሳሙ. 21፡21) እርሱን መስለን ባደረግነው ስንፍና ምክንያት በኋላ እንዳናዝን እንጠንቀቅ። ለዚያች ታናሽ ነገር ክብርን እንለውጣለንን? (ማቴ. 16፡26) ውጤቱን ሳናስተውል እስከ መቼውም ድረስ የማይበጁትን ነገሮች እንዳናደርግ ወይም እንዳንናገር ይጠብቀን ዘንድ እግዚአብሔርን በጥብቅ እንለምነው።

## ቁ. 18-24

18 ሊዳሰስ ወደ ሚችል ወደ ሚቃጠልም እሳት ወደ ጭጋግም ወደ ጨለማም ወደ
ዐውሎ 19 ነፋስም ወደ ጨለማም ወደ ዐውሎ ነፋስም ወደ መለከት ድምፅም ወደ
ቃሎችም ነገር አልደረሳችሁምና፤ ያም ነገር የሰሙት ሌላ ቃል
እንዳይጨመርባቸው ለመኑ፤ 20 እንስሳ እንኳ ተራራውን ቢነካ ተወግሮ ይሙት
የምትለውን ትእዛዝ ሊታገሡ አልቻሉምና፤ 21 ሙሴም፦ እጅግ እፈራለሁ
እንቀጠቀጥማለሁ እስኪል ድረስ የሚያተው እጅግ የሚያስፈራ ነበረ፤ 22 ነገር
ግን ወደ ጽዮን ተራራና ወደ ሕያው እግዚአብሔር ከተማ ደርሳችኋል፥ ወደ
ሰማያዊቱም ኢየሩሳሌም፥ በደስታም ወደ ተሰበሰቡት ወደ አእላፋት መላእክት፥
23 በሰማያትም ወደ ተጻፉ ወደ በኩራት ማኅበር፥ የሁሉም ዳኛ ወደሚሆን ወደ
24 እግዚአብሔር ፍጹማንም ወደ ሆኑት ወደ ጻድቃን መንፈሶች፥ የአዲስም ኪዳን
መካከለኛ ወደሚሆን ወደ ኢየሱስ፥ ከአቤልም ደም ይልቅ የሚሻለውን ወደሚናገር
ወደ መርጨት ደም ደርሳችኋል።

ሐዋርያው አሁን በትዕግሥት የሚሮጡበትን፥ የላሉትን እጆችና የሰለሉትን ጉልበቶች የሚያቀኑበትን፥ ሰላምን የሚከታተሉበትና ይቀደሱ ዘንድ የሚፈልጉበትን፥ ለራሳቸውና ለማኅበሩም የሚጠነቀቁበትን ምክንያት ያስረዳቸዋል። (ቁ. 1፡2፥12፥14፥15፥16) እንደ ተለምዶም በማስጠንቀቂያና በተስፋም ሊያደፋፍራቸው ነው። የሚታገሡበትና የሚጸኑበት ምክንያት አፈግፍገው ወደ ኋላ የተመለሱ እንደሆነ እጅግ በጣም ወደሚያስፈራ አኳኋን ስለሚደርሱ ነው፤ በተቃራኒው ደግሞ የጸኑ እንደሆነ ወደማይነገር ደስታና ክብር ስለሚደርሱ ነው።

ከኋላቸው ግዙፋዊ ተራራ፥ እርሱም ደብረ ሲና፥ ከነፍርሃቶቹ ሁሉ አለ። (ዘጸአ. 19፡10-25፤ 20፡18-21፤ ዘዳግ. 4፡11፥12፤ 5፡22-33) የተራራውም ማስፈራራት በእርሱ ላይ የተሰጠውን የሕጉን ጽናት ያመለክታል። እንደዚያ ሕግ ሰው ፍጹም መሆን አለበት፥ አንድ ጉድለት አንድ ኃጢአትም ቢገኝበት ፍርድ ይፈረድበታል። የእግዚአብሔር ሰው የሆነ ሙሴ ስንኳ ያ ሕግ በተሰጠ ጊዜ እጅግ ፈራ ተንቀጠቀጠም። ዕብራውያን ወደዚያ ሊመለሱ ይወዳሉን?

በፊታቸውስ ምን አለ? በፊታቸውማ መንፈሳዊ ተራራ፥ እርሱም ደብረ ጽዮን፥ ማለት የእግዚአብሔር ከተማና አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ከነክብሩ ሁሉ አለ። (ም. 11፡16፤ መዝ. 47፡1፥2፤ አብድ. ቁ. 17፤ ራእ. 21፡2) በደብረ ሲና ሁሉም ፍርሃት ሲሆን በደብረ ጽዮን ሁሉም ዋስትናና ደስታ ነው። እዚያ በደብረ ሲና መላእክት በተራራ ላይ ለብቻቸው ሆነው እየቆሙ ለጠቅላላው ፍርሃት ፍርሃትን ይጨምራሉ (ዘዳግ. 33፡2)፤ እዚህ በደብረ ጽዮን ግን፥ የአንድ ከተማ ሰዎች በዓመት በዓል ቀን ደስተኞች ሆነው በመንገድ ላይ እንደሚሰራጩ እንዲሁም አእላፋት መላእክት በጠቅላላው ደስታ ላይ ደስታን እየጨመሩ ከሕዝቡ ጋር ይገኛሉ። መላእክትም እዚያ አሉ ሰአውችም አሉ። ስሞቻቸው በሕይወት መጽሐፍ የተጻፉ ሁሉ እዚያ ይገኛሉ። (ሉቃ. 10፡20፤ ፊልጵ. 4፡3፤ ራእ. 3፡5፤ 13፡8፤ 17፡8፤ 20፡12፥15፤ 21፡27) በደብረ ሲና የሕጉ ሰጭ የማይታይ ሆኖ በሚያስፈራ ድምፅ አሥር ቃሎችን (ዐሥርቱ ቃላትን) ያሰማ ነበር፥ ከሕዝቡም ወደ እርሱ የቀረበ ከቶ አንድም የለም፤ በጽዮን ግን የዚያ ሕግ አስፈጻሚ ዳኛ አለ፥ ሕዝቡንም በጸጋና በኅብረት ይቀበላል፥ ይቀርባሉ ፊቱንም ያያሉ። (ሮሜ 8፡33፤ ራእ. 21፡3፤ 22፡3፥4) በም. 11 ላይ እንደ ተመሰከረላቸው በብሉይ ዘመን የኖሩትም የቅዱሳን መንፈሶች እዚያ አሉ (ራእ. 6፡9-11)፤ በሲና ተራራ ላይ የነበረው የብሉይ ኪዳን መካከለኛ ሙሴ ሳይገኝ የአዲስ ኪዳን መካከለኛ ኢየሱስ እዚያ አለ። (ዘዳግ. 5፡5፤ ገላ. 3፡19፤ ዕብ. 8፡6፤ 9፡15፤ ሮሜ 8፡34) ደምም አለ፤ ሆኖም እንደ አቤል ደም ሆኖ ለበቀል የሚጮህ ደም ሳይሆን (ዘፍጥ. 4፡10) የይቅርታንና የሰላምን ቃል የሚናገር የኢየሱስ ደም ነው።

ዕብራውያን ወደዚህ ሁሉ የደረሱ ሲሆኑ ወደዚያ ወደፊተኛው ይመለሳሉ እንዴ? መንፈሳዊውን ለግዙፉ፥ የዘላለሙን ለሚያልፈው ይተዋሉን? (2ኛ ቆሮ. 4፡17፥18) የደብረ ሲናን ፍርሃት መውደድና የደብረ ጽዮንን ክብር መካድ ምንኛ ስንፍና ኖሮአል!

<u>ማስገንዘቢያ</u>፡-

ሀ) ደብረ ሲና . . . ደብረ ጽዮን። መጀመሪያው በስም ባይጠቀስ እንኳ በተነገረለት ነገር ሁሉ ደብረ ሲና መሆኑ ታውቆአል። ሐዋርያውም «ደብረ ጽዮን» ሲል ስለ ግዙፋዊ ተራራ ሳይናገር ስለ መንፈሳዊው፥ ስለ እግዚአብሔር ተራራ ወይም ከተማ፥ እንደሚናገር ግልጥ ነው።

እነኝህ ሁለት ተራራዎች የሁለት ኪዳኖች ሥዕሎች ወይም ምሳሌዎች ሆነዋል። (ገላ. 4፡24-26ትን አነጻጥሩ) ዕብራውያን አፈግፍገው ወደ አሪት ቢመለሱ ወደ ደብረ ሲና እንደ መመለሳቸው ነው። ቢወዱ ወደዚያ፥ ወደ ፍርሃቱና ወደ ባርነቱ፥ ወደ ፍርዱና ወደ ሞቱም፥ ሊመለሱም ይችላሉ፤ ይሁን እንጂ፥ ደስታና ነፃነት ሕይወትም ባለበቱ ዘንድ፥ ማለት በክርስቶስ፥ ቢጸኑ አይሻላቸውምን? እንዲህ ብሎ ሐዋርያው ያን የመጀመሪያ እምነታቸው እስከ መጨረሻው አጽንተው እንዲጠብቁ ያደፋፍራቸዋል፤ እኛም ቃሉን እንስማ።

ለ) «በሰማያት ወደ ተጻፉ ወደ በኩራት ማኅበር» (ቁ. 23) የበኩራት ማኅበር የተመረጠ የእግዚአብሔር ሕዝብ፥ እስራኤል፥ ነው። ምድራውያን እስራኤላውያን በብሉይ ኪዳን «የበኩራት ማኅበር» እንደ ሆኑ እንዲሁም መንፈሳውያን እሥራኤላውያን፥ ማለት ክርስቲያኖች፥ «የበኩራት ማኅበር» ናቸው። (ዘጸ. 4፡22፤ ኤፌ. 2፡19፥20፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡9) ስማቸው በሰማያት ተጽፎአልና እነኝህ የተጠቀሱቱ ሰዎች እውነተኞች አማኞች መሆናቸው ታውቆአል። (ሉቃ. 10፡20)

እንግዲያውስ ሐዋርያው «የበኩራት ማኅበር» ሲል የሚናገረው በዓለም ስላሉት ቅዱሳን አማኞች ነው። እነኝህ ደግሞ ከመላእክትና ከብሉይ ኪዳን ቅዱሳን ጋር የሰማያዊት ኢየሩሳሌም ማኅበርተኞች ናቸው።

ሐ) «ደርሳችኋል» (ቁ. 22፥24) አንድ ሰው «እርሱ መድኃኔ ዓለም ነውና የእኔ መድኃኒት ነው» ብሎ ኢየሱስን ሲቀበል በዚያን ጊዜ በሁለተኛ ልደት የእግዚአብሔር ልጅ ነውና ስሙ በሰማያት ይጻፋል፥ እርሱም ወዲያውኑ የጽዮንና የተድላዋ ሁሉ ወራሽ ወይም ማኅበርተኛ ሆኖአል። (ዮሐ. 1፡12፥13) በዚህ ምክንያት ሐዋርያው ዕብራውያንን «ደርሳችኋል» ይላቸዋል። ተቸግረው ተሰድደው ደክመው ይሆኑ ይሆናል፥ ይሁን እንጂ ወደ ደብረ ጽዮን ደርሰዋል። ጥቂቶች መሆናቸው ይመስላቸዋልን? አእላፋት መላእክትና የዱሮ ቅዱሳን፥ ስማቸው በሰማያት የተጻፉትም ሁሉ አብረው መኖራቸውን አስበው ይጽናኑ!

አንባቢ ሆይ፥ እኔና አንተ እንደዚሁ ነን። ደርሰናል! የክርስቶስ ወገኖች የእግዚአብሔርም ሕዝብ በእውነት ብንሆን «ከበኩራት ማኅበር» ነን በዚህም በማይነገር ክብር ሁሉ ላይ ስማችን ተጽፎአል። (1ኛ ጴጥ. 1፡8፥9) ያለብን መጠንከር ብቻ ነው። አናደርገውምን?

### ቁ. 25-29

25 ለሚናገረው እምቢ እንዳትሉ ተጠንቀቁ፤ እነዚያ በምድር ላስረዳቸው እምቢ
ባሉ ጊዜ ካላመለጡ፥ ከሰማይ ከመጣው ፊቀቅ የምንል እኛስ እንዴት
እናመልጣለን? 26 በዚያም ጊዜ ድምፁ ምድርን አናወጠ፥ አሁን ግን፡- አንድ
ጊዜ ደግሜ እኔ ሰማይን አናውጣለሁ እንጂ ምድርን ብቻ አይደለም ብሎ ተስፋ
ሰጥቶአል። 27 ዳሩ ግን፡- አንድ ጊዜ ደግሜ የሚል ቃል፥ የማይናወጡት ጸንተው
እንዲኖሩ፥ የሚናወጡት የተፈጠሩ እንደሚሆኑ ይለወጡ ዘንድ ያሳያል። 28 ስለዚህ
የማይናወጥን መንግሥት ስለምንቀበል በማክበርና በፍርሃት እግዚአብሔርን ደስ
እያሰኘን የምናመልክበትን ጸጋ እንያዝ፤ 29 አምላካችን በእውነት የሚያጠፋ እሳት
ነውና።

ማስጠንቀቂያ ከሆኑት ክፍሎች መጨረሻ አሁን ይገባል፤ ይህም በእውነት ትምህርቱን ወደ ፍጻሜ ያደርሳል። ትምህርቱ በዚህ ማስጠንቀቂያ ተጀምሮአል፥ በዚህም ይጨረሳል። ሐዋርያው

«ለሚናገረው እንቢ እንዳትሉ ተጠንቀቁ» ይላል፡ ስለሚናገረውም በም. 1፡1፡2 ላይ እንብበናል። «እነዚያ ካላመለጡ እኛስ እንዴት እናመልጣን?» ይላል፡ ይህንም አነጻጸር፡ ማለት በደብረ ሲና ላይ የተነገረውን ቃልና በጌታ የተነገረውም ከነማስጠንቀቂያው በም. 2፡1-4 ላይ አግኝተናል።

በኢየሱስ ክርስቶስ የተገኘው መዳን ከናካቴው በዕብርውያን ፊት ተዘርግቶአል (ገላ. 3፡1)፤ ሰምተው ሲያበቁ እያመካኙ እንቢ እንዳይሉ አሁን ይጠንቀቁ። (ሉቃ. 14፡18) አሪት በተሰጠበት ጊዜ ደብረ ሲና እጅግ ተናወጠች (ዘጸአ. 19፡18፤ መዝ.67፡7፥8)፤ እግዚአብሔር ግን አንድ ጊዜ ደግሞ ታላቅ መናወጥን እንደሚያደርግ ተስፋ ሰጥቶአል፥ ያን ጊዜ ምድርን ብቻ ሳይሆን ሰማይንም ያናውጣል። (ሐጌ 2፡6) «አንድ ጊዜ» ማለቱ የፍጻሜ ጊዜ መሆኑን ሲያመለክት ነው። የሚያናውጠውም አላፊ የሆኑት ነገሮች እንዲያልፉና ነዋሪዎቹ፥ የማይናወጡቱ፥ እርሱም የጽዮን ነገሮች፥ ጸንተውእንዲኖሩ ነው። ስለዚህ እኛ ክርስቲያኖች እስከ መቸውም ድረስ የማይናወጥ መንግሥት ስለምንቀበል እንደዚያ መንግሥት ዜጎች ሆነን እንኑር። የሚሰጠን መንግሥት የዚህ ዓለም መንግሥታት ዓይነት ቢሆን ኖሮ እኛ እንደ ምድራውያን መኳንንት ሁሉ መንግሥትን በምድራዊ አገልግሎት «እናገለግል» ነበር። እኛ የምንቀበለው መንግሥት ግን ምድራዊ ሳይሆን ሰማያዊና መንፈሳዊ፥ ነውና እኛም ምድራውያን መኳንንት፥ ሳንሆን መንፈሳዊያን መኳንንት ማለት ካህናት፥ ነንና ያን መንግሥት የምናገለግለው እንደ ካህናት ነው፥ አገልግሎቻችንም «አምልኮ» ይባላል። (ሉቃ. 12፡32፤ 22፡29፥30፤ ዮሐ. 18፡36፡ ራእ. 1፡6፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡5፥9) እንግዲያውስ እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ እንደ ታየው ሁሉ በእውነት የሚባላ እሳት ሆኖ በማክበርና በፍርሃት የምናመልከው አምላክ ነውና በመንፈሳዊ አገልግሎታችን ደስ እናሰኘው ዘንድ ጸጋውን አጥብቀን እንያዝ።

<u>ማስገንዘቢያ</u>፡-

ሀ) «የሚናወጡት የተፈጠሩ እንደሚሆኑ ይለወጡ ዘንድ» (ቁ. 27) የተፈጠሩ ነገሮች ለጊዜው ናቸው እንጂ ለዘላለም አይደሉም። ለምሳሌ፥ ሕንጻ ወይም ድልድይ ሲሠራ ሳለ ለጊዜው የሚሆኑ እንጨቶች በዙሪያቸው እንደሚበጁና በውስጥ ያለው ሲጨረስ እንደሚወገዱ እንዲሁም ፍጥረት ሁሉ የተፈጠረው ጽዮን እስኪመጣ ድረስ፥ ለጊዜው ብቻ ነው። ጽዮን ሲመጣ፥ ማለት አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ከሰማይ ስትወርድ፥ የተፈጠረው ሁሉ ይለወጣል። (ራእ. 21፡1-4፤ መዝ. 101፡26)

ለ) «እኛ የማይናወጥን መንግሥት ስለምንቀበል» (ቁ. 28) በዓለም ውስጥ ሁሉም ልውውጥና ጥርጥር ነው እንጂ የማይናወጥ ነገር የለም። ቀን የሚያመጣውን ምን እንደ ሆነ በፍጹም አናውቅም። (ምሳ. 27፡1) በክርስቶስ ለሆነ ሰው ግን ሚዳዊ እንጂ ውስጣዊ መነቃነቅ የለም። በክርስቶስ ዘንድ ሁሉም ያው ነው፥ የረጋም ነው። እንግዲያውስ በእርሱ ዘንድ ሁሉም ደኅና፥ ሁሉም ጸጥታ፥ ሁሉም ሰላም ነው። (2ኛ ተሰ. 3፡16)

ውድ ወንድሜ ሆይ፥ አንተ አሁን ያለህበት ሁኔታ እጅግ አስቸጋሪ ነውን? አንተንና ቤተ ሰቦችህን የሚበጠብጥ ነገር ተነሥቶአልን? ልውውጥና ጥርጥር፥ ሁከትና ቅሥፈት ከብበውሃልን? በፊትህ ያለው መንገድ ጨለማ ብቻ ነውን? አሻቅበህ እይ! የማይናወጥ ማንግሥት አለልህ። በዙሪያህ ያለው ሁሉ ይፋለስና ይጠፋ ይሆናል፥ የምትቀበለው መንግሥት ግን በፍጹም አይነካም ለዘላለምም አይጠፋም። (1ኛ ጴጥ. 1፡3-13) ስማ እባክህ፥ የሚለወጡት የሚናወጡትም እንጨቶቹ ብቻ ናቸው፤ በውስጥ ያለውን እውነተኛውን ነገር

የሚወስድብህ የለም። በተጨማሪ ደግሞ፥ ጠፊ ገንዘቡን ላለመስደድ የሚግተረተርን ንፉግ መስለህ የሚናወጠውንና የሚለወጠውን ለማስቀረት እጅግ አትጨነቅ። የማይናወጥን መንግሥት በመቀበል ላይ ነህና ይህ ሌላው ነገር ሁሉ ቢሄድ አንተ በእውነት አትጎዳም።

ሐ) «በማክበርና በፍርሃት፥ አምላካችን በእውነት የሚያጠፋ እሳት ነውና» (ቁ. 28፡29) እነኝህ ቃሎች ከዘዳግ. 4፡24 የተጠቀሱ ናቸው። በማክበርና በፍርሃት የምናመልክበት ምክንያቱ እግዚአብሔር የሚያጠፋ እሳት ስለ ሆነ ነው። ይህም የገንዘቡ ተቃራኒ ፊት ነው። እግዚአብሔር የፍቅር አምላክ መሆኑንም እናውቃለን፤ የሚባላ መሆኑን እንወቅ። በጸጋ የዳንን እንሆን ይሆናል (ኤፌ. 2፡4፥5)፤ ይሁን እንጂ፥ በእግዚአብሔር ፊት ስንቀርብ በማክበርና በፍርሃት መቅረብ ያሻናል። እግዚአብሔር የሚያስፈራ እንጂ የሚጫወቱበት አምላክ አለመሆኑ በደብረ ሲና ተገልጦአል። የፍቅር አምላክ ነው፤ ይሁን እንጂ ንጹህ (እምባ. 1፡13)፥ ኃያል (ዘዳግ. 10፡16፥17) ቅዱስም ሆኖ (ኢሳ. 6፡3-5) የፍርድ አምላክ ነውና በማክበርና በፍርሃት እንጂ በቅሌት ልንቀርበው አናስብ። (ዘጸአ. 34፡7፤ ዘኁል. 14፡18፤ ኢሳ. 33፡14-16)

# ምዕራፍ አሥራ ሦስት

## አማኝ በፍቅር ይመላለሳል

ይህ ስለ ፍቅር የሚናገር ምዕራፍ ነው። ይሁን እንጂ፡ ሐዋርያው መውደድ ስለሚገባና መውደድ ስለማይገባ ነገር ጥቂት ከተናገረ በኋላ (ቁ. 1-6) ሐሳቡን ወደ ዕብራውያን ማመንታት ይመልስና የአይሁድን ሥርዓት በፍጹም እንዲተዉና በክርስቶስ እንዲካፈሉ እንደ ገና ይመክራቸዋል። (ቁ. 7-16) ቀጥሎም ለዋኖቻቸው አመራር እንዲታዘዙ እያሳሰበ ጸልዩልኝ ይልና ለእነርሱ እየጸለየ መልእክቱን በሰላምታ ይጨርሳል። (ቁ. 17-25)

### ቁ. 1-6

1፥2 የወንድማማች መዋደድ ይኑር። እንግዶችን መቀበል አትርሱ፤ በዚህ
እንዳንዶች ሳያውቁ መላእክትን እንግድነት ተቀብለዋልና። 3 ከእነርሱ ጋር እንደ
ታሰረ ሆናችሁ እስሮችን አስቡ፥ የተጨነቁትንም ራሳችሁ ደግሞ በሥጋ እንዳለ
ሆናችሁ አስቡ። 4 መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን፤
ሴሰኞችንና አመንዝሮችን ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል። 5 አካሄዳችሁ
ገንዘብን ያለ መውደድ ይሁን ያላችሁም ይብቃችሁ፤ እርሱ ራሱ፡- አልለቅህም
ከቶም አልተውህም ብሎአልና፤ 6 ስለዚህ በድፍረት፡- ጌታ ይረዳኛልና
አልፈራም፤ ሰው ምን ያደርገኛል? እንላለን።

አማኞች ክርስቲያኖች ሁሉ ከአንድ አባት፥ ከእግዚአብሔር የተወለዱ ናቸውና ሁሉም ወንድማማች ናቸው። (ዮሐ. 1፡12፥13፤ ገላ. 3፡26) ይህም ስለ ሆነ እርስ በርሳቸው በወንድማማች መዋደድ መኖር ይገባቸዋል። (ዮሐ. 13፡35) ይህን ስለ ሆነ መዋደድ ወይም ፍቅር የሚያሳዩት እንግዶችን መቀበል የታሰሩትንና የተጨነቁትን በማሰብ ነው። እንግዶች የተባሉት በስደት ምክንያት ቤትን ያጡ፥ ወንጌልን ለማስተማር ከአገር ወደ አገር የሚዘዋወሩ በግል ጉዳያቸውም የትዘው መንገድ የሚሄዱ ክርስቲያኖች ይሆናሉ። (ም. 11፡37፥38፤ 1ኛ ቆር. 9፡3-12፤ ሮሜ 16፡1፥2) ወድማማችን እንግድነት ሲቀበሉ አብርሃምና ሣራ 3ቱን ሰዎች ተቀብለው አንዱ እግዚአብሔር፥ ሁለቱም መላእክት መሆናቸውን በኋላ እንደ ተረዱና ታላቅ በረከትን፥ ይስሐቅን እንዳገኙ እንዲሁም ዕብራውያን እነዚህን ቅዱሳን ወደ ቤታቸው ቢቀበሉ ከእነርሱ ዘንድ በረከትን ያገኙ ይሆናል። (ዘፍጥ. 18፡1-15፤ 19፡1፥2) ስለ ሃይማኖታቸው ከታሰሩት ወንድማማችም ጋር የጠበቀ ኅብረት ተሰምቶአቸው በሚችሉት ሁሉ ፍቅራቸውን ያሳዩ፤ ይህንም ብም. 10፡32-39 ሥር ላይ ሀ) በተባለው ማስገንዘቢያ አግኝተነዋል። እንደዚሁም ስለ ክርስቶስ በመነቀፍ ወይም ከሥራ በመለየት ወይም ወገኖቻቸው በስደት በመሞት ወይም ንብረታቸውን በመነጠቅ ምክንያት የተጨነቁትን ርኅሩኅ በሆነ ልብ ያስቡ፤ ስለምን? ቢሉ ያ ጭንቀት በእነርሱም ላይ ምናልባት ይደርሳልና።

በቁ. 4 ላይ ሐዋርያው ጾታዊ ፍቅርን ያስብና «መጋባት ቀላል ነገር አይደለምና አክብሩት እንጂ አታቃልሉት፤ ተጋብታችሁ ስታበቁም መኝታችሁ ንጹሕ ይሁን እንጂ እንግዳ ፍቅር አይገኝበት» ይላል። የተጋቡትን ሰዎች መኝታ በሚያረክስ ሴሰኛና አመንዝራ ላይ ምድራዊ ዳኛ ባይፈርድ እንኳ ራሱ እግዚአብሔር ይፈርድበታል።

ገንዘብን መውደድ ግን ተገቢ አይደለም፤ ከክርስቲያናዊ ምልክቶችም አንዱ የገንዘብ መውደድ ተቃራኒ የሆነው የበቃኝ ማለት መንፈስ ነው። ሰው ገንዘብን የሚወደው ሀብትን ለማብዛት ወይም ለችግር ጊዜ ቅርስ ለማቆየት ነው። እግዚአብሔር ግን አረጋግጦ «እጄን አንሥቼ ለቅቄ ከቶ

አላስወድቅህም፥ ከቶ ምንም ቢሆን ከቶ አልተውህም» ሲለን (ዘፍ. 28፡15፤ ዘዳግ. 31፡6፤ ኢያ. 1፡5፤ ኢሳ. 41፡17) ካለን በላይ ለማግኘት ሳንመኝ «ራሱ ጌታ ይረዳናልና አንፈራም፤ ሰው ምን ያደርገናል?» ብለን በድፍረት እንናገር የለምን? (መዝ. 117፡6)

<u>ማስገንዘቢያ</u>፡-

ሀ) «እንግዶችን መቀበል አትርሱ፤ እስሮችንም አስቡ»። (ቁ. 2፡3) በእንግድነት ነገር ሱነማዊቱንና ጋይዮስን በእስሮችም ነገር ሄኔሲፎሩን መምሰ ያሻናል። (2ኛ፥ ነገ. 4፡8-10፤ 3ኛ ዮሐ. 5-8፤ 2ኛ ጢሞ. 1፡16-18) ደግሞ በማቴ. 25፡35፥36፥40 ላይ ስለ እነዚህ ሁለት ነገሮች እንግዶችን ስለ መቀበልና እስሮችን ስለ ማሰብ የተጻፈውን እናስብ። ወንድማማችን ወደ ቤታችን መቀበልና እንደ ተተረከላቸው እንደ ካህኑና እንደ ሌዋዊው ሆነን ገለል ብለን ሳናልፍ «ወንድሞቻችን ናቸው» ብለን የታሰሩትን ክርስቲያኖች መጠየቅ ተገቢ ሥራችን ነው። የክርስቲያን ማኅበራችንን የምናጠነክር እንዲህ ያለውን ነገር ስናደርግ ነው።

ለ) «መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን» (ቁ. 4) «መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር ይሁን» የተባሉት ቃሎች በሁለት መንገድ ይተረጎማሉ። 1ኛ፥ በሰው ሁሉ አሳብና አስተያየት ክቡር ይሁን ማለት ነው። መጋባትን የከለከሉ ሰዎች በዚያ ዘመን ቢገኙ ነው። መጋባት ግን ርኩሰት ወይም ኃጢአት ሳይሆን ይልቁንም እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ የመደበው ነገር ነው። (የሐዋርያት አመክንዮን ተመልከት) የሚፈርድባቸው ሴሰኞችንና አመንዝሮችን ነው እንጂ የተጋቡትን አይደለም። «ምነው፥ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ መጋባትን ነቅፎ የለም ወይ?» የሚሉ ቢኖሩ፥ ቅዱስ ጳውሎስማ በ1ኛ ጢሞ. 4፡3 ላይ «እነዚህ ሐሰተኞች መጋባትን ይከለክላሉ» ይላል ይህንም የዕብራውያንን መልእክት የጻፈው እርሱ የሆነ እንደሆነ እዚሁ በም. 13፡4 ላይ «መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር ይሁን» ይላል። «ይሁን እንጂ፥ በሌላ መጽሐፍ ይህን ንግግሩን ክዶ የለምን?» ቢባል፥ ይህስ ከቶ አይደለም። መንፈስ ቅዱስ በአንዱ መጽሐፍ «አዎን» ሲል በሌላው «አይደለም» ይላልን? አይልም! (2ኛ ቆሮ. 1፡17-20) ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮ. 7፡1፥2 ላይ እንዲህ ይላል፡- «ከሴት ጋር አለመገናኘት ለሰው መልካም ነው፤ ነገር ግን ስለ ዝሙት ጠንቅ ለእያንዳንዱ ለራሱ ሚስት ትኑረው ለእያንዳንዲቱ ደግሞ ለራስዋ ባል ይኑራት» ይህንም ሲል ይልቁንም መጋባትን እንደሚደግፍ እንጂ እንደማይነቅፈው ግልጥ ነው። (በዚያውም ምዕራፍ በቁ. 10፡11 ላይ የተጻፈውን ብናስተውል መልካም ነው) «ሰው ከእግዚአብሔር ዘንድ ልዩ የሆነ የራስን መቻል ስጦታ ከተቀበለ ሚስት ሳያገባ ቢኖር መልካም ነው» ይላል፤ ምክንያቱም የጊዜው ችግር አይገጥመውም አሳቡም ሳይባክን ጌታን ሊያገለግል ይችላል። (1ኛ ቆሮ. 7፡26፥32-35) ይሁን እንጂ፥ የሚችሉት ጥቂቶች ናቸውና ጠቅላላው የእግዚአብሔር ፈቃድ ሰው ሁሉ እንዲያገባ ነው። ፈቃዱም ይህ ከሆነ መጋባት በሰው ሁሉ ዘንድ ክቡር ይሁን እንጂ ሰው መጋባትን «ርኩስ ነው» እንደምን ይላል?

2ኛው ትርጉም፥ መጋባት በሁሉ ዘንድ፥ እርሱም በሰው ሁሉ ወይም በመጋባቱ አኳኋን ሁሉ፥ ክቡር ሆኖ ይጠበቅ የሚል ነው። ቤተ ሰብ የማኅበራዊ ኑሮ መሠረት ነውና ይህ በብርቱ የምንጠነቀቅበት ነገር ነው። እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳንም ላይ በአዲስም ላይ ቅድስናን አዝዞአል፥ በዓይኖቹም ፊት መጋባት ክቡር ነው። (ዘሌዋ. 11፡44፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡13-16፤ ማቴ. 19፡3-6) በዘመናችን ግን የጾታ ነገሮች በጣሙን ተቃልለዋል፥ መጋባትም አይከበርም

የመኝታውም ንጽሕና አይጠበቅም። «እግዚአብሔር አይፈርድብንም» ብለን እናስብ። ኧረ ይፈርዳል! እግዚአብሔር መጋባትን ክቡር አድርጎ ያልጠበቀውንና መኝታውን ያረከሰውን ሰው «አመንዝራ» ይለዋል፥ እንደሚፈርድበትም መጽሐፍ ቅዱስ እጅግ በሚያስፈራ ቃል በአያሌ ቦታዎች ላይ ያረጋግጣል። (1ኛ ቆሮ. 6:9፥10፤ ኤፌ. 5:5፥6፤ ቆላ. 3:5-7፤ ዕብ. 13:4)

የተወደድህ ልጅ ሆይ፥ መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያው አድሮ የተናገረውን ቃል ስማ። «መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን፤ ሴሰኞችንና አመንዝሮችን ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል» ይላል። ቸል ሳትል ይህን ቃል በልብህ አኑር።

ሐ) «አካሄዳችሁ ገንዘብን ያለ መውደድ ይሁን፥ ያላችሁም ይብቃችሁ» (ቁ. 5) ገንዘብ ርኩስ ወይም ክፉ ነገር አይደለም። ርኩስ ወይም ክፉ የሚያደርገው የምናጠራቅምበት መንፈስና የምናውልበት ነገር ነው። ልባችንን ከመጠን በላይ ሳንጥልበትና በልጆቻችን ወይም መልካምና አስፈላጊ በሆነ ነገር ሁሉ በጠቅላላው በመሻሻል ላይ ልናውለው ገንዘብን ብናጠራቅም መጥፎ አይደለም። ነገር ግን «ሕይወት እኮ ገንዘብን ማጠራቀም ነው!» ብለን የሕይወታችን ዓላማ ብናደርገውና በምኞታችንና በምቾታችን ላይ የገዛ ራሳችንንም ክብር ለማላቅ ልናውለው በመጎምጀት መንፈስ ገንዘብን ብናጠራቅም ይህስ መጥፎ ነው። እኛ በዘመናዊ ንግግራችን «ሕይወት እኮ ገንዘብን ማጠራቀም ነው!» ስንል ጌታ «የሰው ሕይወት በገንዘቡ ብዛት አይደለም» ይላልና ንግግራችን የሐሰት መሆኑን ያስረዳል። (ሉቃ. 12:15) ሕይወት ገንዘብን ማጠራቀም አይደለም። ሕይወት ከእግዚአብሔር ጋር በኅብረት መኖር ነው። (1ኛ ዮሐ. 1:1-4)

«ያላችሁ ይብቃችሁ» የሚለው ቃል ለክርስቲያን ተገቢ ቃል ነው፤ ስለምን? ቢሉ፥ በዙሪያ ካለው ሁሉ ክርስቲያን ነፃ ሊሆን ይችላልና። አሁን ያለን ሀብት፥ አሁን ያለንበት ሁኔታ ይበቃናል። (ፊልጵ. 4:11-13) ገንዘብ ክፉ ነገር መሆኑ አይደለም፤ ገንዘብ ግን በቀላሉ ወደ ክፉ ነገር ሊያደርስ ይችላል። (1ኛ ጢሞ. 6:6-11) ለምሳሌ በእነዚያ ዕብራውያን መካከል ብዙ ሀብት ያለው ሰው ቢኖር ኖሮ ክርስትናን ለመካድ በብርቱ ይፈተን ባልነበረምን? በእኛም ዘንድ እንደዚሁ ነው። ገንዘብን አጠራቅሞ ያለ እግዚአብሔር መኖር፥ ወይስ ገንዘብን አጥቶ ከእግዚአብሔር ጋር መኖር፥ ማናቸው ይሻላል? ሁለቱንም መውደድና ለሁለቱም መገዛት እንደማንችል ተጽፎአል። (ማቴ. 6:24) እግዚአብሔር ግን እዚህ በቁ. 5 ላይ እንደ ተጻፈ ከተናገረ፥ እኛ በቁ. 6 ላይ የተጻፈውን ልንል አንችልምን? (ሉቃ. 12:16-21)

## ቁ. 7-16

[7] የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩአችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ፥ የኑሮአቸውንም ፍሬ
እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሉአቸው። [8] ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ
እስከ ዘላለምም ያው ነው። [9] ልዩ ልዩ ዓይነት በሆነ በእንግዳ ትምህርት አትወሰዱ፤
ልባችሁ በጸጋ ቢጸና መልካም ነው እንጂ በመብል አይደለም፤ በዚህ የሚሠሩባት
አልተጠቀሙምና። [10] መሠዊያ አለን ከእርሱም ሊበሉ ድንኳኒቱን የሚያገለግሉ
መብት የላቸውም። [11] ሊቀ ካህናት ስለ ኃጢአት ወደ ቅድስት የእንስሶችን ደም
ያቀርባልና፥ ሥጋቸው ግን ከሰፈሩ ውጭ ይቃጠላል። [12] ስለዚህ ኢየሱስ ደግሞ
በገዛ ደሙ ሕዝቡን እንዲቀድስ ከበር ውጭ መከራን ተቀበለ። [13] እንግዲህ
ነቀፌታውን እየተሸከምን ወደ እርሱ ወደ ሰፈሩ ውጭ እንውጣ፤ [14] በዚህ የምትኖር
ከተማ የለችንምና፥ ነገር ግን ትመጣ ዘንድ ያላትን እንፈልጋለን። እንግዲህ ዘወትር

> ለእግዚአብሔር የምስጋናን መሥዋዕት፥ ማለት ለስሙ የሚመሰክሩ የከንፈሮችን
> ፍሬ፥ በእርሱ እናቅርብለት። 16 ነገር ግን መልካም ማድረግን ለሌሎችም
> ማካፈልን አትርሱ፤ እንዲህ ያለው መሥዋዕት እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋልና።

ሐዋርያው አሁን ወደ ዓይነተኛ አሳቡ ተመልሶ ዕብራውያን የአይሁድን ሥርዓት ትተው በክርስቶስ ብቻ እንዲታመኑ ያደፋፍራቸዋል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ 3 ጊዜ ስለ ማኅበራቸው ዋኖች ወይም መሪዎች፥ በቁ. 7 ላይ ስላለፉቱ ወይም ስለ ሞቱት በቁ. 17ና 24 ላይም ገና በሕይወት ስላሉቱ ይናገራል። «አስቡአቸው፥ የኑሮአቸውንም ፍሬ (ማለት አሁን ያገኙትን ደስታና ክብር) እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሉአቸው» ይልና በተጨማሪ «ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ዘላለምም ያው ነው» ይላል። ማለት፥ እነዚያን የዱሮዎችን ያጸናውና በሕይወታቸው ዘመን ፍጻሜ ላይ «መልካም፥ አንተ በጎ ታማኝም ባሪያ፥ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ» እያለ ወደ ክብሩ የተቀበላቸው ጌታ ገና ዛሬ ያው ነውና ለእነርሱ የነበረው ሁሉ ለዛሬ ዕብራውያን ደግሞ ይሆናል። የዕብራውያን እምነት ግን የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩአቸውን የዱሮዎችን እምነት ይምሰል እንጂ በእንግዳ ትምህርት አይወሰዱ። (ም. 2:1) ሐዋርያው ይህን የሚለው «ዋስትናችሁን የምታጸኑ ቅዱስ መብልንም በመብላት ነው እንጂ በክርስቶስ በማመን ብቻ አይደለም» የሚሉ አስተማሪዎች ተነሥተው ስለ ነበር ነው። ሐዋርያው ግን «እንዲህ ያለ ትምህርት ዝም ብሎ ነው» ይላል፥ ምክንያቱም እነዚህን የመብል ሕግጋት የጠበቁ አይሁድ አልተጠቀሙባቸውምና። (ም. 9:9፥10፤ የሐዋ. 15:10፥11፤ ገላ. 2:14-16) በሁለቱ፥ ማለት በምሳሌውና በእውነተኛው ነገር በአይሁድ ሥርዓትና በክርስቶስ ሊጠቀም የሚችል ማንም የለም። እነዚህ ሁለቱ እርስ በርሳቸው ይከላከላሉና ክርስቶስን መያዝና የአይሁድን ሥርዓት መተው ወይም የአይሁድን ሥርዓት መያዝና ክርስቶስን መተው የግዱታ ነገር ነው። ይህን ግዴታ የሚያስረዳው ራሱ የአይሁድ ሥርዓት ነው። እንደዚያ ሥርዓት፥ ካህናት ከመሥዋዕቱ፥ ሥጋ ይበሉ ነበር፥ ይህንም በማድረግ ከመሠውያ ጋር ኅብረትን ያገኙ ነበር። (ዘሌዋ. 6:26፤ 7:15፥34፤ ዘሌዋ. 18:9፥10፤ 1ኛ ቆሮ. 10:18) ይሁን እንጂ አንድ የተለየ ነገር ነበረ፥ እርሱም ደሙ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን የገባ የኃጢአት መሥዋዕት ሥጋ ከሰፈሩ ወደ ውጭ ይጣል ነበር እንጂ ካህናት ከእርሱ አይበሉም ነበር፥ መብላት ክልክል ነበረ። (ዘሌዋ. 4:3-12፤ 6:30፤ 16:11፥14፥27) ይህም ማለት የብሉይ ኪዳንን ሥርዓት እስከ አሁን የያዛው ሰው ከኃጢአት መሥዋዕት መካፈል አልተፈቀደለትምና ከክርስቶስ እድል ፈንታ የለውም፥ ምክንያቱም ክርስቶስ የኃጢአት መሥዋዕት ነበርና። ማስረጃውም፥ ምሳሌ የሆነ ለኃጢአት የቀረበው የእንስሳ ሥጋ ከሰፈሩ ውጭ ተወስዶ እንደ ተቃጠለ እንዲሁም ምሳሌውን ፈጻሚ ክርስቶስ ከከተማ ውጭ ተወስዶ መከራን ተቀበለ። (ዮሐ. 19:17፥20) እንደዚሁም አሁን ዕብራውያን፥ ከክርስቶስ ሊካፈሉ ቢወዱ፥ የመሪአቸው የሙሴን መንፈስ ለብሰው ነቀፌታን እየተሸከሙ ከክርስቶስ ጋር ይሆኑ ዘንድ ከአይሁድ ሰፈር፥ ማለት ከሥርዓቱ ሁሉ ይውጡ። (ም. 11:25፥26) ይህንም የሚያደርጉት በዚህ ዓለም ሳትነቃነቅ የምትቀር ከተማ ስለሌለችን ነው። የአይሁድ ሥርዓት ቤተ መቅደስ፥ ዓለምም በሞላ ለጊዜው የሚሆኑ አላፊዎች ነገሮች ናቸው። እኛ ግን ነዋሪ የሆነችውን፥ እስከ መቼውም ድረስ የማንሰደድባትን የምትመጣውን አዲሲቱን ኢየሩሳሌምን እንጠብቃለን። (ም. 12:26-28፤ ም. 11:14-16) እንግዲያውስ ከእነዚያ ከዱሮ መሥዋዕቶች መካፈል አሁን አንመኝ፥ ዳሩ ግን መንፈሳውያን ካህናት መሆናችንን ተገንዝበን መንፈሳውያን መሥዋዕቶችን፥ እነርሱም ምስጋናን እያቀረብን ክርስቶስ ለሠራልን ሥራ መመስከርንና ይኸም ብቻ ሳይሆን መልካም ማድረግንና ለሌሎች ማካፈልን (ማቴ. 25:37፤ የሐዋ. 2:44፥45፤ 4:32-35) በሊቀ ካህናታችን በኢየሱስ በኩል ለእግዚአብሔር እናቅርብ። የዱሮ መሥዋዕቶች አሁን ደስ አያሰኙትም፥ እንደነዚህ ያሉቱ

ግን ደስ ያሰኙታል። (ሮሜ 15፡15፥16፤ 1ኛጴጥ. 2፡5፤ ዕብ. 10፡5-8፤ ሮሜ 12፡1ንም አነጣጥሩ)

ማስገንዘቢያ፡-

ሀ) «ልዩ ልዩ በሆነ በእንግዳ ትምህርት አትወሰዱ» (ቁ. 9) በዕብራውያን ዘንድ ምን ዓይነት የእንግዳ ትምህርት እንደ ገባ ባናውቅም ቅሉ በሐዋርያት ዘመን በየቤተ ክርስቲያኑ ዘንድ ልዩ ልዩ ዓይነት ትምህርት እንደ ገባ እናውቃለን፤ ይህም ትምህርት አብዛኛው ምእመናንን ወደ ኋላ ወደ አይሁድ ሥርዓት የሚስባቸው ነበር። (የሐዋ. 15፡1፤ 20፡29፥30፤ ገላ. 5፡1-4፤ ቆላ. 2፡16፥ 20-23) በዕብራውያን ዘንድ እንግዳ ትምህርቱ «ክርስቲያኖች በክርስቶስ ብቻ ሳያምኑ በአይሁድ መሥዋዕቶችም ሊካፈሉ ይገባቸዋል» የሚል እንደ ነበር ይመስላል። ሐዋርያው ግን «ልባችሁ በጸጋ ቢጠግብ መልካም ነው እንጂ በመብል አይደለም» ብሎ ይህም ትምህርት ይቃወማል፤ ቃሉንም መቀበል ዛሬ ምንኛ ያሻናል! «የምትድኑበት በክርስቶስና ... (በእገሌ፥ በሌላ ተጨማሪ ነገር) ነው» የሚሉ ድምፆች ዛሬ በርከት ያሉ ናቸው። ይሁን እንጂ የሚያድነን መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ ብቻ ነው፥ ይህንም የሚያስረዳ የደብረ ታቦር ታሪክ ነው። ጌታ ወደ ተራራ ወጥቶ መልኩ በተለወጠ ጊዜ የኦሪትና የነቢያት እንደራሴዎች የሆኑት ሙሴና ኤልያስ አብረውት ተገኙ። ጴጥሮስ ግን ሊያቆያቸውና ከክርስቶስ ጋር ሊያደርጋቸው በወደደ ጊዜ ልዑል እግዚአብሔር «አይሆንም፥ የመረጥሁት ልጄ ይህ ነው፥ እርሱን ስሙት» ብሎ ሙሴንና ኤልያስን ወደ ሰማያት መልሶ ነጠቃቸው። (ሉቃ. 9፡28-36) ክርስቶስ ሕግንና ነቢያትን ፈጽሞአልና ከእነርሱ ዛሬ ለደኅንነታችን የሚያስፈልገን አንድም ነገር የለም። (ማቴ. 5፡17፤ ሉቃ. 16፡16) እንግዲያውስ እኛ ወንጌልን የተቀበልን ከጥንት ነውና ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለ ተሰጠ ሃይማኖት እንጋደል እንጂ በክርስቶስ ላይ አንዳችን ነገር መጨመር በእንግዳ ትምህርት እንዳንወሰድ እንጠንቀቅ። (ይሁዳ ቁ. 3)

ለ) «መሠውያ አለን» (ቁ. 10) ሐዋርያው «መሠውያ አለን» ሲል ምን ማለቱ ነው፥ መሠውያውስ ምንድር ነው? ቢሉ፥ ተናጋሪው ለዕብራውያን የሚናገር ዕብራዊ መሆኑንና በዕብራዊ ንግግር እንደሚናገር ማስታወስ ነው። በዕብራውያን ዘንድ የሥርዓታቸው ዋና ነገር፥ የሥርዓታቸው ልብ መሠውያ ነበረ። ማለት፥ ሥርዓቱ በሞላ በመሠውያ ላይ ተመሥርቶአል መሠዊያውም ባልኖረ ሥርዓቱ ባልጸናም ነበር። እንግዲያውስ ሐዋርያው የሚናገረው ስለአንድ መሠዊያ አይደለም፥ የሚናገረው ምሳሌው ወይም ምልክቱ መሠውያ ስለ ሆነ ስለ ሥርዓቱ ነው። «መሠውያ አለን ከእርሱም ሊበሉ ድንኳኒቱን የሚያገለግሉ መብት የላቸውም» ሲልም የክርስትናን ነገሮች በዕብራዊ ንግግር ሲያስረዳ ነው። ይህስ በምን ይታወቃል? ቢሉ፥ ማስረጃው፥ ከመሠውያ የበላ በእውነቱ ማንም ሰው ከቶ ባለመኖሩ ነው። በኋላ ወደ መሠዊያ ከሚቀርበው ሥጋ ይበሉ ነበር። እንጂ በመሰዊያ ላይ ከቀረበው ሥጋ የበላ በፍጹም የለም። ስለዚህ፥ «መሠውያ አለን» የሚለው ቃል ዕብራዊ ንግግር ሆኖ በክርስቲያናዊ ንግግር «ሥርዓት አለን» ማለት ነው፥ «ከእርሱም መብላት» ማለትም በክርስቲያናዊ ንግግር «ከእርሱም መካፈል» ማለት ነው። ዕብራዊ አሳቦችን በክርስቲያናዊ ንግግር ወይም ቃላት መተርጎም ነው።

ሐ) «ኢየሱስ በገዛ ደሙ ሕዝቡን እንዲቀድስ» (ቁ. 12) በዚያ በፈሰሰው በኢየሱስ ደም ምእመናን ለእግዚአብሔር የተለዩ ሕዝብ ሆነዋል። አሳቡ ከም. 10፡10 ጋር ተመሳሳይ

ነው። በዚያ ደም ከኃጢአት ነጽተን ከዓለምና ከርኩሰቱ ሁሉ ተለይተን ለእግዚአብሔር ሆነ፥ በፊቱም ልንቆም ተገቢዎች ነን። እንግዲያውስ «ነቀፌታውን እየተሸከምን ወደ እርሱ ወደ ሰፈሩ ውጭ እንውጣ» (ቁ. 13)። አንባቢ ሆይ፥ ይህን ነገር ልብ አድርገው። እኛ በኢየሱስ ደም የተዋጀንና ለእግዚአብሔር የተለየን የእግዚአብሔር ገንዘቦች ነን። (1ኛ ቆሮ. 6:20፤ 2ኛ ጢሞ. 2:1) ስለዚህ፥ ከዓለምና ከርኩሰቱ ሁሉ እንለይ ቅዱሳንም እንሁን።

## ቁ. 17

17 ለዋኖቻችሁ ታዘዙና ተገዙ፤ እነርሱ ስሌትን እንደሚሰጡ አድርገው፥ ይህንኑ በደስታ እንጂ በኃዘን እንዳያደርጉት፥ ይህ የማይጠቅማችሁ ነበርና፥ ስለ ነፍሳችሁ ይተጋሉ።

ሐዋርያው አሁን የሚናገረው ስለ ዛሬ መሪዎቻቸው ነው። «እነርሱ ስለ ነፍሳችሁ ይተጋሉና በዚህ ምክንያት ታዘዙላቸውና ተገዙላቸው» ብሎ ዕብራውያንን ይመሰክራቸዋል። የሚታዘዙና የሚገዙበት ምክንያቱ፥ እናት ስለ ልጆችዋ እረኛም ስለ በጎቹ እንደሚተጉ እነዚህ «ዋኖች» ስለ ማኅበርተኞች፥ ማለት ስለ ሕዝበ ክርስቲያን ነፍሳት ስለሚተጉ ነው። መንፈሳውያን መሪዎች፥ ማለት ቀሳውስት፥ ስሌትን እንደሚሰጡ ሰዎች ናቸው፤ ማለት፥ ወደ እግዚአብሔር ቅርበው በሕዝበ ክርስቲያን ዘንድ የነበራቸውን አካሄድ ሁሉ ይዘረዝራሉ። (ማቴ. 18:23፤ ሉቃ. 19:15) እነዚህ መሪዎቻቸው ሲያዝዙአቸውና ሲመክሩአቸው ክርስቲያኖቹ ዕብራውያን ቃላቸውን አክብረው ይታዘዙና ይገዙላቸው፤ ይህን ያደረጉ እንደሆነ ተጠቅመው መንፈሳዊ እርምጃ ያደርጋሉና መሪዎቹ ስሌታቸውን ሲሰጡ በደስታ ይሰጡታል፤ ቃላቸውን የማይሰሙ እንደሆነ ግን ሳይጠቀሙ ይቀራሉና መሪዎቹ ስሌታቸውን በኀዘን ይሰጡታል። በኃዘን ቢሰጡት ለዕብራውያን ምን ዋጋ አለው? እንግዲያውስ ይታዘዙላቸውና ይገዙላቸው።

<u>ማስገንዘቢያ</u>:- በቁ. 7ና 17 ላይ የቤተ ክርስቲያንን ዋኖች፥ ወይም የቀሳውስትን፥ ሥራ እናያለን። ሥራቸው የእግዚአብሔርን ቃል መናገርና ስለ ሕዝበ ክርስቲያን ነፍሳት መትጋት ነው። እነዚህን ሥራዎች የሚፈጽሙላት ቀሳውስት ያሉአት ቤተ ክርስቲያን ምንኛ የተመሰገነች ናት!

እኛም ልንታዘዝና ልንገዛላቸው ይገባናል። ምክንያቱስ? ቢሉ፥ 1ኛ፥ በዚህ ነገር የሚተጉ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸውና፥ ከእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው። (ሮሜ 13:1-7) እግዚአብሔር በአሥርቱ ቃላት ላይ «አባትህንና እናትህን አክብር» ባለው ጊዜ ለበላይ የመታዘዝንና የመገዛትን ሕግ መሥርቶአል። (ዘጸአ. 20:12) በዚህ ምክንያት ለዋኖቹ መገዛት ይገባናል። 2ኛ ሥራቸውን የሚሠሩት ለእኛ ጥቅም ነው። የነፍሳችንን ደኅንነት ይሻሉና ለትእዛዛቸውና ለምክር ቃላቸውም መታዘዝ ይገባን የለምን? ይገባናል! የተሰጣቸውን ሥራ ባይሠሩ ያን ጊዜ ብቻ ነው «ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል» ልንላቸው የሚገባን። (የሐዋ. 4:18-20፤ 5:27-29፤ ሕዝ. 34:1-10)

የእነዚህ ዋኖች ኃላፊነት ምንኛ ከባድ ነው! የብዙዎች ሰዎች ነፍስ በእነርሱና በሥራቸው ላይ ተንጠልጥሎአል። የእግዚአብሔርን ቃል፥ እርሱም ወንጌልን ባይሰብኩ ወዮላቸው! (1ኛ ቆሮ. 9:16) በትምህርታቸውም ሆነ በኑሮአቸው ሰውን ያስቱ እንደሆነ ፍርዳቸው የሚያስፈራ ነው። (1ኛ ቆሮ. 3:10-17፤ ያዕ. 3:1) ስሌትን እንደሚሰጡ ሰዎች ናቸው፤ ማለት፥ እግዚአብሔር ለእኛ ኃላፊዎች አድርጎአቸዋል፥ ይቆጣጠርባቸዋልም። (ሕዝ. 33:1-6) በክርስቶስ ፍርድ ወንበር ፊት ሲቆሙ ስሌታቸውን መስጠት አለባቸው። ሉሪ ወንድሞቼ ሆይ፥ እንጸልይላቸው እነርሱም እንድንጸልይላቸው ይለምኑ! (ቁ. 18:19)

## ቁ. 18፥19

[18] ጸልዩልን፥ በነገር ሁሉ በመልካም እንድንኖር ወደን መልካም ሕሊና እንዳለን ተረድተናልና። [19] ይልቁንም ፈጥኜ እንድመለስላችሁ ይህን ታደርጉ ዘንድ አጥብቄ እለምናችኋለሁ።

በቁ. 18 ላይ «ጸልዩልን» ይላል፤ ይሁን እንጂ «ለእኔ» ማለቱ እንደ ሆነ በቁ. 19 እንረዳለን። እንዲጸልዩለት ይለምናቸው ዘንድ የሚያደፋፍረው በእግዚአብሔር ዓይን ፊት አንዋንዋሩ በነገር ሁሉ ቅን ሕሊናውም መልካም እንደ ሆነ ስለ ተማመነ ነው። (የሐዋ. 23፡1) ይልቁንም የሚጸልዩት ሐዋርያው ደኅና ሆኖ እንዲመለስላቸው ነው።

ማስገንዘቢያ፡- ሐዋርያው ስለ አንዋንዋሩ ቅንነትና ስለ ሕሊናው መልካምነት የሚናገረው በምን ምክኒያት እንደ ሆነ አናውቅም። ይሁን እንጂ፥ በዕብራውያን መካከል የጠረጠሩት ሰዎች የነበሩ ይመስላል። ቢጠረጥሩትም አያስገርምም። እንደ እስጢፋኖስ ሆኖ «የአይሁድ ሥርዓት በክርስቶስ ተፈጽሞ አልፎአል፥ ከአይሁድ ሰፈር ውጡ» ብሎ ሰውን ሁሉ ያስተምር አልነበረምን? (የሐዋ. 6፡11-14) የሚጠረጥሩት ቢኖሩም ቅሉ ሐዋርያው «አንዋንዋሬ ቅን ሕሊናዬም መልካም ነውና ጸልዩልኝ» ይላል። ጨምሮም «ይልቁንም ፈጥኜ እንድመለስላችሁ» በማለቱ ከዚያ በፊት ከእነርሱ ጋር ኖሮ እንደ ነበር ያስረዳናል።

## ቁ. 20፥21

[20] በዘላለም ኪዳን ደም ለበጎች ትልቅ እረኛ የሆነውን ጌታችንን ኢየሱስን ከሙታን ያወጣው የሰላም አምላክ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል [21] በፊቱ ደስ የሚያሰኘውን በእናንተ እያደረገ፥ ፈቃዱን ታደርጉ ዘንድ በመልካም ሥራ ሁሉ ፍጹማን ያድርጋችሁ፤ ለእርሱ እስከ ዘላለም ድረስ ክብር ይሁን፤ አሜን!

ዕብራውያን እንዲጸልዩለት ሐዋርያው ለምኖአል አሁንም ለእነርሱ ይጸልያል። ጸሎቱን የሚያደርሰው አዲስ ኪዳን በተመረቀበት በደሙ ምክንያት ለእግዚአብሔር በጎች ትልቅ እረኛ ለመሆን የበቃውን ጌታችንን ኢየሱስን ከሙታን በማስነሣት ሰላምን ለሰበከ አምላክ ነው። (ም. 9፡12፤ ኢሳ. 63፡11-13፤ ዮሐ. 10፡11-30፤ ዕብ. 9፡18-23፤ ኢሳ. 52፡7፤ የሐዋ. 10፡36፤ ኤፌ. 2፡17፤ ቆላ. 1፡19-22) የሚጸልይላቸውም፥ እግዚአብሔር በመልካም ሥራ ሁሉ ፈቃዱን ያደርጉ ዘንድ እንዲያስችላቸው ነው፥ የሚያስችላቸውም እርሱ ራሱ በመካከለኛው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በፊቱ ደስ የሚያሰኘውን በውስጣቸው በመሥራት ነው። ሐዋርያውም «ለዚህ ለሰላም አምላክ እስከ ዘላለም ድረስ ክብር ይሁን፤ አሜን» ብሎ ጸሎቱን በሚገባ ምስጋና ይጨርሳል። (ፊልጵ. 4፡6)

<u>ማስገንዘቢያ</u>፡-

ሀ) «የዘላለም ኪዳን» (ቁ. 20) ይህ አዲሱ ኪዳን ነው። ብሉይ የተባለ ፊተኛው ኪዳን አላፊ ሆኖ ለጊዜው ብቻ ነበረ፤ አዲሱ ግን ለመቼውም የማይሻር ዘላለማዊ ነውና «የዘላለም ኪዳን» የተባለ። (ም. 8፡7-13፤ ም. 10፡9)

ለ) «ትልቅ እረኛ» (ቁ. 20) ኢየሱስ በቁ. 17 ላይ ከተነገረላቸው «ዋኖች» አንዱ ሳይሆን የዋኖቹ አለቃ፥ ትልቁ እረኛ ነው። (1ኛ ጴጥ. 5፡4) በብሉይ ኪዳን የተነገረለት ነው። (መዝ. 77፡70-72፤ ኢሳ. 40፡11፤ ሕዝ. 34፡23) አስተማሪና መምህር ብቻ ሳይሆን

ንጉሥና መሪ አለቃ ሆኖ ሕዝቡን ይገዛል፥ ይመራል፥ ይጠብቃልም፥ ለደስታቸውም አስፈላጊ የሆነውን ሁሉ ለመስጠት ተሾሞአል።

ሐ) «ከሙታን ያወጣው የሰላም አምላክ» (ቁ. 20) የጌታ መነሣት የሰላም ማስረጃ ነው፤ ምክንያቱም፥ ኢየሱስ ሊሠራ የመጣበትን ሥራ ባልፈጸመና እግዚአብሔር ከሰው ጋር ባልታረቀ ኖሮ እግዚአብሔር ከሙታን ባላወጣውም ነበር። አሁን ግን ክርስቶስን በማስነሣት መታረቁን አስታውቆአልና «የሰላም አምላክ» ይባላል። (ሮሜ 15፡33፤ 16፡20፤ 2ኛ ቆሮ. 13፡11፤ ፊልጵ. 4፡9፤ 1ኛ ተሰ. 5፡23)

መ) «በእናንተ እያደረገ» (ቁ. 21) እግዚአብሔር በእኛ ካልሰራ እኛ ልናደርግ አንችልም። (ፊልጵ. 2 12) የሰላም አምላክ፥ አብዛኛውን ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ፥ ፈቃዱን ያስታውቀናል፤ ሲያስታውቀንም በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በልባችን እየሠራ ፈቃዱን እናደርግ ዘንድ ያስችለናል። (ዮሐ. 14፡16፥17፤ ገላ. 2፡20፤ 1ኛ ተሰ. 5፡23፥24)

ሠ) «ፍጹማን ያድርጋችሁ» (ቁ. 21)። «ፍጹማን ማድረግ» የተናጋውን ወደ ቦታው በመመለስ ወይም የጠመመውን በማቅናት ያልተቻለውን ሥራ ለመፈጸም ማስቻል ማለት ነው። ብሉይ ኪዳን በተሰጠ ጊዜ እስራኤላውያን «እግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እናደርጋለን እንታዘዛለንም» አሉ። (ዘጸአ. 24፡3-8) ይሁን እንጂ፥ በሥጋ ድካም ምክንያት መፈጸሙ አቃታቸው። በአዲስ ኪዳን ግን አድራጊው ራሱ እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር በክርስቶስ መታመናችንን አይቶ በውስጣችን ንጹሕን ልብና የቀናውን መንፈስ በመስጠት ቀድሞ ልናደርግ ያልቻልነውን አሁን ለማድረግ ያስችለናል። (ሮሜ 7፡15-24፤ 8፡2-4) ፈቃዱን የምናደርገው እኛ ስንታገል ሳይሆን እርሱ ፍጹማን ሲያደርገን ነው።

## ቁ. 22-25

22 ወንድሞች ሆይ የምክርን ቃል እንድትታገሡ እመክራችኋለሁ፥ በጥቂት ቃል ጽፌላችኋለሁና። 23 ወንድማችን ጢሞቴዎስ እንደ ተፈታ እወቁ፤ ቶሎ ብሎም ቢመጣ ከእርሱ ጋር አያችኋለሁ። 24 ለዋናቻችሁ ሁሉና ለቅዱሳን ሁሉ ሰላምታ አቅርቡልኝ። ከኢጣልያ የሆኑቱ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል። 25 ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን፤ አሜን!

ሐዋርያው በመልእክቱ ውስጥ ብዙ ምክርን ሰጥቶአልና «ምናልባት ያስቀይማቸው ይሆን?» በማለት «ይህን ያህል ሰፋፊ ትምህርት በጠባብ ስፍር ሰፍሬአለሁና እባካችሁ በትዕግሥት አንብቡት በትዕግሥትም ተቀበሉት» ይላቸዋል። ስለ ጢሞቴዎስ መታሰር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፈ ነገር የለም፤ ቢሆንም ሐዋርያው «እኔ በቅርቡ ልመጣ አስብያለሁና ከመነሣቱ በፊት የመጣልኝ እንደሆነ አብረን እንመጣለን» ይላል። ቀጥሎም ለማኅበሩ ዋኖችና አባሎች ሁሉ የራሱን ሰላምታ፥ ከእርሱም ጋር ያሉትን ከኢጣልያ የሆኑትን ምእመናን ሰላምታ እያቀረበ «ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን፤ አሜን!» ብሎ መልእክቱን ያቆማል።

<u>ማስገንዘቢያ</u>፡-

ሀ) «በጥቂት ቃል ጽፌላችኋለሁ» (ቁ. 22) አሥራ ሦስት ምዕራፎች ያሉበት መልእክት «ጥቂት ቃል» እንደምን ይባላል? ቢሉ፥ መልእክቱ ትምህርት ጥቅጥቅ ብሎ የሞላበት

ነውና እኔ ይህን ትርጓሜ ስጽፍ ምን ያህል ወረቀት እንደ ፈጀብኝ ታስተውሉ የለምን? እንግዲያውስ ሐዋርያው «በጥቂት ቃል ጽፌላችኋለሁ» ማለቱ የእውነት ነገር ነው!

ለ) «ከኢጣሊያ የሆኑት» (ቁ. 24) አንድ ዕብራዊ በሌላ አገር ላሉት ዕብራውያን ይጽፋል፥ ከእርሱ ጋር ከኢጣሊያ የሆኑትም አሉ፥ እንግቢዎችም ዛሬ እኛ ነን። በኢየሱስ ክርስቶስ ምንና ምን ያለ ኅብረት አለ! ከሕዝብና ከነገድ ከወገንም ከቋንቋም ሁሉ የሆኑትና ከማናቸውም የቤተ ክርስቲያን ቅርንጫፍ የመጡት ሰዎች በክርስቶስ አንድ ሰው ናቸው። (ራእ. 7:9፤ ገላ. 3:28) በእርሱ፥ ልዩነቶች ሁሉ፥ የአገርና የቀለም፥ የሥልጣኔ ደረጃና የእድሜ የጾታም፥ ሁሉም ተወግደዋል በዓለምም ውስጥ የምእምናን ማኅበር በእውነት አንድ ብቻ ነው። (የኒቅያን የኃይማኖት ሥርዓት ተመልከት። ዮሐ. 17:20-23)

ሐ) «ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን! አሜን» (ቁ. 25) ጸጋ ምንድር ነው? ቢሉ፥ ጸጋ ከእግዚአብሔር ፍቅር የሚወጣ መልካም ነገር ሁሉ ነው። በአንድ ምንጭና በውኃው ብንመስለው፥ ምንጩ የእግዚአብሔር ፍቅር ነው፤ ከምንጩም የሚፈሰው ውኃ ጸጋ ነው። በሥራችን የምንገዛው ወይም እንዲያው የሚገባን ነገር ሳይሆን እግዚአብሔር በመልካም ፈቃዱ የሚያሳትፈን ነገር ነው። በጸጋ ውስጥ ሞገስ ምሕረት ይቅርታ፥ ጽድቅ፥ መታደስ፥ ኅብረት፥ ረድኤት፥ የዘላለምም ሕይወት ተጠቅለሉአል። (1ኛ ዮሐ. 4:16፤ ሮሜ 5:15-18፤ 6:23)

ይህን መልእክት ከነትርጓሜው ያነበባችሁ ሆይ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ስለሚገኝልን ታላቅ መዳን እግዚአብሔር የተናገረውን ቃል ሰምታችኋልን? ኃጢአትን ፈጽሞ የሚያስወግድና ወደ እግዚአብሔር አቅርቦ የማይቋረጥን ኅብረትን የሚያስገኝልን ሊቀ ካህናት አስፈላጊ መሆኑን ተገንዝባችኋልን? የተሾመልን ሊቀ ካህናት ኢየሱስ መሆኑን አስተውላችኋልን? እጅግ በጣም ተስማሚ መሆኑን ተረድታችኋልን? የአዲስ ኪዳንን ተስፋ ቃሎች ያስገነዘበን ዘንድ በሰማያት መቀመጡን አይታችኋልን? እምነት፥ ተስፋ፥ ፍቅር፥ እነዚህ ሦስቱ ለክርስቲያን አመላለስ አስፈላጊ መሆናቸውን አውቃችኋልን? እንግዲያውስ፥ ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን አሜን!

አነሳስቶ ላስጀመረን፥ አስጀምሮ በጸጋው ላስጨረሰን ለእግዚአብሔር
ክብር ምስጋና ይግባው ለዘላለም።
አሜን!